አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረምረቃ መርሀ ግብር

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ተዛምዶ (የካ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገ ጥናት)

የተግባራዊ ስነልሳን ጥናት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ማስተማር
ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
መሰሉ መንግስቱ

ሰኔ 2012
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ተዛምዶ (የካ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገ ጥናት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረምረቃ መርሀ ግብር

የተግባራዊ ስነልሳን ጥናት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ማስተማር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
መሰሉ መንግስቱ
አማካሪ፡ ጌታሁን አማረ (ፕሮፌሰር)

ሰኔ 2012
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረምረቃ መርሀ ግብር

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ተዛምዶ (የካ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገ ጥናት)

በመሰሉ መንግስቱ
2012ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም፡
ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ .....

የውጭ ፈታኝ ስም፡
ዶ/ር ሙሉጌታ ተካ .....

የውስጥ ፈታኝ ስም፡
ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው .....

ማረጋገጫ

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ተዛምዶ (የካ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገ ጥናት) በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር ለተግባራዊ ስነልሳን ጥናት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ማስተማር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- *መሰሉ መንግስቱ*

ፊርማ፡- .....

ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለጥናቱ ትኩረት በመስጠት ውድ ጊዜያቸውን መስዋእት አድርገው የተጣመመውን በማቃናት፣ የጎደለውን በማሟላትና በፍጥነት አንብቦ አስተያየት በመስጠት ጥናቱ ከፍጻሜ እንዲደርስ እገዛ ያደረጉልኝን አማካሪዬን ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረን ከልቤ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ። አምላክ ረጅም እድሜና ጤና ይስጥልኝ።

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ አስፈላጊ ምክር በመለገስ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ላይ አስተያየት በመስጠት፣ ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ፣ የመረጃ ምንጮችን በመጠቆምና ረቂቁን አርሞ አስተያየት በመስጠት አስተዋጽኦ ያደረጉልኝን ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው፣ ደ/ር ሙሉሰው አስራቴ፣ ዶ/ር ሰዋገኝ አሰራት፣ ዶ/ር ደመወዝ አድማሱ፣ ዶ/ር ስለሺ አባተ፣ ዶ/ር የሺጥላ መንግስቴ፣ ዶ/ር ግርማ ሀይሉ፣ ዶ/ር ፍቅሩ ወልደ ኪዳን፣ ዶ/ር ዳንኤል ጥሩነህ፣ ዶ/ር አታክልት ረዳና አቶ የሻው ተሰማን ከልብ አመሰግናለሁ።

ስወድቅና ስነሳ አብረውኝ እየወደቁና እየተነሱ ጥናቱ ከፍጻሜ እንደደርስ ከጎኔ የቆሙት እናቴ፣ እህቶቼ ወንድሞቼና መላው ቤተሰባቸው፤ ወ/ሮ እመቤት ዘነበ ከነቤተሰባቸው፤ ዶ/ር መንበረ ወርቅ ጫንያለው ከነቤተሰባቸው፤ አቶ ነገሰ ሀብተ ጊዮርጊስ ከነቤተሰባቸው፤ አቶ ሙሉነህ አጥናፉ፤ አቶ እንግዳው አዲስ፤ ቀሲስ ሀብተማርያም ካሳዬ፣ ሲስተር የወግነሽ ወርቁ እንዲሁም በጸሎትና በሀሳብ የረዱኝ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። እግዚአብሔር ብድራቸውን ይክፈላቸው።

ከመጀመሪያ ዲግሪ አንስቶ አሁን እስካለሁበት ደረጃ እስክደርስ ኮትኩቶ ላሳደገኝ፣ እውቀት ላስገበየኝና ለቀረጸኝ እንዲሁም ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በተለይም ለዩኒቨርሲቲው የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ።

ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ እንድማር የትምህርት እድል የሰጠኝን ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲን ከልብ አመሰግናለሁ።

እንደኔው ሆነው በማሰብ ውድ ጊዜያቸውን መስዋእት በማድረግ በሙሉ ፈቃደኝነት በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ትብብር ያደረጉልኝን መረጃ አቀባዮቼን፣ በተጠኝነት የተወሰዱ ትምህርት ቤቶች ርእሳነ መምህራንን፣ መረጃ እንዳገኝ የረዱኝን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ቢሮ ሰራተኞች፣

በመረጃ አሰባሰብ ሂደት የተሳተፉ ተመልካቾች፣ በቀረጻ የተሳተፉ የካሜራ ባለሙያዎች ያለነሱ ቀና ትብብር ጥናቱ እዚህ አይደርስም ነበርና ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

ለስራዬ መቃናት ለተባበሩኝ ጓደኞቼ፣ የስራ ባልደረቦቼ፣ የክፍል ጓደኞቼ፣ የቀድሞ ተማሪዎቼና አቶ አብይ ይመር ምስጋናዬ ይድረሳቸው። ትእግስትንና ብርታትን ያስተማሩኝ ሰዎች ትልቅ የህይወት ልምድ እንድቀስም አድርገውኛልና ባለውለታዬ ናቸው።

በኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ የስራ ባልደረባዬ በነበረበት ወቅት በቅንነት ለስራዬ በማሰብ የመረጃ ምንጮችን ሲጠቁመኝ የነበረው አቶ ሰይፈ ሀሰን አሁን በህይወት ባይኖርም ልባዊ ምስጋናዬን ልገልጽለት እወዳለሁ።

በሞራል፣ በገንዘብና በሀሳብ የረዱኝንና ያበረታቱኝን ወዳጅ ዘመዶቼን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

መሰሉ መንግስቱ

ሰኔ 2012 ዓ.ም.

ማውጫ

የሰንጠረዥ ዝርዝር V

የስእል ዝርዝር VII

አጠቃሎ VIII

ምእራፍ አንድ

መግቢያ ..... - 1 -

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... - 1 -

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... - 6 -

1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ..... - 9 -

1.4. የጥናቱ አላማ ..... - 9 -

1.5. የጥናቱ አድማስ ..... - 10 -

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... - 12 -

1.7. የጥናቱ ውሱንነት ..... - 13 -

1.8. የቁልፍ ቃላት ትርጓሜ ..... - 13 -

ምእራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት ..... - 15 -

2.1. የትምህርታዊ ተግባቦት መሰረተ ሀሳብ ..... - 15 -

2.1.1. የትምህርታዊ ተግባቦት ምንነት ..... - 15 -

2.1.2. የትምህርታዊ ተግባቦት መሰረታዊ ነገሮች ..... - 18 -

2.2. የተግባቦት ክህሎት ..... - 22 -

2.2.1. ቃላዊ መግባቢያዎች ..... - 23 -

2.2.2. ኢቃላዊ መግባቢያዎች ..... - 24 -

2.2.3. የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ..... - 26 -

2.2.4. የጥያቄ አጠያየቅ ..... - 28 -

2.2.5. የመረጃ ግብይት ..... - 30 -

2.3. የክፍል ውስጥ መስተጋብር ..... - 33 -

2.3.1. የተማሪዎችን በይነሰባዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ተግባራት ክንውን ..... - 34 -

2.3.2. የክፍል አያያዝ ..... - 36 -

2.3.3. ትምህርታዊ መስተጋብር ..... - 39 -
2.3.4. የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር ..... - 42 -
2.4. ድኅረ አወንታዊ ቀመረ እሳቤ ..... - 48 -
2.5. የመማር ንድፈ ሀሳብ ..... - 50 -
2.5.1. ባህሪያዊ የመማር ንድፈ ሀሳብ ..... - 50 -
2.5.2. የግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ ..... - 51 -
2.5.2.1. አእምሯዊ ግንባታውያን ..... - 55 -
2.5.2.2. ማህበራዊ ግንባታውያን ..... - 56 -
2.5.2.3. የግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ ፈርጆች የትኩረት ነጥብ ተመሳስሎና ልዩነት ..... - 57 -
2.5.3. መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ..... - 58 -
2.6. የግንባታውያን ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ ..... - 59 -
2.7. ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ..... - 59 -
2.7.1. አውድ ..... - 61 -
2.7.2. ግብኣት ..... - 61 -
2.7.3. የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ..... - 62 -
2.7.4. ውጽኣት ..... - 67 -
2.8. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ተኮር ዳራ ..... - 67 -
2.9. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... - 68 -

ምእራፍ ሶስት

የአጠናን ዘዴ ..... - 72 -
3.1. የጥናቱ ንድፍ ..... - 72 -
3.2. የጥናቱ የምርምር ስልት ..... - 72 -
3.3. የንሞና ዘዴዎች ..... - 74 -
3.4. የሚጠኑ ተላውጦዎች ..... - 76 -
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..... - 76 -
3.5.1. የአጭር ጊዜ ቀጥተኛ ምልከታ ..... - 76 -
3.5.2. የሰነድ ምርመራ ..... - 78 -
3.5.3. የተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ ..... - 78 -
3.6. የመረጃ አሰባሰብ ..... - 79 -

3.7. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ..... - 80 -
3.8. የመረጃ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት ..... - 81 -
3.9. የቅኝት ጥናት ውጤት ..... - 83 -

ምእራፍ አራት

የውጤት ትርጎማና ማብራሪያ ..... - 85 -

4.1. የውጤት ትርጎማ ..... - 85 -
4.1.1. የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ..... - 85 -
4.1.1.1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ ..... - 85 -
4.1.1.2. ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኘ መረጃ ..... - 123 -
4.1.1.3. ከሰነድ ምርመራ የተገኘ መረጃ ..... - 128 -
4.1.2. የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ..... - 129 -
4.1.2.1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ ..... - 129 -
4.1.2.2. ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኘ መረጃ ..... - 157 -
4.1.2.3. ከሰነድ ምርመራ የተገኘ መረጃ ..... - 162 -
4.2. የውጤት ማብራሪያ ..... - 163 -
4.2.1. የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ..... - 163 -
4.2.1.1. የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ..... - 167 -
4.2.1.2. የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ..... - 169 -
4.2.1.3. የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ..... - 171 -
4.2.1.4. የጥያቄ አጠያየቅ ..... - 173 -
4.2.1.5. የመረጃ ግብይት ..... - 175 -
4.2.2. በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ በትምህርት ደረጃ የታየ ልዩነት ..... - 179 -
4.2.3. የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ..... - 180 -
4.2.3.1. የተማሪዎች በይነሰባዊ ፍላጎት መሟላት ..... - 184 -
4.2.3.2. የክፍል አያያዝ ..... - 186 -
4.2.3.3. ትምህርታዊ መስተጋብር ..... - 189 -
4.2.3.4. የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር ..... - 191 -
4.2.4. በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር አተገባበር ረገድ በትምህርት ደረጃ የታየ ልዩነት ..... - 194 -

4.2.5. የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ተዛምዶ ..... - 196 -
4.3. የጥናቱ ግኝትና ድምዳሜ ..... - 199 -

ምእራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ..... - 210 -

5.1. ማጠቃለያ ..... - 210 -
5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ..... - 218 -

የማጣቀሻ ጽሁፎች ..... - 221 -

ሙዳየ ቃላት ..... - 221 -

አባሪዎች III

አባሪ 1 iii
አባሪ 2፡- xiii
አባሪ 3 xvi
አባሪ 4 xvii
አባሪ 5 xxi
አባሪ 6 xxii
አባሪ 7 xxvii
አባሪ 8 xxviii
አባሪ 9 xxix
አባሪ 10 xxxi
አባሪ - 11 xxxiii
አባሪ 12 xxxv

የሰንጠረዥ ዝርዝር

ሰንጠረዥ 1፡- የተጠኝዎችን ዳራ የሚያሳይ መረጃ ..... - 75 -
ሰንጠረዥ 2፡ የአስተማማኝነት ትንተና ውጤት ..... - 82 -
ሰንጠረዥ 3፡-: የመምህራኑን ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 86 -
ሰንጠረዥ 4፡ የቃላዊ መግባቢያዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ..... - 88 -
ሰንጠረዥ 5፡ የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 89 -
ሰንጠረዥ 6: የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቴስት ውጤት ..... - 96 -
ሰንጠረዥ 7፡ የትምህርታዊ መረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ውጤት ..... - 97 -
ሰንጠረዥ 8፡ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ..... - 104 -
ሰንጠረዥ 9፡ የመምህራኑን ጥያቄ አጠያየቅ ችሎታ የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ውጤት- 106 -
ሰንጠረዥ 10፡ የመምህራኑን የጥያቄ አጠያየቅ ክህሎት የሚያሳዩ መረጃዎች ..... - 111 -
ሰንጠረዥ 11፡ የመረጃ ግብይት ሂደትን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ውጤት ..... - 112 -
ሰንጠረዥ 12፡ የመረጃ ግብይት ሂደትን የሚያሳዩ መረጃዎች የቲ-ቴስት ስልት ውጤት ..... - 121 -
ሰንጠረዥ 13: አጠቃላይ የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 122 -
ሰንጠረዥ 14፡ የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ..... - 123 -
ሰንጠረዥ 15፡ የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 130 -
ሰንጠረዥ 16፡ የተማሪዎቹን በይነ ሰባዊ ፍላጎት መሟላት የሚያስችሉ ተግባራትን የክንውን ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ..... - 133 -
ሰንጠረዥ 17፡ የክፍል አያያዙን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 135 -
ሰንጠረዥ 18፡ የክፍል አያያዙን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት: ..... - 138 -
ሰንጠረዥ 19፡ የመማር ማስተማር መስተጋብርን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 139 -

ሰንጠረዥ 20፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለውን ትምህርታዊ መስተጋብር የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቴስት ውጤት ..... - 146 -
ሰንጠረዥ 21፡ የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበርን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 148 -
ሰንጠረዥ 22፡ የመማር ማስተማር ስልቶችን የአተገባበር ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት ..... - 155 -
ሰንጠረዥ 23፡ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን በጥቅል የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት ..... - 156 -
ሰንጠረዥ 24፡ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን በጥቅል የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት ..... - 157 -
ሰንጠረዥ 25፡ የትምህርት ደረጃ ልዩነት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ያመጣውን ልዩነት የሚያሳዩ መረጃዎች ..... - 179 -
ሰንጠረዥ 26፡ የትምህርት ደረጃ ልዩነት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ያመጣውን ልዩነት የሚያሳዩ መረጃዎች ..... - 195 -
ሰንጠረዥ 27፡ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያሳዩ መረጃዎች ..... - 197 -

የስእል ዝርዝር

ስእል 1፡ ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ..... - 60 -
ስእል 2፡ በመማሪያ ክፍል የሚከናወን የትምህርታዊ ተግባቦት ስርአተ ሂደት ..... - 65 -

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ መኖሩን መመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ የተጠኝ መምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን እንዴትነት ከተመለከተ በኋላ በመካከላቸው ተዛምዶ መኖሩን መርምሯል፡፡ ምርምሩ የተከናወነው በድኅረ አወንታውያን የምርምር ቀመረ እሳቤና በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ማሕቀፍነት ነው፡፡ መነጸሪያው እስካሁን ድረስ የተሰነዘሩ ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ሲሆን የጥናቱ ሞዴል ለጥናቱ እንዲመች ተደርጎ የተቀናበረ ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ሂደት ማሕቀፍ ነው፡፡ ለጥናቱ ጥምር የምርምር ንድፍና ተዛምዷዊ የምርምር ስልት በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ መረጃዎች በይዘትና ኢይዘትዊ የንሞና ዘዴዎች ከተመረጡ ተጠኝዎች በአጭር ጊዜ ምልከታ፣ በተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና በሰነድ ምርመራ የተሰበሰቡ ሲሆን የተተነተኑት በይዘት ትንታኔና በሰነድ ትንታኔ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ጠንካራ አወንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምም ሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ናቸው፡፡ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምም ሆነ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ ከሆኑ መምህራን ተሸሎ የተገኘ ቢሆንም በሁለቱም የትምህርት ደረጃ ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው፡፡

ምእራፍ አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

አብዛኛውን ሙያዊ ተግባራቸውን ከሰዎች ጋር ፊት ለፊት በሚያደርጉት መስተጋብር ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሚሰጥ ስልጠና በሶስት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል (Hargie, 2006)። እነዚህ ጉዳዮች አእምሯዊ ክህሎት፣ ስልታዊ ክህሎትና የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ናቸው። ሰልጣኞች አእምሯዊ ክህሎትን ሲያዳብሩ ከስልጠና በኋላ የሚሰማሩበት የሙያ መስክ ከሌሎቹ ልዩ የሚያደርገውን መሰረተ ሀሳብ ያውቃሉ። በስልታዊ ክህሎት ደግሞ በሚሰማሩበት የሙያ መስክ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችሏቸውን የአተገባበር ችሎታዎች ይላበሳሉ። እንዲሁም በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በተሰማሩበት የሙያ መስክ ሙያዊ መስተጋብር በሚያከናውኑበት ወቅት በስራ ሂደት ከሚያገኟቸው ሰዎች ጋር ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመግባባት የሚያስችሏቸውን የመረጃ መለዋወጫ ዘዴዎች አውቀው በጥቅም ላይ ያውላሉ። እንደዚህ አይነት ስልጠና ማግኘት ከሚጠበቅባቸው ባለሙያዎች መካከል መምህራን ተጠቃሽ ናቸው። Dufresne, Gerace, Leonard & Mestre (1996)፣ Wrench, Richmond & Gorham (2009)ና Ilias & Nor (2012) እንዳሉትም በማስተማር ስራቸው ውጤታማ መሆን ይችሉ ዘንድ መምህራን የሶስቱም ዘርፎች እውቀትና የአጠቃቀም ችሎታ (የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት እውቀት፣ የማስተማር ዘዴና የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም) ባለቤት መሆን ይጠበቅባቸዋል።

የመማር ማስተማር ሂደት መምህራንና ተማሪዎች ተግባቦትን የሚያከናውኑበት ስርአት ሲሆን ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ተብሎ ይጠራል። ተሳታፊዎቹ መምህራንና ተማሪዎች ሲሆኑ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር አማካኝነት የጋራ ግንዛቤን ይጨብጡበታል። የጋራ ግንዛቤን መጨበጣቸው ደግሞ የትምህርቱ ዓላማ ግቡን እንዲመታ ያደርጋል Wrench et al. (2009)። መማር ተማሪዎች የተሻለ ችሎታ ባላቸው አካላት ድጋፍ እየተደረገላቸው በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ውስጥ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር እውቀታቸውን የሚገነቡበት ሂደት ነው። የላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል የሚባለው ተማሪዎች ቀደም ሲል የማያውቁትን ጉዳይ ለማወቅ የሚያስችል የእውቀት ማጎልበቻ የሆነ የአእምሮ ክልል ነው። ማስተማር ደግሞ ተማሪዎች በላቀ የእውቀት ደረጃ ግንባታ ክልል ውስጥ ትምህርታዊ ተግባራትን ማከናወን እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግ መቻል መሆኑን Brown & Athkins (2002)ና Shabani, Khatib & Ebadi, (2010) ያስገነዝባሉ።

ተማሪዎች በዚህ የእውቀት ግንባታ ክልል ውስጥ እውቀታቸውን እንዲገነቡ በተግባቦት ሂደት በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ተሳታፊ መሆን አለባቸው (Brown, 2007; Osakwe, 2009)። ለዚህ ደግሞ መምህራን መስተጋብሩን ማደራጀትና ክንውኑን በአመራር ሰጪነት መምራት ይጠበቅባቸዋል። መምህራን ጥሩ አመራር መስጠት እንዲችሉ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የተካኑ መሆን ይጠበቅባቸዋል (Hargie, 2006)። ከዚህ በተጨማሪ ጥሩ የማስተማር ቴክኒኮች የአተገባበር ችሎታ ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ምክንያቱም Shahzadi & Ahmad (2011) እንደገለጹት የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች በክፍል ውስጥ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር ይወሰናል።

ትምህርታዊ መስተጋብር የተግባቦቱ ተሳታፊዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚሰራጩ ትምህርታዊ መረጃዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማስተማር ቴክኒኮች አማካኝነት በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ማህበራዊ ተራክቦ ነው (Richards & Schmidt, 2003)። የክፍል ውስጥ መስተጋብር ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ሀሳብ ይለዋወጡበታል። በሂደቱ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች ትምህርታዊ መረጃዎችን በአመዛኙ በንግግር የሚለዋወጡ ሲሆን በልውውጡ ሂደት መረጃን መረዳት፣ መገንዘብ፣ ማብላላት፣ ማዋሀድና እውቀትን መገንባት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል። ይህም የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡና የትምህርቱ አላማ ግቡን እንዲመታ ያደርጋል።

የትምህርታዊ መስተጋብሩ የክንውን ሁኔታ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በማስተማር ስልቶች አተገባበር ላይ የተመሰረተ ነው (Sarode, 2018; Duta, Panisoara & Panisoara, 2015; Muste, 2016; Osakwe, 2009)። የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት በመማር ማስተማር ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር መምህራን የሚጠቀሙበት ችሎታ ሲሆን ከተማሪዎቻቸው ጋር መግባባት እንደሚያስችላቸው Hargie & Dickson (2005)ና Akpınar (2009) ያስገነዝባሉ። መምህራን በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት የመረጃ ፍሰትን የሚያሳልጡበትና ትምህርታዊ መረጃን በምልክት ወክለው ወደ ተማሪዎች የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው። Hargie (2006) እንደገለጹት ይህ ችሎታ በበይነ ሰባዊ የሀሳብ ልውውጥ ሂደት የሚኖር፤ በትምህርትና በስልጠና የሚዳበር እንዲሁም በመጓደሉ መልእክትን ጎደሎ የሚያደርግ ነው።

የክፍል ውስጥ መስተጋብር የሚባለው የተግባቦቱ ተሳታፊዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚሰራጩ ትምህርታዊ መረጃዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማስተማር ስልቶች አማካኝነት የሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር ነው (Richards & Schmidt, 2002)። በትምህርታዊ

ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል የሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል (Rahman, 2016)። እንደ Muste (2016) አገላለጽ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴትነት በመማር ማስተማሩ ሂደት በጥቅም ላይ በሚውሉት የማስተማር ስልቶች ይወሰናል። የማስተማር ስልቶች የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳፊዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ አዲስ ለቀረበው ትምህርታዊ መረጃ የሚጋለጡባቸው፣ መረጃውን የሚገበያዩባቸው፣ ፍቺን የሚመሰርባቸውና እውቀትን የሚገነቡባቸው የመልእክት መተላለፊያ ናቸው (Wrench et al., 2009)። የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ ተሳፊዎች የሚቀርቡላቸውን ትምህርታዊ መረጃዎች አስመልክቶ የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጡና የቋንቋ ችሎታቸው እንዲዳብር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

Wrench et al. (2009)ና McPheat (2010) እንደገለጹት ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት በውስጡ ሰባት መሰረታዊ ነገሮችን ይይዛል። እነዚህም የትምህርት አውድ (የተግባቦት አውድ)፣ መምህር (የመልእክት ምንጭ/ ተቀባይ)፣ የትምህርት ይዘት (መልእክት)፣ የትምህርት አቀራረብ ስልት (የመልእክት መተላለፊያ)፣ ተማሪ (የመልእክት ተቀባይ/ ምንጭ)፣ ግብረመልስና የተግባቦት እንቅፋት ናቸው። የትምህርቱ አውድ የመማር ማስተማሩ ሂደት መከሰቻ ሲሆን የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወንበትን ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታን ይመለከታል። ትምህርታዊ ተግባቦቱ እንዲከናወን የሚቀሰቅሰው የትምህርቱ ዓላማ ቃላዊ ወይም ኢቃላዊ በሆኑ ምልክቶች ሲወከል የትምህርት ይዘት ይሆናል። መምህራንና ተማሪዎች የተግባቦት ሂደቱ መልእክት የሆነውን የትምህርት ይዘት የስርአቱ የመልእክት መተላለፊያ በሆኑት የማስተማሪያ ዘዴዎች አማካኝነት ያስተላልፋሉ። በዚህም መልእክትን ይለዋወጣሉ፤ መልእክቶቹንም ተርጉመው የጋራ ግንዛቤዎችን ይጨብጣሉ። የጋራ ግንዛቤዎችን መጨበጣቸውና አለመጨበጣቸው ደግሞ ከሁለቱም ወገኖች በሚሰጥ ግብረመልስ አማካኝነት ይታወቃል። በዚህ ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ አሰናካይ ጉዳዮች የስርአቱ የተግባቦት እንቅፋቶች ሲሆኑ ስርአቱ እውን የሆነበት ዋንኛ ምክንያት የትምህርቱ ዓላማ ግቡን እንዳይመታ ያደርጋሉ።

በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውጤታማ የሆነ ተግባቦት ይኖር ዘንድ መምህራን በነዚህ መሰረታዊ ነገሮች መረጃ የሚዘዋወርበትን ሁኔታ ማወቅ ይኖርባቸዋል (Oskawe, 2009)። ይህም ትምህርታዊ ተግባቦቱ ስርአተ ሂደቱን ጠብቆ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወን የሚያስችሉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። እንደ Wrench et al. (2009)፣ Creese (2005)፣ McLeod, Fisher & Hoover (2003) Balli (2009) አገላለጽ ይህ ከሆነ በትምህርቱ አውድ ውስጥ በተግባቦቱ ተሳታፊዎች መካከል እንዲኖር የሚጠበቀው ተግባቦት እንቅፋት ሳይገጥመው ስለሚከናወን የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት ይችላል። ለዚህ ደግሞ ወሳኝ ሚና የሚጫወተው መምህራን የተግባቦት ክህሎታቸውን በአግባቡ ተጠቅመው የሚሰጡት ትምህርታዊ አመራር ነው። ትምህርታዊ አመራሩ በተግባቦት ክህሎት አማካኝነት ወደ ተማሪዎቹ የሚደርስ ሲሆን የማስተማር ስልቶች በጥቅም ላይ

በሚውሉበት ሁኔታ ላይ ተመስርቶ በሚያከናውኑት የክፍል ውስጥ መስተጋብር ከተማሪዎቻቸው ጋር የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ ያስችላቸዋል፡፡

መምህራን የለውጥ መዘውር መሆን የሚችሉት የተግባቦት ክህሎታቸውን በአግባቡ ተጠቅመው የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ ጥሩ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንዲከናወን ማድረግ ሲችሉ ነው (Kumaravadivelu, 2008)፡፡ Muste (2016)ና Robinson (1994) እንደገለጹት በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን የመረጃ ፍሰትን የሚያሳልጡበትና መልእክትን የሚያስተላልፉበት መንገድ በክፍል ውስጥ በሚከናወነው መስተጋብር ውጤታማነት ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወጣል፡፡ Oskawe (2009) እንደገለጹት መማር-ማስተማር በአንድ በተወሰነ የትምህርታዊ ተግባቦት አውድ የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ እንዲኖር ማድረግ የሚያስችል መሰረታዊ እውቀትን የመጋራትና የመገበያየት ሂደት ነው፡፡ በትምህርትነት በቀረበው መረጃ ረገድ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ያስችላል፡፡

Moreno (2009); Wrench et al. (2009)ና Samson & Collins (2012) እንደገለጹት ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደትን በደንብ የተረዱና የተግባቦት ክህሎትን በጥሩ ሁኔታ መጠቀም የሚችሉ መምህራን እርስ በእርስም ሆነ ከተማሪዎቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት አላቸው፡፡ ይህ ማለት ተማሪዎቻቸው በትምህርታዊ መስተጋብር አማካኝነት በሚያገኙት መረጃ አማካኝነት እውቀትን፣ ልምድንና አወንታዊ አመለካከትን እንዲቀስሙ፣ እንዲገነቡና እንዲያጎለብቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ:: ካልቻሉ ግን በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቁባቸውን ተግባራት ማከናወን የተሳናቸው ይሆኑና የትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት እንዲመክን ምክንያት ይሆናሉ፡፡

በኢትዮጵያ ያለው የትምህርት አሰጣጥ በከፍተኛ ሁኔታ ለትምህርት ጥራት ችግር የተጋለጠ ነው (Ethiopian National Agency for UNESCO, 2001; JICA, 2012)፡፡ በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ አሰራር ያለውን ችግር አውቆ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ስልት ለመቀየስ ያስችላል (Tavakoli, 2012)፡፡ የመምህራኑን አሰራር የሚመረምር ጥናትና ምርምር ይህንንም ሆነ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚታዩ ሌሎች ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል መፍትሄ ለማግኘት ያስችላል (Kumaravadivelu, 2008)፡፡ ምክንያቱም ጥናትና ምርምር በሚያስገኘው ውጤት ላይ በተመሰረተ ስልጠና መሥያቸውን ያጎለበቱ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ በተሰማሩ ቁጥር ተማሪዎች በትምህርት የሚኖራቸው ውጤታማነት ይጨምራል (Seider & Lemma, 2004; Ulla, 2018)፡፡ ይህ ደግሞ በትምህርት ጥራት ላይ ያለው ችግር እንዲቀረፍ ማድረግ የሚያስችል አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በጥራት የሰለጠኑ መምህራን ከሚጠበቁባቸው ችሎታዎች መካከል የተግባቦት ክህሎትና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ተጠቃሽ ናቸው (Dufresne et al., 1996; Wrench et al., 2009; Ilias & Nor, 2012)፡፡

አማርኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ የትምህርት ስርአት ውስጥ ከተካተቱት የትምህርት አይነቶች አንዱ እንደመሆኑ መጠን በሀገሪቷ የትምህርት ጥራት ላይ አወንታዊ ተጽእኖ ማሳደር ይቻል ዘንድ መምህራኑ በጥራት የሰለጠኑ እንዲሆኑ ይጠበቃል። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ለማየት በተደረገው ሙከራ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ጥናት አልተገኘም። አለመገኘቱ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ጋር ባለው ተዛምዶ ረገድ የመማር ማስተማር ሂደቱ በምርምር ግኝት ላይ የተመሰረተ እንዳይሆን ያደርጋል። እናም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህም ርእሰ ጉዳዩ ቢጠና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ብሎም ለትምህርት ጥራት መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑ ከግንዛቤ እንዲገባ አድርጓል፤ የጥናቱን አቅራቢ ትኩረትም ስቧል። በመሆኑም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ መርምሯል።

Hargie (2006) እንደገለጹት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ጥናት አዲስ ሲሆን አሁን አሁን ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ መጥቷል። ለዚህ ምክንያቱ በክህሎቱ አጠቃቀም የበለጸገ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በተሰማሩበት የሙያ መስክ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ከሌሎቹ የበለጠ ውጤታማ መሆናቸው መረጋገጡ ነው። በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ጥናት በሶስት መንገዶች ይከናወናል። የመጀመሪያው የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚዳብርበትን መንገድ የሚመለከት ሲሆን ቀደም ሲል በዘዴዎቹ አጠቃቀም ስልጠና ወይም ትምህርት የሌላቸው ሰዎች ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ይመለከታል። ሁለተኛው በተለያዩ አውዶች በሚከናወኑ ማህበራዊ መስተጋብሮች የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን በጥቅም ላይ የማዋል ችግር ያለባቸውን ሰዎች ችግር መፍታት የሚቻልበትን መንገድ ይመረምራል። ሶስተኛው በተለያዩ የሙያ መስኮች የተሰማሩ ሰዎች በስራ ሂደት ከሚያጋጥሟቸው ሰዎች ጋር ወይም ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር የተግባቦት ክህሎትን በጥቅም ላይ የሚያውሉበት ሁኔታ የሚጠናበት ነው። ይህኛው በተለያዩ የሙያ መስኮች የተሰማሩ ሰዎች በሙያቸው የተለያዩ ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ በጥቅም ላይ የሚያውሉትን የተግባቦት ክህሎትና ውጤታማነቱ ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ መርምሯል።

ይህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ የካ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች የመረመረ ጥናት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠናባቸው ሶስት መንገዶች መካከል በመጨረሻው ላይ ያተኮረ ነው። በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስራ ላይ የተሰማሩ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ምን እንደሚመስልና አጠቃቀማቸው

ከክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ መርምሯል። በመጀመሪያው ዘርፍ ላይ ያላተኮረበት ምክንያት መምህራኑ በማስተማር ሙያ ሰልጥነው በስራ ላይ የተሰማሩ በመሆናቸው በስልጠና ሂደት እውቀቱንና የአጠቃቀም ችሎታውን ያዳብራሉ የሚል እምነት በመኖሩ ነው (ሰንጠረዥ 2ን ይመልከቱ)። በሁለተኛው ዘርፍ ላይ ያላተኮረው ደግሞ ካሁን ቀደም በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ የተደረገ ጥናት ባለመኖሩ ዘዴዎቹን የሚጠቀሙበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ማግኘት ስላልተቻለ ነው። የዳበረ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን የሚፈልጉ የተለያዩ የሙያ መስኮች ቢኖሩም፤ ይህ ጥናት በማስተማር ሙያ ላይ ያተኮረው የመምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በጥናትና ምርምር ውጤት ላይ ተመስርቶ መሻሻሉ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በየትኛውም የሙያ መስክ የሚሰማሩ ሰዎችን መሰረት ማስያዝ ስለሚያስችል ነው። ጥናቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሚያስተማሩበት ጊዜ የተግባቦት ክህሎትታቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙና አጠቃቀማቸው ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ያለው ተዛምዶ ተመርምሮ ውጤቱ በተግባር ሲተረጎም መምህራኑ በማስተማር ሙያቸው ስኬታማ እንዲሆኑ በር የሚከፍት ጉዳይ እንደሚሆን ይታመናል።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ትምህርት ሀገርን፣ ማህበረሰብንም ሆነ ግለሰብን የሚለውጥና የሚመራ ትውልድ የሚቀረጽበት ተግባር ነው (Bhargava, 2011)። ይህ ተግባር ሰዎች ራሳቸውን፣ ሀገራቸውን፣ ማህበረሰባቸውንና ቤተሰባቸውን ለመጥቀም የሚያስችላቸውን ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማድረግ ይረዳል። በመሆኑም አንድ የተወሰነ ማህበረሰብ አባል የሆነ ግለሰብ እውቀትን የተላበሰ፣ ኃፊነትን መቀበል የሚችል፣ የተለያዩ ማህበራዊ እሴቶችንና ቅርሶችን ጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍ፣ በሀብት አጠቃቀም ረገድ የተዋጣለትና በአጠቃላይ ለሚኖርበት ማህበረሰብ የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክት አድርጎ ይቀርጻል።

Brown & Athkins (2002)፣ Beatty (2004)ና Ilias & Nor (2012) እንዳሉት በአንድ ሀገር ውስጥ ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ዜጎችን ማፍራት የሚቻለው ውጤታማ ትምህርታዊ ተግባቦት የሚተገበርበት የትምህርት ስርአት ሲኖር ነው። እንዲህ አይነት የትምህርት ስርአት ሊኖር የሚችለው ደግሞ የተግባቦት ክህሎትን በአግባቡ በመጠቀም በክፍል ውስጥ በሚከናወነው መስተጋብር ላይ አወንታዊ ተጽእኖ ማሳደርና የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ጥሩ እንዲሆን ማድረግ የሚችሉ መምህራን ሲኖሩ ነው። ይህ አገላለጽ ትምህርት ቤቶች ትውልድ የሚቀረጽባቸው ሥፍራዎች እንደመሆናቸው መጠን ትምህርታዊ የተግባቦት ስርአትን በጥሩ ሁኔታ በመምራት በተማሪዎች የእውቀት ግንባታ ላይ አወንታዊ ተጽእኖ ማሳደርና የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ጥሩ እንዲሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚችሉ ለውጥ አምጪ መምህራን እንደሚያስፈልጉ ያስገነዝባል።

Wahyuni (2017) እንደገለጹት በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራን ተግባራቸውን በሚገባ እንዲያከናውኑ የተግባቦት ክህሎታቸውን በአግባቡ በጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋቸዋል። መምህራን በትምህርትነት የሚያቀርቡት መረጃ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች የጋራ ግንዛቤ ሊሆን የሚችለው የተግባቦት ክህሎት በጥሩ ሁኔታ በጥቅም ላይ ውሎ የመረጃ ፍሰቱ ሲሳለጥና በማስተማር ቴክኒኮች አማካኝነት ጥሩ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ሲተገበር ነው። እንደ Muste (2016)ና Rahman (2016) አገላለጽ የመረጃ ፍሰቱ ካልተሳለጠ መምህራኑ የሚያስተላልፉት ትምህርታዊ መረጃም ሆነ የትምህርታዊ ተግባራት አተገባበር በትክክል ተማሪዎቹ ዘንድ መድረስ ስለማይችል የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች የሚጠበቀውን ተግባር የማከናወናቸውና አንድ አይነት ፍቺን የመመስረት እድላቸው የጠበበ ይሆናል። ስለዚህም የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ይመክናል ማለት ነው።

በFDRE (1994) እንደተገለጸው በሀገሪቷ እድገት ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል፣ አካባቢንና የተፈጥሮ ሀብትን በብቃት በጥቅም ላይ የሚያውል፣ ሰብኣዊ አመለካከት ያለው፣ ኃላፊነትን መሸከም የሚችል፣ ስራ ፈጣሪና ማድነቅ የሚችል ትውልድ መገንባት የሚያስችል ትውልድ መቅረጽን አላማው ያደረገ የትምህርት ፖሊሲ ተቀርጾ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይህንን ለማሳካት ለውጥ አምጪ መምህራን ያስፈልጋሉ (Kumaravadivelu, 2008)። በዚህ መሰረት የትምህርት ጥራትን ማሻሻል ይቻል ዘንድ መምህራኑ በማስተማር ስነዘዴ ብቻ ሳይሆን በስነምግባር ረገድም የሚሻሻሉበት የስልጠና መርሀ ግብር ተቀይሶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል (Ethiopian National Agency for UNESCO, 2001; FDRE, 2004)።

ይሁን እንጂ በFDRE (2004) እንደተገለጸው የትምህርት ጥራትን እሚፈለገው ደረጃ ላይ ማድረስ አዳጋች ሆኗል። Ethiopian National Agency for UNESCO (2001) ባደረገው ጥናት በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የትምህርት ማሻሻያ መርሀ ግብር የትምህርት ጥራት ችግር ያለበት መሆኑን አረጋግጧል። EGRA (2010) ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሁለተኛና የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን ጨምሮ በስድስት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ባላቸው የንባብ ችሎታ ላይ ጥናት አድርጎ ነበር። የተማሪዎቹ የንባብ ችሎታ የተመዘነው በትምህርት ሚኒስቴር የብቃት መመዘኛ መስፈርት ሲሆን ተማሪዎቹ በሁሉም ቋንቋዎች ያላቸው የንባብ ችሎታ ከብቃት መመዘኛ በታች ሆኖ ተገኝቷል። በምዘናው በአብዛኞቹ ክልሎች ያሉ ከ25% በላይ የሆኑ የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ ቃል ማንበብ የማይችሉ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። በJICA (2012) የቀረበው ሪፖርት እንደሚያሳየው በ4ኛና በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በ2010 ዓ.ም.፣ (እ.ኤ.አ) በተደረገው ሀገር አቀፍ ምዘና (National Learning Assessment) የተማሪዎቹ ውጤት ከትምህርት ሚኒስቴር የብቃት መመዘኛ በታች ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ ስለሚያስተምሩት የትምህርት አይነት በቂ ግንዛቤ የላቸውም። በመማር ማስተማሩ ሂደት ከተለምዷዊው የማስተማር ዘዴ ወጣ ያለ አሰራርን የሚተገብሩበት ሁኔታም

አይስተዋልም። ሌላው ቀርቶ "...የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን እንዴት እንደሚያስተምሩ አያውቁም" (JICA, 2012፡v)። በጥቅሉ የትምህርት ጥራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የሄደበት ሁኔታ ይታያል (EGRA, 2010; JICA, 2012)።

አማርኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ የትምህርት ስርአት ውስጥ ከተካተቱት የትምህርት አይነቶች አንዱ እንደመሆኑ መጠን በሀገሪቷ የትምህርት ጥራት ላይ አወንታዊ ተጽእኖ ማሳደር ይቻል ዘንድ መምህራኑ በጥራት የሰለጠኑ እንዲሆኑ ይጠበቃል። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ለማየት በተደረገው ሙከራ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ችግር ያለበት መሆኑን የሚያመለክቱ ጥናቶች ተገኝተዋል (መሰለ፣1990፤ ሰይድ፣ 1993፤ ሂሩት፣ 1997፤ ኤልያስ፣ 1997)። ከዚህ በተጨማሪ በደቡብ ብሔር በሐረሰቦችና በጋምቤላ ክልላዊ መንግስታት የተደረገ አንድ ጥናት በጋምቤላ ክልል የ5ኛና የ6ኛ ክፍል ተማሪዎችን ጨምሮ በአማርኛ ቋንቋ ለማንበብ እንደሚቸገሩና ለዚህ ክስተት ተጠቃሽ ከሚሆኑት ምክንያች አንዱ የማስተማር ስነዘዴ ችግር ሊሆን እንደሚችል አመልክቷል (Berhanu, 2009)።

እነዚህ ጥናቶች የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ችግር ያለበት መሆኑን ቢዳስሱም የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ አልተመለከቱም። አለመመልከታቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት የመረጃ ፍሰት በሚሳለጥበት ሁኔታ ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴትነት ጋር ባለው ተዛምዶ ረገድ የምርምር ክፍተት መኖሩን ያመለክታል። በክፍተቱም የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት መምህራኑ ትምህርታዊ መረጃን ከተማሪዎች ጋር የሚለዋወጡበት ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ባለው ተዛምዶ ላይ ትኩረት ያልተሰጠው በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ጉዳይ መኖሩን ያመላክታል። የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖርና የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በጥሩ ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችል ከመሆኑ አንጻር በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችና መምህራን የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡ ለማድረግ በሚያስችል ጉዳይ ላይ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ መኖሩን ያሳያል። ይህ ደግሞ በምርምር ውጤቶች የተደገፈ የመማር ማስተማር ሂደት የሚተገበርበት ሁኔታ ክፍተት እንዲኖርበት ያደርጋል። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

ከዚህ በተጨማሪ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተና ወስደው ለቅድመ መደበኛና ለመጀመሪያ ደረጃ መምህርነት በዲፕሎማ ለመሰልጠን ወደ በሀገሪቷ ወደሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚገቡ ተማሪዎች በሙሉ በትምህርቱ የመጀመሪያ አመት ላይ መሰረታዊ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የእጅ ጽህፈት ክህሎት /Mother Tongue Basic Hand Writing Skills (TMOT 111)/ የሁለት ክሬዲት ሀወር ኮርስ ይወስዳሉ (Mother Tongue Curriculum, 2004):: በዚህ መሰረት በአዲስ አበባ በሚገኙ ቅድመ

መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህር እንዲሆኑ ከአዲስ አበባ ከተማ ተመልምለው በኮተቤ ሜትሮ ፖሊታን ዩኒቨርሲቲ የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች በአማርኛ ቋንቋ መሰረታዊ የእጅ ጽሁፍ ኮርስ ይሰጣል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ኮርሱን ስትሰጥ እንደተመለከተችው አብዛኞቹ ተማሪዎች በኮርሱ መጀመሪያ ላይ በተለይም የአንዳንድ ፊደል ዝርያዎችን (የ፣ደ፣ጸ፣ጨ፣ን፣ገ፣ፐ) በጽኑፍ ለይቶ ለማሳየት ይቸገራሉ (አባሪ 1ን ይመልከቱ)፡፡ ይህ ሁኔታ ተማሪዎቹ አንደኛ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ሲማሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋን (አማርኛ) ያስተማሯቸው መምህራን ሲያስተምሩ የተግባቦት ክህሎታውን እንዴት ቢጠቀሙበት ነው? ይህስ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ ከታየው ችግር ጋር ምን አይነት ተዛምዶ አለው? የሚል ጥያቄ በጥናቱ አቅራቢ ዘንድ እንዲነሳ አድርጓል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ መርምሯል፡፡

1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ

ይህ ጥናት ያነሳው መሰረታዊ ጥያቄ "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ አለ ወይ?" የሚል ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች አንስቶ መልስ ሰጥቷል፡፡

1ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴት ያለ ነው?

2ኛ. የትምህርት ደረጃ ልዩነት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት እንዲኖር አድርጓል?

2ኛ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ እንዴት ያለ ነው?

3ኛ. የትምህርት ደረጃ ልዩነት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት እንዲኖር አድርጓል?

3ኛ. በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ አለ?

1.4. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ መኖሩን መመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አንስቷል፡፡

1ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴት ያለ እንደሆነ መመርመር፡፡

2ኛ. የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑን መመርመር

3ኛ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ እንዴት ያለ እንደሆነ መመርመር፡፡

4ኛ. የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑን መመርመር

5ኛ. በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ መኖሩን መመርመር።

1.5. የጥናቱ አድማስ

ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴትነት ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ተዛምዶ ያለው መሆኑን በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው። ስለዚህም የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን እንዴትነት ከመረመረ በኋላ የተለያዩ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑንና በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር መካከል ተዛምዶ መኖሩን ተመልክቷል።

ከዚህ ውጪ ተማሪዎቹ መረጃዎችን የሚወክሉበት መንገድ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ አልተመለከተም። ምክንያቱም Hargie (2006)፣ Hargie & Dickson (2005)ና Akpınar (2009) እንደገለጹት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በትምህርት የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በተግባራዊ ልምምድ፣ በግብረመልስና በጽብረቃ ሊዳብር የሚችል ሙያዊ ክህሎት ነው። ከዚህ አንጻር መጠናት የሚገባው ሙያዊ ስልጠና ወስደው በማስተማር ሙያ ላይ የተሰማሩት መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ነው። እንዲሁም ተማሪዎቹ መረጃ በሚወክሉበት መንገድ ላይ ችግር ቢኖር እንኳ መምህራኑ የተግባቦት ክህሎታቸውን ተጠቅመው ችግሩን ሊያቃልሉት እንደሚገባ Wrench et al. (2009)ና Brok, Brekelmans' & Wubbels (2007) ያስገነዝባሉ።

ከዚህ በተጨማሪ የመማሪያ መጻህፍቱ አዘገጃጀት፣ የክፍለ ጊዜ ስርጭት፣ የፈተና አዘገጃጀት፣ የመምህራኑን የትምህርት አይነት እውቀትና አስተዳደራዊ ጉዳዮች በመማር ማስተማሩ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ቢሆኑም በዚህ ጥናት አልተመረመሩም። ለዚህ ምክንያቱ ጥናቱ ያተኮረው መምህራኑ ራሳቸው በመረጃ ግብይት ሂደት የመረጃ ፍሰትን በሚያሳልጡበት መንገድና በክፍል ውስጥ በሚከናወነው መስተጋብር ላይ ብቻ መሆኑ ነው። እንዲሁም የተማሪዎቹ ዳራ፣ ግለ ግንዛቤ፣ አመለካከት፣ ጾታ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ትምህርቱን እንደ አፍ መፍቻ ወይም እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት መሆን አለመሆኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። መምህራን የተግባቦት ክህሎትን በአግባቡ በመጠቀም ይህ ተጽእኖ እንዲቀንስና የመረጃ ፍሰቱ እንዲሳለጥ ማድረግ

እንደሚጠበቅባቸው Wrench et al. (2009)ና Samson & Collins (2012) ያስገነዝባሉ፡፡ ስለዚህም በጥናቱ አልተዳሰሱም፡፡

Khan, Khan, Zia-Ul-Islam & Khan (2017) እንደገለጹት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከመምህራኑ የማዳመጥ፣ የማንበብ፣ የመናገርና የመጻፍ ክሂሎች ጋር ተያያዥነት ቢኖረውም በመማር ማስተማሩ ሂደት አብዛኛውን ጊዜ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ትምህርታዊ መረጃን የሚለዋወጡበት በክፍል ውስጥ በሚከናወን አንደበታዊ የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ ስለዚህም መምህራንና ተማሪዎች በጽሁፍና በንባብ የሚያደርጉት ተግባቦት በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ተጽእኖ የሚያሳደር ጉዳይ ቢሆንም በመረጃ አያያዝ ላይ ሊከተል የሚችለውን መዝረክረክ ከግንዛቤ በማስገባት በዚህ ጥናት አልተዳሰሰም፡፡ ጥናቱ ከአንደበታዊ ተግባቦት ጋር ግንኙነት ባላቸው ክንውኖች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡

የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም መምህራን በስልጠና የሚያዳብሩት ችሎታ በመሆኑ የመምህራን የስልጠና ሁኔታ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር መሆኑን Hargie (2006)፣ Hargie & Dickson (2005)ና Akpınar (2009) ከገለጹት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ርእሰ ጉዳዩ ያለው ስፋትና ጥልቀት ለመረጃ አያያዝ የማያመች ከመሆኑም በላይ ባለው የጊዜ የገንዘብና የሰው ሀይል አቅም ጥናቱን ማከናወን አስቸጋሪ ስለሚሆን በዚህ ጥናት በከፍተኛ ትምህርትና በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ የሚሰጠው የስልጠና ሁኔታ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ መዳሰስ አልተቻለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ መስተጋብር በተማሪዎችና በመምህራን፤ በተማሪዎች መካከል እርስ በእርስ እንዲሁም በተማሪዎችና በማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ይከሰታል (Gibbons, 2006; Rahman, 2014)፡፡ ከነዚህ መካከል ይህ ጥናት የተመለከተው በተማሪዎችና በመምህራን እንዲሁም በተማሪዎች መካከል ያለውን የእርስ በእርስ መስተጋብር ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ የትምህርት ስርአት የማስተማሪያ መሳሪያዎችን የሚያዘጋጁት ትምህርቱን የሚያስተምሩት መምህራን ሳይሆኑ ሌሎች የማስተማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች ናቸው፡፡ እነዚህ የማስተማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች ትምህርታዊ መረጃዎችን ወደ ማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ተገልጋዮች ያስተላለፉበት መንገድ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴትነትና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴትነት ላይ ያሳደረው ተጽእኖ በዚህ ጥናት ቢዳሰስ ጥናቱን በጣም ሰፊና ለመረጃ መዝረክረክ የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ የተግባቦት ክህሎታቸውን በአግባቡ በጥቅም ላይ በማዋል ተጽእኖውን መቆጣጠር የሚችሉ መሆኑን Nunan (2001) ያስገነዝባሉ፡፡ ስለዚህም የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት በመምህራኑ የተግግበቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ በዚህ ጥናት አልተዳሰሰም፡፡

Larsen-Freeman (1990)፣ Harmer (1991)፣ Doff (1995)ና Laber (1996) ከተገለጹት ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ ትምህርት ሂደት አጠቃላይና ውሱን ገጽታዎች አሉት፡፡ አጠቃላይ ገጽታዎች የሚባሉት ለተወሰኑ የእውቀት ዘርፎች ወይም ክሂሎች ውሱን ያልሆኑና የትኛውም አይነት የእውቀት ዘርፍና ክሂል በትምህርትነት ቢቀርብ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው፡፡ ውሱን ገጽታዎች የሚባሉት ደግሞ የተወሰኑ የቋንቋ ክሂሎች ወይም የእውቀት ዘርፎች በትምህርትነት ሲሰጡ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ያነሳው ርእሰ ጉዳይ የመማር ማስተማር ሂደትን በተግባቦት ስርአትነቱ የተመለከተ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ እያንዳንዱ ክሂል በትምህርትነት የሚሰጥት ሁኔታ ቢዳሰስ ርእሰ ጉዳዩ ሰፊ ከመሆኑ አንጻር የጥናት መለጠጥና የመረጃ መዝረክረክ ይከሰታል፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት አጠቃላይ በሆኑት የመማር ማስተማር ሂደት ገጽታዎች ላይ አተኩሯል፡፡

ይህ ጥናት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የተከናወነውን መማር ማስተማር ተመልክቶ መምህራኑ የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ በስራ ላይ የሚያውሉትን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴትነት፤ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን እንዴትነት፤ የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑን እንዲሁም በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ መኖሩን መርምሮ በሳይንሳዊ ንድፈ ሀሳቦች ላይ የተመሰረተ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል፡፡

- በጥናቱ የተደረሰበትን ውጤት መነሻ በማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ጠንካራው የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ደካማ ጎኑ ደግሞ እንዲስተካል ለማድረግ የሚያስችል መጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፡፡
- በጉዳዩ ላይ መረጃ ማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወነውን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር አስመልክቶ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፡፡
- በጉዳዩ ላይ መረጃ ለሚፈልጉ ሁሉ የጥናቱን ውጤት መነሻ በማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ተገቢውን ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል የመፍትሄ ሀሳብ ይሰነዝራል፡፡
- በጥናቱ የተደረሰበትን ውጤት መነሻ በማድረግ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ለሚያሰለጥኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ

መስተጋብር አተገባበሩ ረገድ መምህራንን በሚያሰለጥኑበት ሁኔታ ላይ ሊመረመሩ ስለሚገባቸው ጉዳዮች የተመለከቱ ጠቃሚ መረጃዎች ይሰጣል፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ለሚያሰለጥኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ተሳታፊዎችና በመምህራን ስልጠና ረገድ ፖሊሲ ለሚቀርጹ አካላት የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ትኩረት ሊደረግባቸው ስለሚገባቸው ጉዳዮች ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፡፡
- በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት መሻሻል አወንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- በቀጣይ በመስኩ ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

1.7. የጥናቱ ውሱንነት

ይህ ጥናት ሲከናወን በመረጃ ምንጭና በመረጃ አሰባሰብ ረገድም ያጋጠሙ ችሮች ነበሩ፡፡ በጥናቱ ዳራ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመማር ማስተማር ሂደትን በተግባቦት ሂደትነቱ የተመለከተ የምርምር ርእሰ ጉዳይ አዲስ እንደ መሆኑ መጠን ይህ ጥናት ሲጠና በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተጻፉ ድርሳናትን በተለይም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ የተጻፉ የመረጃ ምንጮችን እንደልብ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ነበር፡፡ በመሆኑም በስነትምህርትና በሌሎች የጥናት መስኮች የተጻፉ ምንጮችን በመጠቀም ችግሩን መቅረፍ ግድ ብሏል፡፡ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴትነትና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር እንዴትነት ላይ ለሚደረግ ጥናት መረጃዎች በምልከታ እንዲሰበሰቡ ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ተጠኝዎች በቪዲዮ ካሜራ መቀረጽ አለመፈለጋቸው በጥናቱ ሂደት ያጋጠመ ሁለተኛው አብይ ችግር ነበር፡፡ ስለዚህም በናሙናነት በተመረጡት ወረዳዎች ካሉ ትምህርት ቤቶች በመረጃ አሰባሰብ ሂደት በቪዲዮ ካሜራ ለመቀረጽ ፈቃደኛ ሆነው የተገኙ ተጠኝዎችን በሙሉ በናሙናነት በመውሰድ ችግሩን ለመቅረፍ ተችሏል፡፡

1.8. የቁልፍ ሀሳቦች ትርጓሜ

የተግባቦት ክህሎት፡- የተግባቦት ክህሎት የሚባለው በመማር ማስተማር ሂደት የመረጃ ፍሰትን የሚያሳልጥ፤ በትምህርት የሚገኝ፤ በእውቀት የሚጎለብት፤ እንዲሁም በተግባራዊ ልምምድ፣ በግብረመልስና በጽብረቃ የሚዳብር ችሎታ ነው፡፡ መረጃዎችን በምልክት ወክሎ ወደ ተግባቦት ሂደት ተሳፊዎች ለማድረስ ያስችላል፡፡

የክፍል ውስጥ መስተጋብር፡- የክፍል ውስጥ መስተጋብር የሚባለው በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚተላለፉት መረጃዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የማስተማር ስልቶችን በመጠቀም

የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች ሀሳብ ለመለዋወጥ የሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ነው። በክንውኑ ሂደት ትምህርታዊ መረጃ በአመዛኙ በንግግር በሚከናወን የሀሳብ ልውውጥ የሚቀርብ ሲሆን ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ትምህርታዊ መረጃ ረገድ የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጡና የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ምእራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት

2.1. የትምህርታዊ ተግባቦት መሰረተ ሀሳብ

2.1.1. የትምህርታዊ ተግባቦት ምንነት

የትምህርታዊ ተግባቦት መሰረተ ሀሳብ የመነጨው ከተግባቦት መሰረተ ሀሳብ በመሆኑ ምንነቱን ለመረዳት የተግባቦትን ምንነት መረዳት ያስፈልጋል (Wrench et al. 2009)።

ምሁራን ለተግባቦት የተለያዩ ብያኔዎችን የሰጡ ሲሆን ብያኔዎቹ እንደየ ዘመኑ ወደ ተለያዩ የትኩረት ነጥቦች ያዘነበሉ ናቸው። Fluharty & Ross (1981:7) "ተግባቦት መልእክትን ማእከል አድርገው መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ በአንድ በተወሰነ የመልእክት መተላለፊያ አማካኝነት ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያከናውኑበት ሂደት ነው።" ብለውታል። እንዲሁም Khattak, Yaqoob & Basri (2003) ተግባቦት የጋራ ተረዳድቶ ላይ ለመድረስ የሚያስችል በግብይት የሚከናወኑ ተግባራት ሂደት ሲሆን ተሳታፊዎቹ መረጃን የሚቀበሉበትና የሚተረጉሙበት ብቻ ሳይሆን ፍቺን የሚያፈልቁበት፣ የሚያጎለብቱበትና የሚጋሩበትም ሂደት ጭምር መሆኑን አስገንዝበዋል። Rosenbaum (2005)ም እንደዚሁ ስርዓታዊ በሆነ ሁኔታ ቃላዊ ወይም ኢቃላዊ በሆነ መንገድ መረጃ የሚተላለፍበት ሂደት መሆኑን ገልጸዋል። እንደዚሁም McPheat (2010:9) ተግባቦት የሀሳቦች መፍለቅና መጋራት የሚከናወንበት ሂደት መሆኑን የገለጹ ሲሆን Barker (2011:1) ደግሞ "መረጃን የማስተላለፍና የመቀበል ተግባር ነው።" ብለውታል።

እነዚህ ምሁራን ከሰጧቸው ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው ተግባቦት ሰዎች በአንድ በተወሰነ አውድ ውስጥ በሚከናወን ማህበራዊ መስተጋብር ቃላዊ ወይም ኢቃላዊ በሆነ መንገድ የወል የሆኑ ምልክቶችን፣ የአካል እንቅስቃሴዎችንና በአካል ላይ የሚነበቡ ስሜቶችን በመጠቀም እርስ በእርስ መረጃ የሚለዋወጡበት፣ የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበትና እውቀትን የሚገነቡበት ሂደት ነው። ይህ ሂደት መረጃን የማስተላለፍ፣ የመቀበል፣ የመተርጎምና የጋራ ግንዛቤን የመጨበጥ ተግባር ይከናወንበታል። ስለዚህም የመስተጋብሩ ተሳታፊ የሆኑት ሰዎች የመረጃ አስተላላፊነትንና የመረጃ ተቀባይነትን ሚና ይጫወታሉ። ወደ መልእክት ተቀባዮቹም ሆነ ወደ መልእክት አስተላላፊዎቹ መረጃ የሚፈሰው በአንድ ጊዜ በመሆኑ ሁለቱም በተመሳሳይ ጊዜ መረጃን አፍልቀው ያስተለላፋሉ፤ ሌሎች የሚያስተላልፉትንም መረጃ ይቀበላሉ፤ እርስ በእርስ ሀሳብ ይለዋወጣሉ፤ የጋራ መግባባት ላይ ሲደርሱም መረጃን ይጋራሉ።

ይህም ተሳታፊዎቹ በአንድ ጉዳይ ላይ የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡ የሚያደርጋቸው ሲሆን የተግባቦቱን ሂደት ግብይታዊ ያደርገዋል።

McKenna (1998)ና Barker (2007) እንደገለጹት ተግባቦት የሚለው ቃል የመጣው ኮሚዩኒስ "communis" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን "መጋራት" የሚል ፍቺ አለው። ስለዚህ ተግባቦት ማለት በአንድ ጉዳይ ላይ ፍቺን የመጋራትና የጋራ ግንዛቤን የመጨበጥ ሂደት ነው። ይህም Khattak et al. (2003)፣ Dixon & Hara (2006)ና Barker (2011) እንደገጹት የጋራ ግንዛቤ መፍጠር መቻልን የተግባቦት መሰረታዊ ነገር ያደርገዋል። የጋራ ግንዛቤን ለመጨበጥ ዋና መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ቋንቋ ሲሆን ተግባቦት ሊኖር የሚችለው የተግባቦቱ ተሳታፊ የሆኑት ሰዎች በተግባቦቱ ሂደት መልእክትን በምልክት ወክለው ሲያስተላልፉ፣ የተላለፈውን መልእክት ሲረዱ፣ እርስ በእርስ መረጃን ሲለዋወጡና አንዳቸው የሌሎቹን ሀሳብ ሲገነዘቡ ነው።

ሰዎች ህልውናቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ በተግባቦት ሂደት ተሳታፊ መሆን ግድ እንደሚላቸው Dixon & Hara (2006) ከገለጹት ሀሳብ መረዳት ይቻላል። የሰው ልጆች በሚኖሩበት ማህበራዊ አካባቢ ጤናማ ማህበራዊ ህይወት እንዲኖራቸው፣ በተሰማሩበት የስራ መስክ ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን እንዲችሉና በሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉ ስኬትን እንዲገበዩ ከመሰሎቻቸው ጋር ማህበራዊ መስተጋብርን ማከናወን፣ መረጃዎችን መለዋወጥና አንደኛው የሌላውን ሀሳብ መረዳት መቻል ይጠበቅባቸዋል። በተፈጥሯቸው ማህበራዊ እንደ መሆናቸው መጠን መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የግድ እርስ በእርስ መግባባት ይጠበቅባቸዋል። መግባባታቸው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤዎችን እንዲጨብጡና በሚያከናውኗቸው ተግባራት ረገድ ሁሉ ስኬታማነትን እንዲገበዩ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል። ሰዎች ከሰዎች ጋር ካልተግባቡ ግላዊ የሆኑትንም ሆነ ማህበራዊ የሆኑትን ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ይቸገራሉ።

ትምህርታዊ ተግባቦት የመማር ማስተማር ሂደት ተሳታፊ የሆኑት መምህራንና ተማሪዎች መረጃዎችን የሚለዋወጡበትና የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሂደት ነው (Kumpulainen & Wary, 2004; Schwarz, Dreyfus & Hershkowitz, 2009; Wrench et al., 2009; NCLRC, 2014)። ግቡ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በቀሰሙት እውቀት አማካኝነት እውቀታቸውን እንዲገነቡና በህይወት ዘመናቸው ከመማሪያ ክፍል ውጪ በሚያደርጉት ማህበራዊ መስተጋብር በገነቡት እውቀት እንዲጠቀሙ አእምሯቸውን ማስላት ነው። ይህ ወደ ቋንቋ ትምህርት ሲመጣ የቋንቋ ትምህርት ግብ ተማሪዎች በትምህርትነት በቀረበላቸው የቋንቋ አይነት የዳበረ የተግባቦት ችሎታ እንዲኖራቸውና ባካበቱት እውቀት ከመማሪያ ክፍል ውጪ ወይም በስራ አለም በሚሰማሩበት ጊዜ በሚያደርጉት መስተጋብር እንዲጠቀሙበት ማድረግ ነው ተብሎ ሊገለጽ ይችላል ።

የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መምህራን ለተማሪዎች ምን እንደሚያስተምሩ መርጠውና አደራጅተው ተማሪዎቻቸው ሊገነዘቡት በሚችሉበት መንገድ ያቀርባሉ፤ ተማሪዎችም የቀረበላቸውን ትምህርታዊ ተግባር በተሰጣቸው ትምህርታዊ መመሪያ መሰረት ያከናውናሉ፡፡ ይህ ተግባር የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲገነዘቡ የሚጠበቀውን ጽንሰ ሀሳብ እንዲገነዘቡ፣ መጨበጥ የሚገባቸውን እውቀት እንዲጨብጡና ማዳበር የሚገባቸውን ክሂል እንዲያዳብሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ ስለዚህም ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት የሚባለው መምህራንና ተማሪዎች የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊ በመሆን ትምህርታዊ መስተጋብርን የሚያከናውኑበት፣ አዳዲስ ግንዛቤዎችን የሚጨብጡበት፣ የአሰራር ክሂሎችን የሚያዳብሩበት፣ አዳዲስ መልእክቶችን የሚገነዘቡበት፣ ሀሳብ የሚጋሩበት፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት፣ እውቀታቸውን የሚገነቡበት፣ ግንዛቤያቸውን አስመልክቶ ግብረመልስ የሚሰጣጡበትና ስብእናቸው የሚቀረጽበት የመማር ማስተማር ሂደት መሆኑን Khattak et al. (2003)፣ Wrench et al. (2009) ያስገነዝባሉ፡፡

ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎቹ የሆኑት መምህራንና ተማሪዎች ውጤታማ የሆነ የእርስ በእርስ ግንኙነት የሚመሰርቱበትና የሚማማሩበት ነው (Khattak et al., 2003; Akpınar, 2009; Wrench et al., 2009)፡፡ ውጤታማነቱ የተግባቦቱ ሂደት አመራር ሰጪ የሆኑት መምህራን በሚሰጡት ትምህርታዊ አመራርና ተማሪዎቹ በሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ላይ ይመሰረታል፡፡ በተማሪዎቹ ላይ በሚታየው የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ፣ በክፍል ውስጥ በሚያሳዩት የትምህርታዊ ተግባራት አተገባበርና በትምህርታቸው በሚያስመዘግቡት ውጤት ይገለጣል፡፡ በሌላ አገላለጽ በትምህርቱ ሂደት የሚተላለፈውን የትምህርት ይዘት ተማሪዎቹ ከተገነዘቡትና የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ካመጡ በእርግጠኝነት የተግባቦቱ ሂደት ግቡን መትቷል ብሎ መናገር ይቻላል ፡፡

ውጤታማ የሆኑ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር የተግባቦት ሂደት መዘውሮች ናቸው (Khattak et al., 2003; Wrench et al. 2009)፡፡ የተግባቦቱ ሂደት የሚፈለገውን ውጤት አስገኝቶ ተሳታፊዎቹ በአንድ የትምህርት ርእሰ ጉዳይ ላይ የጋራ መረጃ እንዲኖራቸውና ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፡፡ እንደዚህ አይነት መምህራን መማርና ተግባቦት እርስ በእርስ የተሳሰሩ መሆናቸውን የተገነዘቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚያስተምሩት ጉዳይ በተማሪዎቹ ዘንድ መስረጽ የሚችል ስለመሆኑ፤ ተማሪዎቹ የሚያከናውኗቸው ተግባራት የሚፈለገውን ክሂልና ግንዛቤ የማስጨበጥ ብቃት ያላቸው ስለመሆናቸው፤ በትምህርት ድባብ ውስጥ ተገቢ የሆነው መስተጋብር በጥቅም ላይ እየዋለ ስለመሆኑ ይጨነቃሉ፡፡ ምክንያቱም ተግባቦት ማለት መልእክትን በምልክት ወክሎ ማስተላፍ ብቻ ሳይሆን፤ የተግባቦቱ ተሳታፊዎች የሚጠበቅባቸውን ሀላፊነት እንዲወጡ ማድረግን፤ ተሳታፊዎቹ በሚያከናውኗቸው ተግባራት አማካኝነት የተላለፈውን መልእክት

መረዳታቸውን ማረጋገጥን፤ እንዲሁም መልእክቱን ተሳታፊዎቹ በቀላሉ ሊገነዘቡት የሚችሉት መሆን አለመሆኑን መገምገምን ይመለከታል። ስለዚህም አስተዋይነት በተሞላበት ሁኔታ በተግባቡቱ ሂደት ምን አይነት መረጃ እንዴት ባለ መንገድና እንዴት ባለ ትምህርታዊ መስተጋብር ለተማሪዎች መድረስ እንዳለበት ይወስናሉ ።

2.1.2. የትምህርታዊ ተግባቦት መሰረታዊ ነገሮች

መማር ማስተማር የተግባቦት ሂደት እንደመሆኑ መጠን ይህ ጥናት Wrench et al. (2009)ና McPheat (2010) ያቀረቡትን ሀሳብ በማቀናጀት በውስጡ ሰባት መሰረታዊ ነገሮች አሉት የሚለውን ሀሳብ መነሻ ያደርጋል። እነዚህም የትምህርት አውድ (የተግባቦት አውድ)፣ መምህሩ/ተማሪ (መልእክት አስተላላፊ)፣ የትምህርት ይዘት (መልእክት)፣ የትምህርት አቀራረብ ስልት (የመልእክት መተላለፊያ)፣ ተማሪ/መምህር (መልእክት ተቀባይ)፣ ግብረመልስና በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ የተግባቦት እንቅፋት ናቸው። ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት የሚባለው በእነዚህ መሰረታዊ ነገሮች መረጃ የሚያልፍበትና የተግባቦቱ ተሳታፊዎች የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሂደት ነው።

ትምህርታዊ ተግባቦት የሚካሄድበት ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ የትምህርት አውድ ተብሎ ይጠራል (Wrench et al., 2009)። Fisher & Frey (2010) እንደገለጹት በመደበኛ የመማር ማስተማር ሂደት ይህ አውድ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገለጣል። የትምህርት አውድ በተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ስለዚህም ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ውጤታማ እንዲሆንና በተማሪዎቹ ላይ የሚፈለገውን የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት እንዲችል አውዱ ምቹና ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት ለማከናወን የሚያስችል መሆን መቻል ይኖርበታል። የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖርም የአውዱ መኖር ግድ ይላል (McLeod et al., 2003; Fisher & Frey, 2010; Wrench et al., 2009)።

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ሲከናወን ትምህርታዊ አመራር የሚሰጡት፤ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ማድረስ የሚያስችል የትምህርት ይዘት መርጠው የሚያቀርቡት፤ እንዲሁም ተገቢ በሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅመው በማስተማር ሂደት ትምህርታዊ መልእክት ወደ ተማሪዎቹ እንዲደርስ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹት መምህራን ናቸው (Wrench et al., 2009; Fisher & Frey, 2010)። ስለዚህም ያላቸው የትምህርት አይነት እውቀት፣ የሙያ ክህሎት፣ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም፣ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራትና የግብረመልስ አሰጣጥ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውጤታማነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። መምህራን የትምህርቱን ዓላማ መነሻ አድርገው ትምህርታዊ መረጃን በምልክት

ወክለው በመልእክትነት ወደ ተማሪዎቻቸው በማስተላለፍ የተግባቡን ሂደት የማስጀመር ኃላፊነትን ይወጣሉ። በሂደቱም ትምህርታዊ መረጃ ወደ ተማሪዎቻቸው እንዲደርስና ተማሪዎች እርስ በእርስም ሆነ ከመምህራን ጋር መረጃ እንዲለዋወጡ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናሉ። ስለዚህም ተማሪዎቹን በመረጃ የሚሞሉ ሳይሆኑ የተለያዩ የትምህርት ተግባራትን ቀርጸው ወደ ተማሪዎቹ በማድረስ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ መስተጋብር የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ፣ በክፍል ውስጥ እንዲኖር የሚጠበቀው መስተጋብር በሚፈለገው መንገድ መከናወኑን የሚከታተሉ፣ ከተማሪዎቻቸው መረጃን የሚቀበሉና ግብረመልስ የሚሰጡ የተግባቡ ሂደት ተሳታፊዎች ናቸው (Robinson, 1994; Fisher & Frey, 2010)።

የትምህርት ይዘት በትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ቃላዊና ኢቃላዊ በሆነ ምልክት ተወክሎ በትምህርታዊ መረጃ መገበያያዎች አማካኝነት ከመምህራን ወደ ተማሪዎች፣ ከተማሪዎች ወደ መምህራንና ከተማሪዎች ወደ ተማሪዎች የሚተላለፈው ትምህርታዊ መረጃ ወይም መልእክት ነው። ይህ መልእክት Wrench et al. (2009) Bloom et al. (1956)ን በምንጭነት ጠቅሰው እንደገለጹት በብሉም የትምህርት ይዘት ፍረጃ መሰረት በሶስት የሚፈረጁ የትምህርት ግቦችን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ሊሆን ይችላል። እነዚህም አእምሯዊ፣ ሕውስታዊና ስሜታዊ የእውቀት ፈርጆች ናቸው። አእምሯዊ የሚባሉት ነገሮችን የማወቅ፣ የመረዳት፣ የመተንተን፣ የመፈረጅና በአንድ በተወሰነ ማስረጃ ወይም እውቀት ላይ ተመስርቶ መገምገምን የተመለከቱ የእውቀት ዘርፎች ናቸው። አመለካከታዊ የሚባሉት ነገሮችን ወይም ሀሳቦችን የመቀበል፣ ያለመቀበል፣ ወይም ደግሞ አንድ የተወሰነ አይነት ስሜት የማዳበርን ሁኔታ የተመለከቱ ሲሆኑ ሕውስታዊ የሚባሉት ደግሞ አእምሮንና አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በማጣመር የሚከናወኑ ተግባራትን የተመለከቱ ናቸው።

ይህ ከቋንቋ ትምህርት አንጻር ሲታይ አንድ ተማሪ አንድ የሽለላ ግጥም ከነአተገባበሩ ከሚከወንበት ማህበራዊ አጋጣሚ ተምሮ ቢቀሰቀስና እየተንጎራደደ ቢሸልል ሕውስታዊ እውቀቱ ተተግብሯል ማለት ነው። ይኸው ተማሪ ግጥሙን ሰምቶ የግጥሙን ይዘትና ቅርጽ ተንትኖ ቢረዳውና ግጥሙን ከግጥም አጻጻፍ መስፈርት አኳያ ቢገመግም አአምሯዊ እውቀቱ ዳብሯል ማለት ነው። ከዚህ ባሻገር ግጥምን የመውደድ ስሜት ቢያድርበትና ገጠመኞቹን በግጥም የመግለጽ ባህሪን እያዳበረ ቢመጣ በግጥም ረገድ የዚህ ተማሪ አመለካከታዊ እውቀት ዳብሯል ማለት ነው። በመማር ማስተማር ሂደት ቋንቋም ሆነ ሌሎች የትምህርት አይነቶች በትምህርትነት ሲቀርቡ የትምህርት ይዘቱ መቅረብ ያለበት ለሶስቱ የእውቀት ፈርጆች ትኩረት በሰጠ ሁኔታ መሆን እንደሚኖርበት Wrench et al. (2009) ያስገነዝባሉ።

መምህራንና ተማሪዎች በምልክት የተወከሉት ትምህርታዊ መረጃዎች ላይ የጋራ ግንዛቤን ለመጨበጥ ይችሉ ዘንድ በክፍል ውስጥ በሚከናወን ማህበራዊ መስተጋብር ሀሳብ የሚጋሩት በማስተማር ስልቶች

አማካኝነት ነው (Harmer, 1991; Doff,1995; McLeod et al., 2003; Wrench et al., 2009)። ስለዚህም በWrench et al. (2009) እንደተገለጸው የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት መተላለፊያ ተደርገው ይወሰዳሉ። ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የሚመረጡት የማስተማር ስልቶች ከተማሪዎቹ ችሎታና ፍላጎት ጋር የሚራመዱና ተማሪዎች እርስ በእርስ በሚያደርጉት መስተጋብር እውቀትን እንዲገነቡ ወይም የሚፈለገውን ክሂል እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። በመማር ማስተማር ሂደት የተለያዩና ተማሪዎችን በመማር ማስተማሩ ሂደት ማሳተፍ የሚያስችሉ የትምህርት አቀራረብ ስልቶችን መጠቀም ትምህርቱን ተማሪዎቹ በትኩረት እንዲከታተሉትና ጥሩ የትምህርት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው፤ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር እውቀትን እንዲገነቡ፤ የመረዳዳት ስሜትን እንዲያዳብሩ፤ በራስ የመተማመን ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ፤ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ እንዲሁም ክሂሎችን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ያስችላሉ (Harmer, 1991; Doff,1995; McLeod et al., 2003)።

ተማሪዎች በትምህርት አውድ ውስጥ መምህራን በሚያቀርቡላቸው ትምህርታዊ አመራር መሰረት የቀረበላቸውን ትምህርታዊ መረጃ ማእከል በማድረግ ከመምህራንና እርስ በእርስ በሚያርጉት መስተጋብር የትምህርቱን ይዘት በመልእክትነት የሚቀበሉ፣ የተቀበሉትን ተርጉመው በመረዳት ለመልእክት አስተላላፊዎቹ ወይም ለተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች ግብረመልስ የሚሰጡና እውቀታቸውን የሚገነቡ የመማር ማስተማር ሂደት ተሳታፊዎች ናቸው (Wrench et al., 2009; Fisher & Frey, 2010; Samson & Collins, 2012)። በተግባቦቱ ሂደት የመልእክት ተቀባይነትንና የመልእክት አስተላላፊነትን ሚና ስለሚጫወቱ መልእክትን ተቀብሎ የመተርጎምና በመልክት ወክሎ የማስተላለፍን ተግባር ያከናውናሉ። እንዲሁም በትምህርታዊ መረጃዎች ረገድ ከሌሎቹ የተግባቦቱ ሂደት ተሳፊዎች ጋር የጋራ ግንዛቤን ለመጨበጥና እውቀትን ለመገንባት የሚያስችሉ ትምህርታዊ የሆኑ መስተጋብሮችን በክፍል ውስጥ ያከናውናሉ (Harmer, 991; Doff,1995; Fisher & Frey, 2010)። Samson & Collins (2012) እንደገለጹት ወደ መማሪያ ክፍል የሚመጡት የተለያዩ ልምዶችን፣ እውቀቶችንና ግለ ግንዛቤዎችን ይዘው በመሆኑ የመማር ማስተማር የተግባቦት ሂደት የተዋጣለት እንዲሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርትና ትምህርቱ የሚቀርብበት ስልት በተቻለ መጠን የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት፣ ልምድና ችሎታ ከግንዛቤ ያስገባ መሆን ይኖርበታል። ይህም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚተላለፈውን ትምህርታዊ መረጃ ተቀብለው እንዲረዱት፣ እንዲተረጉሙት፣ እንዲረዱትና የሚፈለገውን የጋራ ግንዛቤ መጨበጥ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል።

ተማሪዎች ትምህርታዊ መረጃዎችን ተቀብለው የሚረጉሙ ብቻ ሳይሆኑ ከመጀመሪያዋ መልእክት በኋላ መልእክትን በምልክት ወክለው የሚያስተላልፉም የተግባቦት ተሳታፊዎች ናቸው (Hargie & Dickson, 2005; Dixton & Hara, 2006; McPheat, 2010)። በመሆኑም መምህራን ያስተላለፏትን

የመጀመሪያዋን መልእክት ከመተርጎም አንስቶ የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን የማከናወንንና ግብረመልስ የመስጠት ተግባራትን ያከናውናሉ። ትርጎማ በመልእክት አስተላላፊው አማካኝነት የተላለፈውን መልእክት ተቀብሎ በትክክል የመተርጎም፣ የመረዳትና ከመልእክት አስተላላፊው ጋር የጋራ ግንዛቤን የመጨበጥ ሂደት ነው። በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት በተግባቦቱ ሂደት ውስጥ የመልእክት ተቀባይነትን ሚና የሚጫወቱት የተግባቦቱ ተሳፊዎች ተማሪዎችና መምህራን ሲሆኑ መልእክት አስተላላፊዎቹ ያስተላለፉትን መረጃ መረዳታቸውን በተለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ። ትርጎማ ንቁ የማዳመጥ ችሎታን፣ አንብቦ መረዳትንና እንደ አስፈላጊነቱ ማብራሪያ የመጠየቅና የመስጠት ችሎታን የሚጠይቅ ሲሆን የተግባቦቱን ተሳታፊዎች ግንዛቤን ለመጨበጥና በተጨበጠው ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ ግብረመልስ ለመስጠት ያስችላቸዋል። እንደ Harmer (1991)፣ Doff (1995)፣ Hargie & Dickson (2005)ና Samson & Collins (2012) አባባል በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተማሪዎች የትርጎማ ችግር ያለባቸው መሆኑን መምህራን ከተገነዘቡ በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ እንዲቻል ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ፣ ማብራሪያ መስጠት፣ መልእክት የወከሉበትን መንገድ ማስተካከል ወይም የትምህርት አቀራረብ ስልቱን መቀየር ያስፈልጋቸዋል።

ግብረመልስ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች በተረዱት መልእክት ወይም ባገኙት ግንዛቤ ላይ ተመስርተው እርስ በእርስ የሚሰጣጡት ምላሽ ነው (Wrench et al., 2009; Hamm, 2006)። እንደ Harmer (1991)፣ Doff (1995)፣ Hamm (2006)ና Fisher & Frey (2010) አገላለጽ በትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ግብረመልስ የሚሰጣጡት መምህራንና ተማሪዎች ሲሆኑ የሚከተሉትን ሶስት አበይት ተግባራት ለማከናወን ይጠቅማል። በመጀመሪያ ደረጃ ለመምህራን ያቀረቡትን ትምህርት ተማሪዎቹ በሚገባ የተረዱት መሆን አለመሆኑን ለመገምገም ያስችላል። በሁለተኛ ደረጃ መምህራኑ ትምህርታዊ መረጃውን ወደ ተማሪዎቹ ለማድረስ የተጠቀሙበት የተግባቦት ክህሎትና የትምህርት አቀራረብ ስልት ተገቢ መሆን አለመሆናቸውን እንዲሁም የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት መቻል አለመቻላቸውን እንዲገመግሙ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በመጨረሻም ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት ባከናወኗቸው የተለያዩ ተግባራት ላይ ተመስርቶ ከመምህራን ተገቢውን ግብረመልስ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችላል። በጥቅሉ በትምህርትነት በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ረገድ ተማሪዎቹና መምህራኑ የጋራ ግንዛቤ የጨበጡ መሆን አለመሆኑን ለማወቅና ተገቢውን ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ ማግኘት የሚያስችል የተግባቦቱ ሂደት መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን ከገለጹት ሀሳብ መረዳት ይቻላል።

የመማር ማስተማር ሂደት የተግባቦት እንቅፋቶች የሚባሉት በተግባቦቱ ሂደት ውስጥ መረጃ ከመልእክት አስተላላፊዎቹ ወደ መልእክት ተቀባዮቹ ሲተላለፍ በትምህርቱ አውድ ውስጥ በሚፈጠሩ እንከኖች

የተነሳ የትምህርቱ ሂደት በሚፈለገው ደረጃ ውጤት እንዳያስገኝ ወይም ሙሉ በሙሉ ውጤት አልባ እንዲሆን የሚያደርጉ መሰናክሎች ናቸው (Harmer, 1991; Khattak et al., 2003; Hamm, 2006; Wrench et al., 2009; Fisher & Frey, 2010)። እነዚህ መሰናክሎች በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ በሚያስመዘገቡት ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ። የሚመነጩት ከዓላማ አነዳደፍ፣ ከተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም፣ ከማስተማሪያ ዘዴዎች አጠቃቀም፣ ከክፍል አያያዝ፣ ከግብረመልስ አሰጣጥ፣ ከትምህርቱ አውድ ምቹነት፣ ከማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም፣ ከተማሪዎቹና ከመምህራኑ የመልእክት አተረጓጎም ወይም ተማሪዎቹና መምህራኑ ለትምህርት አይነቱ ካላቸው አመለካከትና ተነሳሽነት ሊሆን ይችላል።

2.2. የተግባቦት ክህሎት

የተግባቦት ክህሎት በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ረቂቅ የሆነውን ትምህርታዊ መረጃ ተስተዋይ በሆኑ ምልከቶች በመወከል በተሳታፊዎቹ መካከል የሚከናወነው የመረጃ ልውውጥ ሂደት በተሳለጠ ሁኔታ እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታን የሚያስችል የመምህራን ችሎታ ነው (McKenna, 1998; Sultmann & Burton 2003; Wrench et al., 2009)። በትምህርትና በስልጠና የሚዳብር ሲሆን በጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል (Muste, 2016)። ምክንያቱም Creese (2005)፣ Mackay (2006)ና Schwarz et al. (2009) እንደገለጹት መምህራን የመማር ማስተማሩ ሂደት አመራር ሰጪዎች በመሆናቸው ትምህርታዊ አመራርን በመስጠት ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከግብ የሚያደርሱ ተግባራትን ያለምንም ችግር ማከናወን እንዲችሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት መልእክትን በምልክት ወክለው ያስተላልፋሉ። እንዲሁም በማስተማር ስራ የተሰማሩ ሰዎች ውጤታማነት የሚመሰረተው በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ላይ በመሆኑ የተግባቦት ክህሎትን በጥሩ ሁኔታ መጠቀም የሚችሉ መምህራን ለትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ (Hargie, Dickson &Tourish, 2004; Hargie, 2005) ።

ትምህርታዊ የተግባቦት ክህሎት በሌሎች የሙያ መስኮች የተሰማሩ ባለሙያዎች ከሚገለገሉበት የተግባቦት ክህሎት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በአጠቃቀም፣ በሚከሰቱበት አውድና ከግብ እንዲደርስ በሚፈለገው የተግባቦት ዓላማ የሚለያይ መሆኑን Hargie (2006)፣ Wrench et al. (2009)ና Barker (2011) ከገለጹት ሀሳብ መረዳት ይቻላል። የሁሉም ባለሙዎች የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ተመሳስሎ በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መካከል የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ማድረግ ማስቻሉ ነው። ልዩነታቸው ደግሞ ትምህርታዊ የሆኑ የተግባቦት ክህሎት መማር ማስተማር በሚከናወንበት የትምህርት አውድ ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቡድን ተብለው ሊጠሩ በሚችሉ ሰዎች መካከል ትምህርታዊ መስተጋብር ሲከናወን በመስተጋብሩ ተሳታፊዎች መካከል

የሚኖረውን የመረጃ ፍሰት ያሳልጣል። በሌሎች የሙያ መስኮች ሙያው በሚተገበርበት አውድ ውስጥ በመከሰት በተግባቡቱ ሂደት ከግብ ማድረስ የሚፈለገውን የተግባቦት ግብ ለማሳካት በጥቅም ላይ ይውላሉ። ለምሳሌ ያህል በትምህርት አውድ ውስጥ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በጥቅም ላይ ሲውል፣ በህክምና ሙያ በሀኪምና በታካሚ መካከል እንዲሁም በአስተዳደር ሙያ በአመራር ሰጪዎች፣ በሰራተኞችና በደንበኞች መካከል የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ ያገለግላል።

በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን በጥቅም ላይ የሚያውሉት የተግባቦት ክህሎት የሚከተሉትን ሁለት አበይት ዘርፎች ሊይዝ ይችላል (Hargie & Dickson, 2005; Akpınar, 2009)::

2.2.1. ቃላዊ መግባቢያዎች

ቃላዊ መግባቢያዎች የሚባሉት ሰዎች ቃላትን በመጠቀም መረጃ የሚለዋወጡባቸው መንገዶች ሲሆኑ የተግባቡቱን ተሳታፊዎች የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የተመለከቱ ናቸው (Barker, 2011; Dixton & Hara, 2010; McPheat, 2010)። ጥሩ የሆነ የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም መልእክት በሚተላለፍበት ጊዜ ተገቢ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀምን በጥቅም ላይ ማዋል መቻል ነው። እንየትኛውም የተግባቦት ሂደት በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት የሚፈለገውን ግብ ማግኘት እንዲቻል ቀላል፤ የተግባቡቱ ተሳታፊዎች በቀላሉ የሚረዱትና አግባቢ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም በጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል (Hargie et al., 2004; Hargie; 2005)። በጥቅም ላይ የሚውለው ቋንቋ ግልጽ ካልሆነላቸው የተግባቡቱ ተሳታፊዎች ንቁ ተሳታፊ ከመሆን ወደ መታቀብ ሊያመሩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ በተግባቡቱ ሂደት እንቅፋት እንዲፈጠር ያደርጋል።

ተማሪዎች ትምህርታዊ ተግባራትን በአግባቡ ማከናወን እንዲችሉ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚሰነዝሩት ሀሳብ ግልጽነት ሊኖረው ይገባል (Robinson, 2005; Wrench et al., 2009)። በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውጤታማ የሆነ የተግባቦት ሂደት እንዲኖር ለማድረግ መምህራን አጭር፣ ግልጽ፣ መደበኛ፣ ከውስብስብነት የጸዳና መልእክት ተቀባዮች በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት የቋንቋ አጠቃቀም በጥቅም ላይ እንዲያውሉ ይጠበቃል። Robinson (1994) እንዳሉት እንዲህ አይነቱ አጠቃቀም በተግባቡቱ ሂደት የሚተላለፈው መልእክት በቀላሉ መልእክት ተቀባዮች ዘንድ ደርሶ የሚፈለገውን ግብ እንዲያስገኝ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ተማሪዎቹ ምንን እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው እንዲረዱ፣ በትምህርትነት የሚቀርበውን መረጃ በቀላሉ ተርጉመው እንዲረዱትና እንዲተገብሩት ለማድረግም ያስችላል።

2.2.2. ኢቃላዊ መግባቢያዎች

ኢቃላዊ መግባቢያዎች ሰዎች በቃላት አማካኝነት የሚያስተላልፏቸው መረጃዎች የተሟሉ እንዲሆኑ የሚጠቀሙባቸው አካላዊ ቋንቋ (Body Language)ና ልዕለ ልሳናዊ ባህርያት (paralinguistics) ናቸው (Barker, 2011; Dixton & Hara, 2010; McPheat, 2010)። አካላዊ ቋንቋ የሚባሉት ሰዎች በተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ማለትም በአቋቋም፣ በገጽ ግላጼዎች (facial expressions)፣ በአይን ግጥምጥሞሽ፣ ጭንቅላትን በማወዛወዝና በማነቃነቅ መልእክትን የሚያስተላልፉባቸው መንገዶች ናቸው፡ ፡ ልዕለ ልሳናዊ ባህርያት የሚባሉትም እንደዚሁ በንግግር ሂደት በሚደመጡ ድምጸ ቅላጼዎች፣ የንግግር ፍጥነት፣ በንግግር ቆምታ፣ በድምጽ መጠን አማካኝነት መልእክት የሚያስተላልፉባቸው መንገዶች ናቸው።

ኢቃላዊ መግባቢያዎች ሰዎች በቃላት አማካኝነት የሚያስተላልፏቸውን መረጃዎች የሚደግፉ ሲሆኑ አይኖች፣ እጆች፣ እግሮች፣ አለባበስና አካላዊ ሁኔታ በአንድ ጊዜ መልእክት የሚያስተላልፉባቸው መንገዶች በመሆናቸው በመልእክት ተቀባዩ ላይ ከሚያሳድሩት ስሜት አንጻር ይተረጎማሉ (Barkai, 1990; Barker, 2011; Barry, 2011)። ሰዎች በቃላት አማካኝነት የሚያስተላልፉት መልእክት በንግግር ቅላጼ፣ በአካላዊ ምልክቶች፣ በአይን እንቅስቃሴዎች፣ በአቋቋም ሁኔታዎችና በገጽ ግላጼ ይደገፋል። እነዚህ መወከያዎች ውስጣዊ ስሜትን አውጥቶ የማሳየት ሀይል ያላቸው ሲሆኑ በመልእክት አስተላላፊዎቹ የመገራታቸው ሁኔታ ዝቅተኛ ነው። እንደ Robinson, (1994)ና McPheat (2010) አባባል በአብዛኛው ከመልእክት አስተላላፊዎቹ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ውስጣዊ ስሜትን አውጥተው ያሳያሉ። ስለዚህም አንዳንድ ጊዜ በምስጢርነታቸው ተሸፍነው እንዲቀሩ የሚፈለጉ መረጃዎችን እንኳ ሳይቀሩ ይፋ ወጥተው እንዲነበቡ ያደርጋሉ። ይህ ሁኔታ ጠንካራና ወሰን የለሽ የሚያደርጋቸው ሲሆን በባህላዊ ጉዳዮች ይወሰናሉ (Barkai, 1990; Barker, 2011)። በባህላዊ ጉዳዮች የሚወሰኑ መሆናቸው ሁሉን አቀፍና ኢሁሉን አቀፍ ተብለው እንዲለዩ ያደርጋቸዋል። ሁሉን አቀፍ የሚባሉት በሁሉም ባህሎች የጋራ የሆኑት ሲሆኑ ኢሁሉን አቀፍ የሆኑት እንደየ ባህሉ የሚለያዩ ናቸው። ለምሳሌ እያንዳንዱ ሰው ደስታውን በፈገግታ መግለጹ ሁሉን አቀፍ ነው። አለባበስ ግን እንደየባህሉ የሚለያይ በመሆኑ ኢሁሉን አቀፍ ነው።

Barkai (1990)ና Matsumoto, Ekman, & Fridlund (1991) እንደገለጹት በአካል ላይ የሚነበቡ ምልክቶች በአራት ፈርጆች ሊፈረጁ ይችላሉ። የመጀመሪያው መሳሪያዊ ግላጼ (instrumental action) ሲሆን ስሜትን ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ምልክቶችን ያካትታል። ለዚህ ጥርስን ማፋጨት፣ ከንፈርን መጠራረግና ከንፈርን መንከስ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሁለተኛው ተምሳሌታዊ ግላጼ (emblematic action) ሲሆን በትምህርት የሚገኙ፣ በአንድ ባህል ውስጥ በስፋት በጥቅም ላይ

የሚውሉና የሚሸከሙት ፍቺ በቋንቋ የሚተረጎም ግላጼዎችን ያካትታል። ለዚህ ደግሞ የአይን ጥቅሻና ምላስ ማውጣት እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሶስተኛው ጭውውታዊ ግላጼ (conversational action) ሲሆን በምልልስ ሂደት መረጃን አጉልቶ ለማሳየት የሚያገለግል ነው። የአንድ ሰውን ንግግር ለማብራራት ወይም ለመግለጥ፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለመቆጣጠር፣ ተናጋሪው ንግግሩን እንዲቀጥል ለማበረታታት፣ የበለጠ መረጃን ለመጠየቅና ንግግሩ መቋረጡን ወይም እንቅፋት የገጠመው መሆኑን ለማመልከት የሚያገለግሉ ምልክቶችን በውስጡ ይይዛል። አራተኛው ተፈጥሯዊ በሆኑ ምልክቶች የተለያዩ መረጃዎችን ማግኘት የሚያስችል ሲሆን በተፈጥሮ በአካል ላይ የሚከሰቱ ምልክቶችን በውስጡ ይይዛል። ዝምድናን፣ ዘርን፣ አመልን፣ ጾታን፣ ውበትን፣ ማራኪነትን፣ ስብእናን፣ የማሰብ ችሎታንና እድሜን ማሳወቅ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከነዚህ ኢቃላዊ ባህርያት መካከል በዚህ ጥናት ትኩረት የሚሰጣቸው ከማህበራዊ መስተጋብር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጭውውታዊ ግላጼዎች ናቸው።

ኢቃላዊ ምልክቶች አሻሚ፣ ቀጣይ፣ በተለያዩ የመልእክት መተላለፊያ መንገዶች የሚተላለፉና በባህላዊ ጉዳዮች የሚወሰኑ በመሆናቸው በተሳሳተ መንገድ ሊተረጎሙ ይችላሉ (Barkai, 1990; Barker, 2011)። ኢቃላዊ ምልክቶች አሻሚ ናቸው ማለት በትክክል የሚበይናቸው መዝገበ ቃላት የሌለ ከመሆኑም በላይ የሚያስተላልፉት መልእክት እንደየ አውዱና እንደየ አጠቃቀማቸው ሊለያይ ይችላል። መልእክት አስተላላፊነታቸው ቀጣይነት ያለው በመሆኑ መናገርን በማቆም በቃላዊ ምልክቶች የሚተላለፈውን መልእክት ማቆም ቢቻልም በኢቃላዊ ምልክቶች የሚተላለፈውን መልእክት ማቆም አይቻልም። ኢቃላዊ ምልክቶች በራሳቸው ጊዜ ተገልጠው መልእክት ማስተላለፋቸውን ስለሚቀጥሉ ከመልእክት አስተላላፊው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ውስጣዊ ስሜትን አውጥተው ያሳያሉ (Barkai, 1990; Barker, 2011; Hargie, 2011)። ቃላዊ መግባቢያዎች በሰዋስዋዊ ህግጋት የሚገዙ ሲሆን ኢቃላዊ የመግባቢያ መንገዶች በሰዋስዋዊ ህግጋት የሚገዙና በስርአት የተዋቀሩ አይደሉም። ይልቁንም በባህላዊ ጉደዮች ይወሰናሉ። ቢሆንም የዳበረ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ችሎታ ያላቸው የተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች ባህሪያቸውን በመግራት በኢቃላዊ መግባቢያዎች የሚያስተላልፉት መልእክት በቃላዊ መግባቢያዎች ከሚያስተላልፉት መልእክት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ ይተጋሉ።

እንደ McKenna, (1998)፣ Hybels & Weaver II (2004)ና McPheat (2010) አባባል በፊት ለፊት የተግባቦት ሂደት ባላቸው ሚና ከቃላዊ መግባቢያዎች ጋር ሲነጻጸሩ ኢቃላዊ መግባቢያዎች የጎላ መልእክትን የመወከል ድርሻ አላቸው። በተግባቦት ሂደት የሚተላለፍ መልእክት በሶስት መንገዶች ሊወከል ይችላል። እነዚህ መወከያዎች ቃላዊ መግባቢያዎች፣ አካላዊ ቋንቋና ልዕለ ልሳናዊ ባህርያት ናቸው። በሂደቱ ሶስቱም መንገዶች እኩል የመልእክት አስተላላፊነት ሚና ይኖራቸዋል። አካላዊ ቋንቋና ልዕለ ልሳናዊ ባህርያት ኢቃላዊ የመወከያ መንገዶች በመሆናቸው ኢቃላዊ የመወከያ መንገድ

በመልእክት ማስተላለፍ ሂደት ሰፊውን ድርሻ (66.66%) የሚሸፍን መሆኑን ምሁራኑ ከገለጹት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

2.2.3. የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ

የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት የሆነው የትምህርቱ አላማ በተማሪዎች ዘንድ ተተርጉሞ በአእምሯቸው እንዲሰርጽና የመረጃ ፍሰት እንዲሳለጥ ለማድረግ በስርአት ተቀናብሮ የሚቀርብበት መንገድ ነው (Wrench et al. 2009; Creese, 2005; Barker, 2011)፡፡ የመማር ማስተማሩ ሂደቱ ውጤታማ መሆን እንዲችል ትምህርታዊ መረጃዎች በተማሪዎች መቀሰም እንዲችሉ ተደርገው መወከልና መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መረጃዎች የሚባሉት በመማር ማስተማር የተግባበቡት አውድ ውስጥ በተሳታፊዎቹ መካከል ከምንጮቻቸው ወደ ተቀባዮቻቸው የሚፈሱ ወይም የሚንሸራሸሩ የትምህርቱን ዓላማዎች ከግብ ማድረስ የሚያስችሉ መልእክቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መልእክቶች በትምህርት ይዘትነት ተወክለው የቀረቡ የትምህርቱ ዓላማዎች ናቸው፡፡ በተሳታፊዎቹ ዘንድ የነጋሪትና የአግባቢነት ዋጋ አላቸው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወኑ ተግባራት አማካኝነት በመምህራንና በተማሪዎች ዘንድ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያደርጉ በመሆናቸው ያግባባሉ፡፡

በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት የትምህርቱ አላማ በጥሩ ሁኔታ ተነድፎ ለተማሪዎች መቅረብ ይኖርበታል (Barroso & Pon, 2004; Wrench et al, 2009; Jackson, 2011; Moss & Brookhart, 2012)፡፡ የትምህርቱ አላማ ሲነደፍ ግልጽ፣ ውሱን፣ መለካት የሚችል፣ በተወሰነ ጊዜ የሚጠናቀቅና ተተግባሪ መሆን አለበት፡፡ በትምህርትነት የሚቀርበው የትምህርት ይዘትም መምህሩ ለተማሪዎቹ የሚያሳውቋቸውን የትምህርት አላማ በመልእክትነት የተሸከመ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ሁኔታ ከተቀመጠው አላማ አንጻር ምዘናንና ጽብረቃን በጥሩ ሁኔታ ለማናወን ያስችላል፡፡ Irons (2008)ና Schwarz et al. (2009) እንዳሉት በመማር ማስተማሩ ሂደት ትምህርቱ ሲቀርብ ተማሪዎች የትምህርቱን አላማ እንዲያውቁት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለምን እንደሚማሩና ከሚማሩት ትምህርት የሚያገኙትን ጥቅም አውቀው ግብ ተኮር በመሆን ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ ግብረመልስ ሲሰጥ ከተቀመጠው ዓላማ አንጻር ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ራሳቸውን እንዲገመግሙና በአላማው ላይ ተመስርቶ የተቀረጹትን ትምህርታዊ ተግባራት ከውስጣቸው በመነጨ ተነሳሽነት እንዲያከናውኑ ለማድረግ ያስችላል (Jackson, 2011; Moss & Brookhart, 2012)፡፡ እንደ Brown (2007) አባባል ከውስጥ የመነጨ ተነሳሽነት ከተነሳሽነት አይነቶች ሁሉ ጠንካራ የሆነው የተነሳሽነት አይነት ሲሆን ከተግባሩ ውጪ ግልጽ የሆነ ሌላ መቀስቀስ

የሌለበት ነው። ሰዎች ተግባራትን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ከራስ በመነጨ ቁርጠኝነት የሚያከናውኑና የብቁነት ስሜት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ያደርጋል።

እንደ Housen & Pierrard (2005)፣ Jackson (2011)ና Moss & Brookhart (2012) አገላለጽ ተማሪዎቹ ከትምህርት ይዘት ፍቺን የሚሰርቱት ትምህርታዊ መረጃዎች በቅደም ተከተል ተደራጅተው የበለጸገ አስተሳሰብን ሚጣጣፍ በሚያስችሉ የበለጸጉ የትምህርት መሳሪያዎች አማካኝነት ሲቀርቡላቸው ነው። የትምህርት ይዘት ከሚታወቅ ወደ እማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድና ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ ተደራጅቶ መቅረብ ይኖርበታል። ይህም ተማሪዎቹ ቅደም ተከተሉን ጠብቀው ትምህርታዊ ተግባራቱን ሲያከናውኑ በጥሩ ሁኔታ ፍቺን አንዲመሰርቱ ለማድረግ ያስችላል። አለበለዚያ ተማሪዎቹ በቂ የሆነ ዳራዊ እውቀት ለሌላቸው የትምህርት ይዘት ሊጋለጡና ከሚያከናውኑት ተግባር ያልተጠቃለለ ድምዳሜ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ። ይህም የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዳይፋጠን፣ ውጤት እንዳያስመዘግብ፤ አዲስ የእውቀት ግንባታ እንዳይካሄድና የጋራ ግንዛቤ እንዳይጨበጥ ያደርጋል። በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙባቸው ጽሁፎች፣ የመልመጃ ወረቀቶች፣ የአመላክቶ ተግባራትና ድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች የበለጸገ አስተሳሰብን የሚያጣጡፉ የበለጸጉ የትምህርት መሳሪያዎች መሆን ይኖርባቸዋል (Housen & Pierrard, 2005; Moss & Brookhart, 2012)። ይህም ተማሪዎቹ አዲሱን መረጃ ፊልፍለው ማውጣት እንዲችሉ፣ በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልላቸው እንዲማሩ፣ ሂሳዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ፤ ዳራዊ እውቀታቸውን በጥቅም ላይ እንዲያውሉ እንዲሁም ንቁ ተሳታፊና ትጉህ እንዲሆኑ ለማድረግ ያስችላል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚቀርበው መረጃ ተማሪዎቹ ሀሳብ እንዲሰነዝሩና የተግባቡቱ ሂደት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ በሚያስችል መልኩ መቅረብ መቻል ይኖርበታል (Housen & Pierrard, 2005; Schwarz et al., 2009; Moss & Brookhart, 2012)። Khattak et al. (2003)፣ Rosenbaum (2005)፣ McPheat (2010)ና Barker (2011) እንዳሉት ተግባቦት የጋራ ተረዳድቶ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ሂደት ነው። በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚቀርበው ትምህርታዊ መረጃ ሀሳብ ለመሰንዘርና ለማፍለቅ በሚያስችል መንገድ መቅረቡ ተሳታፊዎቹ መረጃን መቀበልና መተርጎም ብቻ ሳይሆን ማፍለቅን፣ ማጎልበትንና መጋራትን እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ስለዚህም መረጃውን በአንድ በተወሰነ አውድ ውስጥ በሚከናወን ማህበራዊ መስተጋብር እርስ በእርስ መረጃን ይለዋወጡበታል። የጋራ ግንዛቤንም በመጨበጥ እውቀታቸውን ይገነቡበታል። ይህ አሰራር የመማር ማስተማር ሂደቱ ግብይታዊ የመረጃ ዝውውር እንዲኖረውና መምህራንና ተማሪዎች የሚያቀርቡት ሀሳብ የተግባቡቱ ሂደት ግብኣት እንዲሆን ያደርጋል።

2.2.4. የጥያቄ አጠያየቅ

የጥያቄ አጠያየቅ ትምህርታዊ መረጃዎችን ጥያቄያዊ አድርጎ የማቅረብ ችሎታ ነው (MARS, 2012; TCEA, 2013)። ጥሩ የጥያቄ አጠያየቅ ችሎታ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች ምልልስ እንዲጀምሩና በቀጣይም ምሁራዊ ትንታኔ መስጠት እንዲችሉ በር ይከፍታል። ስለዚህም መምህራንን በማስተማር ስራቸው የተዋጣላቸው ያደርጋቸዋል። ተማሪዎቻቸው የቀረበላቸውን ትምህርታዊ መረጃ በጥልቀት እንዲፈትሹ፣ ትምህርታዊ መረጃዎች ላይ ትንታኔ እንዲሰጡ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲናበቡና በትምህርቱ ሂደት ስለሚያነሷቸው ጽሁፎች እንዲያስቡ ስለሚያደርግ የተማሪዎቹ አርቆ የማሰብ ችሎታ እንዲዳብር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የትምህርቱን ይዘት መሰረት ያደረገ የክፍል ውስጥ መስተጋብር በማከናወን ደረጃውን የጠበቀ ውይይትና በይነሰባዊ ክህሎትን የሚያያዳብሩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ለማድረግም ይጠቅማል።

Robinson (1994)ና Wlodkowski & Ginsberg (2010) እንደገለጹት ተማሪዎች የተለያየ ተነሳሽነት፣ አመለካከትና ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚሰጥ ምላሽን ይዘው ወደ መማሪያ ክፍል ይመጣሉ። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት በተማሪዎች መካከል ሶስት አይነት ልዩነቶች እንዲኖሩ ያደርጋል (Brown, 2007; Hall, 2011)። የመጀመሪያው መረጃን የሚያብላሉበትና የሚገነዘቡበት መንገድ ሲሆን የመማር ዘይቤ (learning style) ልዩነት ተብሎ ይታወቃል። ሁለተኛው ደግሞ ላይ ላዩን፣ ጥልቅና ስልታዊ በሆነ መንገድ እውቀትን የሚገነቡበት መንገድ ሲሆን የመማር ዘዴ (approaches to learning) ልዩነት ተብሎ ይታወቃል። የመጨረሻው ስለእውቀት ተፈጥሮ፣ አገነባብና አገማገም ያላቸው አመለካከት ነው። በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህራኑ አማካኝነት የሚነሱት ጥያቄዎች እነዚህ ሶስት ልየነቶች የሚንጸባረቁባቸውን ተማሪዎች ፍላጎት ባማከለ መልኩ ሁሉም ተማሪዎች በጋራ ችግርን የመፍታት ችሎታን እንዲያዳብሩ ማድረግ የሚያስችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል (Hargie & Dickson, 2005; Wlodkowski & Ginsberg, 2010)።

በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራኑ የሚያነሷው ጥያቄዎች ተጠየቃዊና ሂሳዊ አስተሳሰብን ማዳበር የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል (Brown, 2000; Learning Express, 2005; Richards & Lockhart, 2007; Karakoç, 2016)። ተጠየቃዊ አስተሳሰብ የሚባለው በስሜት ወይም በፍላጎት ሳይሆን በማስረጃ በተደገፈ የሀሳብ አመክንዮ ላይ ተመስርቶ በነገሮች መካከል ያለን የመንስኤና ውጤት ትስስር የመመልከት ሂደት ነው። አመክንዮ በማስረጃ ላይ ተመስርቶ ስለአንድ ጉዳይ ሀሳብ የማፍለቅ ሂደት ነው። ይህ ሂደት ክህሎት ሲሆን በእውነታና በማስረጃ ላይ ተመስርቶ በነገሮች መካከል ያለን ትስስር በመፈተሽ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስችላል። ሂሳዊ አስተሳሰብ መረጃን ዝም ብሎ የሚቀበል ሳይሆን የሚመረምር፣ የሚተነትን፣ የሚያዋህድ፣ የሚገመግምና ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚያስችል

የአስተሳሰብ መንገድ ነው። ሂሳዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች በሚቀርብላቸው መረጃ ላይ ጥያቄዎችን ያነሳሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይሰበስባሉ፣ ትንታኔ ይሰጣሉ፣ በመጨረሻም ምክንያታዊ ሆነው ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ለአንድ ችግር መፍትሄ በሚፈልጉበት ጊዜ በስሜት ከመመራት ይልቅ ተጠየቃዊና ሂሳዊ አካሄድን ሊከተሉ ይገባል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ መምህራን ቀርጸው በሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች አማካኝነት ሂሳዊና ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ማዳበር የሚያስችሉ ትምህርታዊ ተግባራትን ማከናወን ሲችሉ ነው።

እንደ Brown & Atkins (2002)፣ Hargie & Dickson (2005)፣ Shabani et al. (2010)ና Hall (2011) አባባል መምህራኑ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች በተማሪዎቹ የላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል መልስ ማግኘት የሚችሉና ቁልፍ ሀሳቦችን ከነዝርዝሮቻቸው የሚዳስሱ መሆን ይኖርባቸዋል። በማህበራዊ ግንባታውያን አተያይ መሰረት መማር ማህበራዊ ተግባር በመሆኑ የሚከናወነው ተማሪዎቹ ንቁና መስተጋብራዊ ተግባራትን በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ሲያከናውኑ ነው። የላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ተማሪዎቹ ከእነሱ ሻል ያለ አቅም ባላቸው ሰዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው ትምህርታዊ ተግባራትን ማከናወን የሚችሉበት እምቅ የአእምሮ ችሎታ ነው። ተማሪዎች አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦችንና ክሂሎችን ያዳብሩበታል። የተማሪዎቹን እምቅ የአእምሮ ችሎታ በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል (Shabani et al., 2010)። የመጀመሪያው ተማሪዎቹ ያለማንም ድጋፍ ማንኛውንም ተግባር የሚያከናውኑበት ሲሆን ሁለተኛው ከሚያውቁት ትንሽ ከፍ ባለ ሁኔታ በሌሎች ድጋፍ ትምህርታዊ ተግባራትን እያከናወኑ አዳዲስ መረጃዎችን የሚቀስሙበት ነው። ሶስተኛው ደግሞ ከችሎታ በላይ ነው። ተማሪዎች ትርጉም ያለው ትምህርት መማር እንዲችሉ በሁለተኛው የአእምሮ ችሎታ ክልል ብቻቸውን ማከናወን ከሚችሉት ትምህርታዊ ተግባር በትንሹ ከበድ ያለ ተግባርን በሌሎች ድጋፍ እየተደረገላቸው ማከናወንና በሂደት ራሳቸውን መቻል ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም የሚያከናውኑት ተግባር ቁልፍ ሀሳቦችን ከነዝርዝሮቻቸው የሚዳስስ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል (Halliwell, 1993; Hargie & Dickson, 2005; Brown & Atkins, 2002;)። ይህም በትምህርቱ ሂደት የሚዳሰሱ ቁልፍ ሀሳቸቦን በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በሚከናወኑ ተግባራት አማካኝነት እንዲያብራሩ ለማድረግ ያስችላል። ይህም ቁሳቁሶችን፣ ገጠመኞችን፣ ክስተቶችን፣ ሂደቶችን፣ ድምዳሜዎችን፣ እውነታዎችን፣ የግል አስተያየቶችንና በመካከላቸው ያለውን ትስስር አውጥቶ በማሳየት በአንድ ክስተት ረገድ በመልእክት ተቀባዮቹ ዘንድ ያለን የመረጃ ክፍተት የመሙላት ሂደት እንዲከናወን ያደርጋል። እንደ MARS (2012) አባባል ይህ አሰራር በአግባቡ በጥቅም ላይ ከዋለ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ አመክንዮንና ንጽጽርን እንዲያከናውኑ ለማድረግ ያስችላል።

2.2.5. የመረጃ ግብይት

የመረጃ ግብይት የሚባለው የተግባቡቱ ሂደት ተሳታፊዎች በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ ሀሳብ የሚለዋወጡበት፣ በራሳቸው መርሆዎችን ፈልገው የሚያገኙበትና የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሂደት ነው (Dörnyei & Murphey, 2009; Khalid & Azeem, 2012)። የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት የሆነው የትምህርቱ አላማ በተማሪዎች ዘንድ ተተርጉሞ በአእምሯቸው እንዲሰርጽ፣ የመረጃ ፍሰት እንዲሳለጥና መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡ ለማድረግ የሚያስችል ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ትምህርታዊ መረጃ በተማሪዎች ይቀሰምበታል።

በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ጥሩ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ማድረግ የሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የመረጃ ፍሰቱ ወላንሳነት ነው (McKenna, 1998; Hayes, 2005; Hargie, 2006; Markovic & Axmann, 2007)። ወላንሳ የሆነ የመረጃ ፍሰት ቀጥተኛ፣ ግልጽና ትክክለኛነት በተሞላበት ሁኔታ የሌሎችን ነጻነት ሳይጋፉ፣ መብት ሳይጥሱና ስሜትን ሳይጎዱ፤ ፍላጎትን፣ አመለካከትን፣ ስሜትንና አስተያየትን መግለጽ የሚከናወንበት ነው። የሌሎችን ስሜት የሚጎዱ፣ መብት የሚጋፉና ጫና የሚያደርጉ ሰዎችን ምክንያታዊ ሆኖ ቁጡና አሜነኛ ሳይሆኑ ለመጋፈጥ ያስችላል። እንዲህ አይነቱ የተግባቦት ችሎታ የሌሎችን ስሜት መረዳትን፤ ለሌሎች ሰዎች ሁኔታ፣ ስሜትና ሀሳብ ቦታ መስጠትን እንዲሁም ስሜትን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ መግለጽን ያካትታል። እንደ Hargie (2006) አባባል በአንድ በተወሰነ ሁኔታ የሰዎችን ስሜት ገለልተኛ ሆኖ መግለጽ፣ ሰዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ እድል መስጠትና የንግግር ስርአትን ጠብቆ መግባባትም ያስችላል። Hargie (2006)ና Markovic & Axmann (2007) እንደገለጹት የመረጃ ግብይት ወላንሳ ካልሆነ ሞገደኛ፣ አሜነኛ ወይም አሜነኛ-ሞገደኛ ሊሆን ይችላል። አሜነኛ የተግባቦት ባህሪ ትክክለኛ ስሜትን፣ አስተሳሰብንና እምነትን መግለጽ ስለማያስችል የራስ ሀሳብ በሌሎች ዘንድ ተገቢውን ክብር እንዲያጣ ያደርጋል። ስለዚህም ሰዎችን ለቅቡልነት ይዳርጋቸዋል። ሞገደኛ ባህሪ በተግባቦት ሂደት ቁጣና ሞገድ በተሞላበት ሁኔታ ሀሳብን መግለጽ ሲሆን አሜነኛ-ሞገደኛ ደግሞ የአሜነኛና የሞገደኛ ባህርያት ድብልቅ ነው። አንድን ጉዳይ በፊት ለፊት ወይም በግልጽ ምክንያታዊ ሆኖ ከመጋፈጥ ይልቅ በፍዝ ተከላክሎ፣ በተዘዋዋሪ ሞገደኛ ባህሪን ማሳየት ይንጸባረቅበታል።

Rose (1994)፣ Hargie & Dickson (2005)ና Barker (2011) እንደገለጹት በአንድምታ መሰላል መረጃን መገበያየት የጋራ ግንዛቤ የሚጨበጥበት ጥሩ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል። የአንድምታ መሰላል ሰዎች ለአንድ መረጃ ከተጋለጡበት ጊዜ አንስቶ እስከሚተገብሩት ድረስ ደረጃ በደረጃ መረጃ የሚያልፍበት የአመክንዮ ሂደት ነው። የሂደቱ መጀመሪያ በቀደመ እውቀት ላይ ተመስርቶ መረጃን መምረጥ፣ ለመረጃው መጋለጥና መረጃውን መተንተን ነው። ቀጣዩ የራስን ግምት

መሰረት አድርጎ የተጋለጡለትን መረጃ ጥቅምና ጉዳት ማመዛዘን ነው። የመጨረሻው በተከናወነው ትንታኔና ግምት ላይ ተመስርቶ ድምዳሜ ላይ መድረስና መተግበር ነው። ሰዎች ጥቅል ከሆነው መረጃ ውስጥ ለራሳቸው አስፈላጊ የሆነውን መረጃ መርጠው የሚወስዱበት ሁኔታ በውስጣቸው ባለው እምነት ላይ የተመሰረተ ነው (Hargie & Dickson, 2005; Barker, 2011)። ይህ ደግሞ በአመክንዮው ሂደት ነባራዊ እውነታውን እንዲዘሉትና ግልብ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይችላል። በመረጃ ግብይት ሂደት የአንድምታ መሰላልን መጠቀም ከእንደዚህ አይነት ችግር ይታደጋል። ግልብ ድምዳሜን በአእምሮ ከመመዝገብ ይልቅ ጥቅል ወደ ሆነው መረጃ ተመልሶ በመሄድና በመመርመር በነባራዊ እውነታው ላይ የተመሰረተ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስችላል።

በመረጃ ግብይት ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችለው ሌላኛው ተግባር ጽብረቃዊ ማዳመጥ ነው (Robinson, 2005; Hargie & Dickson, 2005; Hargie, 2006)። በተግባቡቱ ሂደት መልእክት አስተላላፊዎች የሚሉትን፣ የሚያስቡትንና የሚሰማቸውን ስሜት መገንዘብ ብቻ ሳይሆን ስሜቶቹን፣ አስተሳሰቦቹንና የግል አስተያየቶቹን በራስ አባባል ገልጾ ለሌሎች ማስተላለፍ መቻልና በሀሳቡ ላይ መጸብረቅ ይከናወንበታል። ይህም መልእክት ተቀባዮች ትኩረታቸውን በሚተላለፈው መልእክት ላይ አድርገው ግንዛቤን እንዲጨብጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ጽብረቃዊ ማዳመጥን የሚያከናውኑ የተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች የሚተላለፈውን መልእክት በኢቃላዊ ምልክቶች መደገፍን፣ በትኩረት መከታተልን፣ ማበረታታትን፣ ጥያቄ መጠየቅን፣ የተላለፉትን መልእክቶች በራስ አባባል መግለጽንና መገምገምን ያከናውናሉ።

የመረጃ ግብይት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሲከናወን ተማሪዎች በምን አይነት ሁኔታ እየተማሩና ግንዛቤ እየጨበጡ እንደሆነ መረጃ ለማሰባሰብ የሚቻለው በምዘና ነው (Cross, Patricia & Thomas, 1988; Brown, 2000; Jones, 2005; Rose & Shevlin, 2010)። ምዘና የትምህርታዊ መረጃ ግብይት ሂደት አንድ ዋና ክፍል ሲሆን የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማጠናከርና ውጤታማትን ለመለካት ያገለግላል። በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውጤታማነት በግለ ምዘና፣ በብጤ ምዘና፣ በተግባራት ክንውን፣ በውይይትና በትግበራ ጥራዝ አማካኝነት ሊመዘን ይችላል። ይህ አሰራር ለመምህራን የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ለመቆጣጠርና ግብረመልስ ለመስጠት የሚያስችል ምላሽ ለማግኘት፤ ማሻሻያ የሚያስፈልገውን ጉዳይ ለመለየት፤ ተማሪዎችን ለማበረታታት እንዲሁም ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ላከናወኑት ተግባር ማበረታቻን ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ ያገለግላል። ለተማሪዎች ደግሞ ትኩረታቸው ወደ ትምህርቱ እንዲሳብ፣ ትኩረት ሊሰጡ የሚገባቸውን ጉዳይ እንዲለዩ፣ የቀሰሙትን እውቀት እንዲተገብሩና አስፋፍተው በጥቅም ላይ እንዲያውሉ ለማድረግ ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በተከናወነው ተግባር ውጤታማነት ላይ እንዲጸበርቁና ተገቢውን የማሻሻያ ርምጃ መውሰድ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

እንደ Byrd (2008)ና Wlodkowski & Ginsberg (2010) አገላለጽ ግብረመልስ ተማሪዎች ያከናወኑትን ትምህርታዊ ተግባር ትክክለኛነት አስመልክቶ የሚያገኙት ምላሽ ነው። መምህራን መደበኛ በሆነ ሁኔታ የተማሪዎቻቸውን ብቃት ለማሳደግ ይጠቀሙበታል። መምህራንና ተማሪዎች ስለመማር ማስተማር ሂደቱ፣ ስለጨበጡት የጋራ ግንዛቤና ስላከናወኑት ትምህርታዊ ተግባር እርስ በእርስ ምላሽ ይሰጣጡበታል። ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ላይ ያላቸውን ግስጋሴ እንዲገመግሙና በቀረበው መረጃ ረገድ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ አውቀው ራሳቸውን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ካለው ሁኔታ ጋር እንዲያስተካክሉ ለማድረግ ያስችላል። ግብረመልስ ጥሩ ውጤት ማስገኘት እንዲችል ገንቢ፣ ግልጽና ውሱን መሆን ይኖርበታል። ውሱን ግብረመልስ የሚባለው በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን ግልጽ ደግሞ ማስተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ተማሪዎቹ በሚረዱት መንገድ በትክክል ማስተላለፍ የሚችል ነው። ገንቢ ግብረመልስ የሚባለው ደግሞ ተማሪዎች ባከናወኑት ትምህርታዊ ተግባር ረገድ እንዴት የበለጠ መሻሻል እንደሚችሉ የሚያመላክት ነው። ግብረመልስ ገንቢ፣ ግልጽና ውሱን መሆኑ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ያጋጠማቸውን የመረጃ ክፍተት መሙላት እንዲችሉና ለትምህርቱ ተነሳሽ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው የመረጃ ግብይት አዳዲስ ግንዛቤዎችን መፍጠርና እውቀትን መገንባት እንዲቻል በተማሪዎቹ ዳራዊ እውቀት፣ በአዲሱ ትምህርታዊ መረጃና ተማሪዎቹ አዲስ የሚቀሰሙት እውቀት በነባራዊው አለም በጥቅም ላይ በሚውልበት ሁኔታ መካከል ትስስር መፈጠር ይኖርበታል (Bada, 2015)። የግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መስተጋብር ንቁ ተሳታፊ በመሆን እውቀትን እንዴት እንደሚገበዩና እንደሚማሩ የሚገልጽ ሳይንሳዊ አተያይ ነው። ንድፈ ሀሳቡ ሰዎች እውቀትን የሚገነቡት ከገጠመኛቸው በሚመሰርቱት ፍቺ አማካኝነት መሆኑን ይገልጻል። ስለዚህም በዚህ መርህ መሰረት ተማሪዎች ዝም ብለው ከመምህራን የሚተላለፈውን እውቀት የሚቀበሉ ፍዝ አካላት ሳይሆኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበላቸውን ትምህርታዊ ተግባር ንቁ ሆነው እያከናወኑ እውቀትን የሚገነቡ ናቸው። መማር ማስተማሩ ሂደት አዳዲስ መረጃዎችንም ፈልፍለው ያወጡና ይገልጻሉ፤ በቀደመ እውቀታቸው የሀሳብ ስንሰል ውስጥ ያሉትን ጽንሰ ሀሳቦች በመከለስ አዲስ ከቀሰሙት እውቀት ጋር እያስተሳሰሩ በነባራዊው አለም በጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ሁኔታም ይለማመዳሉ።

Reid (1993)፣ Rodgers (2002)፣ Hargie & Dickson (2005)ና McClure (2005) እንደገለጹት መጸብረቅና መከለስ በመረጃ ግብይት ሂደት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ተጠቃሽ ናቸው። መጸብረቅ በመረጃ ግብይት ሂደት የተከናወነን ተግባር በመግለጽ፣ በመተንተንና በመገምገም ውጤታማነቱ የሚፈተሽበት እንዲሁም ከፍተሻው በሚገኘው ውጤት ላይ ተንተርሶ በቀጣይ የሚከናወኑትን ተግባራት አተገባበር ለማሻሻል የሚያስችል ስልት የሚቀየስበት ሂደት ነው። መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት

የነበራቸውን አተገባበር ሙያው በተመሰረተበት ንድፈ ሀሳብ መጠገጊያነት በመፈተሽ የነበረውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተው ድምዳሜ ላይ ይደርሱበታል። ድምዳሜውንም በቀጣይ ለሚያከናውኑት የማስተማር ስራ ውጤታማነት በጥቅም ላይ ያውሉታል። እንዲሁም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራንና ተማሪዎች የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ በእለቱ የተላለፈው ትምህርታዊ መረጃ ጭምቃሳብ መከለስ ይኖርበታል። ጭምቃሳብ በአንድ ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት የተሰራጨ መረጃዎች ጭብጥ ነው። መከለሱ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በተሰራጨው መረጃ ረገድ የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል። ጭምቃሳቡን የመከለሱ ተግባር የሚከናወነው በመምህራኑና በተማሪዎቹ ሲሆን በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ውይይት ወይም የእለቱ ትምህርት ሲጠናቀቅ ሊሆን ይችላል። በመረጃ ግብይት ሂደት ጭምቃሳብን መከለስ የትምህርቱ ሂደት ተሳታፊዎች በተሰራጨው ትምህርታዊ መረጃ ላይ እንዲጸበርቁ፣ የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ የትምህርቱን ሂደት ማጠናከር፣ የተጀመረውን ትምህርታዊ መረጃ ማጠናቀቅና ወደ እሚቀጥለው መሸጋገር የሚስችል ብልሀትን ያጎናጽፋል።

የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ እውቀት በማህበራዊ መስተጋብር የሚገነባ ጉዳይ ነው በሚል መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው (Nunan, 1991; Marzano, Pickering & Pollock, 2001; Littelwood, 2002; Robinson, 2005; Hayes, 2005; Cook, 2008; Khalid & Azeem, 2012)። በዚህ ንድፈ ሀሳብ ላይ የተቀነበበ የመማር ማስተማር ሂደትም እውቀት በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል በሚደረግ ማህበራዊ መስተጋብር ይገነባል የሚል መሰረተ ሀሳብን ያራምዳል። ስለዚህም የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በትምህርት ድባብ ውስጥ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር እውቀታቸውንና ክሂላቸውን ያጎለብታሉ። በመረጃ ግብይት ሂደት ይህን አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን ተማሪዎቹ ዝግጁነት ኖሯቸው በፍላጎት መማር እንዲችሉ የሚያደርጉ ልምዶችንና አውዶችን በጥቅም ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን መረጃ በቀላሉ እንዲገነዘቡትም የትምህርቱን ይዘት በስርአት ወክሎና አደራጅቶ የማቅረብ ሀላፊነት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ መረጃን በተማሪዎቹ አእምሮ ላይ የሚሞላ ሳይሆን መርምሮ ማግኘትን፣ ችግር ፈቺነትን፣ ፈጠራንና ተሳትፎን የሚጋብዝ የትምህርት አቀራረብን በጥቅም ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል። እንዲህ ከሆነ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት እውቀትን በማህበር ይገነባሉ እንጂ አይቀበሉም። ያጎለበቱትን እውቀት ያስቡበታል፣ ያገናዝቡበታል ወይም ይተነትኑታል እንጂ ዝም ብለው አያከማቹትም።

2.3. የክፍል ውስጥ መስተጋብር

የመማሪያ ክፍል ሰዎች የመምህርነትና የተማሪነትን ሚና ወስደው እርስ በእርስ ለማማር የሚሰባሰቡበት ስፍራ ሲሆን በዚህ ስፍራ ሰዎች እርስ በእርስ ሲማማሩ የሚያከናውኑት ማህበራዊ

ግንኙነት ስርአት የሚይዝበት መንገድ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ተብሎ ይጠራል (Kumpulainen & Wary, 2004; Schwarz et al., 2009; Wrench et al., 2009; Richards & Schmidt, 2002)። የክፍል ውስጥ መስተጋብር መምህራንና ተማሪዎች ትምህርታዊ ተግባራትን ሲያከናውኑ እርስ በእርስ የሚራከቡበት ስርአት ነው። በመሆኑም መረጃን ይለዋወጡበታል፤ ይረዱበታል፤ ይገነዘቡበታል፤ ያብላሉበታል፤ ያዋህዱበታል እንዲሁም እውቀትን ይገነቡበታል። ይህ ማለት መስተጋብሩ በቀረበው ትምህርታዊ መረጃዎች ረገድ የጋራ ግንዛቤ እንዲጨበጥና የተሳታፊዎቹ ቋንቋ ችሎታ እንዲዳብር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበት ነው። በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ መስተጋብሮች መሳተፋቸው እርስ በእርስ የመረዳዳት ስሜትን እንዲያጎለብቱ፤ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፤ በተግባቦት ሂደት የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጡ እንዲሁም በራስ የመተማመን ስሜትን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ያስችላል። የክፍል ውስጥ መስተጋብር በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን በሚከተሉት ዘርፎች የተካተቱትን ተግባራት በውስጡ ሊይዝ ይችላል።

2.3.1. የተማሪዎችን በይነሰባዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ተግባራት ክንውን

በይነሰባዊ ፍላጎቶች የሚባሉት የአንድ የተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች ለሚኖራቸው የእርስ በእርስ ግንኙነት መሟላት ያለባቸው ሰብኣዊ ፍላጎቶች ሲሆኑ የቁጥጥር፣ የአካቶና ትኩረት የማግኘት ፍላጎቶች ተብለው ይታወቃሉ (Gomez-Esefan, 2004; Robinson, 2005; Fisher & Frey, 2010; Babonea & Munteanu, 2012)። በአንድ የመማሪያ ክፍል ጥላ ስር ተሰባስበው የሚገኙ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን በጥሩ ሁኔታ ማከናወን እንዲችሉ እነዚህ ሰብኣዊ ፍላጎቶች ሊሟሉላቸው ይገባል። መሟላታቸው በመካከላቸው ሀሳብ ለሀሳብ ያለመረዳዳትንና ግጭትን ማስወገድ እንዲችሉ፤ በትምህርቱ ሂደት ጥሩ የትምህርት ድባብ እንዲፈጠር፤ በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መካከል እርስ በእርስ መተማመን፣ መከባበርና ግልጽነት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። መፈጠሩ ደግሞ ተማሪዎች ከልብ የመነጨ ፍላጎት ኖሯቸው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

Wrench et al. (2009) ምንጭ ጠቅሰው እንደገለጹት የቁጥጥር ፍላጎት ከተማሪዎች መሰረታዊ በይነሰባዊ ፍላጎቶች መካከል አንዱ ሲሆን በሁለት መልኩ ይገለጣል። የመጀመሪያው ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ ክስተቶችንና ሁኔታዎችን በቁጥጥር ስር የማድረግ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ ነው። ስለዚህም በየትኛውም የእድሜ ክልል ያሉ ተማሪዎች በትምህርት ድባብ ውስጥ ያሉ ክስተቶችን የመቆጣጠርና ተጽእኖ የማሳደር ፍላጎት አላቸው። በዚህ መሰረት ውሳኔ መስጠት፣ ህግን በራሳቸው መጠበቅና በራሳቸው ተንቀሳቅሰው የተለያዩ ተግባራትን የማከናወን ሃላፊነት የሚሰማቸው መሆናቸውን ማሳየት ይፈልጋሉ። በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ልጆች እንደመሆናቸው መጠን በሌሎች አቅጣጫ

የሚያስይዝና ተገቢውን አወንታዊ ስነምግባር ማንጸባረቅ እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችል ተገቢ የሆነ ቁጥጥርን መፈለጋቸው ነው።

ትኩረት የማግኘት ፍላጎት ከተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከል ሁለተኛው ሲሆን የመውደድና የመወደድ፣ ሌሎችን የመንከባከብና እንክብካቤን የማግኘት ወይም የመወዳጀት ፍላጎት ነው (Morehead, Lyman & Foyle, 2003; Schwarz et al., 2009; Wrench et al., 2009)። ፍላጎቱ ሶስት መገለጫዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ለሌሎች ያለን የጓደኝነት ስሜት የመግለጽ ፍላጎት ነው። በዚህ መሰረት በየትኛውም የእድሜ ክልል ያሉ ተማሪዎች ለሌሎች ልባዊ የሆነ የጓደኝነት ስሜት ያላቸው መሆኑንና ለሌሎች እንደሚጨነቁ ማሳየት ይፈልጋሉ። ሁለተኛው መገለጫ ከሌሎች ትኩረትንና እንክብካቤን የማግኘት ፍላጎት ነው። ስለዚህም ከመምህራንም ሆነ ከብጤዎቻቸው ተገቢውን ወዳጅነት ማግኘት መቻል ይኖርባቸዋል። ሶስተኛው ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ወላንሳ የሆነ የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲኖር መፈለግ ነው። እንደ Schwarz et al. (2009)ና Wrench et al. (2009) አገላለጽ ይህንን ፍላጎታቸውን ማሟላት ይቻል ዘንድ በመማር ማስተማሩ ሂደት የማንንም መብት ሳይጋፉ ከጫና ነጻ ሆኖ ሀሳብን የመግለጽና የመቀበል ተግባር የሚከናወንበት የእርስ በእርስ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል።

የአካቶ ፍላጎት ከተማሪዎች በይነሰባዊ ፍላጎቶች መካከል ሶስተኛው ሲሆን በአንድ በተወሰነ ቡድን ውስጥ የመካተት፣ ተወዳዳሪ ሆኖ የመገኘትና የዚያ ቡድን አባልነትን የማረጋገጥ ፍላጎት ነው (Marzano, Pickering & Pollock, 2003; Wrench et al., 2009)። ይህ ፍላጎት ማህበራዊ ፍላጎት በመሆኑ የመግባባት፣ የመላመድና ከሰዎች ጋር ማህበራዊ መስተጋብርን የማከናወን ፍላጎት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በአካቶነትና በተካቶነት ይገለጣል። አካቶነት በየትኛውም የእድሜ ክልል ያሉ ተማሪዎች የአንድ ቡድን አባል በመሆን ለሌሎች ድጋፍ የማድረግ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን የተመለከተ ነው። በመሆኑም ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመተዋወቅ፣ በመዛመድ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን በመመስረትና ድጋፍ ማድረግ በመቻል ይሟላል። ተካቶነት ደግሞ በአንድ ቡድን ውስጥ በመካተት ከቡድኑ አባላት እውቅናን፣ ፍቅርን፣ ማህበራዊ ግንኙነትንና ድጋፍን የማግኘት ፍላጎት ነው። ስለዚህ ከቡድኑ ጋር ለመስማማት ትንሽ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ተማሪዎች የቡድን አባላት ሆነው የአካቶ ፍላጎታቸው እንዲረካ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ አሰራር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚከናወን መስተጋብር በጋራ ትምህርታዊ መረጃ እንዲጋሩና እውቀት እንዲገነቡ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር Morehead et al. (2003) ያስገነዝባሉ።
በክፍል ውስጥ መስተጋብር ክንውን ሂደት በተሳታፊዎቹ መካከል ዘላቂ የሆነ መልካም በይነሰባዊ ግንኙነት ሊመሰረት ይገባል (Gomez-Esefan, 2004; Wrench et al., 2009)። ይህም ተማሪዎች ከልብ የመነጨ ፍላጎት ኖሯቸው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ የሚያስችል ወሳኝ ሚና

ይጫወታል። የቁጥጥር፣ የአካቶና ትኩረት የማግኘት ፍላጎቶች እንደ ምግብና እንደ ውሀ ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ፍላጎቶች ናቸው። ስለዚህም በትምህርት ድባብ ውስጥ ሳይሟሉላቸው ሲቀሩ ተማሪዎች አሜነኛ፣ አመጸኛ፣ ቁጡ፣ ገለልተኛ፣ ጋጠወጥ፣ በትምህርት ደካማና ፈሪ በመሆን ከሌሎች ጋር ለመግባባት ይቸገራሉ። ይህም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወነው መስተጋብር በአግባቡ እንዳይከናወንና የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ እንዳይሆን ምክንያት ይሆናል።

2.3.2. የክፍል አያያዝ

የክፍል አያያዝ መምህራን የመማሪያ ክፍሉን ማህራዊ አደረጃትና ውጫዊ ገጽታ ደርዝ የሚያሲይዙበት መንገድ ነው (McLeod et al., 2003)። ማህበራዊ አደረጃጀት የሚባለው የመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ይችል ዘንድ ተማሪዎቹ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚያዋቅሩበትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚፈቱበት መንገድ ነው። ውጫዊ ገጽታ ደግሞ በክፍል ውስጥ ጥሩ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይከናወን ዘንድ የተማሪዎቹን አቀማመጥ ፈር የሚያስይዙበት መንገድ ነው። Rahman et al. (2010) እንደገለጹት የክፍል አያያዝ መምህራን በመምህርነታቸው ከሚያከናውኗው ቁልፍ ተግባራት አንዱ ሲሆን በክፍል ውስጥ ለሚከናወን ትምህርታዊ መስተጋብርና የመማር ማስተማር ዘዴዎች አተገባበር ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መምህራን የተለያዩ የተማሪዎች አቀማመጥ ስልቶችን በጥቅም ላይ የሚያውሉ ቢሆንም በጣም የሚታወቁት ተለምዷዊ፣ የፈረስ ኩቴና ግጥምጥም አቀማመጦች ናቸው (Kress, Jewitt, & Bourne , 2005)። ተለምዷዊ አቀማመጥ የሚባለው በመካከላቸው እኩል ርቀት ያላቸው ስድስትና ሰባት መቀመጫዎችን በያዙ ረድፎች ተማሪዎች ፊታቸውን ወደ ጥቁር ሰሌዳው መልሰው የሚቀመጡበት ነው። ይህንን አቀማመጥ ምሁራን ወታደራዊ ሰልፍ የመሰለ ብለው ይጠሩታል። የፈረስ ኩቴ አቀማመጥ በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሙሉ ከጥቁር ሰሌዳው ፊት ለፊት፣ በስተግራና በስተቀኝ ያለውን ግርግዳ ይዘው ዳር ዳሩን ግማሽ ክብ ሰርተው የሚቀመጡበት ነው፡ ፡ ግጥምጥም አቀማመጥ ደግሞ ተማሪዎች የሚጽፉበትን ጠረጴዛ ከበው እንዲቀመጡ የሚደረግበት ነው። በዚህ አቀማመጥ የተወሰኑ ተማሪዎች ጥቁር ሰሌዳውን ፊት ለፊት የሚያዩት ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ በስተግራና በስተቀኝ ያገኙታል። Rahman et al. (2010) አገላለጽ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ጥሩ የሆነ መስተጋብር እንዲኖር፣ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎቹ በነጻነት መሳተፍ እንዲችሉና፣ መምህሩ ተማሪዎቹ የሚያከናውኑትን ተግባር መቆጣጠር እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችል የተማሪዎች አቀማመጥ በጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል። ጥሩ የመምህር-ተማሪና የተማሪ-ተማሪ መስተጋብር እንዲኖር በማድረግ ረገድ ተመራጩ የፈረስ ኩቴ አቀማመጥ መሆኑን Kress et al. (2005) ከገለጹት ሀሳብ መረዳት ይቻላል። ግጥምጥም አቀማመጥ ለተማሪ ተማሪ መስተጋብር ጥሩ ቢሆንም መምህራንን

ከትኩረት ነጥብነት ስለሚያስወጣ የመምህር ተማሪ መስተጋብርን ይቀንሳል፡፡ ተለምዷዊውም እንደዚሁ የተማሪ ለተማሪ መስተጋብርን ስለሚቀንስ መምህር መራሽ ለሆነ የመማሪያ ክፍል ካልሆነ በስተቀር ተመራጭነቱ እምብዛም ነው፡፡

በክፍል ውስጥ በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችና መምህራን የሚኖራቸው ሚና ፈር የሚይዝበት አሰራር የክፍል አያያዝ ዘይቤ ተብሎ ይጠራል (Goslin, 2003; McLeod et al., 2003; Kumpulainen & Wray, 2004; Driscoll & Frost, 2005)፡፡ አብዛኞቹ ምሁራን ሶስት አይነት የክፍል አያያዝ ዘይቤዎች በመኖራቸው ይስማማሉ፡፡ የመጀመሪያው አምባ ገነናዊ (bureaucratic) ሲሆን ጣልቃ ገባዊ (interventionist) ነው፡፡ ውጫዊው አለም በሰው ልጅ እድገት ላይ ተጽእኖ ስለሚያሳድር መምህራን ተማሪዎቹን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ይኖርባቸዋል በሚል መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ይህንን ዘይቤ የሚጠቀሙ መምህራን የተማሪዎቹን እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራሉ፡፡ ሁለተኛው ታጋሽ (laissez-faire) ሲሆን ኢጣልቃ ገባዊ (non-interventionist) ነው፡፡ የሰው ልጅ የራሱ ፍላጎት ያለው በመሆኑ ሀሳቡን መግለጽ መቻል ይኖርበታል በሚል መርህ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የመምህሩ ቁጥጥር አነስተኛ ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች በራሳቸው ውሳኔ በክፍል ውስጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት ሀላፊነትን ይወስዳሉ፡፡ ሶስተኛው ዲሞክራሲያዊ (democratic) ሲሆን በሁለቱ መካከል ያለ ነው፡፡ በሌላ አጠራር መስተጋብራዊ (interactionist) ተብሎ ይታወቃል፡፡ ሰዎች አካባቢያቸውንና አካባቢ በሰዎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድርበትን ሁኔታ ለመለወጥ መስራት ይኖርባቸዋል በሚል መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ መምህሩም ሆኑ ተማሪዎቹ የተግባቡቱ ሂደት ተሳታፊዎች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ስለዚህም በክፍል ውስጥ የሚከናወነውን ሁኔታ መቆጣጠር የመምህራንና የተማሪዎች የጋራ ኃላፊነት ነው፡፡ Goslin (2003), McLeod et al. (2003)ና Kumpulainen & Wray (2004) እንዳሉት ይህ የክፍል አያያዝ ዘይቤ ከአምባ ገነናዊና ከታጋሽ የክፍል አያያዝ ዘይቤዎች አንጻር ሲታይ የተሻሉ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ መምህሩ ከክፍል ውስጥ ማህበረሰብ እንደ አንዱ ስለሚቆጠሩ ያለተጽእኖ ተማሪዎቻቸው በትምህርቱ ሂደት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፤ ተገቢ የሆነ አመራርም ይሰጣሉ፡፡ የመምህሩ ቁጥጥር አቅጣጫ ከማስያዝ አልፎ የተጋነነና ጫና የሚያሳድር አይደለም፡፡ ይህም በተማሪ-ተማሪና በመምህር-ተማሪ መስተጋብር ሂደት በተሳታፊዎቹ መካከል ነጻ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል፡፡ ተማሪዎች የጋራ ስራን እንዲቀበሉ፣ ሀላፊነትን እንዲወስዱ፣ ከፍተኛ የሆነ እርስ በእርስ መማር ማስተማርን እንዲያከናውኑና ውጤት ላይ ለመድረስ የሚያስችል ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

አስቸጋሪ ባህሪ ወጥ የሆነ ብያኔ ባይኖረውም ከማህበራዊው ስርአት ያፈነገጠና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎችና በሚያከናውኑት ተግባር ደህንነት ላይ እንቅፋት በመፍጠር የመማር ማስተማር ሂደትቱን ያደናቅፋል (Porter, 2000; Ciaccio,

2004; Mackay, 2006)። በቁጡ ባህሪ፣ በመደባደብ፣ በመንጫጫት፣ በመተነኳኮስ፣ ለስራ ባለመተባበር፣ በመረበሽና በስርቆት ሊገለጥ ይችላል። በመማር ማስተማሩ ሂደት እንደዚህ አይነት ባህርያትን ለመቆጣጠር አወንታዊ የሆኑ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። እርምጃዎቹ ሁሉም ተማሪዎች በትምህርታዊ ተግባራት መሳተፋቸውን ማረጋገጥ፣ ለልዩነቶች ቦታ መስጠት፣ ትምህርታዊ ተግባራት የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችን ያማከሉ መሆናቸውን ማረጋገጥና የሁሉም ተማሪዎች ደህንነት ከተንኳሽ ንግግር የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ናቸው። የተማሪዎችን ስም ጠርቶ እንዲሳተፉ ማድረግ፤ ተማሪዎቹን በሙሉ በአይን መቆጣጠር፤ የረብሻ ባህርያትን ሲያሳዩ ወዲያውኑ ርምጃ መውሰድ፤ ተገቢ የሆነ ግብረመልስ መስጠት፤ ጥሩ ባህሪ በአርኣያነት ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ፤ እንዲሁም ተማሪዎች ለሚያበረክቱት አስተወጽኦ አወንታዊ ማበረታቻዎችን መጠቀምም እንደዚሁ ረብሻን አወንታዊ በሆነ መንገድ ለመቆጣጠር ያስችላል። ይህ እንዳለ ሆኖ ተገቢ የሆነ ባህሪ በጥሩ ሁኔታ ሊበረታታ የሚችለው እያንዳንዱ የተግባቡቱ ሂደት ተሳታፊ መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ በማድረግ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም።

አካላዊና አእምሯዊ ቅጣት የባህሪ ለውጥ ማምጣት ይቻል ዘንድ በአካል ላይ የህመም ስሜት እንዲሰማ የሚያደርግ የሀይል እርምጃ የመውሰድ ተግባር ሲሆን በተማሪዎች ላይ የሚታዩ አስቸጋሪ ባህርያትን በማስተካከል ረገድ ውጤታማው እብዛም ነው (UNESCO, 2006; Fisher & Frey, 2010)። ይህ ተግባር መምታትን፣ መግረፍን፣ ተንኳሽ የሆኑ ኢቃላዊ ምልክቶችን መጠቀምን፣ ማግለልን፣ የተለየ ትኩረት በተማሪዎች ላይ ማድረግንና ማንበርከክን ያካትታል። Babonea & Munteanu (2012) ከገለጹት ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ምንም እንኳ የአካላዊ ቅጣት ሀሳብ አራማጆች ትክክለኛ የባህሪ ማረሚያ መንገድ ነው ብለው የሚያምኑ ቢሆንም ሳይንሳዊ የሆኑ ጥናቶች አካላዊ ቅጣት በስነምግባር ማረሚያነቱ ውጤት አልባ ከመሆኑም ባሻገር በተማሪዎች የአካልና የአእምሮ ላይ የጤና ችግር የሚያስከትል ተግባር መሆኑን አረጋግጠዋል። በመሆኑም አካላዊ ቅጣት ተማሪዎችን የሚያሸቆጠቁጥ መስሎ ቢታይም ተማሪዎች እንዲመረምሩ፣ እንዲያስቡ፣ ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ ሂሳዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩና ለጥያቄዎች መልስ መፈለግን እንዲወዱ ከሚያደርገው ከዘመናዊው ተማሪ መራሽ አሰራር አንጻር የሚደገፍ አይደለም (Robinson, 2005; UNESCO, 2006; Fisher & Frey, 2010)። ምክንያቱም አካላዊ ቅጣት ተማሪዎችን ከማሰብ፣ ከመጠየቅ፣ ለጥያቄዎች መልስ ከመፈለግ፣ ነገሮችን በሂስ አይን ከማየትና ግላዊ አላማን ከግብ ከማድረስ ስለሚገድብ የተማሪዎችን ውጤታማነት ያደናቅፋል፤ ማህበረሰብንም ተወዳዳሪ፣ ፈጣሪና ለዋጭ ሀይል እንዳያፈራ ያደርጋል። በጥቅሉ በአንድ የመማሪያ ክፍል ጥላ ስር ተሰባስበው የሚገኙ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን በጥሩ ሁኔታ ማከናወን እንዲችሉና በትምህርቱ ሂደት ጥሩ የትምህርት ድባብ እንዲፈጠር ግጭትን አወንታዊ በሆነ የባህሪ መቆጣጠሪያ መንገድ ማስወገድ ያስፈልጋል (Robinson, 2005; UNESCO, 2006; Walters & Frei, 2007)::

2.3.3. ትምህርታዊ መስተጋብር

ትምህርታዊ መስተጋብር የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች የፍቺ ምስረታን የሚያከናውኑበት የእርስ በእርስ መስተጋብር ሂደት ነው (Macky, 2006; Walters & Frei, 2007; Wang & Castro, 2010)። የፍቺ ምስረታ የሚባለው በትምህርትነት በቀረበው መረጃ ረገድ የሚፈጠር የጋራ ግንዛቤ ነው። የፍቺ ምስረታ የሚከናወንበት የክፍል ውስጥ መስተጋብር ትምህርታዊ ተግባራት የሚከናወኑበትን፣ ተማሪዎች የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑበትን፣ ከመምህራን ወይም የተሻለ ችሎታ ካላቸው ብጤዎች ድጋፍ የሚያኙበትን፣ ሀሳብ የሚለዋወጡበትን፣ የሚተላፍላቸውን የመረጃ ግብኣት የሚቀበሉበትንና እነሱም መረጃን በግብኣትነት የሚያስተላልፉበትን ክንውን ይመለከታል። Cloudhury (2005)፣ Edwards & Willis (2005)ና Wang & Castro (2010) እንደገለጹት ትምህርታዊ መስተጋብር ተማሪዎች የቋንቋ ግብኣት የሚያገኙበትና በቋንቋ ውጽኣት ሀሳባቸውን የሚገልጹበት ሂደት በመሆኑ ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የሀሳብ ልውውጥን የማከናወን፣ መረዳት መቻልን የማረጋገጥ፣ ማብራሪያ የመጠየቅና ሀሳብን ደጋግሞ የመግለጽ ተግባር የሚከናወንበት በመሆኑ ለቋንቋ ችሎታ መዳበር አስተዋጽኦ ያበረክታል። በክፍል ውስጥ በሚከናወን ትምህርታዊ መስተጋብር ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ፍቺን መመስረት እንዲችሉ ጠንካራ ተነሳሽነት ሊኖራቸው ይገባል። ጠንካራው የተነሳሽነት አይነት ውስጣዊ ተነሳሽነት ሲሆን ተማሪዎች ከውስጥ በመነጨ ግፊት የትምህርታዊ መስተጋብር ሂደት ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ለማድረግ ያስችላል (Dörnyei, 2001; Gasoline, 2003)። ለዚህ ደግሞ በትምህርቱ ስለሚደርሱበት ውጤት አወንታዊ ግምት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ በተማሪዎቹ ልቡና ውስጥ በሚኖረው የማወቅ ፍላጎትና ለትምህርቱ በሚኖራቸው ጠንካራ ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ላይ የሚኖረው ተሳትፎ ይቀንሳል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት አብዛኛውን ትምህርታዊ ተግባር ከሚያከናውነው የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ማንነት አንጻር ትምህርታዊ መስተጋብር ተማሪ መራሽ ወይም መምህር መራሽ ሊሆን ይችላል (Attard, Iorio, & Geven, 2010; Massouleh & Jooneghani, 2012)። መምህር መራሽ የሚባለው በመማሪያ ክፍል ውስጥ አብዛኞቹን ትምህርታዊ ተግባራት መምህሩ የሚያከናውኑበት፣ ተማሪዎቹ ንቁ ሆነው የተለያዩ ተግባራትን ከማከናወን ይልቅ ፍዝ ተቀባይ (passive recipient) የሚሆኑበትና በቀረበላቸው ትምህርታዊ መስተጋብር ላይ ተመስርቶ ሀሳብ ከማፍለቅ ይልቅ መምህሩ የሚያስተላልፉትን መረጃ የሚቀበሉበት የክፍል ውስጥ መስተጋብር ነው። በዚህ አሰራር መምህሩ ብዙውን የትምህርት ሰአትና ተግባር ይቆጣጠሩታል። ተማሪዎቹ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ውሱን ስለሚሆኑ ተማሪዎቹ ፍዝ ሆነው ይቀመጣሉ። ተማሪ መራሽ የመማር ማስተማር ሂደት የሚባለው ደግሞ ተማሪዎች ምንን እንዴትና ለምን እንደሚማሩ እንዲያውቁና ኃላፊነትን እንዲጋሩ የሚደረጉበት

የመማር ማስተማር ሂደት ነው። በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ኃላፊነትን የሚወስዱበት ሲሆን በመፍጠር፣ በመገንዘብና በእውቀት ግንባታ ሂደት ንቁ ሆነው እርስ በእርስ እንዲማማሩና በቡድን እንዲሰሩ ያደርጋል። እያንዳንዱን ተማሪ ልዩና የራሱ የሆነ ባህሪ ያለው አድርጎ ስለሚመለከት በውሳኔ ሰጭነት ያሳትፋል። በየትኛውም የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የተለያየ የመማር ፍጥነት፣ ዘይቤ፣ ችሎታ፣ ተሰጥኦ፣ ውጤታማነትና የእድገት ሁኔታ ያላቸው መሆኑን ከግንዛቤ ያስገባል። ተማሪዎች ለትምህርታቸው ኃላፊነትን የሚወስዱበት ሲሆን የንቁ መማር ማስተማር ዘዴዎች ተቀናጅተው በጥቅም ላይ ይውሉበታል። የመምህሩ ተግባር አመራር ሰጪነትና ድጋፍ ሰጪነት በመሆኑ ተማሪዎቹ የበለጠ አዲስ ነገርን ፈልፍለው እንዲያወጡ የሚያደርግ የትምህርት ሂደት እንዲከናወን ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፤ እርስ በእርስ የመማማር ሂደትንም ያበረታታሉ። ገንቢ፣ ትክክለኛና በነባራዊው አለም ካለው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትምህርት በማቅረብ የተማሪዎች ተሳትፎ እንዲጠናከር ያደርጋሉ። የትምህርቱን ሂደት ተማሪዎቹ ከትምህርት ቤት ውጪ በነባራዊው አለም ከሚገጥማቸው ጉዳይ ጋር የሚጣጣምና ፍላጎታቸውን የዳሰሰ እንዲሆን ማድረግ የሚያስችል አመራርም ይሰጣሉ። የትምህርቱ ድባብ ድጋፍ ሰጭ መስተጋብርን የሚያመቻች፣ ተማሪዎች ላከናወኑት ተግባር ዋጋ የሚሰጥና ተማሪዎች የራሳቸውን የመማር ሂደት የመቆጣጠር አቅም ያላቸው አድርጎ የሚመለከት ነው።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ካለው የመረጃ አሰረጫጨት አንጻር ትምህርታዊ ,መስተጋብር ተራና ምልልሳዊ እንዲሁም ፍዝና ንቁ መማር ማስተማር ሆኖ ሊከሰት ይችላል (Edwards & Willis, 2005; Magsoudpour, 2011; Rahman, 2014):: *ተራ መስተጋብር* (Ordinal interaction) በአንድ አቅጣጫ ብቻ መረጃ የሚፈስበት የመስተጋብር አይነት ነው። በስፋት የሚከሰተው መምህር መራሽ በሆነ የመስተጋብር ሂደት ነው። በአንጻሩ ምልልሳዊ መስተጋብር (Reciprocal interaction) ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሀሳቦች የሚፈልቁበትና የሚሰራጩበት የመስተጋብር አይነት ነው። ይህ የመስተጋብር አይነት ተማሪዎች ሀሳብ እንዲያመነጩ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ያመነጩትን ሀሳብ የትምህርት ግብዓት አድርጎ ይጠቀማል። ስለዚህም በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውጤታማ መማር ማስተማር ይከናወንበታል (Edwards & Willis, 2005)። በመሆኑም በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል ጥሩ የሆነ የሀሳብ ልውውጥና የመረጃ ግብይት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ያልተረዱትን ጉዳይ አውቆ እርምጃ እንዲወሰድ፣ አስቸጋሪነት ያለው ግብኣት ሲገጥማቸው ችግራቸው በውይይት እንዲፈታና የጋራ ግንዛቤ እንዲጨበጥ ለማድረግ ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ትምህርታዊ መስተጋብር ፍዝ ወይም ንቁ ሆኖ እንደሚከሰት German (1996)ና Rose & Shelvine (2010) ያስገነዝባሉ። ፍዝ መማር ማስተማር ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን ከማከናወን ይልቅ ሌሎች የሚያከናውኑትን ተግባር የሚመለከቱበት ነው። ንቁ የመማር ማስተማር ሂደት ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች አእምሯቸውን አሰባስበው ትኩረታቸውን

ሙሉ በሙሉ በትምህርቱ ላይ በማድረግ ትምህርታዊ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ነው። በትኩረት ማዳመጥ፤ ማስታወሻ መያዝ፤ ጥያቄ መጠየቅ፤ በክፍል ውስጥ ውይይት መሳተፍ፤ ግለ ምዘናን ማከናወን፤ ትብብራዊ መማር ማስተማርን መተግበር፤ በጥንድና በቡድን ስራ መሳተፍ፤ የቡድን ምዘናን ማከናወን፤ መስተጋብራዊ ገለጻ ማድረግ፤ በአእምሮ ማነቃቂያ ተግባራት መሳተፍ፤ በስብጥራዊ ውይይት መሳተፍ፤ የሚና ጨዋታን ማከናወንና ችግር ፈቺ ተግባራትን መተግበር ይከናወኑበታል። እነዚህ ተግባራት የሚከናወኑበት የማስተማር ሂደት ከፍተኛ የሆነ አእምሯዊ አቅምና ስነልቡናዊ ተሳትፎ የሚወረትበት የመማር ማስተማር ሂደት ነው።

በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ውጤታማ እንዲሆን በተማሪዎች መካከል ላለ ልዩነት ምላሽ የሚሰጥ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል (UNESCO, 2009)። ይህ ሀሳብ ከአካቶ ትምህርት መሰረተ ሀሳብ ጋር ተያያዥነት አለው። የአካቶ ትምህርት ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋው ተማሪዎች ድጋፍ መደረግ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ መሰረተ ሀሳብ ነው። ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በስነትምህርታዊ፣ ማህራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ከሌሎቹ ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ ይደረጋል። ስነትምህርታዊ የሆነው ምክንያት ሁሉንም ተማሪዎች በአንድ ላይ ማስተማር መምህራን ግላዊ ልዩነቶችን ከግንዛቤ የሚያስገቡ የትምህርት አቀራረቦችን በጥቅም ላይ እንዲያውሉ ያደርጋል። ማህበራዊው ደግሞ ሁሉም ተማሪዎች አንድ ላይ በሚማሩበት ጊዜ ከልዩነታቸው ይልቅ ተመሳስሏቸው ጎልቶ እንዲወጣ ያደርጋል። ይህም ሰዎች በልዩነታቸው ላይ ያላቸውን አመለካከት ስለሚለውጠው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን አድልዎና ማግለል ለማስወገድ ያስችላል። ኢኮኖሚያዊው ምክንያት ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸውና ለማያስፈልጋቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ወጪ ከማውጣት ይልቅ በትንሽ ወጪ ሁሉንም ተማሪዎች በአንድ ላይ ማስተማር ያስችላል። በክፍል ውስጥ በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ሂደት በተማሪዎች መካከል ላለ ልዩነት ምላሽ የሚሰጥ ድጋፍ መደረጉ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ያስገቡ የትምህርት አቀራረቦች በጥቅም ላይ እንዲውሉና የተግባቡቱ ሂደት ተሳታፊዎች በጥሩ ሁኔታ የጋራ ግንዛቤን እንዲፈጥሩ ለማድረግ ያስችላል።

ማበረታታት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው የሚያገኙትን አንድ ተግባር በተደጋጋሚ እንዲተገብሩት ወይም እንዳይተገብሩት የሚያነሳሳ መቀስቀስ ነው (Zirpoli & Melloy, 1993; Brown, 2000; Tavakoli, 2012)። በተደጋጋሚ እንዲተገበር የሚያነሳሳው አወንታዊ ማበረታቻ ሲሆን እንዳይተገበር የሚያነሳሳው ደግሞ አሉታዊ ማበረታቻ ነው። መነሻው የባህሪያውያን መሰረተ ሀሳብ ሲሆን ተማሪዎች ስለአንድ ጉዳይ የሚያገኙት ግብአት ድግግሞሽ ከፍተኛ ሲሆን በአእምሯቸው ውስጥ ያለው የመረጃዎች ትስስር እንደሚጠነክርና አነስተኛ ሲሆን ደግሞ እንደሚዳከም የሚነግር ነው። በስነልቡና የጥናት መስክ መደበኛ ትግበራ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን አንድን ጉዳይ በመደበኛነት ደጋግሞ በመተግበር ሊመደበኛ የሆኑ ቅርጾችንና ህግጋትን የማስወገድ ተግባር ይከናወንበታል። በተማሪዎች አእምሮ ውስጥ የሚኖረው

የመረጃዎች ትስስር እንዲጠናከር ስለሚያደርግ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ይህ እንዳለ ሆኖ Zirpoli & Melloy (1993)ና Brown (2000) እንደገለጹት በመማር ማስተማሩ ሂደት አወንታዊ ማበረታቻ ሲደረግ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ምሁራን ያስገነዝባሉ። ምክንያቱም የሚፈለግን ብቻ ሳይሆን የማይፈለግን ባህሪ እንዲያጎለብቱ ወይም አጠናክረው እንዲቀጥሉ ሊያደርግ ይችላል። እንዲሁም ማበረታቻ በቆየ ቁጥር በማበረታቻውና በተገኘው የባህሪ ለውጥ መካከል የሚኖረው ትስስር ስለሚላላ የማበረታታት ሀይሉ እየቀነሰ እንዲሄድና የባህሪ ለውጡ ቀጣይነትን እንዲያጣ ያደርጋል።

2.3.4. የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር

መማር አለምን የመረዳት፣ የመገንዘብና ፍቺ የመመስረት ሂደት ነው። ይህ ሂደት ረቂቅ ጽንሰ ሀሳቦችን የመገንዘብ፤ ማስረጃዎችን የመረዳት፤ ነባራዊ እውነታዎችን የማወቅና የማስታወስ፤ በአተገባበር ብልሀቶች የመጠበብ፤ በነባራዊ እውነታዎች፣ በግላዊ አመለካከቶችና በሀሳብ አመክንዮዎች መካከል ያለውን ልዩነት አብጠርጥሮ የመለየት፤ ክስተቶችን እደየአውዱ የመረዳት፤ ለተወሰኑ አውዶች ምቹ የሆኑ ባህርያትን የማዳበር በአጠቃላይም የመለወጥ ሂደት የሚከናወንበት ነው። እንደ Richards & Schimidt (2002)ና Fry et al. (2009) አባባል የተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች የሚለወጡበት፣ እውቀትን የሚገነቡበት፤ የባህሪ ለውጥ የሚያመጡበት፣ መረጃን የሚገበያዩበትና አዲስ ክህሎትን የሚያዳብሩባቸው ብልሀቶች የመማር ማስተማር ስልቶች ተብለው ይታወቃሉ።

በማህበራዊ ግንባታውያን የትምህርት ፍልስፍና ላይ በተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት ከሚጠበቁ ጉዳዮች መካከል አንዱ የንቁ መማር ማስተማር ስልቶች ትግበራ ነው። የመማር ማስተማር ስልቶች ተማሪዎች የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እያከናወኑ እንዲማሩና ስለሚያከናውኑት ተግባር እንዲያስቡ የሚያደርጉ መማማሪያዎች መሆናቸውን Harmer (1991)፣ Richards & Schimidt (2002)፣ Ciaccio (2004)፣ Fry et al. (2009)፣ Heine (2010)ና Emaliana (2017) ያስገነዝባሉ። እነዚህ ስልቶች ተማሪዎች ሂሳዊና ፈጠራዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ፤ በተማሪ ማሳተፊያ መንገዶች ሀሳባቸውን እንዲገልጹ፤ እርስ በእርስ ሀሳብ እንዲለዋወጡ፤ በጽሁፍ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ፤ ግላዊ አመለካከቶችንና እሴቶችን እንዲመረምሩ፣ ግብረመልስ መቀበልና መስጠት እንዲችሉ፤ እንዲሁም በትምህርቱ ሂደት ላይ እንዲጸበርቁ ለማድረግ ያስችላሉ። ስልቶቹ የሚተገበሩት በተማሪዎቹ ሲሆን ተመርጠው ለትግበራ የሚቀርቡት በመምህራን አማካኝነት ነው። የንቁ መማር ማስተማር ስልቶች በጥቅም ላይ በሚውሉበት ትምህርታዊ መስተጋብር ሂደት መምህራን አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለተማሪዎች ድጋፍ በማድረግና የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች ግብረመልስን ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ያሳልፋሉ። በትምህርቱ ሂደት በጥቅም ላይ ከሚውሉ የንቁ መማር

ማስተማር ስልቶች መካከል ማፋፋሚያ (Brain storming)፣ የጥንድ ስራ (Pair work)፣ የቡድን ስራ (Group work)፣ የቡድን አሰባጥሮ (jigsaw group)፣ ሚና ጨዋታ (role play)፣ ቅረባ (Presentation)፣ የአመላክቶ ስራ (Project work)፣ ተረዳድቷዊ መማር ማስተማር (Cooperative Learning) የብጤ እርማት (peer correction)ና ግለ ግምገማ (self-assessment) እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ (Harmer, 1991; Brown, 2002; Richards, 2003)፡፡ የንቁ መማር ማስተማር ስልቶች ተማሪዎች የቀረበውን የትምህርት ይዘት በብቃት ለመማር የሚያስችሏቸውን የከፍተኛ ደረጃ አስተሳሰብ፣ ልምድና በራስ የመተማመን ስሜትን እንዲያዳብሩ፤ በትምህርቱ ሂደት ነጻነት እንዲሰማቸው፤ ኃላፊነትን መውሰድ እንዲችሉ እንዲሁም ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ያስችላሉ፡፡

ተግባር ተኮር የትምህርት አቀራረብ ማህበራዊ ግንባታውያን የትምህርት ፍልስፍና ላይ በተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲተገበሩ ከሚጠበቁ የመማር ማስተማር ክንውኖች መካከል ተጠቃሽ ነው (Nunan, 1989; Cook, 2008)፡፡ ትምህርቱ በቅድመ ተግባር፣ ተግባርና ድህረ ተግባር ደረጃዎች ይከናወናል፡፡ ቅድመ ተግባር መምህሩ ትምህርቱን ለተማሪዎች የሚያቀርቡበትና ተማሪዎቹን ለተግባር ዝግጁ የሚያደርጉበት ነው፡፡ የተግባር ደረጃ ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ትምህርታዊ ተግባር በተረዳድቶ የሚያከናውኑበት ሲሆን ድህረ ተግባር ደግሞ በተግባር ደረጃ ላይ ያከናወኑትን ተግባር አቅርበው ግብረመልስ የሚያገኙበት ነው፡፡ እንደ Beglar & Hurt (2002) አገላለጽ ዋና ትኩረቱ ፍቺ ላይ ሲሆን የነባራዊውን አለም ሁኔታ መሰረት ባደረገ መንገድ ተማሪዎች የራሳቸውን ፍቺ እንዲመሰርቱ ለማድረግ የሚያስችል፣ በቋንቋ አጠቃቀም ላይ የሚያጠነጥንና ተማሪዎች አንድን ተግባር ካከናወኑ በኋላ ያስመዘገቡትን ውጤት የሚገመግም የመማር ማስተማር ሂደት ነው፡፡ በዚህ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በመምህራኑ አማካኝነት የሚዘጋጁ ሲሆን የተማሪዎቹ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ እንዲዳብርና የተማሩትን በነባራዊው አለም በሚያከናውኑት ተግባር በጥቅም ላይ እንዲያውሉ ለማድረግ ያስችላሉ፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደት ትምህርቱን ለእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት፣ የመማር ስልትና ችሎታ የሚመች አድርጎ ማቅረብ ልይይታዊ መማር ማስተማር (Instructional differentiation) ተብሎ ይታወቃል (UNESCO, 2004; Arends & Kilcher, 2010; Pablico, Diack, & Lawson, 2017)፡፡ የልይይታዊ መማር ማስተማር መሰረት የግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ሲሆን የትምህርት አሰጣጡ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን፣ የማስተማሪያ ስልቶችንና የመማሪያ ክፍሉን ድባብ የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ማሟላት በሚያስችል ሁኔታ በማስተካከል የሚከናወን መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ልይይታዊ የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች የቀረበላቸውን የትምህርት ይዘት እንዲረዱ፣ አዳዲስ መረጃዎችንና ሀሳቦችን እንዲያብላሉና ግንዛቤያቸውን አውጥተው ማሳየት የሚችሉበትን መንገድ እንዲያዳብሩ ለማድረግ ያስችላል፡፡ አሰራሩ ተማሪ መራሽ ሲሆን በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት፣ ፍላጎት፣ ምርጫና

ጥንካሬ በመለየት ይከናወናል፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በጥቅም ላይ ሲውል የተማሪዎቹን የትምህርት ግለ ታሪክ (student Profile) ማዘጋጀት፤ ባለብዙ ደረጃ የመማር ማስተማር ተግባራትን ማቅረብ፤ እንደ ሁኔታው የሚቀያየር ቡድን ማደራጀት እንዲሁም ተረዳድቷዊና ችግር ፈቺ መማር ማስተማርን መጠቀም ይተገበራሉ፡፡ ባለብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራት የሚባሉት በልይይታዊ መማር ማስተማር ተማሪዎች አንድን ጽንሰ ሀሳብ እንደየ ችሎታቸው እንዲማሩ ለማድረግ የለያየ የክብደትና የቅለት ደረጃ እንዲኖራቸው ተደርጎ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጁ መልመጃዎች ናቸው፡፡ አንድን የትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሲሆኑ የተለያዩ የውስብስብነት ደረጃ ያላቸውን ተግባራትና ጥያቄዎችን የያዙ በመሆናቸው የተማሪዎቹን የተለያዩ ችሎታዎችና ፍላጎቶች መዳሰስ ያስችላሉ፡፡ የተግባራቱ ዝግጅት የሚከናወነው በመጀመሪያ ተማሪዎች የሚማሩትን ክሂል ወይም ጽንሰ ሀሳብ ከዚያም ተማሪዎቹን በደረጃ በመለየት ነው፡፡ ተግባራቱ በትምህርቱ ግብ አንድ ሲሆኑ በግብኣት፣ በማስተማሪያ ዘዴና በምዘና ረገድ ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

እንደ UNESCO (2004) አገላለጽ በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ባለብዙ ደረጃ ሆነው የተዘጋጁ የትምህርት ተግባራትን ለማስተማር ባለብዙ ደረጃ የመማር ማስተማር ማእከላት መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ማእከላት ቡድኖች ሲሆኑ የሚደራጁት በተማሪዎች ልዩነት፣ ዳራዊ እውቀት፣ ፍላጎትና የትምህርት ግለ ታሪክ ላይ ተመስርቶ ተማሪዎቹን በሚለያዩዋቸው ጉዳዮች ለይቶ በሚያሳስሏቸው ጉዳዮች ወደ አንድ በማምጣት ነው፡፡ በሁሉም የትምህርት ቡድኖች ወይም ማእከላት የሚሰጠው ትምህርት አንድ አይነት የትምህርት አላማን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ሲሆን በክብደት፣ በርእሰ ጉዳይና በጭብጥ ሊለያይ ይችላል፡፡ በሌላ አገላለጽ በተለያዩ ማእከላት ያሉ ተማሪዎች አንድ የትምህርት አላማን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ የተለያዩ የውስብስብነትና የክብደት ደረጃ ያላቸውን ተግባራት በተመሳሳይ ጊዜ ያከናውናሉ፡፡ ተማሪዎቹ በተመደቡበት ቡድን ሆነው ትምህርታዊ ተግባራትን ሲያከናውኑ መምህሩ በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ተማሪዎቹ የሚያከናውኑትን ተግባር መቆጣጠርና ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ አሰራር ተማሪዎች እንደየ ችሎታቸው ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የቡድኖቹ አደረጃጀት ቋሚ ሳይሆን በፍላጎታቸውና በችሎታቸው ላይ ተመስርቶ የሚለዋወጥ ነው፡፡ በሁሉም የትምህርት ቡድኖች ግልጽ የሆነ የአተገባበር መመሪያ፣ በቂ የሆነ የመሳሪያ አቅርቦት፣ ከትምህርቱ አላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ትምህርታዊ ተግባርና ተማሪዎቹ ያከናወኑት ተግባር የሚመዘንበት መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡ አሰራሩ መምህራኑን ጠመኔ ይዞ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ከመጣበቅ የሚገላግልና በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚጋብዝ ሲሆን ተማሪዎችም ንቁ ሆነው የተሰጣቸውን ተግባር እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በክፍል ውስጥ ብዙ ተማሪዎች የሚገኙ ከሆነ የቡድኖቹን ቁጥር ማሳነስ ስለሚቻል በተጨናነቁ የመማሪያ ክፍሎችም ሊተገበር ይችላል፡፡

ውስብስብ የሆኑ የነባራዊው አለም ችግሮችን በመጠቀም አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች በትምህርትነት የሚቀርቡበት የትምህርት አቀራረብ ችግር ፈቺ የመማር ማስተማር ሂደት ተብሎ እንደሚጠራ Othman & Shah (2013) ያስገነዝባሉ፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ አንድን መሰረተ ሀሳብ ካብራሩ በኋላ ከመሰረተ ሀሳቡ ጋር የተያያዙ ችግሮችን አቅርቦ እንዲፈቱ በማድረግ የሚከናወን ውጤታማ የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ የተማሪዎች የተግባቦት፣ የአስተሳሰብና ችግሮችን የመፍታት ችሎታ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲዳብር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ለቋንቋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለየትኛውም የትምህርት አይነት ማስተማሪያነት የሚያገለግል ሲሆን ከፍተኛ የአስተሳሰብ ደረጃ ተብለው የሚታወቁትን ችሎታዎች (መተንተን፣ ማዋሀድ፣ መገምገምና ሂሳዊ አስተሳሰብ) ለማዳበር የጎላ ጠቀሜታ አለው፡፡

ልቀታዊነት /Scaffolding/ በማህበራዊ ግንባታውያን የትምህርት ፍልስፍና በተመሰረተ መማር ማስተማር የሚተገበር ሌላኛው የትምህርት አሰጣጥ ሲሆን በክፍል ውስጥ በሚደረግ መስተጋብር አማካኝነት ተማሪዎቹ በመምህራን ወይም የተሻለ ችሎታ ባላቸው ተማሪዎች አማካኝነት ድጋፍ እየተደረገላቸው መስራት የማይችሉትን ነገር እንዲሰሩና እውቀታቸውን እንዲገነቡ ድጋፍ የሚደረግበት፤ በሂደትም ራሳቸውን እንዲችሉ፣ ኃላፊነትን እንዲወስዱና ድጋፍ ማድረጉ እንዲቆም ሁኔታዎች እየተመቻቹ ከፍተኛ የትምህርት ግብ ላይ የሚደረስበት የትምህርት አቀራረብ ነው (Reiser, 2004; Puntambekar & Hübscher, 2005; Walqui, 2006; Engin, 2014)፡፡ አሰራሩ ተማሪዎች ሊገጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ የሚያስችል ሲሆን በባህሪው ማህበራዊ፣ መስተጋብራዊና ትብብራዊ በመሆኑ ተማሪዎች እውቀትንና ክህሎትን እንዲያጎለብቱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል:: ተረዳድቷዊነቱ በጋራ የመጨረሻ ግብ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር የአንዱ ውጤታማነት በሌላው ተጽእኖ አድራጊነት ላይ እንዲመሰረት ያደርጋል፡፡ በጋራ ተባብረው የሚሰሩ ሁለትና ከዚያ በላይ ተማሪዎችን በቡድን የሚያሳትፍና ለሚያከናወኑት ተግባራት ተሳታፊዎቹ ኃላፊነትን እንዲወስዱ የሚያደርግ ነው፡፡ ልቀታዊ የመማር ማስተማር ሂደት የሚከናወነው በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ሲሆን ከማህበራዊ መስተጋብር ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች በሌሎች ድጋፍ እየተደረገላቸው በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ውስጥ መማር ማስተማርን በማከናወን ብቻቸውን ሊያገኙ ከሚችሉት የበለጠ ውጤት እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችላል፡፡ አተገባበሩ የሀሳብ ልውውጥ የሚደረግበት በመሆኑም በማህበር እውቀት ይገነባበታል፡፡

Kumaravadivelu (2008) እንደገለጹት በመማር ማስተማሩ ሂደት በጥቅም ላይ በሚውሉ የማስተማር ስልቶች አተገባበር ረገድ መምህራን ያላቸው ሚና ለረጅም ጊዜ የቆየ የውይይት ርእሰ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው ግንዛቤ በጊዜ ሂደት እያደገ የመጣ ሲሆን በሶስት ምድቦች ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡፡ እነዚህ

ምድቦች መምህራን እንደ ፍዝ ባለሙያ፣ ጸብራቂ ባለሙያና የለውጥ መዘውር ተደርገው የሚወሰዱባቸው ናቸው።

እንደ ፍዝ ባለሙያ መታየታቸው የመምህራን የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባር መረጃን ማሰራጨት ተደርጎ የሚታይበት ነው (Kumaravadivelu, 2008)። ይህ አመለካከት ከባህርያውያን ፍልስፍና ጋር የተያያዘ ሲሆን በተለምዷዊነቱ የሚታወቅና እስከ አሁንም ድረስ በብዙ የአለማችን ክፍሎች ተቀባይነት ያለው ነው። ችሎታ ለሚያንሳቸው፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አቅርቦት እጥረት ላለባቸውና ፈጣሪነትን የሚያበረታቱ የማስተማር ስልቶችን የመጠቀም ተነሳሽነት ለሌላቸው መምህራን ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ እንዲኖራቸው ለማድረግ ያስችላል። በዚህ ግንዛቤ የመምህራን ተግባር የንድፈ ሀሳብ አመንጪዎች ያመነጩትን እውቀት ተረድቶ ማሰራጨት ነው። ይህ የእውቀት አስተላላፊነት ተግባር መምህራኑን አቅም የሚያሳጣቸው ከመሆኑም በላይ የሚያስተምሩበትን የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች ልምድንና ገጠመኝን የሚጋሩበት ከመሆን ይልቅ እውቀትን መስጠትና መቀበል የሚከናወንበት ያደርገዋል።

ሁለተኛው ግንዛቤ መምህራን ጸብራቂ ባለሙያ የሆኑበት ነው (Kumaravadivelu, 2008)። ይህ አሰራር ፍዝ ባለሙያነታቸውን ለመጋፈጥ ይቻል ዘንድ እውን የሆነ ሲሆን የመምህራን ተግባር የመማር ማስተማር ሂደቱን እየፈተሹ የአተገባበር ድክመቶችን ለማሻሻል የሚያስችል አዳዲስ አሰራር መቀየስ ነው። ለዚህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ስለሚያነሷቸው ጥያቄዎችና ሀሳቦች ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል (Reid, 1993)። እንደ Kumaravadivelu (2008) አባባል ይህ አተያይ በፊት ከነበረው (ፍዝ ባለሙያ) ከፍተኛ የሆነ መሻሻል እንዲኖር ቢያደርግም በክፍል ውስጥ በሚከናወነው ማህበራዊ መስተጋብር የሚኖራቸውን ሚና የዘነጋ በመሆኑ ያመጣው ለውጥ ያን ያህል ጎልቶ አልወጣም።

ሶስተኛው ግንዛቤ መዘውር ተደርገው የሚታዩበት ነው። ይህ አስተሳሰብ መምህራንን ከአሰራራቸው ጋር ቁርኝት ባላቸው የተለያዩ የአለም አተያዮች ላይ የሚጸበርቁ፤ ስነትምህርታዊ ንድፈ ሀሳቦችንና አተገባበሮችን ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር የሚያስተሳስሩ፤ ሀሳቦችን ለመጋራት ከተማሪዎቻቸው ጋር አብረው የሚሰሩ፤ በሚያከናውኑት ተግባር ረገድ ኃላፊነትን የሚወስዱ እንዲሁም ለማስተማር ስራቸው የተሻለና የበለጸገ የሰው ልጅ አኗኗርን መሰረት ያደረገ ራእይ የሚያላብሱ አድርጎ ይመለከታቸዋል (Kumaravadivelu, 2008)። Kreisberg (1992) እንዳሉት ማስተማር የፈጠራ ችሎታ የሚፈልቅበት፤ የማሰብና የመመራመር አእምሯዊ ተግባር የሚከናወንበት እንዲሁም ሰዎች በስነምግባር የሚታነጹበት ተግባር እንደመሆኑ መጠን መምህራን በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት አወቃቀር፤ እንዲሁም

ከባልደረቦቻቸውና ከተማሪዎቻቸው ጋር ባላቸው በይነሰባዊ ግንኙነት ላይ ሰብኣዊና ተቋማዊ ለውጥ የሚያመጡ መሆን አለባቸው። ይህም የለውጥ መዘውርነታቸውን ያረጋግጣል።

Kumaravadivelu (2008) እንዳሉት በለውጥ መዘውርነታቸው መምህራን ምርምር ተኮር ናቸው። በመማሪያ ክፍል ውስጥና ውጪ እነሱንም ሆነ ተማሪዎቻቸውን የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መመርመርና መፍታት የሚያስችል የምርምር ክህሎት እንዲዳብር ያደርጋሉ። የመማር ማስተማር ሂደቱ ለሚከናወንበት ማህበራዊ አውድ ተገቢውን ትኩረት ይሰጣሉ። አለምን ለማወቅ ዝግጁ ከመሆናቸውም በላይ እውቀት ባለው የትምህርት አውድ ውስጥ መምህራንና ተማሪዎች እርስ በእርስ በሚያደርጉት መስተጋብር የሚገኝና ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን የተገነዘቡ ናቸው። በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባራዊ የሚያደርጉትን የትምህርት እቅድና የመማር ማስተማር ክንውን ለዚያ አውድ በሚመች መልኩ ለማዘጋጀት ራሳቸውን ያዘጋጁ ናቸው። አሳታፊ በመሆናቸው የመማሪያ ክፍሉን ለተማሪዎቹ ልምድ፣ ችሎታ፣ ትኩረትና ልዩነት ምቹ እንዲሆን በማድረግ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያደርጉትን ውይይት ያበረታታሉ። ጽብረቃ በግልም ሆነ በማህበር እንዲከናወን ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። ራሳቸውም ሆኑ ተማሪዎቻቸው በትምህርቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው የሚያደርጉበትን መንገድ ይቀይሳሉ (Cornu, 2005; Richards & Lockhart, 2007)።

Kumaravadivelu (2008) እንደገለጹት እነዚህ ሶስት አተያዮች ፍጹም ተቃራኒ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም። መምህራን በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሁኔታው ከአንዱ ወደ አንዱ ሊያዘነብሉ ይችላሉ።

ይህ ጥናት ያነሳው ርእሰ ጉዳይ በማስተማር ስልቶች አተገባበር ረገድ መምህራንን ለውጥ አምጪ አድርጎ ይመለከታል። ለዚህ ምክንያቱ አተያዩ የጥናቱ ርእሰ ጉዳይ ካነሳው መሰረታዊ ሀሳብ ጋር አብሮ የሚራመድ መሆኑ ነው። እንደ Kumaravadivelu (2008) አባባል ፍዝ ባለሙያ የሆኑ መምህራን ራሳቸውን ቀጣይ በሆነ ግለ-ጽብረቃና የማደስ ተግባር ካላሻሻሉ በስተቀር የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መዘውር ለመሆን ይቸገራሉ። ስለዚህም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች እውቀትን እንዲገነቡ የሚያደርግ አሰራርን እውን ማድረግ የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት ይሳናቸዋል። ምክንያቱም በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥሩ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አለ የሚባለው የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት ያሟላ፣ ጥሩ የክፍል አያያዝ የሚተገበርበት፣ ጥሩ ትምህርታዊ መስተጋብር የሚከናወንበትና የማስተማር ስልቶች በጥሩ ሁኔታ በጥቅም ላይ የሚውሉበት የመማር ማስተማር ሂደት ሲኖር ነው።

2.4. ድኅረ አወንታዊ ቀመረ እሳቤ

ድኅረ አወንታዊ/ ሀዲስ አወንታዊ ቀመረ እሳቤ (post positivism/ Neo positivism) ማህበራዊ ክስተትን ማብራራት የሚያስችል የምርምር ማሕቀፍ ነው (Ayeni, Saman & Kasimu, 2019)። ነባራዊ እውነታን ፈልጎ ማግኘት የሚቻለው በተፈጥሮ ሳይንስ የአጠናን ዘዴ ላይ ብቻ ተመስርቶ እንደሆነ በሚገልጸው አወንታዊ ቀመረ እሳቤ ላይ የተሰነዘሩ ሂሶችን መሰረት አድርጎ የተቀመረ ነው። አወንታዊ ቀመረ እሳቤን በማህበራዊ ሳይንስ በጥቅም ላይ ለማዋል ያስቸግሩ የነበሩ መርሆዎችን አሻሽሎና የአሰራር ክፍተቶችን ሞልቶ በጥቅም ላይ የዋለ የምርምር ማሕቀፍ ነው (Corbetta, 2003)።

Corbetta (2003)ና Tavakoli (2012) እንደገለጹት ስነኑባሬው ሂሳዊ እውነታ (critical realism) ነው። በዚህ ቀመረ እሳቤ አተያይ ነባራዊ እውነታ ያለው ከሰው ልጅ አእምሮ ውጪ ነው:: የሰው ልጅ እውቀት ፍጹማዊ ባለመሆኑና የሚገዛበት ህግ ምናልባታዊ በመሆኑ ይህ እውነታ ሙሉ በሙሉ ላይታወቅ ይችላል። የመንስኤና ውጤት ትስስር የሚከሰተው ከሰው ልጅ አእምሮ ውጪ ሲሆን ተመራማሪዎች ሁልጊዜም የትኛውም ሳይንሳዊ ጉዳይ የሚገኝበትን መንገድ በሂስ አይን ለመመርመር ዝግጁ መሆን እንደሚኖርባቸው ይገልጻል። እንደ Kasimu (2019) አባባል በዚህ ቀመረ እሳቤ የሰው ልጆች በግልና በማህበር በሚያደርጉት መስተጋብር እውቀትን ይገነባሉ ተብሎ ይታመናል። ቢሆንም ስፍር ቁጥር የሌለው የአለም ክፍል ውስብስብና የማይታወቅ ሲሆን ለትንታኔ ክፍት ነው (Tavakoli, 2012)።

ነባራዊ እውነታን ፈልጎ ማግኘት የሚቻለው እንዴት ነው? በሚለው ጉዳይ ላይ የተሻሻለ ሁለታዊ ትክክለኛነት (modified dualism-objectivity)፣ ምናልባታዊነት (probabilistic)፣ እንዲሁም የግምታዊ ህግጋት (conjectural laws) አተያይ አለው (Corbetta, 2003)። የተሻሻለ ሁለታዊ ትክክለኛነት "ተመራማሪውና የሚጠናው ጉዳይ ሁለት የተለያዩ አካላት ናቸው" ይላል። ይህ ሀሳብ በምርምሩ ሂደት የተመራማሪዎቹና የምርምሩ ቁርኝት የግድ ላይሆን መቻሉን ያሳያል። ነገር ግን Kasimu (2019) እንደገለጹት በዚህ ቀመረ እሳቤ የተጠኝዎቹ ልምድና ገጠመኝ ዋንኛ የመረጃ ምንጭ ተደርጎ ይወሰዳል። የተጠኝዎቹ ልምድና ገጠመኝ የተመለከተ መረጃ በምልከታ የሚሰበሰብ ከሆነ ተመራማሪውና የሚመረመረው ጉዳይ መነጣጠል የለባቸውም (Tavakoli, 2012)። ተመራማሪዎቹ በምርምሩ ሂደት አሳታፊና ትብብራዊ በሆነ መንገድ መሳተፍ ይኖርባቸዋል።

እንደ ድኅረ አወንታውያን አስተሳሰብ ይህች አለም አሻሚ ስትሆን በሳይንስ እገዛ አንድ ቀን የማይታወቀው ሊታወቅና ያልተገለጠው ሊገለጥ ይችላል። እውነታ ምናልባታዊ በመሆኑ ከዚህ ቀደም በተሳሳተ መንገድ የተስተዋሉ በጣም በርካታ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ወደፊትም ቢሆን

ውስብስብነታቸው ሙሉ ለሙሉ ሊታወቅና ሊገለጥ የማይችል ጉዳዮች አሉ። በተሳሳተ መንገድ የተስተዋሉ እውነታዎች ትክክለኛ ገጽታ በምርምር ይታወቃል። አለም ውሱን ሳትሆን ተለዋዋጭ ነች። በመሆኑም እውነታ የሚወሰነው ተለዋዋጭ የሆነውን ክስተት የሰው ልጅ በተረዳው መጠን ነው። እውነታ ነቢረ ብዙነት (multiple realities) አለው። ስለዚህም በአንድ ሰው ወይም ባህላዊ ቡድን ዘንድ እውነት የሆነው ጉዳይ በሌላው ዘንድ እውነት ላይሆን ይችላል። ይህ ደግሞ ከባለቤቱ ጋር በሚጣቀስ ምርምር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እውነታን መረዳት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባል። ምርምር በስሜት ሕዋሳቶች አማካኝነት በሚገኙ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን በብልሀት የሚሰራ፣ ግምታዊ፣ እውነታን ለመገንዘብ የሚያስችል፣ አለምን ለመረዳት የሚያስችል ትክክለኛ አካሄድ በጥቅም ላይ የዋለበት ነው። ሁልጊዜም ቢሆን አጠቃላዩ ከክፍልፋዮች ድምር በላይ ተደርጎ ይታያል። ስለዚህም አጠቃላይ የሆነውን ጉዳይ ለመረዳት አጠቃላይ በሆነ ምርምር ስርአቶችን መመርመር ያስፈልጋል (Tavakoli, 2012)።

Corbetta (2003) እንደገለጹት ትክክኛነት አንድ ተመራማሪ በሚመረመረው ጉዳይ ላይ ተጽእኖ ሳያሳድር ወይም የሚጠናው ጉዳይ ተጽእኖ ሳያሳድርበት ገለልተኛ አቋም ይዞ የሚያሳየው ከወገንተኝነት የጸዳ እውነታ ነው። የእውቀት ትክክለኛነት ዋንኛ ግብና መስፈርት ሲሆን የሚደረስበት በግምት ነው። በአእምሯዊ ሂደት መላ ምትን ለማረጋገጥ ቁልቁል የሚከናወኑ ቅደም ተከተሎች ትኩረት ይሰጣቸዋል። የምርምር ግብ አድማሳቸው ውሱን፣ ምናልባታዊና ጊዜያዊ ቢሆንም እንኳ ማጠቃለያዎችን በህግ መልክ ማዘጋጀት ነው። Tavakoli (2012)ና Ayeni et al. (2019) እንዳሉት በምርምሩ ሂደት የተመራማሪ ስሜት በጥናቱ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ስለሚችል ተመራማሪው ስሜታዊ የሆኑ ጉዳዮች ተጽእኖ የሚያሳድርበትን መንገድ አውቆ አስቀድሞ ለመቆጣጠር የሚያደርገው ጥረት በራሱ የጥናቱን ከስሜት የጸዳ መሆን ያረጋግጣል።

እውነታን ፈልጎ ለማግኘት ሁሉም ምርምሮች አንድ አይነት አካሄድን ላይጠቀሙ ይችላሉ። ምክንያቱም አንዳንዶቹ ቀጥተኛ ተሳትፎን የሚፈልግ ምልከታን የሚፈልጉ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ላይፈልጉ ይችላሉ (Tavakoli, 2012)። ስለዚህም Corbetta (2003)ና Kasimu (2019) እንደገለጹት በዚህ የምርምር ማሕቀፍነት እውነታን መርምሮ ለማግኘት የአጠናን ዘይዉ የሻሻለ ሙከራዊ፣ በሂሳባዊ ቀመር የሚከናወን ወይም አይነታዊ ሊሆን ይችላል። ይህም በምርምር ማሕቀፉ ሙከራዊ ጥናት፣ በሂሳባዊ ስሌት ላይ በተመሰረቱ መረጃዎች አማካኝነት የተላውጦዎችን የክስተት ሁኔታ መመርመርና አይነታዊ መረጃዎችን መተንተን ተቀባይነት ያላቸው ክንውኖች መሆናቸውን ያመለክታል። ተመራማሪዎች አዳዲስ መላምቶችን ይፈትሻሉ፣ ሂሳዊ በሆነ መንገድ መረጃዎችን ተንትነው ውጤት ላይ ይደርሳሉ። ውጤቶቹንም በአዳዲስ ሙከራዎች ያረጋግጣሉ። የምርምር ግኝቶች በተደጋጋሚ ተመሳሳይ በሆኑ ቁጥር እውነታነቱን የበለጠ ያረጋግጣሉ (Ayeni et al., 2019)።

2.5. የመማር ንድፈ ሀሳብ

Pritchard (2009) እንደገለጹት ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በስነልቡና የጥናት ዘርፍ ስለመማር የተዘሰነዘሩትን ንድፈ ሀሳቦች በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች የባህሪያውያን ንድፈ ሀሳብና የግንባታውያን ንድፈ ሀሳቦች ናቸው። ሁለቱም ፈርጆች ንኡሳን ፈርጆች ያሏቸው ሲሆን መማርን የሚመለከቱበት መንገድ እንደሚከተለው ያታያል።

2.5.1. ባህሪያዊ የመማር ንድፈ ሀሳብ

ባህርያዊ የመማር ንድፈ ሀሳብ (behaviorism) ለተወሰነ መቀስቀስ በሚሰጥ ምላሽ ረገድ በአይን ከሚታየው ውጫዊ ገጽታ በመነሳት ላይ ተመስርቶ የመማር ሂደትን የሚያብራራ ንድፈ ሀሳብ ነው። በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት መማር የአዳዲስ ባህርያት ምስረታ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ባህርያውያን ይህ የአዳዲስ ባህርያት ምስረታ የሚገኝበትን መንገድ ማስለመድ (conditioning) ብለው ይጠሩታል (Pritchard, 2009; Schunk, 2012)። Pritchard (2009)ና Panasuk & Lewis (2012) እንደገለጹት የባህሪያውያን ንድፈ ሀሳብ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሮ የነበረ በመማር ላይ የተሰነዘረ ስነልቡናዊ አተያይ ሲሆን ውስጣዊ ከሆኑ ሂደቶች ይልቅ በግልጽ መታየት በሚችሉ ባህርያትና በአካባቢያዊ ክስተቶች ላይ በተመሰረቱ የመማር ሂደቶች ላይ ማብራሪያ የሰጠ አተያይ ነው።

የባህሪያዊ ስነልቡናውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ የተመሰረተው አንድ እውነታ (single reality) አለ። ይህም ቁሳዊ እውቀት (Objective Knowledge) ሲሆን መለመድ ወይም በትምህርት መታወቅ ይችላል በሚል የፍልስፍና መሰረት ላይ ነው። የባህሪያውያን አተያይ በስሩ የተለያዩ የአመለካከት ዘርፎች (schools of thoughts) ቢኖሩትም ሁሉም የጋራ የሆነ አንድ አይነት አቋም ነበራቸው። ይኸውም ስነልቡና በሙከራ ጥናት መረጋገጥ ስለማይችለው ስለአእምሮ የግንባታ ሁኔታ (ለምሳሌ ስለአመለካከትና ስለእምነት) ሳይሆን በግልጽ ሊታዩ ስለሚችሉ ባህርያት ሊያጠና ይገባል የሚል ነበር። በአጠቃላይ በአእምሮ ውስጥ ያለውን ክስተትና አእምሯዊ የሆኑ ጉዳዮችን ወደ ጎን በማለት ወይም በመተው የባህሪያውያን ዋንኛ ትኩረት የነበረው የተዛምዶ አይነቶችን (types of association) መለየት፣ አካባቢያዊ ክስተቶች ባህሪን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ መረዳትና በአካባቢ ከሚከሰቱ ለውጦች ጋር ሊከሰቱ የሚችሉ የባህሪ ለውጦችን መተንበይ ነበር (Panasuk & Lewis, 2012; Brown, 2007; Jarvis, Holoford, & Griffen, 2003)።

ይሁን እንጂ Panasuk & Lewis (2012)፣ Brown (2007)፣ Jarvis et al. (2003)ና Light (2008) እንደገለጹት ከአእምሯውያን ንድፈ ሀሳብ ብቅ ማለት ጋር ተያይዞ ግንዛቤ ለመማር ወሳኝ ሚና የሚጫወት ጉዳይ መሆኑ መታወቁ ለባህርያውያን ንድፈ ሀሳብ መውደቅ በር ከፍቷል። ምክንያቱም

ባህርያውያን በቤተ መከራ እንስሳት ላይ ባደረጉት ምርምር በእንስሳቱ ላይ የሚከሰተውን በግልጽ የሚታይ ባህሪ በማብራራት ረገድ የተሳካላቸው ቢሆንም ማብራሪያቸው ውስብስብ የሆነውን የሰው ልጆች የመማር ሂደት በብቃት በማብራራት ረገድ ውስንነት ኖሮበት ተገኝቷል። ስለዚህም በመማር ላይ የሚሰጠው ትንታኔ ከባህሪ ተኮርነት ወደ አእምሮ ተኮርነት ተሸጋግሯል። በመማር ላይ በሚሰጠው ትንታኔ ረገድ ተጽእኖ የማድረጉን ሁኔታም ለአእምሯዊ ግንባታውያን አስረክቧል።

የባህሪያውያን ንድፈ ሀሳብ ውስብስብ የሆነውን የመማር ሂደት በብቃት ማብራራትና መዳሰስ ቢሳነውም ለመማር ሂደት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ሊዘነጋ አይገባም። በስነትምህርት ምርምር፣ በማስተማር ዘዴና በስነልቡና የጥናት መስክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል (Panasuk & Lewis, 2012; Schunk, 2012; Brown,2007)። ምንም እንኳ መማር የባህሪ ለውጥ ነው የሚለው ሀሳባቸው የመማርን አእምሯዊ ገጽታ ባያብራራም ሊጣል የሚገባው ጠቃሚ ያልሆነ ጉዳይ አይደለም። የባህሪያውያን ትውረት መማር የባህሪ ለውጥ መሆኑን ከመግለጽ በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለክፍል አያያዝና ለግብረ መልስ አሰጣጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ከዚህ በተጨማሪ መሰረቱን ያደረገው በግንዝብ ባህርያት ላይ በመሆኑ የተለያዩ ሁሉን አቀፍ የባህርያት ህጎችን ገልጧል። አወንታዊና አሉታዊ የሆኑ የመቀስቀስ ስልቶቹ በእንስሳትም ሆነ በሰዎች ላይ የሚፈጠሩ የባህሪ ችግሮችን በመቆጣጠር ረገድ በጣም ውጤታማ ናቸው። ስለዚህም Brown (2007)፣ Light (2008: 23)ና Pritchard (2009) እንዳሉት የተማሪዎቻቸውን ባህርያት የሚከታተሉና አወንታዊ በሆነ መንገድ የሚቀጡ ወይም የሚሸልሙ መምህራን ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ Panasuk & Lewis (2012:2) ምንጭ ጠቅሰው እንደገለጹት ምንም እንኳ የባህሪያውያን የመማር ትውረት በአእምሯዊ ግንባታውያን መተካት ትክክለኛ ቢሆንም በምርምር አለም ቀደም ሲል የነበረው ንድፈ ሀሳብ ለአዲሱ ንድፈ ሀሳብ መነሻ እንደመሆኑ መጠን የበፊቱን ሙሉ በሙሉ መተው ማለት ሳይንስን ራሱን ሙሉ ለሙሉ እንደ መተው ይቆጠራል። ስለዚህም ደካማ ጎኖቹን ወደጎን በመተው ለዚህ ምርምር የባህሪያውንን ንድፈ ሀሳብ ጠንካራ ጎኖች በቀጣይ ከሚነሱት ሌሎች ንድፈ ሀሳቦች ጋር በማዛነቅ ለምርምር መነጸሪያነት በጥቅም ላይ በጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል።

2.5.2. የግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ

የግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ (constructivism) እውቀት በተለይም ግንዛቤ በእያንዳንዱ ተማሪ ዘንድ የሚገነባበትን ሁኔታ፤ በግንባታው ሂደት የሚከናወነውን አእምሯዊ ሂደት፤ በአእምሮ ውስጥ ያለው የእውቀት አወቃቀር ምን እንደሚመስል እንዲሁም በግንዛቤ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ያደረገ የመማር

ንድፈ ሀሳብ ነው (Pritchard, 2009; Brown, 2007)። ይህ ንድፈ ሀሳብ መማር የሚከናወነው ሰዎች ንቁ ሆነው እውቀትን ሲገነቡ ሲሆን ነባራዊ እውነታ የሚወሰነው ተማሪዎቹ በሚጋለጡለት ልምድና ገጠመኝ ነው የሚል ሀሳብን ያራምዳል (Elliott, Kratochwill, Cook & Travers, 2000)። እንደ Pritchard (2009)፣ Panasuk & Lewis (2012)ና Schunk (2012) አባባል በግንባታውያን አስተሳሰብ መማር ግለሰቦች በሚያከናውኑት ተግባር አማካኝነት የሚያከናውኑት የአዳዲስ ፍቺ ምስረታ ነው። በሰዎች ዘንድ የሚከናወን የአዳዲስ ፍቺ ምስረታ በቀደመ እውቀታቸውና አዲስ በሚያከናውኑት ተግባር መካከል ባለው መስተጋብር ይወሰናል። ስለዚህም ሰዎች በቀደመ እውቀታቸው ላይ ተመስርተው አዲስ እውቀትን የሚገነቡ ሲሆን የቀደመ እውቀታቸው በአዳዲስ ልምዶች አማካኝነት የሚገነቡትን አዲስ እውቀት ይወስነዋል። ይህ ሁኔታ በግንባታውያን መሰረተ ሀሳብ እውቀት የሚገነቡት እንጂ የሚቀበሉት ወይም በዘር የሚወርሱት ጉዳይ አለመሆኑን ያስገነዝባል (Brown፣ 2007)።

የግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ሁሉን አቀፍ የሆነ የመማር ንድፈ ሀሳብ ሲሆን ግንዛቤ ከአእምሮ ውጪ በሰውነትና በስሜት ውስጥም የሚከሰት ጉዳይ አድርጎ ይወስዳል (Richardson, 2003; Pritchard, 2009; Schunk, 2012)። በዚህ መሰረት ግንዛቤ በአእምሮ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በህይወት ውስጥም ጭምር የሚከሰት ውስብስብ ጉዳይ ነው። ፍቺን የመረዳት ሂደት ጥቅል የሆነውን ጉዳይና የጥቅሉን የተለያዩ ክፍልፋዮች መገንዘብ የሚፈልግ ጉዳይ መሆኑ እሙን ሲሆን የጥቅሉ ክፍልፋዮች ሊታወቁ ወይም ግንዛቤ ሊሆኑ የሚችሉት ጥቅል ከሆነው አውድ አንጻር ነው። ምክንያቱም መማር ወደ ትንንሽ ክፍልፋዮች ወይም ጥቃቅን ቅንጣቶች ሊከፈል አይችልም። እንዲሁም ደግሞ መማር በንቁ ህሊና (consciously) ለሚታወቁ ግንዛቤ ጉዳዮች ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ በርካታ በግልጥ የማይታዩ መማሮችንና በተግባር የሚፈጸሙ እውቀቶችንም ጭምር ያካትታል። በግንባታውያን አተያይ እውቀት በግልጽ ተለይተው የማይታወቁ እውቀቶችንና በእለታዊ ህይወት የሚተገበሩ እውቀቶችን ይይዛል። ይህም Brown (2007) እንደገለጹት ንድፈ ሀሳቡ "ሰዎች የሚያውቁት እንደሚያውቁ ከሚያውቁት በላይ ነው።" የሚል መሰረተ ሀሳብን እንደሚያራምድ ያስገነዝባል። በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት መማር ሰዎች ቋሚ በሆነ የለውጥ ሂደት ላይ ካለው አለም ጋር ራሳቸውን የሚያስተካክሉበት ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል። ስለዚህም ሰዎች በአለም ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ እውቀታቸውን ያጎለብታሉ። ይንንም የሚያደርጉት በአእምሯቸው ብቻ ሳይሆን ከነባራዊው አለም ጋር በሚራከበው መላ አካላቸውም ጭምር ነው። ይህም የሰው ልጅ ስነህይወታዊ አካል ወይም ሰውነት ቁመና ከመሆን ባለፈ የሚማሩበት መዋቅር ተደርጎ እንደሚወሰድ ያመለክታል (Richardson, 2003; Light, 2008).

Panasuk & Lewis, (2012)ና Richardson (2003) እንደገለጹት በግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ እውቀት ፍዝ በሆነ ሁኔታ ከአካባቢ የሚቀበሉት ሳይሆን ንቁ በሆነ ሁኔታ እውቀቱን በሚገበዩት ሰዎች አማካኝነት የሚገነባ ጉዳይ ነው። ንድፈ ሀሳቡ ግለሰቦች አስቀድሞ በነበራቸው እውቀት፤ እምነትና

አመለካከት እንዲሁም አዲስ በሚገበዩዋቸው እውቀቶች፣ ሀሳቦችና አመለካከቶች መካከል በሚፈጠር መስተጋብር ሰዎች የራሳቸውን ግንዛቤ ይገነባሉ የሚል መሰረተ ሀሳብን ያራምዳል። ስለዚህም ለማወቅ መጣር ማለት ራስን ለተግባራዊው አለም የማስተወዋወቅ ሂደት ነው። ተማሪዎችን በእውቀት የሚሞሉ ባዶ እቃ አይደሉም። ይልቁንም ከአለም ጋር በሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎ እውቀትን የሚገነቡ ፍጥረታት ናቸው። መረጃን ፍዝ በሆነ ሁኔታ መቀበል ይቻል ይሆናል። ይህ ግን ግንዛቤ እንዲኖር አያደርግም። ግንዛቤ እንዲኖር በቀደመ እውቀታቸው፣ አዲስ በሚያገኙት መረጃና በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚያከናውኗው ተግባራት መካከል ትስስር መፈጠር ይኖርበታል። ስለዚህም Pritchard (2009)ና Schunk (2012) መሰረቱን በግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ላይ ባደረገ የመማር ማስተማር ሂደት መማር አቅምና ነጻነትን ለመገንባት ያስችላል ይላሉ። ይህ ደግሞ የግንባታውያንን ንድፈ ሀሳብ መሰረት ባደረገ የመማር ሂደት የተማሩ ተማሪዎች ፍዝ በሆነ ሌላ መንገድ ከተማሩ ተማሪዎች የተለዩ መሆናቸው በግልጽ እንዲታይ ያደርጋል። ጠቅለል ባለ አገላለጽ በራስ መተማመን በተሞላበት ሁኔታ ይናገራሉ፣ የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥ ዝግጁ ናቸው፣ የራሳቸውንም ሀሳብ በማስረጃ አስደግፈው ያቀርባሉ። ከሌሎች ጋር በመተባበር ይሰራሉ፣ ሀሳቦቻቸው ተገቢነት ያላቸው መሆናቸውን ለመረጋገጥ የሚያስችሉ መንገዶችንም ይቀይሳሉ።

እንደ Dewey (1938) አባባል መማር ማህበራዊ በመሆኑ ሰዎች እርስ በእርስ በሚያከናውኑት መስተጋብር በጋራ የሚያከናውኑት ተግባር ነው። ስለዚህም በፍቺ ምስረታ ሂደት ማህበረሰብ የጎላ ጉልህ ድርሻ አለው። ልጆች የሚያድጉበት በሚያስቡት መንገድና በሚያስቡት ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው። መማር ማስተማር በማህበር የተገነባን እውቀት የመጋራት ሂደት ሲሆን መማር የሚከናወነው በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ነው። ማለትም ተማሪዎች የተሻለ አቅም ባላቸው አካላት ድጋፍ እየተደረገላቸው በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር አማካኝነት በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል እውቀትን ይገነባሉ። እውቀትን በማህበር ቢገነቡም ባላቸው እውቀትና እሴት ላይ ተመስርቶ ሁሉም የየራሳቸው የሆነ አተያይ አላቸው። ይህ ማለት በመካከላቸው ባለ ግላዊ ልዩነት የተነሳ በአንድ አይነት የመማር ማስተማር ሂደት የተሳተፉ ተማሪዎች የተለያየ ግንዛቤን ሊጨብጡ ይችላሉ (Vygotsky, 1978)። ይህ ማለት ግን ሰዎች የጋራ እውቀት የላቸውም ማለት አይደለም። በማህበር የሚገነቡት ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን የሚጋሩት እውቀትም አላቸው። ትምህርት በከፍተኛ ሁኔታ በባህላዊ ጉዳዮች ተጽእኖ ስር የወደቀ ነው። ባህልም ሆነ የሰው ልጆች የእውቀት ክምችት በማህበር የተገነባ ደረቅ ንድፍ ሳይሆን በለውጥ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይ ነው። በመማር ሂደት በማያቋርጥ ሁኔታ ይለወጣል። Driscoll (2000) እንዳሉትም ተማሪዎች አለምን ከተገነዘቡበት እውነታ በመነሳት የየራሳቸውን ግላዊ አእምሯዊ ሞዴል ይገነባሉ። አዳዲስ ገጠመኞችን በተገነዘቡ ቁጥር በአዲሱ መረጃ ላይ ለመጸብረቅ አእምሯዊ ሞዴላቸውን ያድሱታል። ስለዚህም ስለነባራዊ እውነታ የራሳቸውን ግንዛቤ ይገነባሉ።

እንደ Light (2008)፣ Pritchard (2009)ና Panasuk & Lewis (2012) አባባል በግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ መሰረት በመማር ማስተማር ሂደት ተግባራዊ የሚደረጉ የአሰራር መርሆዎች አሉ። ከነዚህ መርሆዎች መካከል አንዱ በትምህርት ይዘት አመራረጥ ረገድ የተማሪዎቹን የብስለት ደረጃና ልምድ ያገናዘበ የትምህርት ይዘት እንዲኖር ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መነሻ ያደረገ የትምህርት ይዘት መቅረብ ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ሌላው መርህ የትምህርቱ አቀራረብ በእውነታዎችና በተማሪዎቹ ዘንድ በሚፈጠሩት አዳዲስ ግንዛቤዎች መካከል ትስስር መፈጠር ይኖርበታል የሚል ነው። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት አሳታፊና ችግር ፈቺ አሰራርን መዘርጋት እንደሚገባ ያስገነዝባል። ከዚህ በተጨማሪ መምህራን የማስተማሪያ ስልቶቻቸውን ተማሪዎች ከሚሰጡት ግብረመልስ ጋር ማጣጣም ይጠበቅባቸዋል። ይህም የቀረበውን የትምህርት ይዘት በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ተማሪዎቹ መረጃዎችን እንዲተነትኑ፣ እንዲተረጉሙና እንዲገምቱ ምቹ ሁኔታን መፍጠርም ሌላው የግንባታውያን የአሰራር መርህ ነው። ስለዚህም መምህራን ለተማሪዎቹ ክፍት ጥያቄዎችን በመስጠት በተማሪዎቹ መካከል የሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግን ትኩረት ሰጥተው ማስተግበር ይጠበቅባቸዋል።

በግንባታውያን መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት በሚከናወንበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያዩ የመማር ማስተማር ተግባራት እንዲተገበሩ ይጠበቃል። ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህም በነባራዊው አለም ላይ የተመሰረቱ ችግር ፈቺ ተግባራትን እንዲያከናውኑ፣ ከሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር የራሳቸውን ፍቺ እንዲመሰርቱ፣ እንዲጸበርቁ፣ ወላንሳነት በተሞላበት ሁኔታ ሀሳብ መሰንዘር እንዲችሉ፣ ለሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ኃላፊነትን መውሰድ እንዲችሉና እርስ በእርስ እንዲረዳዱ ለማድረግ ያስችላል። በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራን ሚና አመራር ሰጪነት ሲሆን የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ ተደርገው ይወሰዳሉ። መምህራኑ ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን የትምህርት ይዘት መረዳት መቻላቸውን፣ የሚጠበቀውን ተግባር በአግባቡ ማከናወናቸውን፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ መቻል ይኖርባቸዋል። ምዘና የመማር ሂደቱ ክፍል እንዲሆንና ተማሪዎች በመማር ሂደቱ ላይ ያላቸውን ግስጋሴ ወይም በራሳቸው ላይ ያለውን ለውጥ እንዲገመግሙ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል (Light, 2008; Panasuk & Lewis, 2012; Schunk, 2012)።

Richardson (2003)፣ Light (2008)ና Pritchard (2009) እንደገለጹት የግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ሁለት ፈርጆች አሉት። እነዚህም አእምሯዊ ግንባታውያን (cognitive constructivism)ና ማህበራዊ ግንባታውያን (social constructivism) ሲሆኑ የሶስቱም አተያይ ከዚህ ቀጥሎ ባጭሩ ተዳስሶ ቀርቧል።

2.5.2.1. አእምሯዊ ግንባታውያን

አእምሯዊ ግንባታውያን መማር ከገጠመኝ ወይም ክልምድ የሚመጣ በአእምሮ ውስጥ የሚከሰት ቋሚ የሆነ የሀሳቦች ስንስል ላይ የሚከሰት ለውጥ ሲሆን ለውጡ ውስጣዊና በቀላሉ ሊታይ የማይችል መሆኑን የሚገልጽ ንድፈ ሀሳብ ነው (Pritchard, 2009)። በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት እውቀት ተማሪዎች ባላቸው አእምሯዊ መዋቅር ላይ ተመስርቶ ንቁ ሆነው የሚመሰርቱት ጉዳይ ነው። ስለዚህም የማስተማር ዘዴዎች ተማሪዎቹ አዲስ የሚያገኙትን መረጃ ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ማስተሳሰር እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህም ቀደም ሲል በነበራቸው የእውቀት ማሕቀፍ ላይ ተገቢ የሆነውን ማሻሻያ ማድረግ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል (Jordan 2004; Schunk, 2012)። Tavakoli (2012) እንደገለጹት የንድፈ ሀሳቡ ትኩረት ተማሪዎች ነባራዊ እውነታ የሚገለጽበትን የራሳቸውን መንገድ በሚገነቡበት ሁኔታ ላይ ነው። ስለዚህም ተማሪዎች ውስብስብ የሆነ መረጃን ፈልጎ ማግኘት፣ መገንዘብና መለወጥ መቻል አለባቸው ብሎ ያምናል። መማር ለውጥ የሚከሰትበት፣ ሀሳብ ማፍለቅ የሚከናወንበትና በቀደመ እውቀት ላይ ተመስርቶ አዲስ እውቀት የሚገነባበት የእድገት ሂደት ነው።

የአእምሯዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ የህጻናት እድገትና መማርን የተመለከተ ንድፈ ሀሳብ ሲሆን ህጻናት ሲያድጉ ለግንዛቤ የሚያገለግሉና በአካባቢው ያሉትን ነገሮች ማወቅ የሚያስችሉ አእምሯዊ መዋቅር ይመሰርታሉ፤ በሌላ አገላለጽ አእምሯዊ ምስል፣ አእምሯዊ የሀሳብ ስንስል ወይም እርስ በእርስ የተሰናሰሉ ጽንሰ ሀሳቦችን ይገነባሉ። የህጻናቱ እድገት እየጨመረ በሄደ ቁጥር የእነዚህ የሀሳብ ስንስሎች እድገት ይጨምራል፤ ተፈጥሯዊ ከሆኑ እንደ ማልቀስና መጥባት ካሉ ጥቂት ምላሾች በነሳት በከፍተኛ ሁኔታ ውስብስብ ወደ ሆኑ የአእምሮ እንቅስቃሴዎች ያድጋል። የህጻናት የአእምሮ እድገት በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች የሚያልፍ ሲሆን በሁሉም የእድገት ደረጃዎች ህጻናቱ የመሰረታቸው አእምሯዊ ምስሎች የአካባቢያቸውን ልምድ ለመቅሰም፣ ለመረዳትና ለማወቅ ይጠቀሙባቸዋል። ከአካባቢያቸው የሚቀስሙት ልምድ በተደጋሚ ሲከሰት በቀላሉ ከህጻናቱ አእምሯዊ ምስል ጋር ይቀላቀላል። ይህም በህጻናቱ አእምሮ ውስጥ የእውቀት ስንስል እንዲኖር ያደርጋል። ልምዱ አዲስ ወይም የተለየ ከሆነ ደግሞ በህጻናቱ አእምሮ ውስጥ ስለዚያ ጉዳይ የተሰናሰለ እውቀት ስለማይኖር አእምሯቸው አዳዲስ ክስተቶችን ለመቀበል ይመቻቻል። በዚህ አይነት ሁኔታ የህጻናት አእምሮ የበለጠ ብቃት ባለው ሁኔታ እየሰፋና እያደገ ይሄዳል (Light, 2008; Jarvis et al. 2004)።

Light (2008)ና Jarvis et al. (2004) እንደገለጹት ይህ ንድፈ ሀሳብ በአብዛኛው የሚያተኩረው ግለሰቦች እውቀት በሚያጎለብቱበት ሁኔታ ላይ ሲሆን መማር አዲስ እውቀት የመገንባት ሂደት መሆኑን ይገልጻል። የእውቀት ግንባታ የቀደመ እውቀትን የማንቀሳቀስ፣ የማንቃት፣ የማደስ ወይም በስራ ላይ

እንዲውል ማድረግ ነው። ይህም ስለአለም የተለየ ግንዛቤ እንዲኖር ወይም አለምን በተለየ ሁኔታ መረዳት እንዲቻል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚያከናውኑት መስተጋብር በቀደመ እውቀታቸው ላይ ተመስርቶ አለምን በተለየ ሁኔታ እንዲረዱ የሚያደርጋቸውን አዲስ እውቀት ይገነባሉ። ስለዚህም እውቀት የሚቀበሉት ወይም የሚወስዱት ሳይሆን ንቁ በሆነ ሁኔታ በመራመር የሚፈክሩት ወይም የሚተረጉሙት ጉዳይ ነው።

2.5.2.2. ማህበራዊ ግንባታውያን

የማህበራዊ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ የነባራዊ እውነታን አእምሯዊና ስሜታዊ ገጽታ ለመገንባት ማህበራዊ መስተጋብርና ተረዳድቷዊ መማር ማስተማር ወሳኝ መሆናቸውን የሚገልጽ የመማር ንድፈ ሀሳብ ነው። መሰረተ ሀሳቡ የሰዎች አስተሳሰብና የፍቺ ምስረታ የሚገነባው ከማህበራዊ አካባቢያቸው ጋር በሚያርጉት መስተጋብር ነው ይላል (Tavakoli, 2012)። Brown (2007)ና Pritchard (2009) እንደገለጹት ማህበራዊ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ በአብዛኛው የVygotsky(1978) ተጽእኖ ያሳደረበት መሰረተ ሀሳብ ነው። በዚህ ንድፈ ሀሳብ ከተነሱት በሳል ጉዳዮች መካከል አንዱ የላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል (Zone of Proximal development) መሰረተ ሀሳብ ነው። የላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ተማሪዎች እስካሁን ያላከናወኑትን ተግባር የተሻለ ችሎታ ባላቸው አካላት ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚያከናውኑበት እምቅ የአእምሮ ችሎታ ነው።

አእምሯዊ እድገት ህጻናቱ በማህበራዊ መስተጋብር ከሌሎች ጋር ሀሳብ ሲጋሩ በማህበራዊ ተራክቦ የሚዳብር ሂደታዊ ውጤት ነው። በመጀመሪያ ከህጻን ጋር የሚራከብ ግለሰብ አብዛኛውን የችግር ፈቺነት ባህሪ የሚለምድበትን ሁኔታ ያስለምደዋል፤ በኋላ ግን ቀስ በቀስ ይህ ኃላፊነት ወደ ህጻኑ ይሸጋገራል። ቋንቋ በዋነኝነት በመስተጋብር ሂደት ህጻናት ከታላላቆቻቸው ጋር ሀሳብን የሚጋሩበት የበለጸገ የእውቀት አካል ነው። የመማር ሂደት እየጨመረ ወይም እየገሰገሰ ሲሄድ ቋንቋ ለህጻናቱ ዋንኛ የማወቂያ መንገድ ይሆናቸዋል። በሂደትም ህጻናት በውስጣቸው ያለውን ቋንቋ የራሳቸውን ባህሪ አቅጣጫ ለማስያዝ ይጠቀሙበታል። ማስረጽ የመማር ሂደትን የሚገልጽ ሲሆን በመጀመሪያ ከህጻናት አእምሮ ውጪ የነበረን የበለጸገ እውቀት ወደ ህጻናት አእምሮ እንዲዘልቅ ወይም እንዲሰርግ የማድረግ ሂደት ነው። ይህም በዋነኝነት የሚሆነው በቋንቋ አማካኝነት-ት ነው (Pritchard, 2009; Schunk, 2012)።

Light (2008)ና Schunk (2012) እንደገለጹት ግንዛቤ ግለሰባዊ ሂደት ሳይሆን የጋራ ሂደት ነው። ከማህበራዊ መስተጋብር የሚመሰረቱ ግንዛቤዎች ወይም ግንዝብ ሀሳቦች በግለ ሰባዊ ደረጃ ከሚከሰቱት ግንዛቤዎች የበለጡ ናቸው። ስለዚህም በማስተማር ሂደት ለማህበራዊ መስተጋብርና ለምልልስ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ህጻናት ሀሳብ ለመጋራት በቡድን ሲሰሩ ትምህርታዊ ችግሮችን በጋራ ይፈታሉ።

ስለዚህም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በትንንሽ ቡድኖች ተከፋፍለው በሚያደርጉት መስተጋብር ችግሮችን እንዲፈቱ መደረግ መቻል ይኖርበታል፡፡

2.5.2.3. የግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ ፈርጆች የትኩረት ነጥብ ተመሳስሎና ልዩነት

Richardson, (2003)ና Pritchard, (2009) እንደገለጹት አእምሯዊና ማህበራዊ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች የሚያመሳስሏቸውና የሚያለያዩዋቸው የትኩረት ነጥቦች አሉ፡፡ ይህንንም እንደሚከተለው ባጭሩ ለማየት ይሞከራል፡፡

ሁለቱም ንድፈ ሀሳቦች አእምሯዊ በሆነው የእውቀት ግንባታ ሂደት ላይ ትንታኔ የሰጡ ናቸው፡፡ እውቀት ወይም ፍቺ ንቁ በሆነ ሁኔታ በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ይገነባል የሚል ጠንካራ አቋም አላቸው (Brown, 2007; Schunk, 2012)፡፡ ስለዚህም የመማር ማስተማሩ ሂደት አሳታፊና ተማሪ ተኮር መሆን ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎች በትምህርትነት በሚሰጠው ጉዳይ ላይ የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ፣ አዲስ ፍቺ መመስረትና እውቀትን መገንባት እንዲችሉ በክፍል ውስጥ በሚከናወን መስተጋብር ንቁ ሆነው መሳተፍ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡ Richardson (2003)ና Pritchard (2009) እንደገለጹት በሁለቱም ንድፈ ሀሳቦች አተያይ ተማሪዎቹ የትኛውንም የመማር ማስተማር ተግባር ማከናወን ያለባቸው ወደ መማሪያ ክፍል ሲመጡ ባላቸው የቀደመ ልምድ ላይ ተመስርቶ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚቀርበው የትምህርት ይዘትም የተማሪዎቹን ችሎታና ፍላጎት ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን በተከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ መጸብረቅ መቻል ይርባቸዋል፡፡

ሁለቱ ንድፈ ሀሳቦች የሚያመሳስል የትኩረት ነጥብ እንዳላቸው ሁሉ የሚያለያይም አላቸው፡፡ እንደ Jupp (2006)ና Brown (2007) አገላለጽ የአእምሯዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ የአእምሮ እድገት ወይም ለመማር ዝግጁ መሆን ከመማር መቅደም እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ለአእምሯውያን አእምሮ የሚዳብርበት ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል ያለው ሲሆን የአእምሮ እድገት ለመማር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት መማርም ሆነ ማህበራዊ መስተጋብር ውጤታማ የሚሆኑት ተፈጥሯዊ ከሆነው የአእምሮ እድገት ጋር አብሮ መራመድ ሲችሉ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Richardson (2003)ና Pritchard (2009) እንደገለጹት የአእምሯዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ በግሰቦች አእምሮ ውስጥ በግል፣ በቡድኖች መካከል ደግሞ በጋራ ፍቺ ወይም እውቀት እንዴት እንደሚገነባ የተመለከተ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ንድፈ ሀሳቡ እያንዳንዱ ተማሪ የቀደመ እውቀቱን መነሻ በማድረግ በግሉ ንቁ በሆነ ሁኔታ ፍቺን የሚገነባበትን ሁኔታ ይተነትናል፡፡ ይህ ግን ፍቺ በጋራ አይገነባም ማለት አይደለም፡፡ በፍቺ ግንባታ

ሂደት ቡድኖች ስለአንድ ክስተት ሁኔታና ተፈጥሮ የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረስ ከቻሉ በቡድኖች መካከል የጋራ የሆነ የፍቺ ግንባታ ሊኖር ይችላል። የጋራ በሆነ የፍቺ ግንባታ የሚመሰረቱ ፍቺዎች የቡድኖቹ የጋራ ግንዛቤ ይሆናሉ።

የማህራዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ማህበራዊ መስተጋብር ለአእምሮ እድገት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ይገልጻል። በዚህ ንድፈ ሀሳብ አተያይ የአእምሮ እድገትና መማር አብረው የሚሄዱ ጉዳዮች ናቸው። ይህ አባባል ንድፈ ሀሳቡ የአእምሮ እድገት ከመማር መቅደም አለበት የሚለውን ሀሳብ የማይቀበል መሆኑን ያስገነዝባል (Jupp, 2006; Brown, 2007)። Richardson (2003)ና Pritchard (2009) እንደገለጹት የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ እውቀት በማህበር በሚገነባበት ሁኔታ ላይ ትንታኔ የሚሰጥ የአስተሳሰብ ማሕቀፍ ነው። አካባቢ የሰው ልጅ አለምን በሚረዳበት ሁኔታ ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር አሳይቷል። እንደ ንድፈ ሀሳቡ አራማጆች እምነት አንድ ሰው በሚኖርበት አለም ውስጥ በዙሪያው ያሉ ማህበራዊ ጉዳዮች ነባራዊውን አለም በሚገነዘብበት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። ሰዎች የሚኖሩበት አለም እንዲሁም በዙሪያቸው ያሉት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚዊ ጉዳዮች ነባራዊውን አለም በሚገነዘብበት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ እስካሳደሩ ድረስ የሰው ልጅ እውቀት ሚዛናዊ ሊሆን አይችልም የሚል አተያይ አለው።

2.5.3. መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ

መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ (constructive based learning theory፡ eclectic approach) መሰረቱን በግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ ላይ ያደረገና በመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማነት አወንታዊ ተጽኦኖ የሚያሳድሩ መሰረተ ሀሳቦችን ከሁሉም ንድፈ ሀሳቦች እንዲወስድ ተደርጎ የተቀነባበረ የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አቀራብ (eclectic approach) ነው:: Brown (2007) እንደገለጹት የመማር ንድፈ ሀሳቦች በተለያዩ የትኩረት ነጥቦች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ የመማርን የተለያዩ ገጽታዎች የተመለከቱ ናቸው። በመሆኑም የተለያዩ የመማር ንድፈ ሀሳቦችን በጥምረት መጠቀም በአንደኛው ያልታየውን ጉዳይ በሌላው ለማየት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በዚህ መሰረት በዚህ ጥናት ውስጥ መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ የሚባለው የመማር ንድፈ ሀሳቦቹን ደካማ ጎኖች ወደ ጎን በማለት የባህርያውያንም ሆነ የግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች የዳሰሷቸውን ነጥቦች ለመዳሰስ የሚያስችልና ጠንካራ ጎኖቻቸውን አቀናጅቶ ለመጠቀም የሚያስችል ጥምረታዊ አሰራር ነው። ስለዚህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ የመረመረው ይህ ጥናት በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ማሕቀፍነት ተከናውኗል።

2.6. የግንባታውያን ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ

ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ (Language Learning Theory) ሰዎች ቋንቋን እንዴት ይማሩታል በሚለው ጉዳይ ላይ ትንታኔ የሚሰጥ ንድፈ ሀሳብ ሲሆን የሚያነሳው ቁልፍ ጉዳይ አንድ ሰው የአፍ መፍቻ ወይም ሁለተኛ ቋንቋውን ሲለምድ የሚከሰተውን ክስተት ነው (Jordan, 2004; Andorson, 2005; Brown, 2007; Assanova & Kim, 2014)። ይህ ክስተት ቋንቋ እንዴት ይለመዳል የሚለውን መሰረታዊ ጉዳይ አስመልክቶ ትንታኔ የሚሰጥ ሲሆን የሚያተኩረው በተግባቦት ችሎታ ላይ ነው። የተግባቦት ችሎታ በማህበራዊ መስተጋብር ሂደት ሰዎች የሚያስተላልፉትን መረጃ የመቀበል፣ የተቀበሉትን መረጃ ተረድቶ በራስ አባባል የመግለጽና ሰዎች እንዲረዱት አድርጎ መልእክትን የማስተላለፍ ችሎታ ነው። ይህ ችሎታ በትምህርት ሊዳብር የሚችል ሲሆን መዳበሩ በተግባቦት ሂደት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመሳተፍ ያስችላል። Xia (2014) እንደገለጹት የዳበረ የተግባቦት ችሎታ የሚባለው ግልጽ በሆነና በማያሻማ ሁኔታ መረጃን ለሌሎች የማስተላለፍና ሌሎች የሚስተላልፉትንም መረጃ የመቀበል ችሎታ ነው። ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ በተግባቦት ችሎታ ረገድ በሰዎች መካከል ልዩነት የሚኖረው እንዴት ነው? ለሚለው ቁልፍ ጉዳይ ማብራሪያ ይሰጣል።

Stern (1991)፣ Jordan (2004)፣ Adamson (2005)ና Brown (2007) እንደገለጹት እሰካሁን ድረስ ስለቋንቋ መማር ሶስት ንድፈ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል። ከነዚህ ንድፈ ሀሳቦች መካከል ይህ ጥናት የግንባታውያንን ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ ተገን አድርጓል። ንድፈ ሀሳቡ ለተገንነት የተመረጠበት ምክንያት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ ማህበራዊ መስተጋብር የሚከናወን የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎችን በትምህርታቸው ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ ከመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ ዝንቅ ጋር አብሮ የሚራመድ በመሆኑ ነው። የግንባታውያን ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በህጻኑ ሰብኣዊ ባህርያትና በሚያድግበት ማህበራዊ አካባቢ መካከል በሚደረግ ማህበራዊ መስተጋብር ይለመዳል የሚል ሲሆን መነሻው የግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ነው። በቋንቋ ለመዳ ሂደት ተማሪዎቹ እድሜያቸውንና ችሎታቸውን ላገናዘበ የቋንቋ ትምህርት ይዘት መጋለጣቸው ለለመዳው ወሳኝነት እንዳለው ያስገነዝባሉ። እንደ Wells (2004) አባባል በቋንቋ ለመዳ ሂደት ለለመዳው መፋጠን ዋንኛና ወሳኝ የሆኑት ጉዳዮች ለማጀቹ የሚያገኙት ስነልሳናዊ ግብዓት ተስተዋይ መሆኑና በተማሪዎቹ መካከል የሚኖር መስተጋብር ናቸው።

2.7. ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ

ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ተግባቦት በግብይት የሚካሄድበትን የመማር ማስተማር ሂደት የሚያሳይ ማሕቀፍ ሲሆን Huitt (2003፡2) የቀረቡትን ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ

(a transactional framework of the teaching/ learning process)ና ግብይታዊ የተግባቦት ማሕቀፎችን መነሻ በማድረግ ለዚህ ጥናት በጥናቱ አቅራቢ አማካኝት የተዘጋጀ ነው። እነዚህን ማሕቀፎች መነሻ በማድረግ አዲስ ማእቀፍ ማዘጋጀት ያስፈለገው ቀደም ሲል የነበሩት ከሁለት በላይ ተሳታፊዎች ባሉበት የመማር ማስማር ሂደት በክፍል ውስጥ የሚከናወነውን ትምህርታዊ ተግባቦትና የመረጃ ፍሰቱን ስለማያሳዩ ነው። ከዚህ በተናጠል በተጨማሪ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት መምህራኑ ወደ መማሪያ ክፍል ከመምጣታቸው በፊት ያዳበሩት ባህሪ መሆኑን አያሳዩም። አዲሱ ማሕቀፍ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት በክፍል ውስጥ በሚከናወን ትምህርታዊ መስተጋብር የሚኖረውን የመረጃ ፍሰትና በዚህ የመረጃ ፍሰት ላይ የመምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚኖረውን ቦታ ያሳያል። ይህ ማሕቀፍ በስእል 1 ላይ የቀረበውን ይመስላል።

ስእል 1፡ ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ



በስእል አንድ ላይ እንደሚታየው አጠቃላይ የመማር ማስተማርን ገጽታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን ገጽታው አካባቢያዊ አውድ፣ ግብኣት፣ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደትና ውጽኣት በተባሉ አራት ፈርጆች ተከፍለው ቀርበዋል። ማሕቀፉ በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በውስጡ ያሉት ፈርጆች እንደሚከተለው ተብራርተው ቀርበዋል።

2.7.1. አውድ

ከውጪ ወደ ውስጥ ሲታይ የመጀመሪያው አካባቢያዊ አውድ ነው። በመማር ማስተማር ሂደት ማሕቀፉ ላይ በአረንጓዴ ቀለም የተመለከተ ሲሆን ከመማሪያ ክፍል ውጪ ያሉትን በመማር ማስተማሩና ተማሪዎቹ በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዮችን በሙሉ ያጠቃልላል (ስእል 1ን ይመልከቱ)። እነዚህ ጉዳዮች ከመማሪያ ክፍል ውጪ በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጪ በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ ጉዳዮች ናቸው። በትምህርት ቤት ያሉት የትምህርት ቤቱ አስተዳደራዊ መዋቅር፤ የትምህርት ቤቱ ሁኔታ፤ ከትምህርት ቤት አመራር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፤ የግምገማና የቁጥጥር ሁኔታ፤ የትምህርት ቤቱ አካባቢ እንዲሁም የትምህርት ቤቱ ፖሊሲ ናቸው። ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ ጉዳዮች ደግሞ ተማሪዎቹን በቤት ውስጥና ከቤት ውጪ የሚጋጥሟቸው ጉዳዮች፣ የብጤ ተጽእኖ፣ ሀይማኖዊ ጉዳዮች፣ አለማቀፋዊ ሁኔታዎች፣ የወላጆች የትምህርት ደረጃ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አቅርቦት፣ መጻህፍት፣ ጋዜጦች፣ ማህበረሰቡ የሚገኝበት መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ማህበረሰቡ ለትምህርት የሚሰጠው ቦታ፣ በአካባቢው ያሉ ማህበራዊ ተቋማት፣ ባህላዊ ዳራ፣ የቋንቋ ዳራ፣ ኪነጥበብ፣ ሙዚቃ፣ የመንግስት ፖሊሲዎችና ለመረጃ ያለ ቀረቤታን ይመለከታሉ።

2.7.2. ግብኣት

ግብኣት በማሕቀፉ ውስጥ ከተነሱት ፈርጆች መካከል ሁለተኛው ሲሆን መምህራንና ተማሪዎች ወደ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሲመጡ የሚኖራቸውን ችሎታ፣ እውቀትና ስሜታዊ ጉዳዮች ይመለከታል።ይ ፈርጅ በስእል አንድ ላይ ከትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ በስተቀኝ ያለውንና በብርቱካናማ ቀለም የተቀባው ነው (ስእል 1ን ይመልከቱ)። በስእላዊ መግለጫው ላይ እንደሚታየው የተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ግብኣት ሁለት አበይት ክፍሎች አሉት። እነዚህም የተማሪዎች ባህርያትና የመምህራን ባህርያት ናቸው። የተማሪዎች ባህርያት የሚባሉት ተማሪዎች ወደ መማሪያ ክፍል ሲመጡ የሚኖራቸውን እውቀት፣ ክህሎት፣ የመማር ስልት፣ የትምህርት አቀባበል ችሎታና ማንነት ናቸው። የመምህራን ባህርያት ደግሞ መምህራን በስራ ልምድና በስልጠና ሂደት ያዳበሩትና የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራትን በብቃት ለማከናወን የሚያስችላቸው እውቀት፣ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም፣ ሙያዊ ብቃት፣ ስብእና ወይም አመለካከት ነው። የዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተት ሲሆን የሚገለጠው በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መማር ማስተማር ሲከናወን ነው።

2.7.3. የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት

ሶስተኛው ፈርጅ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ሲሆን በትምህርቱ ሂደት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራትና ተላውጦዎች በሙሉ የሚያካትት ነው። በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራኑና ተማሪዎቹ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር የሚለዋወጡበትን ሂደትና ሌሎች ጉዳዮችን ያካትታል። መምህራንና ተማሪዎች መረጃ የሚለዋወጡበት ሂደት የመምህርና የተማሪ ተግባራትን ያካትታል። የመምህራን ተግባራት እቅድን መተግበር፣ ትምህርቱን ማቅረብ አመራር መስጠት፣ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግና ግብረመልስ መሰጠት ናቸው። መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚያከናውኑት የክፍል ውስጥ መስተጋብር፣ የተማሪዎችን ባህሪ ለመቆጣጠር የሚያከናውኗቸው ተግባራት፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚመሩበት መንገድ፣ የሚጠቀሙበት የትምህርት አቀራብ ስልት፣ የሚተገብሯቸው ንቁ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲሁም በየክፍለ ጊዜው በሚያከናውኗቸው ተግባራት የእነርሱንም ሆነ የተማሪዎቻቸውን ውጤታማነት የሚመዝኑበት መንገድ በዚህ ስር ይካተታል። እነዚህ ተግባራት መምህራን በስልጠና ሂደት ያካበቱትን አውቀት፣ ልምድ፣ ክህሎት ወይም በግብአት መልክ ወደ መማሪያ ክፍል ያመጡትን እምቅ ችሎታ በጥቅም ላይ የሚያውሉበት ነው። ወደ መማሪያ ክፍል ሲመጡ የታጠቁትን የተግባቦት ክህሎት በጥቅም ላይ ያውሉበታል። የተማሪ ተግባራት የተባሉት ተማሪዎቹ ከመምህራን በሚሰጣቸው አመራር መሰረት የሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ክንውኖች ናቸው። ለመማር ማስተማሩ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ጉዳዮች የተባሉት ደግሞ የመማሪያ መጻሕፍት፣ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች፣ የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ናቸው። በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ላይ በውሀ ሰማያዊ ቀለም የተቀባው ክፍል ነው (ስእል 1ን ይመልከቱ)።

በዚህኛው ክፍል የመምህር ተግባራትና የተማሪ ተግባራት በተግባር ሲገለጡ የትምህርታዊ ተግባቦት ስርአተ ሂደት ይከናወናል። ክንውኑ የትምህርታዊ መረጃ ልውውጥ እውን እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ሲሆን ከፍ ሲል በቀረበው ስእላዊ መግለጫ በቀይ ቀለም ተከበው በቀስት ተመልክተዋል።

የትምህርታዊ ተግባቦት ስርአተ ሂደት መረጃ በትምህርታዊ ተግባቦት አላባውያን ዘንድ የሚዘዋወርበት ሂደት ነው (Krauss & Fussell, 1997; Hill, Watson & Rivers, 2007)። ለትምህርታዊ የተግባቦት ሞዴሎች መነሻ የሆኑት የተግባቦት ሞዴሎች ናቸው። እስካሁን ድረስ የተሰነዘሩት የተግባቦት ሞዴሎች በሁለት አበይት ፈርጆች ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። እነዚህም መስመራዊ ሞዴል (Linear model)ና ጎብረ ስፍረታዊ ሞዴል (Multi-Dimensional Model) ናቸው። መስመራዊ ሞዴሎች መረጃ በአንድ አቅጣጫ ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ የሚፈስበትን ስርአተ ሂደት የሚያሳዩ ናቸው። ጎብረ ስፍረታዊ ሞዴሎች ደግሞ መረጃ ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ እንዲሁም

ከመልእክት ተቀባይ ወደ መልእክት አስተላላፊ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚፈስበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ናቸው። ጎብረ ስፍረታዊ ሞዴሎች በሁለት አበይት አይነቶች የሚከፈሉ ሲሆን መስተጋብራዊ (interactional)ና ግብይታዊ (transactional) ሞዴሎች ናቸው። ከነዚህ መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጠው ግብይታዊ ሞዴል ነው።

Krauss & Fussell (1997) ፣ Hill, Watson & Rivers, (2007)ና Berko, Aithken & Wolvin (2010) እንደገለጹት ግብይታዊ ሞዴል የተግባቦት ሂደት አላባውያን እርስ በእርስ የተሳሰሩና የአንዱ መኖር በሌላው ላይ የተመሰረተ መሆኑን፤ በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊ የሆነ እያንዳንዱ ሰው የመልእክት አስተላላፊነትንና የመልእክት ተቀባይነት ሚና የሚጫወት መሆኑን እንዲሁም የተግባቦቱ ተሳታፊዎች በተመሳሳይ ጊዜ መልእክት ማስተላለፍና መልእክት መቀበል እንደሚችሉ የሚያሳይ የተግባቦት ሞዴል ነው። እንደ Krauss & Fussell (1997) አባባል "ግብይታዊ" የሚለው አገላለጽ ተግባቦት በሂደት የሚከናወን፣ በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ላይ ያለና በሂደቱ በመልእክት ምንጭና በመልእክት ተቀባይ መካከል መረጃ ምልልሳዊ በሆነ መንገድ የሚዘዋወር መሆኑን ያመለክታል። ዝውውሩ አዳዲስ መረጃዎች የሚቀሰሙበትና ግንዛቤ የሚጨበጥበት በመሆኑ መልእክት አስተላላፊ፣ መልእክት ተቀባይም ሆኑ የተግባቦቱ አውድ በማያቋርጥ ሁኔታ ይለወጣሉ። ምልልሳዊነቱ መረጃ ከመልእክት ምንጭ ወደ ተቀባይ እንዲሁም ከመልእክት ተቀባይ ወደ ምንጭ የሚዘዋወር መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ ሁሉም የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መልእክት ያመነጫሉ፤ ያስተላልፋሉ፤ ይቀበላሉ፤ ግብረመልስ ይሰጣሉ፤ እንዲሁም ይገነዘባሉ (Hill et al., 2007)።

በየትኛውም የተግባቦት ግብይታዊ ሂደት፣ እያንዳንዱ የተግባቦት መሰረታዊ ነገር የሚገለጠው ከሌሎቹ የተግባቦት መሰረታዊ ነገሮች መገለጥ ጋር ተያይዞ ነው (Krauss & Fussell, 1997; Hill et al., 2007; Berko et al., 2010; McPheat, 2010)። ይህ የሆነበት ምክንያት የተግባቦት ምንጭ በሌለበት ሁኔታ መልእክት፣ መልእክት ተቀባይ ወይም በጥቅሉ ሌሎቹ የተግባቦት መሰረታዊ ነገሮች ሊኖሩ የማይችሉ በመሆናቸው ነው። በተመሳሳይ የመልእክት መተላለፊያ በሌለበት ሁኔታ መልእክት ከመልእክት ምንጭ ወደ መልእክት ተቀባይ ሊደርስ አይችልም። ሲሰልስ የተግባቦቱ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች እያንዳንዳቸው በተግባቦቱ ሂደት ምላሽ የሚሰጡት ባላቸው ዳራ፣ ልምድ፣ ገጠመኝ፣ የቀደመ እውቀት፣ አመለካከት፣ ባህል፣ እምነትና ግለ ግንዛቤ ላይ ተመስርቶ ነው።

ግብይታዊ ሞዴል ሁለቱንም ተግባቢዎች መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ ብሎ በተመሳሳይ ጊዜ የሚሰይማቸው ከመሆኑም በላይ የተግባቦትን ማህበራዊ ገጽታና በተግባቦት ሂደት የሚኖርን የተግባቦት እንቅፋት ከግንዛቤ ያስገባ ነው (Krauss & Fussell, 1997; Hargie & Dickson, 2005;

Berko et al., 2010)። በይነሰባዊ ተግባቦት በባህሪው ሂደታዊ፣ አሳታፊ፣ መልእክት የሚተላለፍበት፣ መልእክትን የመወከልና የመተርጎም ተግባር የሚከናወንበት፣ በሂደቱ ውስጥ የተግባቦት እንቅፋቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ የሚያሳይ፣ ግብረመልስ የሚሰጥበት፣ በአንድ በተወሰነ የተግባቦት አውድ ውስጥ የሚከሰትና በሂደቱ መረጃዎች በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሰራጩ መሆኑን የሚያሳይ ነው (Krauss & Fussell, 1997)። እንደ እኛሁ ምሁር አገላለጽ ሁለቱም መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ በጋራ መስተጋብር በሚያከናውኑበት የተግባቦት አውድ ውስጥ የጋራ በሆነ ጉዳይ ላይ ሀሳብ ለሀሳብ ሲለዋወጡ ይከሰታል። ከሌሎቹ ሞዴሎች በበለጠ ሁኔታ በሰዎች መካከል የሚካሄደውን የተግባቦት ሂደት ትክክለኛ ተፈጥሮ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ሁሉንም የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በተመሳሳይ ሰአት መልእክት የሚያስተላልፉና መልእክት የሚቀበሉ አድርጎ ይመለከታቸዋል። Hill et al. (2007) እንደገለጹት ለዚህ ምክንያቱ በተመሳሳይ ሰአት መልእክትን በምልክት ወክለው ማስተላለፋቸው፤ ሌሎች የሚያስተላልፉትን መልእክት ተቀብለው በመተርጎም መረዳታቸው እንዲሁም የተናጋሪነትንና የግብረመልስ ሰጪነትን ሚናን መጫወታቸው ነው።

በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚከሰተውን ግብይታዊ የተግባቦት ስርአተ ሂደት የተቀናበረው Dixton & Hara (2006:10)፣ McPheat (2010:13)ና Wrench et al. (2009:4) ካቀረቧቸው የተግባቦት ሞዴሎች በመነሳትና በመማር ማስተማሩ ሂደት ሊኖሩ የሚችሉ ምልልሳዊ የመረጃ ዝውውሮችን ያገናዘበ ማሻሻያ በማድረግ ነው። ይህ ሞዴል አራት ተማሪዎችና አንድ መምህር በሚገኙበት ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት በተግባቦት ተሳታፊዎች መካከል መረጃ በምልልስ የሚሰራጭበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ከተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማእቀፍ ተነጥሎ ወጥቶ ለብቻው ሲታይ በስእል 2 ላይ የቀረበውን ይመስላል።

በስእል ሁለት ላይ እንደሚታየው በውሀ ሰማያዊ ቀለም የተቀባው አራት መአዘን የትምህርቱ አውድ ነው። የትምህርት አውድ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መከሰቻ ነው። በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከሰቱ የተግባቦቱ ሂደት መሰረታዊ ነገሮች ሁሉ በውስጡ ያረፉ ናቸው። በአውዱ ውስጥ በወርቃማ ቀለም ተስለው የሚታዩት ጨረሮች በተግባቦቱ ሂደት መሰረታዊ ነገሮች መካከል ትምህርታዊ መረጃ የሚዘዋወርበትን ሁኔታ ያሳያሉ። እያንዳንዱ ተሳታፊ በትምህርት አውድ ውስጥ በሚኖረው ግላዊ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ በተግባቦቱ ሂደት መልእክትን ከአእምሮ የማፍለቅ፣ በምልክት የመወከልና በመልእክት መተላለፊያ አማካኝነት የማስተላለፍ፤ የተላለፈውን መልእክት ተቀብሎ የመተርጎምና ምላሽ ወይም ግብረመልስ የመስጠት ተግባርን ያከናውናል። አንድ ጊዜ የመጀመሪያው የመልእክት ምንጭ ከሆኑት ከመምህሩ መልእክት ከመነጨ በኋላ ሁሉም የተግባቦት ተሳታፊዎች በተመሳሳይ ጊዜ መልእክትን ከአእምሯቸው ያፈልቃሉ፤ በምልክት ይወክላሉ፤ በመልእክት መተላለፊያ አማካኝነት ወደ መልእክት ተቀባይ ያስተላልፋሉ፤ መልእክትን ይቀበላሉ፤ የተቀበሉትን መልእክት ይተረጉማሉ፤

እንዲሁም ተርጉመው ባገኙት ግንዛቤ ላይ ተመስርተው ግብረመልስ ይሰጣሉ። ይህ ክስተት ከሁሉም ተሳታፊዎች ወደ ሁሉም ተሳታፊዎች በሚሄደው ደማቅ ያልተቆራረጠ ወርቃማ ጨረር ተመልክቷል። ጨረሩ የመጀመሪያው መልእክት ምንጭ የሆኑት መምህሩ ካሉበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ የሆነው በመርህ ደረጃ መምህሩ መልእክቱን የሚያመነጩት ለአውዱና ለትምህርቱ ግብ ምቹ በሆነ ሁኔታ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን አንድ ጊዜ ከመነጨ በኋላ እንቅፋት ካልገጠመው በስተቀር በተግባቦቱ ሂደት የሚሰራጨው መረጃ ሙሉ በሙሉ በዚህ መረጃ ዙሪያ የሚያጠነጥንና ግንዛቤ ሆኖ የሚጨበጥ መሆኑን ለማመላከት ነው።

ስእል 2፡ በመማሪያ ክፍል የሚከናወን የትምህርታዊ ተግባቦት ስርአተ ሂደት



በዚህ ሂደት በትምህርቱ አውድ ውስጥ፣ በተሳታፊዎች ዘንድ፣ በማስተማሪያ ስልት ችግር፣ በመልእክት አወካከል፣ በራሱ በአውዱ ላይ ከሚከሰቱ ችግሮች የተነሳ ወይም በመልእክት አተረጓጎም ረገድ በሚከሰቱ ችግሮች የተነሳ የተግባቦቱን ሂደት የሚያደናቅፉ እንቅፋቶች ሊከሰቱ ይችላሉ። እንቅፋቶቹ በተግባቦቱ ተሳታፊዎች ዘንድ ጥቂት እንቅፋት ከመፍጠር አንስቶ ሙሉ በሙሉ የጋራ መግባባት እንዳይኖር እስከማድረግ ሊደርሱ ይችላሉ። እነዚህ እንቅፋቶች በአውዱ ውስጥ በተቀመጡት የተቆራረጡ ጥቋቁር ጨረሮች ተመልክተዋል።

በዚህ አካሄድ በተግባቦት ሂደት መረጃ ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ አአምሮ ደርሶ ተተርጉሞና ተተንትኖ ግንዛቤ ለመሆን የሚያልፍበት ሂደት አለው። ይህ ሂደት የግንዛቤ መጨበጫ ሂደት ተብሎ ይጠራል። McPheat (2010)ና Barker (2011) እንደገለጹት የሂደቱ የመጀመሪያ ተግባር መረጃ በቃላዊና ኢቃላዊ ምልክቶች ወይም በትምህርታዊ መረጃ መገበያያዎች ተወክሎ ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ አእምሮ ለመድረስ ዝግጁ መሆኑ ነው። ከዚያም የተወከለው መረጃ በአምስቱም የስሜት ህዋሳት አማካኝነት ወደ መልእክት ተቀባዩ አእምሮ ይደርሳል። በመቀጠል መልእክቱ በአእምሮ አማካኝነት ይስተዋልና ይጣራል። ተስተውሎ ሲጣራ አእምሮ ሶስት ነገሮችን ሊያከናውን ይችላል። እነዚህም የማይጠቅሙትን ማስወገድ፣ ከመልእክት አስተላላፊው በተለየ መንገድ አዛብቶ መተርጎምና ቀደም ሲል ከሚያውቁት ጋር አዛምዶ ማጠቃለል ናቸው። መልእክት በዚህ መልኩ ከተስተዋለ በኋላ ምስል ፈጠራ ይከናወናል። ይህንን የተፈጠረ ምስል ቀደም ሲል በነበረው ልምድና ገጠመኝ፣ በተግባቦቱ አውድና ከመልእክት አስተላላፊው ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ራሱ መልእክት ተቀባዩ በሚረዳው መንገድ በቋንቋ አማካኝነት ይተረጉመዋል፤ መልክ ያስይዘዋል፤ በአእምሮው ወስጣዊ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ማለትም በማመዛዘን፣ በአመክንዮና በግምገማ ቅበላ፣ ፍርሀት፣ ተቃውሞ፣ ደስታና ሽሽት የመሳሰሉ ክስተቶችን ይከስታል። ከዚያም በተፈጠረው ውስጣዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ እነዚህን ውስጣዊ ሁኔታዎችና ባህርያት ወደ መልእክት አስተላላፊው የሚያደርሱ ምላሾች (ግብረመልሶች) ከመልእክት ተቀባይ አእምሮ ይወጣሉ። እነዚህ ከመልእክት ተቀባዩ አእምሮ የወጡ ምላሾች አሁንም ወደ መልእክት አስተላላፊው ይደርሱ ዘንድ በተግባቦት ክህሎት አማካኝነት በምልክት ይወከሉና በመልእክት መተላለፊያ በኩል አድርገው ወደ መልእክት ተቀባዮች ይተላለፋሉ። ሂደቱ የተግባቦቱ ሂደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ በተመሳሳይ ሁኔታ ይቀጥላል።

Barker (2011) እንደገለጹት ጥሩ የተግባቦት ሂደት ሊኖር የሚችለው የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መልእክትን በምልክት ከመወከል አንስቶ አእምሮ ምላሽ እስከሚሰጥበት ደረጃ ያለውን ሂደት ትኩረት ሰጥተው ማከናወን ሲችሉ ነው። ተሳታፊዎቹ መልእክትን በምልክት ሲወክሉ ውጤታማ ካልሆኑ በቀጣይ የሚከናወኑት ሂደቶች በሙሉ ችግር ይገጥማቸዋል። ስለዚህም የተግባቦት እንቅፋት ይከሰትና የመልእክት ምንጭና መልእክት ተቀባይ የጋራ ግንዛቤን የመጨበጥ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። ለምሳሌ መምህሩ የእለቱን ትምህርታዊ መረጃ ሲወክሉ የአወካከል ችግር ካለበት ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን የትምህርት ይዘት ሊረዱት አይችሉም። እናም የተግባቦት እንቅፋቶች ይፈጠሩና የትምህርቱ አላማ ግቡን እንዳይመታ መሰናክል ይሆናሉ።

እንደ Crystal (2000)፣ Hybels & Weaver II (2004)ና Barker (2011) አገላለጽ ተግባቦት በማያቋርጥ ሂደት ላይ ያለ፣ ሁልጊዜም ሰዎች ግንዛቤያቸውን የሚያድሱበትና ይዘውት በተነሱት የተግባቦት ዓላማ ስኬታማነትን የሚጎናጸፉበት ጉዳይ ነው። በተግባቦቱ ሂደት በተሳታፊዎቹ መካከል

የሚከናወነው መልእክትን የማፍለቅ፣ በምልክት ወክሎ የማስተላለፍ፤ መልእክትን የመቀበል፣ የመተርጎምና ግብረመልስ የመስጠቱ ሂደት በማያቋርጥ ሂደት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ የተግባቦት ሂደት እውን የሚሆነው መልእክቱ የተወከለባቸው ምልክቶች መረጃን ተሸክመው ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ ማድረስ ሲችሉና መልእክት ተቀባይ የሆኑት የተግባቦት ተሳታፊዎች መልእክቱን ተቀብለው መተርጎም፣ መረዳትና ከመልእክት አስተላላፊዎቹ ጋር የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ ሲችሉ ነው፡፡ መረጃን ተቀብለው መተርጎማቸው፣ መረዳታቸውና ግንዛቤን መጨበጥ መቻላቸው ስፍር ቁጥር የሌላቸው አዳዲስ መልእክቶች ከአእምሯቸው ከመቅጽበት እያፈለቁ መረጃ ሆነው እንዲሰራጩ፣ የተሰራጩት መረጃዎች መልእክት ተቀባዮች ዘንድ ደርሰው መተርጎምና ግንዛቤ ሆነው መጨበጥ እንዲችሉ፣ የተግባቦቱ ተሳታፊዎች የጋራ ግንዛቤን በመጨበጥ እውቀታቸውን እንዲገነቡና የተግባቦቱ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

2.7.4. ውጽኣት

ውጽኣት አራተኛው ፈርጅ ሲሆን የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያስገኘውን ውጤት ይገልጻል፡፡ በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማእቀፉ ላይ ከትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ በስተግራ ያለውና በብርቱካናማ ቀለም የተቀባው ክፍል ነው (ስእል 2ን ይመልከቱ)፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ የሚያስመዘግቡት ውጤት፤ የሚያጎለብቱት የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ፤ በትምህርቱ ሂደት በስተመጨረሻ የሚያዳብሩት የቋንቋ ክሂል፤ ተምረው የሚያገኙት አውቀትና የሚጨብጡት ግንዛቤ እንዲሁም የሚኖራቸው ክህሎታዊ ውጤት ነው፡፡ በውስጡ ሌሎች ጉዳዮች ተብለው የተገለጹት በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው መስተጋብር መምህራኑ የሚያገኟቸው ግንዛቤዎች ናቸው፡፡ ይህ ፈርጅ በማሕቀፉ ውስጥ በተዳሰሱት ሌሎች ሶስት ፈርጆች ውስጥ ያሉ ተላውጦዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ይገለጥበታል፡፡

በተግባ-ግብይታዊ ማሕቀፉ እንደተመለከተው በዚህ ጥናት የሚዳሰሱት ጉዳዮች የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ሲሆኑ በክፍል ውስጥ በሚከናወነው ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት የሚገለጡ ናቸው፡፡

2.8. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ተኮር ዳራ

አማርኛ ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚነገርና ለበርካታ ክፍለ ዘመናት የሀገሪቷ የስራ ቋንቋ ሆኖ ያገለገለ ቋንቋ ነው፡፡ በስፋት በመነገር ረገድ ከሴም ቋንቋዎች መካከል ከአረብኛ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ፤ ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ቋንቋዎች ደግሞ በአራተኛ ደረጃ ይቀመጣል (Brown, 2009)፡፡ ህገ መንግስታዊ እውቅና ያገኘ ዋንኛ የፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የስራ ቋንቋ ነው (የኢፌዲሪ ፌደራል

ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1987፣ ቁጥር 2፤ Brown, 2009)። በዘመናዊ ትምህርትነት መሰጠት የጀመረው ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ከተጀመረበት ከ1905 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) ጀምሮ ነው። በአሁኑ ሰአት የአሰጣጡ ሁኔታ ቢለያይም፤ በሀገሪቷ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ በትምህርት አይነትነት ይሰጣል። ቋንቋው አፍ መፍቻ በሆነባቸው አካባቢዎች ከአንደኛ ክፍል፤ ባልሆነባቸው አካባቢዎች ደግሞ ከሶስተኛ ወይም ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል በአንድ የትምህርት አይነትነት ይሰጣል። በከፍተኛ ትምህርት አስከ ሶስተኛ ዲግሪ ድረስ በዋንኛ የጥናት መስክነት ይሰጣል። እንዲሁም አፍ ፈት ተናጋሪዎች ባሉበት አካባቢ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት መስጫ ሆኖ ያለግላል። የአብዛኞቹ የከተማ ነዋሪ ኢትዮጵውያንም ዋንኛ የመግባቢያ ቋንቋ ነው። አማርኛ ቋንቋ በ1974ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) እስከተከሰተው የአብዮት ፍንዳታ ድረስ በኢትዮጵያ የትምህርት ስርአት ውስጥ የተካተተና ለመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት በጥቅም ላይ የዋለ ብቸኛ የኢትዮጵያ ቋንቋ ነበር። የራሱ ፊደሎች ያሉት የጽሁፍ ቋንቋ ሲሆን እስካሁን ድረስ ያሉት ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በቋንቋው በጽሁፍ የሰፈሩ መዛግብት ተመዝግበው የተገኙት በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው (የኢፌዲሪ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1987፣ ቁጥር 2፤ ኢፌድሪ የትምህርት ፖሊሲ 1987፤ Ethiopian National Agency for UNESCO, 2001፤ Browne, 2002፤ Ministry of Education, 2008፤ Brown, 2009)።

2.9. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች ለመዳሰስ በተደረገው ሙከራ ሙሉ በሙሉ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጥናት ማግኘት አልተቻለም። ነገር ግን በተወሰነ ደረጃ ተቀራራቢነት ያላቸውን እንዲሁም ከዚህ ጥናትና ከአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጋር ትስስር ያላቸው በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የተደረጉ ጥናቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል። እነዚህም እንደሚከተለው በአጭሩ ተዳስሰው ቀርበዋል።

በሀገር ውስጥ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል የመጀመሪያው Mendida (2001) ነው። ጥናቱ “Teacher Behaviour in ESL Large Classes in Bahirdar Senior Secondary Schools.” በሚል ርእስ ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ነው። ዋና ዓላማው በተጨናነቁ ክፍሎች ውስጥ መምህራን እንግሊዝኛ ሲያስተምሩ በአተገባበራቸውና በግንዛቤያቸው ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን ጉዳዮች መመርመር ነበር። ውጤቱም የትምህርቱን አቀራረብ ተማሪ ተኮር እንዳይሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ዋንኛው የተጨናነቀ የመማሪያ ክፍል (Large Class) ነው የሚለው የአብዛኞቹ መምህራን እምነት መሆኑን አመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በተጨናነቀ የመማሪያ ክፍል አልፈው የመጡ በመሆናቸው የትምህርቱ አሰጣጥ ውስንነት የሚታይበት መሆኑንና

የመልእክት የጋራ ተረዳድቶ (meaning negotiation) የሚያንሰው ከመሆኑም በላይ ተማሪዎቹ መምህራኑን ወደ ትምህርት ፍላጎታቸው እንዲያመሩ ማድረግ አለመቻላቸውን አመልክቷል፡፡

ሁለተኛው Yoseph (2008) “The Classroom Language of Primary School Teachers in Ethiopia: a Study in Communication Strategies.” በሚል ርእስ ለፍልስፍና ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማ በኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንግሊዝኛን የሚያስተምሩ መምህራን ሲያስተምሩ የሚያጋጥማቸውን የቋንቋ እጠት ለማካካስ የሚጠቀሙባቸውን የተግባቦት ስልቶች መመርመር ነበር፡፡ ውጤቱም መምህራኑ የቋንቋ እጠታቸውን ለማካካስ በሁለት ዋና ዋና ፈርጆች የተፈረጁ ሁለት አበይት የተግባቦት ስልቶችን ማለትም የስኬት ስልቶች (achievement strategies)ና የቅነሳ ስልቶች (Reduction Strategies) እንደሚጠቀሙ አመልክቷል፡፡

ሌሎቹ በውጪ ሀገር የተደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ የመጀመሪያው Loy (2006) ነው፡፡ ይህ ጥናት "Effective Teacher Communication Skills & Teacher Quality" በሚል ርእስ ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በተማሪዎቹ ውጤት መካከል ያለውን ትስስር መመርመር ነበር፡፡ ውጤቱም በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና ተማሪዎቹ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል አወንታዊ ትስስር መኖሩን አመልክቷል፡፡ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ መሆን እንዲችሉ በክፍል ውስጥ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል የክፍል ውስጥ መስተጋብር መከናወን አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ መምህራኑ ጥሩ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ችሎታ ሊኖራቸው እንደሚገባ አመልክቷል፡፡

Osakwe (2009) ሌላው በውጪ ሀገር የተደረገ ጥናት ሲሆን የተግባቦት የተለያዩ ገጽታዎች ለውጤታማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ተንባይ መሆኑን የተመለከተ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት የተግባቦት የተለያዩ ገጽታዎች ብሎ የተመለከታቸው የመምህራኑ አመለካከትና የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ናቸው፡፡ ውጤቱም የመምህራኑ አመለካከት፣ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር ጉልህ የሆነ ትስስር እንዳላቸውና የተግባቦት የተለያዩ ገጽታዎች ለክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ውጤታማነት ተንባይ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡

Duta et al. (2015). “The Effective Communication in Teaching፡ Diagnostic Study Regarding the Academic Learning Motivation to Students” በሚል ርእስ የተጠና ጥናት ነው፡፡ አላማው መምህራን የተግባቦት ክህሎትና ተነሳሽነት በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ላይ በሚኖራቸው ተጽእኖ ያላቸውን አስተያየት መመርመር ነበር፡፡ በውጤቱም ሁሉም መምህራን የተግባቦት ክህሎትና ተነሳሽነት በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ በሚኖራቸው ተጽእኖ ረገድ ተመሳሳይ

አስተያየት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል። ጥሩ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ችሎታ ያላቸው መምህራን ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግብ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲከናወን ማድረግ፤ በሌሎች ላይ ተጽእኖ ማሳደርና ወደ ውጤት ለማምራት የሚያስችሉ ተግባራት እንዲከናወኑ ማድረግ እንደሚችሉም ታውቋል። በጥቅሉ ጥናቱ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የስራ ተነሳሽነት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸው መሆኑን አመልክቷል።

Muste (2016) ም እንደዚሁ "The Role of Communication Skills in Teaching Process" በሚል ርእስ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ መርምሯል። ውጤቱም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች የሚቀስሙት ልምድና እውቀት በክፍል ውስጥ በሚከናወነው መስተጋብር ጥራት ላይ የተመሰረተ መሆኑን አመልክቷል። የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ጥራት ያለው የሚሆነው ደግሞ መምህራኑ የመረጃ ፍሰትን የሚያሳልጡበት የተግባቦት ክህሎት በጥሩ ሁኔታ በጥቅም ላይ ሲውል መሆኑንም አሳይቷል።

Bambaeeroo & Shokrpour (2017) "The Impact of the Teachers' Non-verbal Communication on Success in Teaching" በሚል ርእስ የተጠና ጥናት ሲሆን የመምህራኑ ኢቃላዊ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ መመርመር አላማው ያደረገ ጥናት ነው። ውጤቱም የመምህራኑ ኢቃላዊ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ አወንታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር አመልክቷል። በተግባቦት ሂደት የኢቃላዊ የመግባቢያ ምልክቶች አስተማማኝነት ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በኢቃላዊና በቃላዊ ምልክቶች በሚተላለፉት መልእክቶች መካከል የተምታታ ጉዳይ ካለ የመልእክት አስተላላፊውን ትክክለኛ ስሜት ስለሚገልጹ በኢቃላዊ ምልክቶች የሚያስተላልፉት ተመራጭነት ያላቸው መሆኑንም አመልክቷል።

በዚህ ጥናት የተዳሰሰው የመጨረሻው ጥናት Sutiyatno (2018) ነው። ይህ ጥናት "The Effect of Teacher's Verbal Communication and Non-verbal Communication on Students' English Achievement" በሚል ርእስ የተጠና ነው። ዓላማው የመምህራኑ ቃላዊና ኢቃላዊ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደትና በተማሪዎቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ መመርመር ነበር። ውጤቱም የመምህራኑ ቃላዊም ሆነ ኢቃላዊ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ተማሪዎቹ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ አወንታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር አመልክቷል። የመምህራኑ ቃላዊና ኢቃላዊ የተግባቦት ችሎታ በጥሩ ሁኔታ በጥቅም ላይ መዋሉ የመማር ማስተማር ሂደቱን በጥሩ ሁኔታ ለማከናወን ያስችላል። በመሆኑም

መምህራን በትምህርት መሳሪያዎች አማካኝነት የቀረበውን ትምህርታዊ መረጃ ወደ ተማሪዎች ማድረስ ይችሉ ዘንድ የዳበረ የተግባቦት ችሎታ ሊኖራቸው እንደሚገባ አስገንዝቧል፡፡

እነዚህ ጥናቶች ከዚህ "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለ ተዛምዶ" በሚል ርእስ በየካ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ ከተጠናው ጥናት ጋር የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው የክፍል ውስጥ መስተጋብር የሚኖረውን ሚና የመረመሩ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ፡፡ በጥናቱ ቦታ፣ በተጠኚዎቹ ማንነት፣ ጥናቱ በሚካሄድበት የትምህርት ዓይነትና በአጠናን ዘዴው ደግሞ ይለያያሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከላይ የተዳሰሱት ጥናቶች ከትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ውስጥ የተወሰኑትን ጉዳዮች በተናጠል እያነሱ የተመለከቱ ናቸው፡፡

ምእራፍ ሶስት

የአጠናን ዘዴ

3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርምር ነው። በመሆኑም በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የሚከናወነውን የመማር ማስተማር ሂደት በመመርመር በመምህራኑ የተግባቦት ክሂሎች አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ መርምሯል። ለዚህም ተዛምዷዊ ጥናት በጥቅም ላይ ይውላል (ያለው፣ 1994; Lodico, Spaulding & Voegtle, 2006; Perry, 2008)። በመሆኑም ለዚህ ጥናት ምቹ ሆኖ ተገኝቷል።

3.2. የጥናቱ የምርምር ስልት

ይህ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን የተጠቀመ ጥናት በመምህራኑ የተግባቦት ክሂሎች አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር ጥምር የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል። Jupp (2006)ና Tavakoli (2012) እንደገለጹት ጥምር የምርምር ዘዴ አንድ ምርምር ያነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ሁለቱንም የመጠናዊና የአይነታዊ ምርምር አካሄዶችን አጣምሮ የሚጠቀም የምርምር ስልት ነው።ይህ ምርምር ያነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በዋናነት በጥቅም ላይ የዋለው መጠናዊ የምርምር ስልት ነው። በዋናነት መጠናዊ የምርምር ስልት በጥቅም ላይ እንዲውል ያደረገው ጥናቱ ይዞት ለተነሳው መላ ምት ምላሽ ማግኘት የሚቻለው በስታቲስቲካዊ ቀመር መሆኑ ነው።

የተለያዩ የጥምር ምርምር ዘዴ አይነቶች ያሉ ሲሆን ከመካከላቸው ለዚህ ጥናት የተመረጠው ቅደም ተከተላዊ ጥምር የምርምር ዘዴ (Sequential mixed-methods) ነው። እንደ Jupp (2006)ና Ary, Jacobs & Sorensen (2010) አገላለጽ ይህ የምርምር ንድፍ መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎችን በቅደም ተከተል የሚሰበሰቡበትና የሚተነተኑበት ነው። በመሆኑም ጥናቱ ያነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ይቻል ዘንድ በመጀመሪያ መጠናዊ መረጃዎች ከዚያ ደግሞ አይነታዊ መረጃዎች በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል። ድምዳሜ ላይ የተደረሰውም በመጠናዊ መረጃዎች ትንተና የተደረሰበትን ውጤት በአይነታዊ መረጃዎች ትንተና በተገኘው ውጤት በማጠናከር ነው።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ የመረመረ ነው። ምርምሩ አስተማማኝ ውጤት ማስገኘት ይችል ዘንድ የድኅረ አወንታውያንን የምርምር ቀመረ እሳቤ (Post Positivist Paradigm) ተከትሏል። የተከተለበት ምክንያት ቀመረ እሳቤው ጥናቱ ያነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል አካሄድን ለመከተል የሚያስችል በመሆኑ ነው። Corbetta (2003)፣ Tavakoli (2012)ና Kasimu (2019) እንደገለጹት በዚህ የምርምር ማሕቀፍነት እውነታን መርምሮ ለማግኘት የአጠናን ዘይዉ በሂሳባዊ ቀመር የሚከናወን ወይም አይነታዊ ሊሆን ይችላል። ይህም በምርምር ማሕቀፉ በሂሳባዊ ስሌት ላይ በተመሰረቱ መረጃዎች አማካኝነት የተላውጦዎችን የክስተት ሁኔታ መመርመርና አይነታዊ መረጃዎችን መተንተን ተቀባይነት ያላቸው ክንውኖች መሆናቸውን ያመለክታል።

የዚህ ምርምር መነጽር መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ነው። መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ የዚህ ምርምር ማሕቀፍ የሆነው በሁለት ምክንያት ነው። የመጀመሪያው በአሁኑ ሰአት በሀገሪቷ የሚሰጠው ትምህርት ይህንን አሰራር የተከተለ መሆኑ ነው (Ethiopian National Agency for UNESCO, 2001; Ministry of Education, 2008)። ሁለተኛው ደግሞ ጥናቱ ያነሳው መሰረታዊ ጥያቄ ይህንን አካሄድ የሚፈልግ ሆኖ በመገኘቱ ነው (2.5ን ይመልከቱ)።

እስካሁን ድረስ ከተሰነዘሩት ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳቦች መካከልም ይህ ጥናት የተራክቢውያንን ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብን ተገን አድርጓል። ንድፈ ሀሳቡ ለተገንነት የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ ያነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል አካሄድን ለመከተል የሚያስችል በመሆኑ ነው። እንደ Stern (1991)፣ Jordan (2004)፣ Adamson (2005)፣ Brown (2007)ና Tavakoli (2012) አባባል የተራክቢውያን ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ በቋንቋ ለመዳ ሂደት የሚከናወነውን የእውቀት ግንባታ ከሚከናወነው አእምሯዊ ሂደት አንጻር የሚተነትን ነው። የቋንቋ ትምህርት ከቋንቋ ከሚሰጠው ጠቀሜታ፣ ፍቺና ቅርጽ አንጻር ሊታይ እንደሚገባ ይገልጻል። በዚህ ንድፈ ሀሳብ አተያይ ለቋንቋ እድገት ማህበራዊ መስተጋብር ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪዎቹ እድሜያቸውንና ችሎታቸውን ላገናዘበ የቋንቋ ትምህርት ይዘት መጋለጣቸው ወሳኝነት እንዳለው ያስገነዝባሉ። በቋንቋ ለመዳ ሂደት ለለመዳው መፋጠን ዋንኛና ወሳኝ የሆኑት ጉዳዮች ለማጀቹ የሚያገኙት ስነልሳናዊ ግብዓት ተስተዋይ መሆኑና በተማሪዎቹ መካከል የሚኖር መስተጋብር ናቸው።

በነዚህ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች ተገንዝቦ ምርምሩን ለማከናወን ይህ ጥናት ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍን ተጠቅሟል (2.7ን ይመልከቱ)። ይህ ማሕቀፍ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት በክፍል ውስጥ በሚከናወን ትምህርታዊ መስተጋብር የሚኖረውን የመረጃ ፍሰትና በዚህ የመረጃ ፍሰት ላይ የመምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚኖረውን ቦታ ያሳያል። አጠቃላይ የመማር ማስተማርን ገጽታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን ማሕቀፉ የተገነባበት መሰረተ ሀሳብ ጥናቱ ከሚከተለው የምርምር ቀመረ እሳቤ፣ የመማር ንድፈ ሀሳብና ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳብ ጋር አብሮ ይራመዳል።

3.3. የንሞና ዘዴዎች

የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው። Dawson (2007) እንደገለጹት የተለያዩ የንሞና ዘዴዎችን አቀላቅሎ መጠቀም በተለያዩ የንሞና ዘዴዎች (Sampling Techniques) ላይ ያለውን ደካማ ጎን ለመቋቋም ያስችላል። በመሆኑም ይህ የምርምር ርእሰ ጉዳይ ያነሳውን መሰረታዊ የምርምር ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ማግኘት ይቻል ዘንድ ተጠኝዎቹን ለመምረጥ እኩል እድል ሰጭና ወሳኝ ንሞና በጥቅም ላይ ውለዋል።

Wrench et al. (2009) እንደገለጹት በመማር ማስተማር ሂደት በመምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ጥናት ቋንቋው በአፍ መፍቻነት ወይም በሁለተኛ ቋንቋነት ከመሰጠቱ ጋር ትስስር የለውም። በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ክልላዊ መንግስታትና መስተዳድሮች ለጥናቱ በቂ መረጃ ሊገኝባቸው ስለሚችል አማርኛን እንደ አፍ መፍቻም ሆነ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ ክልሎች በተጠኝነት ሊወሰዱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ለጥናቱ አቅራቢ ካለው ምቹነት አኳያ በምቾት ንሞና በአዲስ አበባ መስተዳድር የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10፣11ና 12 የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በተጠኝነት ተወስደዋል። ስለዚህም በነዚህ ወረዳዎች ውስጥ 1ኛ-10ኛ ክፍል ያሉ ትምህርት ቤቶች የጥናቱ አካላይ ሆነዋል። የጥናቱ አካላይ በሆኑ ወረዳዎች የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች አሉ። ከነዚህ መካከል ያለው (2006)ን መሰረት በማድረግ ከእጣ ንሞና የእጣ ማውጣት ዘዴን በመጠቀም የመንግስት ትምህርት ቤቶች በተጠኝነት ተወስደዋል። በወረዳዎቹ ከ1-12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን ትምህርቱ በብሄራዊ ፈተናቸው ላይ የማይካተት በመሆኑ ትኩረት አይሰጡትም የሚል ስጋት በማሳደሩ 8ኛ፣ 10ኛ፣ 11ኛና 12ኛ ክፍሎች ከጥናቱ አካላይ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ከCity Government Addis Ababa Education Bureau (2014/15) በተገኘው መረጃ መሰረት ለዚህ ጥናት መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት በወረዳዎቹ አምስት የመጀመሪያ ደረጃና ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ። ከነዚህ መካከል ሁለት አንደኛ ደረጃና አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእጣ ንሞና ተመርጠው በተጠኝነት የተወሰዱ ሲሆን በዚህ ጥናት ውስጥ 01፣ 02ና 03 የሚል ወካይ ተሰጥቷቸዋል (አባሪ 4ን ይመልከቱ)። በአንደኛ ትምህርት ቤት ካሉ ሳይክሎች መካከል የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል የሚማሩ ተማሪዎች ህጻናት በመሆናቸው መምህራኑ ከተማሪዎቹ ጋር የሚግባቡበት መንገድ በጥናቱ ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድር በመስጋት ከጥናቱ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጓል። ስለዚህም 5ኛ፣ 6ኛኛ፣ 7ኛና 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የጥናቱ አካላይ ሆነዋል። በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች በሚገኙ 5ኛ፣ 6ኛኛ፣ 7ኛና 9ኛ ክፍሎች አማርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩ 12 መምህራን መካከል ሲያስተምሩ በቪዲዮ ካሜራ ለመቀረጽ ፈቃደኛ የሆኑ ስድስት መምህራን በተጠኝነት ተወስደዋል። እነዚህ መምህራን ሁለቱ 5ኛ ክፍል፣ አንደኛው 6ኛ ክፍል፣ አንደኛው 7ኛ ክፍልና ሁለቱ 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ ናቸው። የነዚህ መምህራን ዳራ በሰንጠረዥ 1 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 1፦ የተጠኝዎችን ዳራ የሚያሳይ መረጃ

ትምህርት ቤት	ተጠኝ መምህር	መምህራኑን የተመለከቱ መረጃዎች			
		የትምህርት ደረጃ	የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ		የአገልግሎት ዘመን
			ዋና	ንኡስ	
01	011	ዲፕሎማ	አማርኛ ቋንቋ	እንግሊዝኛ	12
01	012	ዲፕሎማ	ቋንቋ	-------	10
02	021	ዲፕሎማ	አማርኛ ቋንቋ	-------	2
02	022	ዲፕሎማ	አማርኛ ቋንቋ	እንግሊዝኛ	4
03	031	ዲግሪ	አማርኛ		8
03	032	ዲግሪ	አማርኛ		10

በሰንጠረዥ 1 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው መረጃው የተሰበሰበው በሶስት ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ ስድስት መምህራን ነው። የትምህርት ደረጃቸው የአራቱ ዲፕሎማ ሲሆን የሁለቱ ዲግሪ በአማርኛ ቋንቋ ነው። በዋናነት የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ የአምስቱ አማርኛ ቋንቋ ሲሆን የአንደኛው ቋንቋ ነው። በዋና የጥናት መስክነት ቋንቋን ያጠኑት ተጠኝ ሶስት የትምህርት መስኮችን ማለትም አማርኛ ቋንቋ፤ ስነዜጋና ስነምግባር እንዲሁም እንግሊዝኛ ቋንቋ ዋና የጥናት መስኮቻቸው ናቸው። ንኡስ የጥናት መስክ ያላቸው ሁለቱ ብቻ ሲሆኑ የጥናት መስኩ እንግሊዝኛ ነው።

ሁሉም መምህራን የጥናቱ ዓላማና በጥናቱ የሚደረስበት ውጤት በአማርኛ ትምህርት ሂደት ላይ ሊያስገኝ የሚችለው ለውጥ ከተብራራላቸው በኋላ ባላቸው ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ በተጠኝንነት

የተወሰዱ ናቸው። ተጠኝዎቹ የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆኑ የሚገኘውን መረጃ የተለያዩ ገጽታዎች (different perspectives) ማግኘት ያስችላል። እንዲሁም Hargie (2006)፣ Hargie & Dickson (2005)ና Akpınar (2009) እንደገለጹት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በትምህርት ሊገኝ፤ በተግባራዊ ልምምድ፣ በግብረመልስና በጽብረቃ ሊዳብር የሚችል ሙያዊ ችሎታ በመሆኑ የመምህራኑ አመራረጥ እድሜንና ጾታን መሰረት አላደረገም።

3.4. የሚጠኑ ተላውጦዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው። Jupp (2006)ና Ari et al. (2010) የገለጹትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ይህ በተላውጦዎች መካከል ያለ ተዛምዶን የመረመረ ጥናት ሁለት አይነት ተላውጦዎችን ዳስሷል። እነዚህም ነጻ ተላውጦና ጥገኛ ተላውጦ ናቸው። ነጻ ተላውጦው የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲሆን ጥገኛ ተላውጦ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ነው። ይህንን መሰረት አድርጎ ጥናቱ ሶስት ዝርዝር ጉዳዮችን መርምሯል። እነዚህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም፣ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩና በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለ ተዛምዶ ናቸው።

3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህ ጥናት ላነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በጥቅም ላይ ውለዋል።

3.5.1. የአጭር ጊዜ ቀጥተኛ ምልከታ

የአጭር ጊዜ ቀጥተኛ ምልከታ የሚባለው ለተወሰኑ ጊዜያት መረጃ በሚሰበሰብበት ቦታ ተገኝቶ ትክክለኛ ክስተቱን በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት ሲሆን ለትንተና እንዲያመች በበጽሁፍ ሊተረጎም ወይም ወደ መጠናዊ መረጃነት ሊለወጥ ይችላል (Camic, Rhodes & Yardley, 2003; Muijs, 2004; Hargie & Dickson, 2005; Ary et al., 2010; Tavakoli, 2012):: ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሏል። ምልከታው የተካሄደው በተጠኝነት የተመረጡት መምህራን በሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ተገኝቶ የመማር ማስተማሩ ሂደትን በመመልከትና በቪዲዮ ካሜራ በመቅረጽ ሲሆን በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጸው መረጃ በጽሁፍ ሳይተረጎም በደረጃዊ ልኬት ወደ መጠናዊ መረጃነት እንዲለወጥ ተደርጓል። ማለትም በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጸውን የመማር

ማስተማር ሂደት የሚያሳይ ምስል በደረጃዊ ልኬት (rating scale) የተዘጋጁ የምልከታ ቅጾችን በመጠቀም ለሶስት ቀናት ስልጠና የተሰጣቸው ተመልካቾች በደረጃ ልኬት እንዲገልጹት ተደርጓል።

የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገለው የምልከታ ቅጽ በይነሰባዊ የተግባቦት ችሎታ አጣርቶ መሰነጃ ሞዴልን (Interpersonal Communication Competence Inventory/ ICCI Model) መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ነው። እንደ Greene & Burleson (2003) አባባል በይነሰባዊ የተግባቦት ችሎታ አጣርቶ መሰነጃ የተግባቦት ሂደትን ውጤታማነትና ግብ ተኮርነት መሰረት አድርጎ የተቀናበረ ሞዴል ነው። የትኩረት ነጥቦቹ የመልእክት አወካከል፣ አተረጓጎምና አቀነባበር ናቸው። ስለዚህም ለተግባቦት ሂደት ገላጭነት፣ ግብ ተኮርነትና ወላንሳነት እንደሁም ለግንዛቤ ማህበራዊነት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል። ቀደም ሲል የተግባቦት ክህሎትን ለመለካት ሲያገለግሉ በነበሩ ሞዴሎች መነሻነት የተዘጋጀ ሲሆን ተግባቦትን በሚያጠኑ ምሁራን ዘንድ በበይነ ሰባዊ የተግባቦት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራትን በብቃት ለመለካት እንደሚያስችል ይታመናል። ይህንን ሞዴል መነሻ በማድረግ Lange, Gallucci & Karremans (2007)፣ Wrench et al. (2009)፣ Gomez-Estifan (2004)፣ Hargie & Dickson (2005)ና ክለሳ ድርሳናቱ ላይ የቀረቡት ሀሳቦች በምልከታ ቅጹ ላይ የቀረቡትን ተግባራት ለመቅረጽ አገልግለዋል።

የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገለው የምልከታ ቅጽ ግንባታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ (constructivist teaching Learning Framework) መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው። Beyhan & Köksal (2013)፣ Bhattacharjee (2015)ና Sharma & Bansal (2017) እንደገለጹት ግንባታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ንቁ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ቀደም ሲል በነበራቸው ላይ እውቀትን እንዲገነቡ፣ ባከናወኑት ትምህርታዊ ተግባር ላይ እንዲጸበርቁና ምን እየሰሩ እንደሆነና ግንዛቤያቸው እንዴት ሊቀየር እንደቻለ እንዲናገሩ ለማድረግ የሚያስችል የአስተሳሰብ ቀመር ነው። ሰዎች በሚያከናውኑት ተግባር አማካኝነት እውቀትን ይገነባሉ በሚል መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተማሪ መራሽ የመማር ማስተማር ሂደትና የፍቺ ምስረታ የግንባታዊ መማር ማስተማር መሰረተ ሀሳብ አስኳል ነው (Beyhan & Köksal, 2013; Sharma & Bansal, 2017)። Beyhan & Köksal (2013)ና Roustaee, Kadir & Asimiran (2014) እንዳሉትም መምህራን የመማር ማስተማሩ ሂደት መዘውር ናቸው። ዋንኛ ተግባራቸው የመማር ማስተማሩን ሂደት ማመቻቸትና አመራር መስጠት ነው። በግንባታዊ መሰረተ ሀሳብ በተመሰረተ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የመማር ባለሙያዎች መሆናቸውን (Sharma & Bansal, 2017) ያስገነዝባሉ። ስለዚህም በትምህርትነት የቀረበውን ጽንሰ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን እንዴት መማር እንዳለባቸውም ጭምር ይማራሉ። በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ፤ የትምህርቱ ድባብ ዲሞክራሲያዊ እንዲሁም ትምህርታዊ ተግባራቱ አሳታፊና ተማሪ መራሽ ናቸው።

መምህራኑ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያመቻቹ ሲሆን ተማሪዎቹ ራሳቸውን እንዲችሉና ኃላፊነት እንዲወስዱ ይበረታታሉ፡፡ ይህንን ንድፈ ሀሳብ መነሻ በማድረግ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ እንዲያስችል የተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ በLange et al. (2007) መሰረት በክፍል አደረጃጀት፣ በተማሪዎች ተሳትፎ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማሪዎቹ በሚደረጉ ድጋፎችና በማስተማር ዘዴዎች አጠቃቀም ላይ እንዲያጠነጥን ተደርጓል፡፡

ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በምልከታ የተገኙትን መረጃዎች ወደ መጠናዊ መረጃነት ለውጦ ለመመዝገብ ያገለገለው ደረጃዊ ልኬት (rating scale) ነው፡፡ Greene & Burleson (2003)፣ Ary et al. (2010)ና Tavakoli (2012) እንደገለጹት ደረጃዊ ልኬት ተመልካቾች ለተመለከቷቸው ባህርያት ያላቸውን ሚዛናዊ ግምገማ የሚገልጹበት መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም በተግባቦት ክህሎትና በክፍል ውስጥ መስተጋብር ላይ ለሚደረጉ ጥናቶች ምቹ የሆነ መረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህ ጥናት መረጃ ለማማባሰብ ያገለገሉት የምልከታ ቅጾች አምስት ደረጃዎች ያሏቸው ሲሆን የነጥብ አሰጣጡ በጣም ጥሩ በሆነ ሁኔታ ተከናውኗል 5፣ በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል 4፣ በመካከለኛ ሁኔታ ተከናውኗል 3፣ በደካማ ሁኔታ ተከናውኗል 2ና በጣም ደካማ በሆነ ሁኔታ ተከናውኗል (አልተከናወነም) 1 ነው (አባሪ 2ና 3ን ይመልከቱ)፡፡

3.5.2. የሰነድ ምርመራ

በሰነድነት ተወስደው የተመረመሩት መምህራኑ ያዘጋጇቸው እለታዊ የትምህርት እቅዶች ሲሆኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ መስተጋብር ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥቅም ላይ ለማዋል ያቀዷቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎችና የተግባቦት ክህሎት አስመልክቶ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አገልግሏል (አባሪ 8ን ይመልከቱ)፡፡ በሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎች በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ለማጠናከር አገልግለዋል፡፡

3.5.3. የተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ

የተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ (Researcher's Diary) አንድ ተመራማሪ የተለያዩ የምርምር ተግባራትን በሚያከናውንበት ወቅት ያጋጠሙትን ክስተቶች በወቅቱ መዝግቦ የሚያስቀምጥበት ግላዊ ሰነድ ነው (Corbeta, 2003)፡፡ ተመራማሪው የተሳተፈባቸውን ገጠመኞች ትክክለኛ ገጽታ ለመገንዘብ የሚያስችሉ መረጃዎችን መዝግቦ ለመያዝ ያስችላል፡፡ ለዚህ ምርምር ለመረጃ ማሰባሰቢያነት በጥቅም ላይ የዋለው እለታዊ ማስታወሻ የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲካሄድ በተከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴትነት ላይ የታዩ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክስተቶች ለመመዝገብ አገልግሏል፡፡

የተዘጋጀው Brumfit & Mitchell (1990) ያቀረቡትን የእለታዊ ማስታወሻ አዘገጃጀት መነሻ በማድረግ ሲሆን ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ማሻሻዎች ተደርገውለታል። ቅጹ ከተዘጋጀ በኋላ የሚፈለገውን መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ በባለሙያ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል። ከዚያም አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎበት በጥቅም ላይ ውሏል። በእለታዊ ማስታወሻው አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተቀናብረው ለትንተና ተወስደዋል (አባሪ 5ና 6ን ይመልከቱ)።

3.6. የመረጃ አሰባሰብ

በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ያሰባሰቡት ሶስት ተመልካቾች ሲሆኑ የጥናቱ አቅራቢና ሁለት ስልጠና የተሰጣቸው ተመልካቾች ናቸው። በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተከናወነው ምልከታ የተሳተፈችው የጥናቱ አቅራቢ ብቻ ነች። ሌሎቹ ተመልካቾች እንዳይሳተፉ የተደረገው በአንድ ጊዜ አራት ሰው በክፍል ውስጥ መግባቱ ተፈጥሯዊ የሆነውን የመማር ማስተማር ሂደት እንዳያዛባው በመፍራት ነው። ስልጠና የተሰጣቸው ተመልካቾች በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጸውን ምስል እየተመለከቱ በምልከታ ቅጹ ላይ ሚዛናዊ የሆነ ግምገማቸውን በደረጃ ልኬት እንዲገልጹት ተደርጓል። የጥናቱ አቅራቢ ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደት ከመመልከት በተጨማሪ በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጸውን ምስል ደጋግማ እየተመለከተች ግምገማዋን በደረጃ ልኬት ገልጻዋለች። ከዚያም የግምገማውን ውጤት ሚዛናዊነት ለመጠበቅ የሶስቱም ተመልካቾች የሰጡት ውጤት ለትንተና ተወስዷል (አባሪ 11ና 12ን ይመልከቱ)። በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ተጠኝዎቹ በሚያስተምሩበት የመማሪያ ክፍል ስድስት ስድስት ጊዜ ምልከታ የተደረገ ሲሆን በድምሩ ሰላሳ ስድስት ምልከታዎች ተከናውነዋል። እያንዳንዱ የመማር ማስተማር ሂደት ደግሞ ለተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና ለክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ሶስት ጊዜ ታይቷል። ስለዚህም በድምሩ ለእያንዳንዱ ተላውጦ የሰላሳ ስድስት ምልከታዎች የደረጃዊ ልኬት ነጥብ ለትንተና ተወስዷል።

ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች ሲሰበሰቡ በሰነድነት የተመረመሩት ምልከታው በተካሄደበት ወቅት መምህራኑ የተገለገሉባቸው እለታዊ የትምህርት እቅዶች ናቸው። ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የክፍል ውስጥ ምልከታው ለሰላሳ ስድስት ክፍለ ጊዜያት የተከናወነ በመሆኑ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን ለሁለት ሳምንታት ያዘጋጇው እለታዊ ትምህርት እቅዶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ ለሶስት ሳምንታት ያዘጋጇቸው እለታዊ የትምህርት እቅዶች ተወስደው ተመርምረዋል። ምርመራውን ያካሄደችው የጥናቱ አቅራቢ ስትሆን የተመረመሩት ከመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴትነት ጋር

ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። በምርመራው የተገኘው ውጤት ተመዘግቦ በምልከታ የተገኘውን መረጃ ለማመሳከር አገልግሏል (አባሪ 8ን ይመልከቱ)።

ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች የተሰበሰቡት የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደባቸው ሰላሳ ስድስት ክፍለ ጊዜያት ነው። መረጃውን የሰበሰበችው የጥናቱ አቅራቢ ስትሆን የመማር ማስተማሩ ሂደት ሲከናወን የተመለከተቻቸውን ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በእለታዊ ማስታወሻዋ መዝግባ ይዛቸዋለች። መረጃዎቹን በእለታዊ ማስታወሻ የመመዝገቡ ተግባር የተከናወነው ምልከታው የተካሄደበት የመማር ማስተማር ሂደት እንደተጠናቀቀ ነው። እነዚህ መረጃዎች በአንድ ላይ ተጠናቅረው በምልከታ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር በጥቅም ላይ ውለዋል (አባሪ 6ን ይመልከቱ)።

3.7. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

የመረጃ ትንተና የሚባለው የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም የተሰበሰቡትን መረጃዎች ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ ማደራጀትና መተርጎም ነው (ያለው፣ 1998; Muijs, 2004; Dörnyei, 2007; Dawson, 2007; Gerring, 2007)። ይህንን ለማከናወን ይህ ጥናት የይዘት ትንታኔ (content analysis)ና የሰነድ ትንታኔ (documentary analysis) የመረጃ አተናተን ሂደትን ተጠቅሟል፡ ፡ Ayeni et al. (2019) እንደገለጹት እነዚህ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በድኅረ አወንታውያን የምርምር ቀመረ እሳቤ ማሕቀፍነት በሚከናወኑ ምርምሮች በጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

የይዘት ትንተና በንግግር ወይም በጽሁፍ የቀረበን መረጃ ወደ መጠናዊ መረጃነት ለመለወጥ የሚያገለግል አካሄድ ነው (Tavakoli, 2012; Ary, et al., 2010)። እንደ Tavakoli (2012) አገላለጽ የይዘት ትንተና አይነታዊ የምርምር ስልት ሲሆን የንግግር፣ የጽሁፍ ወይም በአይን በሚታይ መንገድ የተገለጹ መረጃዎችን ለመቁጠር ያለግላል። በአይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተሰበሰበን መረጃ በቁጥር ለመግለጽ ያገለግላል። በመሆኑም ተመራማሪው ለተለያዩ ተግባራት ወካዮችን በመስጠት (creating codes), እያንዳንዱ ወካይ የተከናወነበትን ሁኔታ በቁጥር ይገልጽበታል (Ary, et al., 2010)። Jupp (2006) እንዳሉት ወካዮቹ በቁልቁል አካሄድ (Deductively) የተዘጋጁ ሲሆኑ በቁጥር መገለጻቸው በወካዮቹ የተገለጹት ተግባራት የክንውን ሁኔታ ምን ያህል እንደሆነ በመጠን ለማወቅ ያስችላል። የተወከሉት ተግባራት የክንውን ሁኔታ በቁጥር የሚገለጽ እንደመሆኑ መጠን መረጃዎቹ በመጠናዊ መረጃ መተንተኛ ዘዴ ይተነተናሉ። ይህም ተላውጦቹን የሚገልጹት መረጃዎች አስተማማኝነት በስታስቲካዊ ስሌት እንዲሰላ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን መረጃዎቹ ከመረጃ ማሳያ መንገዶች መካከል በሰንጠረዥ በየፊርጁ ተደራጅተው ይቀርባሉ (Jupp, 2006; Tavakoli, 2012)። በዚህ ጥናት የይዘት ትንተናን በመጠቀም የተተነተኑት በምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች ናቸው።

Jupp (2006)፣ Ary, et al. (2010)ና Tavakoli (2012) እንደገለጹት የሰነድ ትንታኔ የተጻፉ ወይም ጽሁፋዊ መሰረት ያላቸው ቁሳቁሶች፤ ያልተጻፉ፣ ተቀርጸው የተቀመጡ ቅርጻቅርጾች የሚተነተኑበት መንገድ ነው። መጣጥፎቹ ቀደም ሲል የተጻፉ ወይም ደግሞ አዲስ የሚዘጋጁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል አዲስ ከሚዘጋጁት መካከል ተጠኝዎቹ ልምዳቸውን፣ ገጠመኛቸውን፣ የቤተሰባቸውን ታሪክ አስመልክቶ በስእል የሚገልጿቸው፤ በማስታወሻ መልክ የሚጽፏቸው እንዲሁም በድምጽ መቅረጫ እየተቀረጹ የሚናገሯቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ጥናት በሰነድነት ተወስደው የተተነተኑት ተጠኝዎቹ የመማር ማስተማር ሂደቱ በአግባቡ መከናወን ይችል ዘንድ ለትግበራ ያዘጋጇው እለታዊ የትምህርት እቅዶችና ተመራማሪዋ በተከናወነው ምልከታ ላይ ተመስርታ ያዘጋጀችው የተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ ናቸው።

ይህ ጥናት በቅደም ተከተላዊ ጥምር የምርምር ስልት የተከናወነ እንደመሆኑ መጠን በመጀመሪያ በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመጠን ተገልጸው ከተተነተኑ በኋላ በአይነት ወደተገለጹ መረጃዎች ትንተና ተሸጋግሯል (ምእራፍ አራትን ይመልከቱ)። ይህ ጥናት ያነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ወደ መጠን ተለውጠው የተመዘገቡት በደረጃዊ ልኬት ነው። ያለው (2006) እንደገለጹት ደረጃዊ ልኬት የተለያዩ ሰዎች ወይም ነገሮች ከአንድ የተመረጠ ተላውጦ አንጻር የሚያሳዩትን ባህሪ በማወዳደር አንደኛው ከሌላው የበለጠ ወይም ያነሰ መሆኑን በደረጃ በሚያሳይ አሀዝ የሚገለጽበት መንገድ ነው። ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ምልከታውን ያከናወኑት ሶስት ተመልካቾች ናቸው። ለትንተና የተወሰደው ደግሞ የሶስቱ ተመልካቾች አማካይ ነው (3.5.1ን ይመልከቱ)። የሶስቱ ተመልካቾች አማካይ ሲሰላ በደረጃዊ ልኬት የተገለጸው መረጃ ወደ እኩል ምጣኔ ልኬትነት ተቀይሯል። ስለዚህም በመረጃ ትንተና ሂደት የሚጠበቅ አማካይ ውጤት (expected mean)፣ በምልከታ የተገኘ አማካይ ውጤት (observed mean)፣ መደበኛ ልይይት (standard deviation)፣ ሩብ ልኬታዎችና (inter quartile range)፣ ዝብጠት (kurtosis)፣ ዝመት (skewness)፣ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (One-Sample t-test)ና የፒርሰን የተዛምዶ ስሌት (Pearson's coorelation)፣ የአማካይ ንጽጽር (comparing means) ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡ በደረጃዊ ልኬት የተገለጹ መረጃዎችን ለመተንተን በጥቅም ላይ ውለዋል።

3.8. የመረጃ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት

Ary et al. (2010) እንደገለጹት ለምርምር ተግባር በቀጥተኛ ምልከታ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛነት (validity)ና አስተማማኝነት (reliability) መጠበቅ መቻል ይኖርበታል። ይህን ጥናት ለማከናወን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር በተያያዘ መረጃዎች ተገቢነትና አስተማማኝነት እንዲኖራቸው የሚከተለው ተግባር ተከናውኗል።

የመረጃ ትክለኛነትን ለመጠበቅ የተከናወነው የመጀመሪያው ተግባር የምልከታ ቅጾቹ ተዘጋጅተው ከተጠናቀቁ በኋላ ባለሙያዎች ገምግመው በተገቢነታቸው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ ነው። የምልከታ ቅጾች የተዘጋጁት የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ ነው። በዚህ መሰረት የምልከታ ቅጾቹ ተዘጋጅተው ከተጠናቀቁ በኋላ ሶስት ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጥባቸውና በአስተያየቱም መሰረት እንዲሻሻሉ ተደርጓል። ከዚያም የምልከታ ቅጾቹ አስተማማኝ መረጃ ማስገኘት የሚችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ባለሙያዎች በደረጃ ልኬት እንዲመዝኗቸው ከተደረገ በኋላ የበይነ ገምጋሚ አስተማማኝነት ስሌት ተሰልቷል። አስተማማኝነቱን ለመለካት ያገለገለው ስታስቲካዊ ቀመር ክሮምባኽ አልፋ ሲሆን ውጤቱ የአስተማማኝነት ትንተና ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 2ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 2፡ የአስተማማኝነት ትንተና ውጤት

		ብዛት (N)		ክሮምባኽ አልፋ (α)
		ተግባራት	ግምገማ/ ምልከታ	
የበይነ ገምጋሚ አስተማማኝነት (interrater reliability	የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም	30	3	0.921
	የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የምልከታ ቅጽ	20	3	0.919
የበይነ ተመልካች አስተማማኝነት (interobseber reliability)	የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከምልከታ የተገኘ መረጃ	30	108	0.924
	የክፍል ውስጥ መተጋብር አተገባበር ከምልከታ የተገኘ መረጃ	20	108	0.877

በሰንጠረዥ 2 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ አስተማማኝ መረጃ ማስገኘት የሚያስችል መሆኑን ለማወቅ የተሰላው ክሮንባኽ አልፋ ውጤት α= 0.921 ሲሆን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ የተዘጋጀው የምልክታ ቅጽ ደግሞ α= 0.919 ነው። Ary et al. (2010) በገለጹት መሰረት ይህ ውጤት የሁለቱም የምልክታ ቅጾች አስተማማኝ መረጃ የማስገኘት አቅም በጣም ከፍተኛ መሆኑን አረጋግጧል። በመሆኑም የምልከታ ቅጾቹ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በጥቅም ላይ ውለዋል።

የምልከታ ቅጾቹ አስተማማኝ መረጃ ማስገኘት የሚችሉ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ በምልከታ የሚገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለመጠበቅ ጥሩው መንገድ በምርምሩ የሚጠናውን ባህሪ በጥንቃቄ መግለጽና ምልከታውን የሚያከናውኑ ሰዎችን ማሰልጠን በመሆኑ በጥናቱ አቅራቢ አማካኝነት ምርምሩ ባነሳቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን የስልጠና መምሪያ ተዘጋጅቶ የሶስት ቀን ተከታታይ ስልጠና እንዲሰጣቸው ተደርጓል (አባሪ 1ን ይመልከቱ)። የስልጠና መምሪያውን ትክክለኛነት ለመጠበቅ

ተዘጋጅቶ ከተጠናቀቀ በኋላ በሶስት ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል። በአስተያየቱ መሰረትም ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎበታል። ከዚህ በተጨማሪ በስልጠናው ሂደት ተመልካቾቹ በመረጃ ትክለኛነት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁለት የወገንተኛነት ምንጮችን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ተደርጓል። እነዚህም የተመልካቾቹ ወገንተኝነት (observer bias)ና የተመልካቾቹ ተጽእኖ (observer effect) ናቸው። የተመልካቾቹ ወገንተኝነት የሚከሰተው የተመልካቾቹ ግንዛቤ፣ እምነትና ወገንተኝነት ምልከታውን በሚያከናውኑበትና ትንታኔ በሚሰጡበት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩበት ሁኔታ ሲኖር ነው። ይህንን ችግር ለመቋቋም የሚያስችለው መንገድ ከአንድ በላይ ተመልካች እንዲኖር ማድረግ፤ እንዲሁም ተመልካቾቹ ምንን እንደሚመለከቱና በምልከታው ያኙትን መረጃ እንዴት እንደሚመዘግቡት በቂ የሆነ እውቀት እንዲኖራቸው ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ ተከናውኗል። የተመልካቾቹ ተጽእኖ የሚከሰተው ደግሞ ተጠኝዎቹ ምልከታ እየተካሄደባቸው በመሆኑ በተለየ መንገድ ተግባራቱን ሲያከናውኑ ነው። ይህንን ችግር ለመቋቋም ምልከታውን ደጋግሞ ማካሄድ ያስፈልጋል። ምልከታው በተደጋጋሚ ሲከናወን በአተገባበር ሂደት ፍብርክ የሆነው ባህሪ ይጠፋና ትክክለኛው ባህሪ የሚታይበት ሁኔታ ይከሰታል። ይህንን ለመቋቋም ደግሞ ለስድስት ከፍለ ጊዜያት ተጠኝዎቹ በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች በመገኘት ምልከታው እንዲከናወንና በቪዲዮ ካሜራ እንዲቀረጽ ተደርጓል።

በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጸው እያንዳንዱ የመማር ማስተማር ሂደት በሶስቱም ተመልካቾች እየታየ በደረጃ ልኬት ከተገለጸ በኋላ ሶስቱ ተመልካቾች ለእያንዳንዱ ተግባር አተገባበር በሰጡት ነጥብ መካከል የእርማት አስተማማኝነት መኖሩን ለማረጋገጥ የበይነ ተመልካች አስተማማኝነት (inter observer reliability) እንዲሰላ ተደርጓል። አስተማማኝነቱን ለማስላት ያገለገለው ክሮንባኽ አልፋ ነው። በዚህ መሰረት የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የበይነ ተመልካች አስተማማኝነት α=0.924፤ የከፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን የሚያሳዩ መረጃዎች የበይነ ተመልካች አስተማማኝነት ደግሞ α=0.877 ሆኖ ተገኝቷል (ሰንጠረዥ 2ን ይመልከቱ)። ይህ ውጤት Ary et al. (2010) በገለጹት መሰረት የሁለቱ መረጃዎች አስተማማኝነት እንደየቅደም ተከተላቸው በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ መሆኑን ለማወቅ አስችሏል። በመሆኑም መረጃዎቹ ለትንተና ተወስደዋል።

3.9. የቅኝት ጥናት ውጤት

የዚህ ምርምር የቅኝት ጥናት የተካሄደው ጥናቱ በናሙናነት ከወሰዳቸው ተጠኚዎች መካከል ሁለቱ የሚያከናውኑትን የመማር ማስተማር ሂደት በመመልከትና ለመምህራኑ ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተገኙ መረጃዎችን በመጠቀም ነበር። ጥናቱ ይዞት የተነሳው ርእስ "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለ ተዛምዶ" የሚል ነበር። በዚህ መሰረት አወንታዊና ባዶ መላምቶችን ሰንዝሮ ነበር። የቅኝት ጥናቱ

ውጤት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴትነት መካከል ተዛምዶ መኖሩን ያመለከተ ስለነበር ባዶ መላምቱ አልፏል። የቅኝት ጥናቱ በሁለቱ መካከል ያለውን ተዛምዶ ከማስላቱ በፊት ሁለቱ ተላውጦዎች ምን ገጽታ እንዳላቸው ተመልክቷል። በዚህም የሁለቱም ተላውጦዎች አተገባበር በደረጃ ልኬት ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ ሊመደብ የሚችል መሆኑ ታውቋል።

የቅኝት ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት ጥናቱ ያነሳው ሁለት አይነት ተላውጦዎችን ነበር። እነዚህም ነጻ ተላውጦ (የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም)ና ጥገኛ ተላውጦ (የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴትነት) ነበሩ። በቅኝት ጥናቱ ውጤት በመማር ማስተማሩ ሂደት በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለው ትስስር ከተዛምዶ ያለፈና የመንስኤና የውጤት ትስስር የሚታይበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ይህ እንዳለ ሆኖ አንዳንድ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የሚያስችል አስተያየት ተሰንዝሯል። ይኸውም የቅኝት ጥናት በተካሄደበት ወቅት በጥቅም ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል አንዱ ቃለ መጠይቅ ነበር። ይሁን እንጂ የምርምር ማበልጸጊያው አንባቢዎች በሰጡት አስተያየት መሰረት ጥናቱ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆንና ለመረጃ አያያዝ እንዲያመች ቃለ መጠይቁ ቀርቶ በተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ መረጃ እንዲሰበሰብ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ የቅኝት ጥናቱ ሲካሄድ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ያጠነጠነው በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ፣ በጥያቄ አጠያየቅ በመረጃ ግብይት ላይ ብቻ ነበር። ይሁን እንጂ የተግባቦት ክህሎት የመምህራኑን ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎች ካልዳሰሰ የተሟላ እንደማይሆን የቅኝት ጥናት ውጤቱ አመልክቷል። በመሆኑም የምልከታ ቅጹ ተሻሽሎ ቀደም ሲል ከተዳሰሱት ጉዳዮች በተጨማሪ የመምህራኑን ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም የሚዳስስ እንዲሆን ተደርጓል። በዚህ መሰረት የተከናወነው ምርምር የመረጃ ትንተና በቀጣዩ ምእራፍ ቀርቧል።

ምእራፍ አራት

የውጤት ትርጎማና ማብራሪያ

4.1. የውጤት ትርጎማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ መኖሩን መመርመር ነው። ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ሁለት መሰረታዊ ተላውጦዎችን የሚያሳዩ መረጃዎች በምልከታ፣ በተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና በሰነድ ምርመራ ተሰብስበዋል። ተላውጦዎቹ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ሲሆኑ የክስተታቸውን ሁኔታ የሚያሳዩት መረጃዎች እንደሚከተለው ተተርጉመው ቀርበዋል።

4.1.1. የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም

4.1.1.1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ

የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በአምስት ዘርፎች ተከፍሎ ታይቷል። በነዚህ ዘርፎች የተካተቱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተርጉመው ቀርበዋል።

፩. ቃላዊ መግባቢያዎች

Brown (2007)ና Berko et al. (2010) እንደገለጹት ቃላዊ መግባቢያዎች በተግባቦት ሂደት መልእክትን በንግግር ወይም በጽሁፍ ለመወከል የሚያገለግሉ ምልክቶች ናቸው። መምህራኑ እነዚህን ምልክቶች እንዴት እንደሚጠቀሙ ለማወቅ የሚያስችሉ ሁለት ተግባራት በምልከታ ቅጹ ላይ ተካትተዋል (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። የነዚህን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 3 ቀርቧል።

በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በቃላዊ መግባቢያዎች ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የሚሰነዝሩት ሀሳብ ግልጽ መሆኑን የተመለከተ (Comskill1 1) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። በሰንጠረዥ 3 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 3.6025 ነው፡

፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=1.50966 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት የተለየ ጉድኝት አላቸው፡፡ ዝመቱ -0.822 ሲሆን አብዛኞቹ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካዩ በላይ የተጎዳኙ መሆኑንና የመረጃዎቹ አሰረጫጨት ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ደረጃ በደረጃ እየቀነሰ የሚሄድ ደልዳላ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዝብጠቱ -0.824 ነው፡፡ ይህም በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ጉድኝት ከአማካዩ የራቀና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ (leptokurtic) ላይ እስከሚደርስ ድረስ ደልደል ብሎ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች ከ2.7525 እስከ 5.00 ባሉት ነጥቦች ላይ ነው፡፡ ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንተና እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው፡፡ ይህ የመረጃ ጉድኝት ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የሚሰነዝሩት ሀሳብ ግልጽነት ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡

ሰንጠረዠ 3፡- የመምህራኑን ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የገለጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
comskill1 1	36	3	3.6025	1.50966	-0.822	-0.824	2.7525	4.165	5
comskill1 2	36	3	3.5925	1.41896	-0.992	-0.295	3	4	5
Total	36	6	7.195	2.83699	-1.068	-0.346	5.7525	8.33	9

በቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚሰነዝሩት ሀሳብ ተማሪዎቹ ያከናወኗቸውን ተግባራት የሚያጣጥል ሳይሆን የሚገልጽ መሆኑን የተመለከተ (Comskill1 2) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ በሰንጠረዥ 3 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳየው መረጃ አማካይ 3.5925 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል፡፡ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=1.41896 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ

የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት የተለየ ጉድኝት አላቸው።

ዝመቱ -0.992 ነው። ይህም አብዛኞቹ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.295 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ወደ አማካያቸው በዝቅተኛ ደረጃ መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ወዳለበት ነጥብ እስኪደርስ ድረስ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑንም ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች ከ3.00 እስከ አምስት ባሉት ነጥቦች ላይ ያረፉ ናቸው። ስለዚህም ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ ይታያል። መረጃው በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚሰነዝሩት ሀሳብ ተማሪዎቹ ያከናወኑትን ተግባር የሚገልጽ እንጂ የሚያጣጥል አለመሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል።

አጠቃላይ የመምህራኑን ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ለማወቅ በዘርፉ የተዳሰሱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች በጥቅል ማየት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 3 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የነዚህ መረጃዎች አማካይ 7.195 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 6.00 ይበልጣል። አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃዎች ጉድኝት መኖሩንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=2.83699 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል። ዝመቱ -1.068 ሲሆን በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካዩ በላይ መጎዳኘታቸውን ለመረዳት ያስችላል። ዝብጠቱ -0.346 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ወደ አማካያቸው በዝቅተኛ ደረጃ መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ወዳለበት ነጥብ እስኪደርስ ድረስ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑንም ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ5.7525፣ 8.33ና 9 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ላይ የሚጎዳኙት መረጃዎች በ4፣ 6ና 8 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። ይህም ሶስቱም በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬት መቁረጫ ነጥቦች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው መብለጣቸውን ያሳያል። ስለዚህም ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ ይታያል። ስለዚህም በመደበኛ አስረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ልዩነቱ በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የመምህራኑን ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት የሚያሳዩ መረጃዎች በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 4ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 4፡ የቃላዊ መግባቢያዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 6						Cohen's d effect
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Differen	95% Confidence Lower	95% Confidence Upper	
observed verbal comskill	2.527	35	.016	1.19500	.2351	2.1549	0.842

በሰንጠረዥ 4 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=2.527, df=35, p<0.05)። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ1.6% ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል (በ 1.195 የአማካይ ልዩነት)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው 2.527 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። የጉልህት ደረጃው sig.=0.016 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=0.842 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት መካከለኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

፪. የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም

Brown (2007)ና Berko et al. (2010) እንደገለጹት አካላዊ ቋንቋ፣ የአይን ግጥምጥሞሽ፣ አካላዊ ቅርርብ፣ አለባበስ፣ መንካት፣ ማሽተትና ድምጸ ቅላጼ ኢቃላዊ የሆኑ መልእክት መወከያ መንገዶች ሲሆኑ በተግባቦት ሂደት የመረጃ ፍሰትን ከሚያሳልጡ ጉዳዮች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። በዚህ መሰረት የመምህራኑን ኢቃላዊ የመግባቢያ ዘዴዎች አጠቃቀም ለማወቅ የሚያስችሉ ስምንት ተግባራት

በምልከታ ቅጹ ላይ ተካትተዋል (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ የነዚህን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 5 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 5፡ የኢ.ቃ.ላ.ዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝሙት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
comskill1 3	36	3	4.1853	.96108	-1.246	1.747	3.4975	4.3350	5.0000
comskill1 4	36	3	3.2503	1.39230	-.436	-.929	2.7525	3.0000	4.3300
comskill1 5	36	3	3.7778	1.43235	-1.261	.084	3.6700	4.3300	4.9175
comskill1 6	36	3	3.5833	.93712	-.267	-.775	3.0000	3.8350	4.3300
comskill1 7	36	3	3.7597	1.47762	-.829	-.863	2.7525	4.6700	5.0000
comskill1 8	36	3	3.9261	1.16091	-.856	-.370	3.0000	4.3300	5.0000
comskill1 9	36	3	3.5097	.82597	-.255	-.318	3.0000	3.6700	4.0000
comskill1 10	36	3	2.5186	.89938	-.560	-.605	2.0000	2.6700	3.0000
Total	36	24	28.5108	6.96934	-1.006	-.316	25.9200	30.6700	33.9975

የመምህራኑን ኢ.ቃ.ላ.ዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ለማወቅ ይቻል ዘንድ በምልከታ ቅጹ ላይ ከተካተቱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው የመምህራኑ ንግግር የተቆራረጠ አለመሆኑን፤ የተቆራረጠ ንግግራቸውን ለመሙላትም የተቆራረጠ ንግግር መሙያዎችን (እም.....) አለመጠቀማቸውን የተመለከተ (comskill1 3) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 4.1853 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=0.96108 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል፡፡ ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል፡፡

ዝመቱ -1.246 ሲሆን በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ በላይ ባለው ምድብ መጎዳኘታቸውን ያመለክታል፡፡ ዝብጠቱ 1.747 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ወደ አማካዩ ቀርበው የቀረበ ጉድኝት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ያረፉት መረጃዎች በ3.4975፣ 4.335ና 5 ላይ ያረፉ ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት በ2፣ 3ና 4 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህም ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ መረጃ በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንተና እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች በመደበኛ

አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው፡፡ ስለዚህም የመምህራኑ ንግግር የተቆራረጠ አለመሆኑና መምህራኑ የተቆራረጠ ንግግራቸውን ለመመሳት የንግግር መሙያዎችን (እም…) አለመጠቀማቸው ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው መምህራኑ በተማሪዎቻቸው ላይ ለሚነበቡ ኢቃላዊ ምልክቶች ተገቢውን ምላሽ የሚሰጡ መሆኑን የተመለከተ (Comskill1 4) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 3.1853 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=1.3923 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል፡፡ ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ላይ ተጎዳኝተዋል፡፡

ዝመቱ -0.436 ሲሆን በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ በላይ መጎዳኘታቸውን ያመለክታል፡፡ዝብጠቱ -0.929 ሲሆን መረጃዎቹ በዝቅተኛ ደረጃ ወደ አማካዩ መጎዳኘታቸውን ያሳያል፡፡ በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ያረፉት መረጃዎች በ2.7525፣ 3.00ና 4.33 ላይ ያረፉ ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ላይ የሚያርፉት መረጃዎች በ2፣ 3ና 4 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህም በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ ይህ መረጃ በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ በተማሪዎቻቸው ላይ ለሚነበቡ ኢቃላዊ ምልክቶች ተገቢውን ምላሽ የመስጠታቸው ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚኖረው የመረጃ ፍሰት ላይ አወንታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡ :

በኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሶስተኛው የመምህሩ አካላዊ ሁኔታና አለባበስ በተማሪዎች ዘንድ ጥሩ ስምና ክብር ሊያሰጣቸው የሚችል መሆኑን የተመለከተ (Comskill1 5) ነው (አባሪ 2ን 4ን ይመልከቱ)፡፡ አካላዊ ሁኔታና አለባበስ ከኢቃላዊ መግባቢያዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን የመምህራን አለባበስ በቀለም ምርጫም ሆነ በስፌት ማህበረሰቡ

ከሚጠቀምበት መደበኛ አለባበስ ያላፈነገጠ ወይም ጫፍ ያልወጣ እንዲሆን ይጠበቃል። በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 3.7778 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል። የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሬ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=1.43235 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት ለየት ባለ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ዝመቱ -1.261 ሲሆን በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ በላይ ባሉት ምድቦች የተጎዳኙ መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 0.084 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ለአማካይ ውጤታቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውን ያሳያል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ3.67፣ 4.33ና 4.9175 ላይ ያረፉ ናቸው። ይህም ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያሳያል። መረጃው በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አተገባበር ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው። መረጃው የመምህራኑ አካላዊ ሁኔታ (የጥፍር አቆራረጥ፣ የጸጉር አበጣጠር፣ የጌጣጌጥ አጠቃቀም፣ የመዋቢያዎች አጠቃቀም)ና አለባበስ በተማሪዎች ዘንድ ጥሩ ስምና ክብር ሊያሰጣቸው የሚችል መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል። ይህ ሁኔታ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል በመከባበር ላይ የተመሰረተ መልካም ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል።

በኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ዘርፍ የተዳሰሰው አራተኛው ተግባር መምህራኑ የሚጠቀሙባቸው ድምጸ ቅላጼዎች ተገቢ የሆነ የተግባቦት ሂደት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill1 6) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ድምጸ ቅላጼ ኢቃላዊ መልእክት መወከያ መንገድ እንደመሆኑ መጠን መምህራን መልእክት ሲያስተላልፉ ተገቢ የሆነ ድምጸ ቅላጼን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል። በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 3.5833 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል። የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሬ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.93712 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት የተለየ ጉድኝት አላቸው ማለት ነው።

ዝመቱ -0.267 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.775 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው የተጎዳኙ መሆኑን ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ያረፉት መረጃዎች በ3.00፣ 3.835ና 4.33 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ላይ የሚያርፉት መረጃዎች በ2፣ 3ና 4 ላይ የተጎዳኙ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ስለዚህም በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። በመሆኑም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ የሚጠቀሙባቸው ድምጸ ቅላጼዎች ተገቢ የሆነ የተግባቦት ሂደት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸው ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል።

አምስተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው አካላዊ ቅርርብ ማህበራዊ መሆኑን የተመለከተ (Comskill1 7) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። በተግባቦት ሂደት በተሳታፊዎች መካከል የሚኖር አካላዊ ቅርርብ መልእክት ወካይ ከሆኑ ኢቃላዊ ምልክቶች መካከል አንዱ ሲሆን በተግባቦቱ ሂደት የሚተላለፈውን መልእክት ግብ መች የማድረግና ያለማድረግ አቅም አለው። በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩት መረጃዎች አማካይ 3.7597 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=1.47762 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.829 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ የተጎዳኙ መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.863 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ጉድኝት ከአማካዩ የራቀ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ላይ ያረፉት መረጃዎች በ2.7525፣ 4.67ና 5.00 ላይ ያረፉ ናቸው። ይህ ሁኔታ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይበት መሆኑን ለመገንዘብ ያስችላል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩንም ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው።ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ከተማሪዎቻቸው

ጋር ያላቸው አካላዊ ቀረቤታ ማህበራዊ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በመምህራኑና በተማሪዎች መካከል ምቹ የሆነ በይነሰባዊ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።

ስድስተኛው ተግባር በመምህራኑ ላይ የሚነበቡት ኢቃላዊ ምልክቶች በቃላዊ ምልክቶች የሚያስተላልፉትን መልእክት የሚያጠናክሩ ወይም የተሟላ የሚያደርጉ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill1 8) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ቃላዊና ኢቃላዊ ምልክቶች በመልእክት አወካከል ተደጋጋፊ እንደመሆናቸው መጠን በመልእክት አስተላላፊዎች ላይ የሚነበቡት ኢቃላዊ ምልክቶች በቃላዊ ምልክቶች የተወከለውን መልእክት የተሟላ የሚያደርጉ እንዲሆኑ ይጠበቃል። በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 3.9261 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል። የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ መረጃዎች መጎዳኘታቸውንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=1.16091 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ዝመቱ -0.856 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.370 ሲሆን በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ጉድኝት ከአማካያቸው የራቀና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ደልደል ብሎ የሜሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ3.00፣ 4.33ና 5.00 ላይ ያረፉ ናቸው። ስለዚህም በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያሳያል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለመረዳት ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በመምህራኑ ላይ የሚነበቡት ኢቃላዊ ምልክቶች በቃላዊ ምልክቶች የሚተላለፈውን መልእክት የሚያጠናክሩ ወይም የተሟላ የሚያደርጉ መሆናቸው ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም መምህራንና ተማሪዎች እንዲግባቡ ማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ሰባተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት በመምህራኑ ላይ የሚነበቡ ገጸ ግላጼዎች የተግባቡቱን ሂደት የሚያሳልጡ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill1 9) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ገጸ ግላጼ ከኢቃላዊ የመልእክት መወከያዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን መምህራኑ ከተማሪዎቻቸው ጋር

መግባባት ይችሉ ዘንድ የተግባቦቱን ሂደት የሚያሳልጡ ገጸ ግላጼዎችን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል። በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 3.5097 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል። መብለጡ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.82597 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ መደበኛ አሰረጫጨትን ከሚያሳይ ወስከምባይነት ለየት ባለ መጠን በምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.255 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.318 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው የራቀ ጉድኝት ያላቸው መሆኑን ለመረዳት ያስችላል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ3.00፣ 3.97ና 4.00 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ላይ የሚያርፉት መረጃዎች በ2፣ 3ና 4 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። ከዚህ አንጻር በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘተቸው ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በመምህራኑ ላይ የሚነበቡት ገጸ ግላጼዎች የተግባቦቱን ሂደት የሚያሳልጡ መሆናቸው ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ለሚኖር የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

በኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጨረሻው መምህራኑ ለትምህርት የተመደበላቸውን ጊዜ በአግባቡ የሚጠቀሙ መሆኑን የተመለከተ (Comskill1 10) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። የጊዜ አጠቃቀም ኢቃላዊ የመልእክት መወከያ መንገድ ነው። በመማር ማስተማሩ ሂደት መከናወን የሚገባው ተግባር በአግባቡ መከናወን እንዲችልም ሆነ ተማሪዎች ጊዜን በአግባቡ የመጠቀም ባህልን እንዲያዳብሩ ለማድረግ መምህራን ለመማር ማስተማሩ ሂደት የተመደበላቸውን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ይጠበቃል። በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.5186 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.89938 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ

የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ዝመቱ -0.560 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ከፍ ሲል ለማየት እንደተሞከረው አማካዩ ላይ በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች የተጎዳኙ መሆኑን ያሳያል። ይህ ሁኔታ ከዝመቱ ዋጋ ጋር ተዳምሮ ሲታይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት ያለው በምልከታ ከተገኘው አማካይ በመደበኛ አሰረጫጨት እስከሚጠበቀው አማካይ ድረስ ባሉት ነጥቦች ላይ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል። ዝብጠቱ -0.605 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ጉድኝት ከአማካያቸው በመጠኑ የራቀ መሆኑን ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ2.00፣ 2.67ና 3.00 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት ማእከላይ ሩብ ልኬታዎች በ2.00፣ 3.00ና 4.00 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና በመደበኛ አስረጫጨት የሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨቶች በንጽጽር ሲታዩ የሁለተኛው ሩብ ልኬታ መነሻ ነጥቦች ተመሳሳይ ቢሆኑም የሁለተኛውና የሶስተኛው ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦችና የሶስተኛው ሩብ ልኬታ መጨረሻ ነጥቦች ልዩነት አላቸው። በምልከታ የተገኘው መረጃ ከሚጠበቀው አንሶ ይታያል። ስለዚህም በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም መምህራኑ ለትምህርት የተመደበላቸውን ጊዜ በአግባቡ በጥቅም ላይ የማዋላቸው ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ደካማ መሆኑ መምህራኑ ስራቸውን በተመደበላቸው ጊዜ የማከናወንና ለተማሪዎች በጊዜ አጠቃቀም ረገድ ጥሩ ባህልን የማዋረስ ችግር የሚታይባቸው መሆኑን ያስገነዝባል።

አጠቃላይ የመምህራኑን ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ለማወቅ የሁሉንም ተግባራት አተገባበር በድምር ማየት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 5 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራኑን ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 28.5108 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 24.00 ይበልጣል። መብለጡ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=6.96934 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት የተለየ ጉድኝት አላቸው ማለት ነው።

ዝመቱ -1.006 ሲሆን በጣም በርካታ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካዩ በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.316 ሲሆን መረጃዎቹ ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ25.92፣ 30.67ና 33.9975 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የሚጎዳኙት መረጃዎች በ16፣ 24ና 32 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። ሶስቱም የሩብ ልኬት መቁረጫ ነጥቦች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ይበልጣሉ። ይህም ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑንና በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የመምህራኑን ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 6ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 6: የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቴስት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 24						Cohen's d effect
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Differen	95% Confidence Lower	95% Confidence Upper	
observed nonverbal		35	.000	4.51083	2.1527	6.8689	1.29448

በሰንጠረዥ 6 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=3.883, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው 3.883 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ4.51085 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። የዚህ ውጤት ስህተት የመሆን እድል 0.0% መሆኑንም ለማወቅ ያስችላል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=1.294478 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም የመምህራኑ ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ለሚኖረው የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት አወንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

፫. የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ

የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ መምህራን ያቀረቡትን መረጃ ተማሪዎቻቸው በግብኣትነት መቀበል እንዲችሉ ወክለውና አሰናስለው የሚያፈልቁበት መንገድ ነው (Wrench et al., 2009; McPheat, 2010)። ተግባቦት መረጃን የመጋራት ሂደት እንደመሆኑ መጠን አንዱ የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ያስተላለፈውን መልእክት ሌላው መገንዘብ የሚችለው መረጃዎቹ በአግባቡ ተደራጅተው ሲቀርቡ ነው። በዚህ ጥናት የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ማወቅ ይቻል ዘንድ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን የተመለከቱ ሰባት ተግባራት በምልከታ ቅጹ ላይ ተካትተዋል (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። የአተገባበራቸውን ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 7 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 7፡ የትምህርታዊ መረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
comskill2 11	36	3	1.1203	.46562	3.966	14.749	1.0000	1.0000	1.0000
comskill2 12	36	3	1.1203	.46562	3.966	14.749	1.0000	1.0000	1.0000
comskill2 13	36	3	1.0922	.21956	2.817	8.527	1.0000	1.0000	1.0000
comskill2 14	36	3	1.1106	.25148	2.726	7.494	1.0000	1.0000	1.0000
comskill2 15	36	3	2.4719	1.04349	-.150	-1.381	1.3300	2.6700	3.3300
comskill2 16	36	3	2.3144	1.02939	.111	-1.305	1.0825	2.0000	3.3300
comskill2 17	36	3	2.5458	1.03931	-.150	-1.062	1.6700	3.0000	3.3300
Total	36	21	11.7756	2.86344	-.546	-1.006	9.4150	12.6700	13.9900

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎቻቸው ማሳወቃቸውን የተመለከተ (Comskill2 11) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ረገድ ከመምህራን ጋር የጋራ መግባባት ላይ መድረስ እንዲችሉ የትምህርቱን ዓላማ ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህም ትምህርቱን ለምን እንደሚማሩ አውቀው የሚፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ የሚያስችሏቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.1203 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከመጠበቀው 3.00 በጣም ያነሰ ነው። የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። ሶስቱ ተመልካቾች በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጸውን ምስል እየተመለከቱ በደረጃዊ ልኬት የሰጧቸው ነጥቦች እንደሚያሳዩት መረጃዎቹ በይበልጥ የተጎዳኙት በጣም ደካማ አተገባበርን

በሚያሳየው ደረጃዊ ልኬት ላይ ነው (አባሪ 9ን ይመልከቱ)። መደበኛ ልይይቱ s=0.46562 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል። በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ በታች በጣም ዝቅተኛ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ ላይ ችምችም ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 3.966 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ጠንካራ አተገባበር በሚያሳዩትና ከአማካዩ በስተግራ ባሉት ምድቦች በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 14.749 ሲሆን በጣም ብዙ መረጃዎች ለአማካዩ በጣም ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ጠንካራ አተገባበር በሚያሳዩትና ከአማካዩ በስተግራ ባሉት ምድቦች ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው። ይህ ነጥብ በጣም ደካማ አተገባበርን የሚያሳይ ምድብ ነው። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎቻቸው የማሳወቃቸው ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ ነው። ይህ ሁኔታ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ግብ ተኮር ሆነው ትምህርታዊ ተግባራትን እንዳያከናውኑ፣ በግብረመልስ አሰጣጥ ሂደት ከተቀመጠው አላማ አንጻር ራሳቸውን እንዳይገመግሙና በመማር ማስተማሩ ሂደት ምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው አስበው እንዳይንቀሳቀሱ ምክንያት ይሆናል። አለመንቀሳቀሳቸው ደግሞ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ረገድ ከመምህራን ጋር የጋራ መግባባት ላይ መድረስ እንዳይችሉ እንቅፋት ይሆናል።

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበው ትምህርታዊ መረጃ መምህሩ ለተማሪዎቻቸው ያስተዋወቁትን ዓላማ መሰረት ያደረገ መሆኑን የተመለከተ (Comskill 2 12) ነው (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። ይህ ጉዳይ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ የሚያገኙት ትምህርታዊ መረጃ የታለመውን አላማ ከግብ ማድረስ የሚያስችል እንዲሆን ያደርጋል። በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.1203 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.46562 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ

በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት ለየት ባለ መልኩ ከአማካዩ በታች ችምችም ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 3.966 ሲሆን በጣም በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ በታች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ምድብ በስተግራ ወደሚገኙትኛ ጠንካራ አተገባርን ወደሚያሳዩት ምድቦች በጣም እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 14.749 ሲሆን መረጃዎቹ ወደ አማካዩ በጣም ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ጠንካራ አተገባበርን በሚያሳዩት ምድቦች በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ ላይ ያረፉ ናቸው። ስለዚህም በምልከታ በተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያሳያል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በጣም በርካታ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ባለውና በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ በመጎዳኘታቸው ነው፡ ፡ በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበው ትምህርታዊ መረጃ መምህሩ ለተማሪዎቻቸው ያስተዋወቁትን ዓላማ መሰረት ያደረገ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ ነው። ይህ ሁኔታ የመማር ማስተማሩ ሂደት ግብ ተኮር እንዳይሆንና ምዘናና ጽብረቃ በተገቢው መንገድ እንዳይከናወኑ ያደርጋል።

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሶስተኛው በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ ከሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት የሚያገኙትን ጥቅም እንዲያውቁ መደረጉን የተመለከተ (Comskill2 13) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ይህ ተግባር ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.0922 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.21956 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ በታች ባለው ምድብ ችምችም ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 2.817 ሲሆን በጣም በርካታ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች ባለውና በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ የተጎዳኙ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ

የመረጃ ጉድኝት ካለበት ምድብ በስተግራ ወደሚገኙትና ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ለማወቅ ያስችላል፡፡ ዝብጠቱ 8.527 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች ወደ አማካያቸው በጣም ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ በጣም እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው፡፡ ይህ ነጥብ በጣም ደካማ አተገባበርን የሚያሳይ ምድብ ነው፡፡ ስለዚህም በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል፡፡ ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው፡፡ መረጃው በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት የሚያገኙትን ጥቅም እንዲያውቁ መደረጉ ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በጣም ደካማ መሆኑ ተማሪዎቹ ከውስጥ በመነጨ ተነሳሽነት ትምህርቱን እንዳይከታተሉና የሚፈለገው ውጤት ላይ እንዳይደርሱ ትልቅ መሰናክል ይፈጥራል፡፡

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል አራተኛው ለተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸው መልመጃዎች የበለጸገ አስተሳሰብን (rigorous thinking) የሚያጣጡፉ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill2 14) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.1106 ነው፡ ፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል፡፡ ማነሱ በመደበኛ አተገባበር ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=0.25148 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል፡፡ አብዛኞቹ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ ሁኔታ ከአማካዩ በታች ባለውና በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ ችምችም ብለው ተጎዳኝተዋል ማለት ነው፡፡

ዝመቱ 2.726 ሲሆን ከአማካዩ በታች ባለው ምድብ በርካታ መረጃዎች መጎዳኘታውንና ከዚህ ምድብ በስተግራ ወደሚገኙትና ጠንካራ አተገባርን ወደሚያሳዩት ምድቦች እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ዝብጠቱ 7.494 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች በከፍተኛ ሁኔታ ወደ አማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ወዳለበት ነጥብ እስኪደርስ በጥቂቱ እየቀነሰ የሚሄድ የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት

በሚጠበቀው ማእከላይ ሩብ ልኬታዎች 2.00፣ 3.00ና 4.00 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። ስለዚህም በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለመገንዘብ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸው መልመጃዎች የበለጸገ አስተሳሰብን ማጧጧፍ የሚያስችሉ መሆናቸው ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ ነው። ይህም በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ እርስ በእርስና ከመምህራን ጋር መረጃ በሚገበያዩበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል አምስተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበው ትምህርታዊ መረጃ በቅደም ተከተል የተደራጀ መሆኑን የተመለከተ (Comskill2 15) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን ትምህርታዊ መረጃዎች በሚገባ እንዲረዷቸው ከሚታወቅ ወደማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድና ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ መደራጀት ይኖርባቸዋል። በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ ከ2.4719 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያስገነዝባል። መደበኛ ልይይቱ s=1.04349 ሲሆን አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት ለየት ባለ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ዝመቱ -0.150 ሲሆን በመጠኑ በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ ባሉት ምድቦች መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ምድብ በስተግራ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ደልደል ያለ ዝቅታ ያለው መሆኑንም ለመረዳት ያስችላል። ዝብጠቱ -1.381 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው የተጎዳኙ መሆናቸውንና አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን ያሳያል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ1.33፣ 2.67ና 3.33 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር የሚታይበት መሆኑን መረዳት አያዳግትም። በሌላ አገላለጽ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎላ ማለቱንና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው

በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው ከምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበው ትምህርታዊ መረጃ በቅደም ተከተል የተደራጀ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር መጠነኛ ድክመት ይታይበታል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል። ይህም ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ትምህርታዊ መረጃ በሚረዱበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ስድስተኛው በትምህርቱ ሂደት በጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ አቀራረብ ተማሪዎቹ የሚሰነዝሯቸውን ሀሳቦች የትምህርት ግብኣት ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን የተመለከተ (Comskill2 16) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። በመሰረተ ማህበራዊ ግንባታውያን ዝንቅ የትምህርት ፍልስፍና መሰረተ ሀሳብ ላይ በተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት የጋራ ግንዛቤን መፍጠር የሚቻለው ተማሪዎቹ ለተግባቡቱ ሂደት ግብኣት መሆን የሚችል ሀሳብ ሲያመነጩ ነው። ለዚህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት በጥቅም ላይ የሚውለው የትምህርታዊ መረጃ አቀራረብ ተማሪዎቹ የሚሰነዝሯቸውን ሀሳቦች የትምህርት ግብኣት ለማድረግ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል። በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.3144 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ለመረዳት ያስችላል። መደበኛ ልይይቱ s=1.02938 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑንና በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ መጎዳኘታቸውን ያመለክታል።

ዝመቱ 0.111 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በመጠኑ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካዩ በታች መጎዳኘታውን ያሳያል። ዝብጠቱ -1.305 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ1.0825፣ 2.00ና 3.33 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች በ2.00፣ 3.00ና 4.00 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት የሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ያስገነዝባል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ አቀራረብ

ተማሪዎቹ የሰነዘሩትን ሀሳብ የትምህርት ግብኣት ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህ ሁኔታ ትምህርታዊ የተግባቦት ስርአቱ ተሳታፊዎቹ መረጃን የሚለዋወጡበት፣ የጋራ ግንዛቤን በመጨበጥ እውቀታቸውን የሚገነቡበትና ነጻ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ የሚያካሂዱበት እንዳይሆን ያደርጋል። የተግባቦት ስርአቱን ግብይታዊ የመረጃ ፍሰት ያለበት ሳይሆን መረጃ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚፈስበት መስመራዊ እንዲሆን ያደርገዋል። ተማሪዎችንም ንቁ ተሳታፊ ሳይሆን ፍዝ ተመልካች ለሚያደርጉ ችግሮች ይዳርጋቸዋል።

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጨረሻው በትምህርቱ ሂደት የቀረበው መረጃ በየእውቀት ፈርጁ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን የተመለከተ (Comskill2 17) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። በብሉም ፍረጃ የተማሪዎችን ሁለንተናዊ እውቀት ለመገንባት ይቻል ዘንድ በትምህርትነት የሚቀርቡ መረጃዎች በአእምሯዊ፣ በሕውስታዊና በስሜታዊ ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል። በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.5458 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=1.03931 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.150 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በመጠኑ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ ባሉት ምድቦች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨታቸው ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ምድብ በስግራና በስተቀኝ ደልደል ያለ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ -1.062 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ደልደል ያለ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ1.67፣ 3.00ና 3.33 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት በንጽጽር ሲታዩ ደካማ አተገባበር የጎላ መሆኑን ማወቅ ይቻላል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ይህም የትምህርት አሰጣጡ የተማሪዎችን ሁለንተናዊ እውቀት መገንባት የሚያስችል መረጃ በማስተላለፍ ረገድ ድክመት የሚታይት መሆኑን ያስገነዝባል። አእምሯዊ፣

ሕውስታዊና ስሜታዊ ዘርፎችን በማካተትና ነገሮችን ማወቅ፣ መረዳት፣ መተንተን፣ መፈረጅና በአንድ በተወሰነ ማስረጃ ወይም እውቀት ላይ ተመስርቶ መገምገምን በመዳሰስ ረገድ በተወሰነ ደረጃ ጥንካሬ ይታይበታል ማለት ነው።

በጥቅሉ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረቡ ምን እንደሚመስል ለማየት በዘርፉ የተካተቱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች በድምር ማየት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 7 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የትምህርታዊ መረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን በድምር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 11.7756 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 21.00 በጣም ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=2.86344 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ተቀራራቢ በሆኑ ምድቦች ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.546 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ ባሉት ምድቦች የተጎዳኙ መሆኑን ያመለክታል። ዝብጠቱ -1.006 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውን ያሳያል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የተጎዳኙት መረጃዎች በ9.415፣ 12.670ና 13.990 ላይ ያረፉ ናቸው። መደበኛ አሰረጫጨትን በሚያሳይ የመረጃ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የመቁረጫ ነጥቦች 14፣ 21ና 28 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ሲታይ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያስገነዝባል። ስለዚህም በመደበኛ አተገባበር በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ሰንጠረዥ 8፡ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 21						Cohen's d effect
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence		
					Lower	Upper	
observed organization & presentation of information -comskill	-19.335	35	.000	-9.22444	-10.1930	-8.2559	-6.4452

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 8ን ይመልከቱ)። በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-19.335, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -19.335 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-9.22444 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰና ደካማ አተገባበር የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-6.44516 ሆኖ ተገኝቷል፡ ፡ ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየውና የአማካይ ልዩነትን የሚያሳየው ውጤት እንዳመለከተው በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የትምህርታዊ መረጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የመረጃ ፍሰት የተሳለጠ እንዳይሆን አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሁኔታም የደከመ እንዲሆን ያደርጋል።

፬. የጥያቄ አጠያየቅ

የጥያቄ አጠያየቅ ትምህርታዊ መረጃዎች በምልክት የሚወከሉበት መንገድ ሲሆን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት አማካኝነት ግንዛቤን እንዲጨብጡና እውቀት እንዲገነቡ ለማድረግ ያስችላል። በዚህ መሰረት የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ያስችል ዘንድ በተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ የጥያቄ አጠያየቅን የተመለከቱ አምስት ተግባራት ተካትተዋል። የአተገባበራቸውን ሁኔታ የሚያሳዩት መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ውጤት በሰንጠረዥ 9 ቀርቧል።

በጥያቄ አጠያየቅ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በጋራ ችግር የመፍታት ችሎታን እንዲያዳብሩ ለማረግ የሚያስችሉ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill 2 21) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። የማህበራዊ ግንባታውያን የትምህርት ፍልስፍና አሰራሮች በሆኑት የጋራ ውሳኔ ሰጭነት፣ የመረጃ መጋራት፣

ትብብራዊነት፣ ፈጣሪነትና ፍጥነት ከፍተኛ ውጤት ላይ መድረስ የሚቻለው በመግባባት፣ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት መረጃ በመለዋወጥ፣ በመደጋገፍና አዳዲስ እውቀቶችን በመገንባት ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራን በሚጠይቋቸው ጥያቄዎች አማካኝት ተማሪዎች በጋራ ችግር የመፍታት ችሎታን ሊያዳብሩ ይገባል። በሰንጠረዥ 9 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.7964 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.86646 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ሰንጠረዥ 9፡ የመምህራኑን ጥያቄ አጠያየቅ ችሎታ የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኪታ (inter quartile range)		
							25	50	75
comskill2 21	36	3	1.7964	.86646	1.050	.462	1.0000	1.6700	2.5850
comskill2 22	36	3	1.1108	.32786	3.243	10.009	1.0000	1.0000	1.0000
comskill2 23	36	3	2.6944	1.10559	-.450	-1.346	1.4150	3.0000	3.6700
comskill2 24	36	3	2.2772	.77914	-.102	-.832	1.4150	2.3300	3.0000
comskill2 25	36	3	2.4722	.87031	-.538	-1.099	1.6700	2.6700	3.2475
Total	36	21	10.3511	2.71740	-.783	-.493	9.4125	11.1600	12.2500

ዝመቱ 1.050 ሲሆን በጣም በርካታ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች ባሉት ምድቦች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ምድብ በስተግራ ወዳሉትና ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ዝብጠቱ 0.462 ሲሆን በምልከታ የተገኙት የበርካታ መረጃዎች ጉድኝት ወደ አማካያቸው የተጠጋ መሆኑንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ አስከሚደርስ ድረስ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በማእከላይ ሩብ ልኬታዎች በ1.00፣ 1.67ና 2.585 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች በ2.00፣ 3.00ና 4.00 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች ሲነጻጸሩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይበት መሆኑን ያስገነዝባል። በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች

ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በጋራ ችግር የመፍታት ችሎታን እንዲያዳብሩ ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸው ለድክመት የተጋለጠ ነው። ተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች መሰረት አድርገው በሚያከናውኗቸው ተግባራት አማካኝነት በጋራ ችግር የመፍታት ችሎታን እንዲያዳብሩ የሚደረግበት ሁኔታ የአተገባበር ችግር ያለበት መሆኑን ያሳያል።

በጥያቄ አጠያየቅ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው መምህራኑ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ተጠየቃዊ አስተሰብን እንዲያዳብሩ ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill 2 22) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ተጠየቃዊ አስተሳሰብ በስሜት ወይም በፍላጎት ሳይሆን በማስረጃ ወይም በሀሳብ አመክንዮ ላይ ተመስርቶ በነገሮች መካከል ያለን የመንስኤና ውጤት ትስስር የመመልከትና ትንታኔ የመስጠት ችሎታ ነው። የሚዳብረው መምህራኑ ትምህርታዊ መረጃን ወደ ተማሪዎቹ ለማድረስ በሚያነሷቸው ጥያቄዎች አማካኝነት ነው። በሰንጠረዥ 9 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩት በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.1108 ነው። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ (3.00) በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.32786 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ ሀኔታ ከአማካዩ በታች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 3.243 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ ባሉትና ጠንካራ አተገባበርን በሚያሳዩት ምድቦች በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 10.009 ሲሆን አብዛኞቹ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ወደ አማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውን ያሳያል። የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች ሙሉ በሙሉ በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው። ስለዚህም በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ ይታያል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ ላይ የተጎዳኙት መረጃዎች ብዙ በመሆናቸው ነው። መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች የተማሪዎቹን ተጠየቃዊ አስተሳሰብ ለማዳበር የሚያስችሉ መሆናቸው ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ይህም ተማሪዎቹ በነገሮች

መካከል ያለን የመንስኤና የውጤት ትስስር ፈትሾ በአመክንዮ ድምዳሜ ላይ የመድረስ ችሎታዎችን እንዳያዳብሩ ምክንያት ይሆናል፡፡

በጥያቄ አጠያየቅ ዘርፍ ከተካተቱት ተግባራት መካከል ሶስተኛው መምህራኑ የሚጠይቋቸው መሪ ጥያቄዎች የተማሪዎቹን ሂሳዊ አስተሳሰብ የሚያዳብሩ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill2 23) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ ሂሳዊ አስተሳሰብ ተማሪዎች ስለራሳቸው፣ ስለክስተቶች ወይም በትምህርቱ ሂደት ስለሚቀርብላቸው መረጃ ጥያቄዎችን አንስቶ መጠየቅ፣ ትንታኔ መስጠት፣ የተነተኑትን መረጃ ማዋሀድ፣ አዳዲስ መላምቶችን ማፍለቅ፣ ያፈለቁትን መላምት በእውነታ ላይ ተመስርቶ መፈተሽ፣ መገምገምና ድምዳሜ ላይ መድረስ እንዲችሉ የሚያደርግ አእምሯዊ ሂደት ነው፡፡ የሚዳብረው በመማር ማስተማሩ ሂደት ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት አማካኝነት ነው፡፡ በሰንጠረዥ 9 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.6944 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል፡፡ ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=1.10559 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል፡፡ መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው፡፡

ዝመቱ -0.450 ሲሆን በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካዩ በላይ መጎዳኘታቸውን ያመለክታል፡፡ ዝብጠቱ -1.346 ሲሆን መረጃዎቹ ከአማካዩ ርቀው መጎዳኘታቸውን ያሳያል፡፡ የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች በ1.415፣ 3.00ና 3.67 ላይ ያረፉ ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች በ2.00፣ 3.00ና 4.00 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል፡፡ በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ የመቁረጫ ነጥቦች ሲነጻጸሩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ እንደሚታይበት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው፡፡ መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች የተማሪዎቹን ሂሳዊ አስተሳሰብ የሚያዳብሩ መሆናቸው ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት የሚታይበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ሂሳዊ አስተሳሰብ መረጃዎችን መመርመር፣ መተንተን፣ ማዋሀድ፣ መገምገምና ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚያስችል እንደመሆኑ መጠን መምህራኑ የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ሂሳዊ አስተሳሰብን በማዳበር ረገድ ድክመት ያለባቸው መሆናቸው ተማሪዎች የችሎታው ባለቤት እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

በጥያቄ አጠያየቅ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል አራተኛው መምህራኑ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች በተማሪዎቹ የላቀ እውቀት ግንባታ ክልል መልስ የሚያገኙ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill2 24) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። በማህበራዊ ግንባታውያን የትምህርት ፍልስፍና አተያይ መሰረት መማር ማህበራዊ ተግባር በመሆኑ የሚከናወነው ተማሪዎቹ ንቁ ሆነው በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል በሚያከናውኗቸው ተግባራት አማካኝነት መምህራን ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ ነው። በሰንጠረዥ 9 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.2772 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ 0.77914 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ ሁኔታ በተወሰኑ ምድቦች ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.102 ሲሆን በጥቂቱ በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። ዝብጠቱ -0.832 ሲሆን በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው ራቅ ብለው መጎዳኘታቸውን ያሳያል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የመቁረጫ ነጥቦች በ1.4150፣ 2.33ና 3.00 ናቸው። እነዚህ ነጥቦች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቁት 2.00፣ 3.00ና 4.00 ጋር ሲነጻጸሩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይት መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም። ስለዚህም በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች በተማሪዎቹ የላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል መልስ በሚከናወኑ ተግባራት የሚያገኙ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህ ሁኔታ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ መረጃን በሚገነዘቡበት ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

በጥያቄ አጠያየቅ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጨረሻው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ቁልፍ ሀሳቦችን ከነዝርዝሮቻቸው የሚዳስሱ መሆናቸውን የተመለከተ (Comskill 2 25) ነው (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ መሆን እንዲችል የትምህርታዊ መረጃው ቁልፍ ሀሳቦች በማብራሪያ ተደግፈው በጥያቄዎች አማካኝነት መቅረብ ይኖርባቸዋል። በሰንጠረዥ 9 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 2.4722 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት

መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.87031 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየደረጃዊ ልኬቶቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.538 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -1.099 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው የተጎዳኙ መሆናቸውን ያሳያል። የማእከላይ ሩብ ልኬታ የመቁረጫ ነጥቦች 1.670፣ 2.670ና 3.2475 ናቸው። በመደበኛ አተገባበር 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃበል። በምልከታ የተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች ሲነጻጸሩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ እንደሚታይበት ለመረዳት ይቻላል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ቁልፍ ሀሳቦችን ከነዝርዝሮቻቸው የሚዳስሱ መሆናቸው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህም ተማሪዎቹ ቁልፍ የሆነውን ትምህርታዊ መረጃ በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በሚከናወኑ ተግባራት አማካኝነት ማብራራት እንዳይችሉ ያደርጋል። ሽቅብ አመክንዮን፣ ቁልቁል አመክንዮንና ንጽጽርን በመጠቀም ቁሳቁሶችን፣ ገጠመኞችን፣ ክስተቶችን፣ ሂደቶችን፣ ድምዳሜዎችን፣ እውነታዎችን፣ የግል አስተያየቶችንና በመካከላቸው ያለውን ትስስር አውጥቶ የማሳየት ችሎታን እንዳያዳብሩም እንቅፋት ይሆናል።

አጠቃላይ የመምህራኑን የጥያቄ አጠያየቅ እንዴትነት ለማወቅ በዘርፉ የተካተቱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች በድምር ማየት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 9 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የመምህራኑን የጥያቄ አጠያየቅ የሚያሳዩ መረጃዎች ድምር አማካይ 10.3511 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 15 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=2.71740 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል። ዝመቱ -0.783 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.493 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውን ያሳያል። የማእከላይ ሩብ ልኬታ የመቁረጫ ነጥቦች 9.4125፣ 11.160ና 12.250 ናቸው። መደበኛ አሰረጫጨትን በሚያሳይ

የመረጃ አሰረጫጨት 10፣ 15ና 20 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 8ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 10፡ የመምህራኑን የጥያቄ አጠያየቅ ከሀሎት የሚያሳዩ መረጃዎች

One-Sample Test

	Test Value = 15						Cohen's d effect
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence		
					Lower	Upper	
observed questioning skills	-10.265	35	.000	-4.64889	-5.5683	-3.7295	-3.4216

በሰንጠረዥ 10 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-10.265, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -19.335 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ--4.64889 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰና ደካማ አተገባበር የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-3.42157 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ እንደታየው በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም የመምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህም ተማሪዎቹ ቁልፍ የሆነውን ትምህርታዊ መረጃ በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በሚከናወኑ ተግባራት አማካኝነት ፈልገው ማግኘት እንዳይችሉ ያደርጋል። የአመክንዮ ተግባራትን፣ መገምገምን፣ መተንተንን፣ ማነጻጸርና ማወዳደርን በመጠቀም መረጃን ፈልፍሎ የማውጣትና የመገንዘብ ችሎታን እንዳያደብሩ ያደርጋል።

ገጠመኞችን፣ ክስተቶችን፣ ሂደቶችን፣ ድምዳሜዎችን፣ እውነታዎችን፣ የግል አስተያየቶችንና በመካከላቸው ያለውን ትስስር አውጥቶ የማሳየት ችሎታን እንዲያዳያጎለብቱም እንቅፋት ይሆናል።

፩. የመረጃ ግብይት

የመረጃ ግብይት በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል መረጃ የሚንሸራሸርበት ኡደታዊ አሰረጫጨት ነው። የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ማወቅ ይቻል ዘንድ በዚህ ዘርፍ ስምንት ተግባራት ተካትተዋል። የነዚህን ተግባራት የክንውን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 11 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 11፡ የመረጃ ግብይት ሂደትን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
comskill2 18	36	3	1.6569	.62506	1.365	2.629	1.0825	1.6700	2.0000
comskill2 19	36	3	2.6486	1.16248	.032	-1.428	1.6700	2.6650	3.6700
comskill2 20	36	3	1.3239	.65449	2.440	5.795	1.0000	1.0000	1.3300
comskill2 26	36	3	2.8517	1.06143	-.783	-.573	2.0825	3.0000	3.6700
comskill2 27	36	3	3.1569	1.29390	-.441	-1.118	2.0825	3.5000	4.3300
comskill2 28	36	3	3.0653	1.14332	-.412	-.740	2.0825	3.3300	3.9175
comskill2 29	36	3	1.1294	.34101	3.390	12.543	1.0000	1.0000	1.0000
comskill2 30	36	3	2.7781	1.20257	-.215	-1.080	1.6700	3.0000	3.6700
Total	36	24	18.6108	5.32820	-1.083	-.112	17.7425	20.3400	21.9125

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የመረጃ ግብይት ወላንሳ መሆኑን የተለመከተ (Comskill 2 18) ነው (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። ወላንሳ የሆነ የመረጃ ፍሰት የሌሎችን መብት ሳይጥሱና ስሜትን ሳይጎዱ ፍላጎትን፣ አመለካከትን፣ ስሜትንና አስተያየትን ቀጥተኛነት፣ ግልጽነትና ትክክለኛነት በተሞላበት ሁኔታ ለመግለጽ ያስችላል። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 1.6569 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.62506 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 1.365 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ በታች መጎዳኘታቸውን ለማወቅ ያስችላል። ዝብጠቱ 2.629 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ለአማካዩ ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ ጠንካራ አተገባርን ወደሚያሳዩት ምድቦች በጣም እየመነመነ የሜሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። የማእከላይ ሩብ ልኬታ የመቁረጫ ነጥቦች 1.0825፣ 1.6700ና 2.00 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩንም ያስገነዝባል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው።

መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የመረጃ ግብይት ወላንሳ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የመረጃ ፍሰት የሌሎችን ነጻነት ሳይጋፉ እሴቶችን፣ ሀሳቦችን፣ እምነቶችን፣ አስተያየቶችንና ፍላጎቶችን ቀጥተኛነት፣ ግልጽነትና ትክክለኛነት በተሞላበት ሁኔታ በነጻነት መግለጽ በማስቻል ረገድ ድክመት ያለበት መሆኑን ያሳያል። ድክመት መኖሩ ተማሪዎቹ የሌሎችን ስሜት የሚጎዱ፣ መብት የሚጋፉና ጫና የሚያደርጉ ሰዎችን ምክንያታዊ ሆኖ ቁጡና አሜነኛ ሳይሆኑ የመጋፈጥ ችሎታን እንዳያዳብሩ ያደርጋል። የመረጃ ግብይት ሂደቱም ሞገደኛ፣ አሜነኛ ወይም አሜነኛ-ሞገደኛ እንዲሆን ያደርጋል። ተማሪዎቹ የሚያስቡትንና የሚፈልጉትን ጉዳይ በራስ መተማመን በተሞላበት ሁኔታ መግለጽ እንዳይችሉም እንቅፋት ይሆናል።

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት በአንድምታ መሰላል መረጃን መገበያየት የሚከናወን መሆኑን የተመለከተ (Comskill 2 19) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። በአንድምታ መሰላል መረጃን መገበያየት በትምህርትነት በቀረበው መረጃ ላይ በቂ ግንዛቤ ለመጨበጥ ያስችላል። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.6486 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=1.16248 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 0.032 ሲሆን በጥቂቱ በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካዩ በታች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከአማካዩ በስተግራና በስተቀኝ በመጠኑ የተቀራረበ የመረጃ ጉድኝት

ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ዝብጠቱ -1.428 ሲሆን በምልከታ የተገኙ የበርካታ መረጃዎች ጉድኝት ከአማካዩ የራቀ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 1.6700፣ 2.6650ና 3.6700 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ የመቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር የሚታይበት መሆኑን ያስገነዝባል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያሉ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ይህ መረጃ በመማር ማስተማሩ ሂደት መረጃን በአንድምታ መሰላል የመገበያየቱ ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት የሚታይበት መሆኑን ያስገነዝባል። ድክመቱ የአንድምታ መሰላል ሰዎች ለአንድ መረጃ ከተጋለጡበት ጊዜ አንስቶ እስከሚተገብሩት ድረስ ደረጃ በደረጃ መረጃ የሚያልፍበት የአመክንዮ ሂደት ከመሆኑ አንጻር ተማሪዎቹ በቀደመ እውቀት ላይ ተመስርተው መረጃን በመምረጥ፣ ለመረጃው በመጋለጥና መረጃውን በመተንተን ድምዳሜ ላይ እንዳይደርሱ ያደርጋል። ይህ ደግሞ መረጃን ሲቀስሙ ነባራዊ እውነታውን እንዲዘሉትና ግልብ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይችላል።

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሶስተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት ጽብረቃዊ ማዳመጥ የሚከናወን መሆኑን የተመለከተ (Comskill 2 20) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። ጽብረቃዊ ማዳመጥ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚተላለፈውን መልእክት አስተውለው የተሟላና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙና እንደገመግሙ ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 1.3239 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 በጣም ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች መጎዳኘታቸውን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሪ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ 0.65449 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 2.440 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ዝብጠቱ 5.795 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ጉድኝት ለአማካያቸው በጣም የቀረበ መሆኑንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ከግራ ወደ ቀኝ ከፍታው በጥቂቱ እየጨመረ የሚሄድ በጣም የመነመነ

ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ 1.00፣ 1.00ና 1.33 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00. 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ የመቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያስገነዝባል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩንም ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በጣም በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ጽብረቃዊ ማዳመጥን እንዲያከናውኑ መደረጉ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል። ደካማ መሆኑ ተማሪዎቹ የሚተላለፈውን መልእክት በትኩረት መከታተልን፣ ጥያቄ መጠየቅን፣ የተላለፉትን መልእክቶች በራስ አባባል መግለጽንና መገምገምን እንዳያከናውኑ ያደርጋል። አለማከናወናቸው ደግሞ በተላለፈው መረጃ ረገድ የጋራ ግንዛቤን እንዳይጨብጡ ለሚያደርግ ችግር ያጋልጣቸዋል።

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል አራተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት ከትምህርቱ አላማ ጋር አብረው የሚራመዱ ሂደታዊ የምዘና ስልቶች በጥቅም ላይ መዋላቸውን የተመለከተ (Comskill2 26) ነው (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.8517 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=1.06143 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.783 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.573 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ወዳለበት ነጥብ እስኪደርስ በስተግራና በስተቀኝ ደልደል ያለ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.0825፣ 3.00ና 3.6700 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች ሲነጻጸሩ በመጀመሪያው ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥብ ላይ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ይበልጣል። ሁለተኛው መቁረጫ ነጥብ ተመሳሳይ ሲሆን ሶስተኛው የመቁረጫ ነጥብ ላይ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የመቁረጫ ነጥብ አንሶ ይታያል። የመጨረሻው ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥብ

ከሚጠበቀው የሚያንስ መሆኑ የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች ከሚያሳዩት ውጤት ጋር ተዳምሮ ደካማ አተገባበር የጎላ መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የመጀመሪያውና ሁለተኛው የማእከላይ ሩብ ልኬታ ነጥቦች ተቀራራቢ መሆናቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ከትምህርቱ አላማ ጋር አብረው የሚራመዱ ሂደታዊ የምዘና ስልቶች በጥቅም ላይ መዋላቸው ድክመቱ የጎላ ቢሆንም ጠንካራ አተገባበር የሚታይበት መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። በጥቅሉ ሲታይ ግን በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ያለው የመረጃ ጉድኝት በርከት ያለ በመሆኑ ነው።

ይህ መረጃ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከትምህርቱ አላማ ጋር የሚራመዱ የሂደታዊ ምዘና ስልቶች በጥቅም ላይ መዋላቸው ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ደካማነቱ መምህራን የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ በሚቆጣጠሩበት፤ ግብረመልስ በሚሰጡበት፤ ማሻሻያ የሚያስፈልገውን ጉዳይ በሚለዩበት እንዲሁም ተማሪዎችን በሚያበረታቱበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ተማሪዎቹም በትምህርቱ ሂደት ትኩረት የሚሰጠውን ጉዳይ በሚለዩበት፣ የቀሰሙትን እውቀት በሚተገብሩበትና አስፋፍተው በጥቅም ላይ በሚያውሉበት ሁኔታ ላይ እንቅፋት ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በተከናወነው ተግባር ውጤታማነት ላይ እንዲጸበርቁና ተገቢውን የማሻሻያ ርምጃ እንዲቀይሱ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደርጋል።

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል አምስተኛው መምህሩ የሚሰጡት ግብረመልስ ገንቢ፣ ግልጽና ውሱን መሆኑን የተመለከተ (Comskill2 27) ነው። ግብረመልስ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የሚያደርጉትን ጥረት ወደ ትምህርቱ ግብ እንዲያደርጉ፣ ስህተታቸውን በትክክል እንዲገመግሙና እንዲያርሙ ለማድረግ ይረዳል። ጥሩ ውጤት ማስገኘት እንዲችል ገንቢ፣ ግልጽና ውሱን መሆን ይኖርበታል። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር አስመልክቶ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 3.1569 ነው። ይህ ነጥብ መደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል። መብለጡ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=1.29390 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ዝመቱ -0.441 ሲሆን በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -1.118 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአይነተኛ ውጤት ልኬታቸው ርቀው

መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.0825፣ 3.500ና 4.3300 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች ሲነጻጸሩ በምልከታ የተገኘው ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያሉ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ይህ መረጃ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚሰጡት ግብረመልስ ገንቢ፣ ግልጽና ውሱን መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን ያመለክታል። በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ብቃት ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። መምህራንና ተማሪዎች ስለጨበጡት የጋራ ግንዛቤና ስላከናወኑት ትምህርታዊ ተግባር እርስ በእርስ ምላሽ እንዲሰጣጡ ለማድረግም ያስችላል። ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ላይ ያላቸውን ግስጋሴ እንዲገመግሙ፤ በቀረበው መረጃ ረገድ በትምህርታዊ መረጃ ማሕቀፉ ውስጥ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ እንዲያውቁና ራሳቸውን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ካለው ሁኔታ ጋር እንዲያስተካክሉ ለማድረግ የሚያስችል በር ይከፍታል። በመማር ማስተማሩ ሂደት ያጋጠማቸውን የመረጃ ክፍተት መሙላት እንዲችሉም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ስድስተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት አዲስ በቀረበው የትምህርት ይዘት፣ በተማሪዎች ዳራዊ እውቀትና በነባራዊው አለም አተገባበሩ መካከል ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን የተመለከተ (Comskill2 28) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 3.0653 ሲሆን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ይበልጣል። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር በጥቂቱ ጎላ ብሎ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=1.14332 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየደረጃዊ ልኬቶቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.412 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ጠንካራና ደካማ አተገባበር በሚያሳዩት ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ደልዳላ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ዝብጠቱ -0.740 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ

ጉድኝት ወዳለበት ነጥብ እስኪደርስ ድረስ እየቀነሰ የሚሄድ ደልደል ያለ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ ነጥቦች 2.0825፣ 3.3300ና 3.9175 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኘው ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህም በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በመጠኑ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት አዲስ በቀረበው የትምህርት ይዘት፣ በተማሪዎች ዳራዊ እውቀትና በነባራዊው አለም አተገባበሩ መካከል ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸው ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን ያሳያል። በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ ተማሪዎቹ አዲስ የቀረበላቸውን ትምህርታዊ መረጃ ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ማያያዝ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሰባተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት በተከናወነው የመረጃ ግብይት ላይ ጽብረቃ መከናወኑን የተመለከተ (Comskill2 29) ነው (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። ጽብረቃ በመግለጽ፣ በመተንተንና በመገምገም የአንድ ተግባር አተገባበር የሚፈተሸበትና ከሚገኘው ውጤት በቀጣይ የሚከናወኑትን ተግባራት አተገባበር ለማሻሻል የሚያስችል ትምህርት የሚቀሰምበት ሂደት ነው። መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የነበረውን አሰራር ድክመትና ጥንካሬ በመፈተሽ አሰራራቸውን የበለጠ የሚያሻሽሉበትን መንገድ እንዲቀይሱ ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 1.1294 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 በጣም ያነሰ ነው። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.34101 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ችምችም ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 3.390 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ነጥቦች ከፍታው በጣም እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 12.543 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ለአማካዩ በጣም ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ከፍታው በጥቂቱ እየጨመረ የሚሄድ በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ ነጥቦች ሙሉ በሙሉ

በ1.00 ላይ ያረፉ ናቸው። ይህ ነጥብ በጣም ደካማ አተገባበርን የሚያሳይ ነው። ስለዚህም በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚያሳይ መሆኑን ለመገንዘብ ያስችላል። በመሆኑም በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በጣም በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ጽብረቃ የመከናወኑ ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ደካማ መሆኑ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የነበረውን የአተገባበር ሁኔታ በመፈተሽ ከድክመታቸውና ከጥንካሬያቸው እንዳይማሩ፣ አንድን ተግባር ሲያከናውኑ ከንውኑ በሚፈልገው አተገባበርና በክንውኑ መካከል የነበረውን ክፍተት ፈትሸው ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችሉ አካሄዶችን እንዳይቀይሱ፣ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት የነበራቸውን አተገባበር መለስ ብለው ሙያው በተመሰረተበት ንድፈ ሀሳብ መጠገኒያነት እንዳይፈትሹና ድምዳሜውን በቀጣይ ለሚያከናውኑት የማስተማር ስራ ውጤታማነት በጥቅም ላይ እንዳያውሉ ያደርጋል።

በመረጃ ግብይት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጨረሻው በመማር ማስተማሩ ሂደት ግብረመልስ ሲሰጥ የትምህርታዊ መረጃዎች ጭምቃሳብ መከለሱን የተመለከተ (Comskill2 30) ነው (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። ጭምቃሳብ በአንድ ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት የተሰራጩ መረጃዎች የሚያስተላልፉት መልእክት ወይም ጭብጥ ነው። የትምህርቱ ሂደት ሲጠናቀቅ ወይም ከአንድ የትምህርት ርእስ ወደ ሌላ ሽግግር ሲደረግ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በተሰራጨው መረጃ ረገድ የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ ይከናወናል። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.7781 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=1.20257 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ መጠን በየደረጃዊ ልኬቶቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.215 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ለመረዳት ያስችላል። ዝብጠቱ -1.080 ሲሆን መረጃዎቹ አማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 1.6700፣ 3.000ና 3.6700 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ የማእከላይ ሩብ ልኬታ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ የመሀከለኛው መቁረጫ ነጥብ ተመሳሳይ ቢሆንም የመጀመሪያውና የመጨረሻው የተለያዩ ናቸው። በምልከታ የተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህም በምልከታ በተገኘውና

መደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ ላይ ያለው የመረጃ ጉድኝት ከሚጠበቀው በላይ በመሆኑ ነው (አባሪ 9ን ይመልከቱ)። ይህ መረጃ በመማር ማስተማሩ ሂደት ግብረመልስ ሲሰጥ የትምህርታዊ መረጃዎች ጭምቅ ሀሳብ የሚከለስ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት የሚታይበት መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት የተሰራጩ መረጃዎች የሚያስተላልፉት መልእክት ወይም ጭብጥ ተጨምቆ በሚቀርብበት ሁኔታ ላይ እንቅፋት መኖሩን ያሳያል። የትምህርቱ ሂደት ተሳታፊዎች ባከናወኑት ተግባርና በተሰራጨው መረጃ ረገድ የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውን ማረጋገጥ እንዳይችሉ፣ በተሰራጨው ትምህርታዊ መረጃ ላይ እንዳይጸበርቁና የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደርሱ ለሚያደርግ ችግር እንዲጋለጡ ያደርጋል። የትምህርት አቀራረቡ የተቀሰመው መረጃ እንዲጠናከርና በብልሀት ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው እንዲሸጋገር የማድረግ ችግር ያለበት መሆኑንም ያስገነዝባል።

አጠቃላይ የመረጃ ግብይቱ እንዴት ያለ እንደሆነ ለማወቅ በስሩ የተካተቱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች ድምር ውጤት ማየት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 11 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለውን የመረጃ ግብይት እንዴትነት የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 18.6108 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 24.00 ያንሳል። በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች መጎዳኘታቸውን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=5.32820 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -1.083 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -1.080 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው የተጎዳኙ መሆኑን ያመለክታል። የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 17.7425፣ 20.34ና 21.9125 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ ነጥቦች 16፣ 24ና 32 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው ሲነጻጸሩ የመጀመሪያው የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ላይ በምልከታ የተገኘው በልጦ ያታያል። ስለዚህም በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው።

ልዩነቱ በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለውን የመረጃ ግብይት የሚያሳዩ መረጃዎች የቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 12ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 12፡ የመረጃ ግብይት ሂደትን የሚያሳዩ መረጃዎች የቲ-ቴስት ስልት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 24						Cohen's d effect
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence Lower	95% Confidence Upper	
observed tranasaction of informaton	-6.069	35	.000	-5.38917	-7.1920	-3.5864	-2.0229

በሰንጠረዥ 12 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-6.069, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -6069 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-5.38917 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰና ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-2.0229 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ እንደታየው በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም የመረጃ ግብይቱ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ደካማ መሆኑ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች በተግባቦቱ ሂደት በተላለፈው መረጃ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደርሱ ያደርጋል። ጽንሰ ሀሳቦችን፣ አመለካከቶችን፣ ሀሳቦችን፣ ነባራዊ እውነታዎችንና የግል አስተያቶችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መጋራት እንዳይችሉ የሚያደርግ የተግባቦት እንቅፋት መኖሩንም ያመለክታል። ሁኔታው የተግባቦቱን ሂደት ያውከዋል። ስለዚህም በትምህርቱ ሂደት በተሰራጨው መረጃ ረገድ መምህራንና ተማሪዎች የጋራ ግንዛቤን ለመጨበጥ ይቸገራሉ። በዚህም የተነሳ የትምህርቱ ሂደት የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ የተሳነው ይሆናል።

፮. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ማጠቃለያ

የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ ይቻል ዘንድ 30 ተግባራትን የያዘ የምልከታ ቅጽ ተዘጋጅቶ መረጃዎች ተሰብስበዋል (አባሪ 2ና 11ን ይመልከቱ)። እነዚህ መረጃዎች በአምስት ዘርፎች ተከፋፍለው ታይተዋል። ቀጥሎ ደግሞ የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች አጠቃላይ ገጽታ ምን እንደሚመስል ይታያል። የነዚህ መረጃዎች ጥቅል እንዴትነት በገላጭ ስታቲስቲክስ ተሰልቶ በሰንጠረዥ 13 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 13: አጠቃላይ የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ሰሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
comskill Total	36	90	76.4433	18.73160	-1.485	.425	80.0725	85.0050	88.2575

በሰንጠረዥ 13 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 76.4433 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 90.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=18.73160 ሲሆን በምልከታ የተገኘው መረጃ አሰረጫጨት የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -1.485 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ ባሉት ምድቦች ላይ የተጎዳኙ መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 0.425 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ወደ አማካያቸው ቀርበው የተጎዳኙ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 80.0725፣ 85.0050ና 88.2575 ላይ ያረፉ ናቸው። መደበኛ አሰረጫጨትን በሚያሳይ የመረጃ አሰረጫጨት 60፣ 90ና 120 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። ከዚህ አንጻር በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ሲታይ ምንም እንኳ የመጀመሪያው ማእከላይ ሩብ ልኬት መነሻ ነጥብ ከሚጠበቀው የሚበልጥ ቢሆንም ቀሪዎቹ ሁለቱ ከሚጠበቀው በታች ናቸው። ይህ ሁኔታ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በጥቅል የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 14ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 14፡ የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ተ-ቴስት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 90						Cohen's d effect size
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence		
					Lower	Upper	
observed comminicative skills	-4.342	35	.000	-13.55667	-19.8945	-7.2188	-1.4475

በሰንጠረዥ 14 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-4.342, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -4.342 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-13.55667 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-1.4475 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ እንደታየው በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም አንጻር ደካማ ነው። ደካማ መሆኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት ችግር የተጋረጠበት መሆኑን ያመለክታል።

4.1.1.2. ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኘ መረጃ

የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች በአምስት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

፭. ቃላዊ መግባቢያዎች

የመምህራኑን ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች በሁለት ነጥቦች ዙሪያ ያጠነጥኑ ናቸው። የመጀመሪያው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚሰነዝሩትን ሀሳብ ግልጽነት፤ ሁለተኛው ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ የሚሰነዝሩት ሀሳብ ተማሪዎቹ ያከናወኗቸውን ተግባራት የሚያጣጥል ሳይሆን የሚገልጽ መሆኑን የተመለከቱ ናቸው። መረጃዎቹ እንደሚያሳዩት በመማር ማስተማሩ ሂደት ሁለቱም ተግባራት በአብዛኛው በጥሩ ሁኔታ የሚከናወኑ ናቸው (አባሪ 6ን ይመልከቱ)።

፮. ኢቃላዊ መግባቢያዎች

የመምህራኑን ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች ጠንካራና ደካማ አተገባበሮች የሚታዩ መሆኑን ያመለክታሉ። ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ የሚታይባቸው ተግባራት የመምህራኑ ንግግር የተቆራረጠ አለመሆኑንና የተቆራረጠ ንግግራቸውን ለመሙላትም መሙያዎችን (እም.....) አለመጠቀማቸው፤ መምህራኑ ተማሪዎቻቸው ላይ ለሚነበቡ ኢቃላዊ ምልክቶች ተገቢውን ምላሽ መስጠታቸው፤ የመምህራኑ አካላዊ ሁኔታ (የጥፍር አቆራረጥ፣ የጸጉር አበጣጠር፣ የጌጣጌጥ አጠቃቀም፣ የመዋቢያዎች አጠቃቀም)ና አለባበስ በተማሪዎች ዘንድ ጥሩ ስምና ክብር ሊያሰጣቸው የሚችል መሆኑ፤ መምህራኑ የሚጠቀሙባቸው ድምጸ ቅላጼዎች ተገቢ የሆነ የተግባቦት ሂደት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸው። በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው አካላዊ ቅርርብ ማህበራዊ መሆኑ፤ በመምህራኑ ላይ የሚነበቡት ኢቃላዊ ምልክቶች በቃላዊ ምልክቶች የሚያስተላልፉትን መልእክት የሚያጠናክሩ ወይም የተሟላ የሚያደርጉ መሆናቸውና በመማር ማስተማሩ ሂደት በመምህራኑ ላይ የሚነበቡ ገጸ ግላጼዎች የተግባቦቱን ሂደት የሚያሳልጡ መሆናቸው ናቸው። በነዚህ ተግባራት ረገድ ጠንካራ ጎኖች ጎልተው መታየታቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖርና በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ሀሳብ ለሀሳብ መረዳዳት እንዲኖር ማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይበት ተግባር የጊዜ አጠቃቀም ነው። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው መምህራኑ ለትምህርት የተመደበላቸውን ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም ረገድ የተወሰነ ችግር ይታይባቸዋል። ጊዜ ኢቃላዊ የመልእክት ማስተላለፊያ ከመሆኑ አንጻር የሚፈለገውን መረጃ በአግባቡ የማስተላለፍ ችግር እንዲገጥማቸው ከማድረጉም በላይ በተማሪዎቻቸው ላይ ጥሩ የሆነ የጊዜ አጠቃቀምን እንዳያዋርሱ ያደርጋል (አባሪ 6ን ይመልከቱ)።

፫. የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ

በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ስር ከተነሱት ዘርፎች መካከል ሶስተኛው የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ነው። ይህ ዘርፍ ስድስት ተግባራትን የያዘ ሲሆን ሁሉም ተግባራት ደካማ አተገባበር ጎልቶ ይታይባቸዋል (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎቻቸው ሲያሳውቁ አልታየም። ስለዚህም የሚያስተምሩት ትምህርት ለተማሪዎቻቸው ያስተዋወቁትን አላማ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ማወቅ ያዳግታል። ከዚህ በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ከሚያከናውኑት ተግባር የሚያገኙትን ጥቅም እንዲያውቁ አይደረግም። በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚቀርቡት ትምህርታዊ ተግባራት የበለጸገ አስተሳሰብን የሚያጣጡፉ፣ በቅደም ተከተል የተደራጁ፣ ተማሪዎቹ የሚሰነዝሯቸውን ሀሳቦች የትምህርት ግብኣት ለማድረግ የሚያስችሉና በየእውቀት ፈርጁ ላይ ትኩረት ያደረጉ በመሆናቸው ረገድ ድክመት ይታይባቸዋል። ምልከታው በተካሄደበት ወቅት የቀረቡት ትምህርታዊ ተግባራት የበለጸገ አስተሳሰብን በሚያዳብር መልኩ ሲቀርቡ አልታየም። መምህራኑ ሲያስተምሩ በቀጥታ በመማሪያ መጽሀፉ ላይ የቀረበውን ቃል በቃል ከማሰራትና ከመናገር ውጪ ተጨማሪ ድጋፍ ሰጭ ተግባራትን በትምህርቱ አላማና ይዘት ላይ ተመስርቶ ማዘጋጀት፣ የአመላክቶ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግና የመልመጃ ወረቀቶችን አዘጋጅቶ መስጠት ሲከናወኑ አልታየም። ከመማሪያ መጽሀፉ ላይ የሚቀርቡት ይዘቶችም ቢሆኑ የክፍለ ጊዜውን ትምህርት ለማስተማር በሚያመች መልኩ በቅደም ተከተል ተደራጅተው የሚቀርቡበት ሁኔታ አነስተኛ ነው። ማለትም የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተላዊ አካሄዶችን (መግቢያ፣ ማቅረቢያ፣ ማጠናከሪያ፣ ግምገማ) ተከትሎ በመማሪያ መጻህፍቱ ላይ የቀረበውን የትምህርት ይዘት አደራጅቶ የማቅረብ ሁኔታ አይታይም። ይህም ትምህርቱ ከሚታወቅ ወደ የማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድና ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ የሚሄድበትን ሁኔታ ሲያዛባው ታይቷል።

በክፍል ውስጥ በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑ ተማሪዎች መኖራቸው የማይካድ ቢሆንም ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ አይደለም። ተሳታፊ የሚሆኑት በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ታዋቂነትን ያገኙ ጥቂት ተማሪዎች ብቻ ናቸው። ስለዚህም ሁሉም ተማሪዎች ለትምህርቱ ግብኣት መሆን የሚችል ሀሳብ የመሰንዘር እድል የሚያገኙበት ሁኔታ በጣም የጠበበ ነው። የትምህርቱ ይዘት በየእውቀት ፈርጁ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ የሚጠበቅ ቢሆንም በአብዛኛው በእውቀት ዘርፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ሆኖ ታይቷል። ይህም መተንተን፣ ማገናዘብና መገምገም ብዙ ቦታ እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ሁኔታው የትምህርታዊ መረጃ አደረጃጀትና አቀራረቡ ድክመት ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ይህም ተማሪዎቹ የሚፈለገውን ግንዛቤ እንዳይጨብጡና ከሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር እውቀትን እንዳይገነቡ ለሚያደርግ ችግር እንዲጋለጡ ያደርጋል።

፬. የጥያቄ አጠያየቅ

የጥያቄ አጠያየቅ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ስር ከተዳሰሱት ዘርፎች መካከል አንዱ ነው። በዚህ ዘርፍ አምስት ተግባራት የተካተቱ ሲሆን ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች በአምስቱም ተግባራት አተገባበር ረገድ ድክመት የሚታይ መሆኑን ያሳያሉ (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ በጋራ ችግር የመፍታት ችሎታን እንዲያዳብሩ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ቀርጸው የሚያቀርቡበት ሁኔታ ብዙ አይደለም፤ አልታየምም። መምህራኑ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ተጠየቃዊና ሂሳዊ አስተሰብን የሚያዳብሩ ናቸው ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ተጠየቃዊ አስተሳሰብን የሚያያዳብሩ መተንተን፣ ማገናዘብ፣ መገምገም፣ አስተያየት መስጠት፣ የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን ለይቶ ማውጣት የመሳሰሉ ተግባራትን የሚጋብዙ ሆነው አልታዩም። በመማር ማስተማሩ ሂደት በአብዛኛው የሚከናወነው በመማሪያ መጽሀፉ ላይ የቀረበውን ጥያቄ መጠየቅና ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ አዳምጦ ትክክለኛውን መልስ መስጠት ነው። ከዚህ ውጪ በትምህርቱ ሂደት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች የሚያቀርቡት ሀሳብ በሌሎች ተሳታፊዎች ማብራሪያ፣ አስተያየት ወይም ትንታኔ ሲሰጥበት አልታየም። ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ሲሰሩም በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል መልስ ማግኘት ይችሉ ዘንድ የተሻለ ችሎታ ባላቸው ተማሪዎች ድጋፍ ሲደረግላቸው አልታየም። በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚቀርቡት ጥያቄዎች ቁልፍ ሀሳቦችን ከነዝርዝሮቻቸው የሚዳስሱ እንዲሆኑ ቢጠበቅም ጥያቄዎቹ በአብዛኛው በዝርዝር ሀሳቦች ላይ የሚያተኩሩ ሆነው ታይተዋል። ስለዚህም የመምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ድክመት ይታይበታል። ይህም ተማሪዎች የሚፈለገውን እውቀት በራሳቸው ፈልፍለው እንዲያወጡ የማድረጉ ሁኔታ ለአተገባበር ችግር የተጋለጠ መሆኑን ያሳያል። ሁኔታው ትምህርታዊ መረጃዎች ተማሪዎች ግንዛቤን እንዲጨብጡ በሚያደርግ ሁኔታ ወደ ተማሪዎች በሚደርሱበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

፭. የመረጃ ግብይት

የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ማወቅ ይቻል ዘንድ በስሩ ከተካተቱት ዘርፎች መካከል አምስተኛውና የመጨረሻው የመረጃ ግብይቱን እንዴትነት የተመለከተ ነው። የመረጃ ግብይት ዘርፍ በስሩ ስምንት ተግባራትን የያዘ ሲሆን ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች በሁሉም ተግባራት አተገባበር ረገድ ድክመት የሚታይ መሆኑን ያስገነዝባል (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። የመረጃ ግብይቱ ከወላንሳነት ይልቅ አሜንተኛነት ያመዝንበታል። ማለትም አብዛኞቹ ተማሪዎች የሌሎችን ሀሳብ የመግለጽ ነጻነት ሳይጥሱ እምነታቸውን፣ አስተሳሰባቸውን፣ ግንዛቤያቸውን፣ ድጋፋቸውንና ተቃውሟቸውን በማስረጃ አስደግፈው በግልጽ ከማቅረብ ይልቅ ከመምህራኑ ወይም ሻል ካሉ ተማሪዎች የሚተላለፈውን ሀሳብ አሜን ብሎ የመቀበል ሁኔታ ጎልቶ ይታይባቸዋል። በክፍል ውስጥ ተማሪዎቹ

ትምህርታዊ ተግባራትን ሲያከናውኑ የአንድምታ መሰላል በጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ሂደት የሚከናወንበትም የማይከናወንበትም ሁኔታ አለ። መከናወኑ ተማሪዎቹን የተሳሳተ ግንዛቤ ላይ ከመድረስ የሚታደጋቸው ጉዳይ ቢሆንም አለመከናወኑ ግልብ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ለሚያደርግ ችግር ያጋልጣቸዋል። የማመዛዘን ችሎታቸው እንዳይዳብር የሚያደርግ የትምህርት አሰጣጥ ሂደት መኖሩንም ያመለክታል። በመማር ማስተማሩ ሂደት የጽብረቃዊ ማዳመጥ ተግባራት አይከናወኑም። ስለዚህም በትምህርቱ ሂደት የተሰነዘሩ ሀሳቦችን መገምገም፣ በራስ አባባል መግለጽ፣ ጨምቆ የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረስ፣ በተገለጹ ሀሳቦች ላይ ተንተርሶ ማብራሪያ የሚሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጎልቶ አይታይም።

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎችን ያሳተፈ የምዘና ሂደት (ግለ ምዘና፣ የብጤ ምዘና፣ የቡድን ምዘና) ሲከናወን አልታየም። የተማሪዎቹን ትምህርታዊ ክንውን ለመመዘንም የቤት ስራዎች፣ የአመላክቶ ስራዎች፣ የቡድን ስራዎች፣ የግል ስራዎችና ውይይት ለምዘና አገልግሎት የዋሉበት ሁኔታ የለም። ይህም ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራቱን በብቃት ማከናወናቸውን አስመልክቶ በቂ መረጃ እንዳይገኝ ያደርጋል። አለመገኘቱ በግብረመልስ አሰጣጡ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚሰጠው ግብረ መልስ ገንቢ፣ ግልጽና ውሱን የሚሆንበት ሁኔታ ጥቂት ባይሆንም የማይሆንበት ሁኔታ መኖሩንም መረጃዎቹ ያሳያሉ። አብዛኛውን ጊዜ ግብረመልስ የሚሰጠው በቃል ነው። በጽሁፍ ግብረመልስ የሚጥበት ሁኔታ ብዙ አይደለም። ይህም ተማሪዎቹ ተረጋግተው በግንዛቤያቸውና እንዲገነዘቡት በሚጠበቀው መረጃ መካከል ያለውን ክፍተት እንዳያገናዝቡ ያደርጋል። አብዛኛውን ጊዜ በመማር ማስተማሩ ሂደት አዲስ በቀረበው የትምህርት ይዘት፣ በተማሪዎች ዳራዊ እውቀትና በነባራዊው አለም አተገባበሩ መካከል ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት አይከናወኑም። ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት በተከናወነው መረጃ ግብይት ላይ መምህራኑ አይጸበርቁም፤ ተማሪዎቻቸውም እንዲጸበርቁ አያደርጉም። በመማር ማስተማሩ ሂደት ግብረመልስ ሲሰጥ የትምህርታዊ መረጃዎች ጭምቅ ሀሳብ የሚከለስ ቢሆንም የማይከለስበት ሁኔታ ጥቂት አይደለም። ይህም ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበውን መረጃ ጭምቃሳብ እንይጨብጡ ያደርጋል። በጥቅሉ መረጃዎቹ የመረጃ ግብይቱ ድክመት ያለበት መሆኑን ያመለክታሉ። ድክመት መኖሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ እንዲገበዩ የሚፈለገውን እውቀት በበቂ ሁኔታ እንዳይገበዩ የሚያደርግ የተግባቦት እንቅፋት መኖሩን አመላካች ነው። ሁኔታው ተማሪዎቹ በሚያከናውኑት የእውቀት ግንባታ ሂደትና አዲስ በቀረበው መረጃ ላይ ግንዛቤ በሚጨብጡት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

4.1.1.3. ከሰነድ ምርመራ የተገኘ መረጃ

የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምን፤ የይዘት አደረጃጀትና አቀራረብብን እንዲሁም የመረጃ ግብይትን የተመለከቱ ናቸው (አባሪ 8ን ይመልከቱ)። የኢቃላዊ መግባቢያዎችን የተመለከተው መረጃ በእለታዊ የትምህርት እቅዱ ላይ የጊዜ አጠቃቀሙ በግልጽ አለመቀመጡን የተመለከተ ነው። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ለማስተማር የተመደበላቸውን ጊዜ በአግባቡ እንዳይጠቀሙ ያደርጋል። በጊዜ ተወስኖ የተሰጣቸውን የትምህርት ይዘት በተመደበለት ጊዜ አስተምሮ የመጨረስ ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል ያሳያል። ችግሩ ተማሪዎቹ ለክፍል ደረጃው የተቀመጠውን ትምህርታዊ መረጃ በአግባቡ እንዳያገኙና ጥሩ ያልሆነ የጊዜ አጠቃቀም በተማሪዎቹ ዘንድ እንዲሰርጽ ያደርጋል።

የይዘት አደረጃጀትና አቀራረብን በተመለከተ ከሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በእለታዊ የትምህርት እቅዱ ላይ የተቀመጡት ዝርዝር አላማዎች ግልጽ፣ ውሱን፣ ተተግባሪ፣ ተለኪና ተማሪዎቹ ከሚያከናውኗው ተግባራት አንጻር የመገለጽ ችግር ይታይባቸዋል። በትምህርቱ አላማና በይዘቱ መካከል ያለው ትስስር በግልጽ አይታይም። በትምርህርቱ ሂደት የትምህርቱን ዓላማ ወደ ተማሪዎቹ ለማድረስ የሚከናወኑት ተግባራት በግልጽ አልተቀመጡም። እንዲሁም የትምህርት እቅዱና የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ትስስር በግልጽ አይታወቅም። የትምህርቱ ይዘት ከቀረበ በኋላ በጥቅም ላይ የሚውሉት የማጠናከሪያ ተግባራት በግልጽ አልተቀመጡም። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት ትምህርታዊ መረጃ የሆነው የትምህርቱ አላማ በምልክት ተወክሎ ወደ ተማሪቹዎቹ በሚደርስበት ሁኔታ ላይ የተግባቦት እንቅፋት ሊፈጥር የሚችል ችግር መኖሩን ያሳያል። አላማዎቹ ሲነደፉ የዝርዝር አላማን ባህሪ አለሚሟላታቸው ለመተግር የሚያስቸግሩ፣ በአንድ በተወሰነ ትምህርታዊ መረጃ ላይ የማያተኩሩ፣ ከትግበራ በኋላ ከግብ መድረሳቸውን ለመለካት የሚያዳግቱና በተማሪዎች የሚተገበሩ የመሆን ችግር ያለባቸው መሆኑን ያሳያል። አላማዎቹ ወደ ተማሪዎቹ የሚደርሱበት መንገድ በግልጽ አለመቀመጡ በራሱ የመልእክት ማስተላለፊያ መንገዱ ላይ ችግር መኖሩን ያሳያል። የማስፋፊያ ተግባራቱ በግልጽ አለመታወቃቸውም እንደዚሁ ተማሪዎቹ የተማሩትን ትምህርት ለመገንዘብ፣ ለመገምገም፣ ለማብላላት ወይም ለማዋሀድ የሚያስችሉ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ሁኔታ ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ መሆኑን ያሳያል። ሁኔታው በትምህርቱ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

በተመሳሳይ ከሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎች በግብረ መልስ፣ በምዘናና በጽብረቃ አተገባበር ረገድም ችግር መኖሩን ያሳያሉ። የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተከናወነ እያለም ሆነ ክንውኑ ሲጠናቀቅ ተማሪዎቹ ያጉት ግንዛቤ በምዘና ተገምግሞ ተገቢ የሆነ ግብረ መልስ ሊሰጥበት ይገባል። ይሁን እንጂ መረጃዎቹ እንደሚያሳዩት በጥቅም ላይ የሚውሉት የምዘና ስልቶች፣ የግብረመልስ አሰጣጥ ስልቶችና

የጽብረቃ ተግባራት በትምህርት እቅዱ ላይ በግልጽ አልተቀመጡም፡፡ ምዘና ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ትምህርታዊ መረጃ ምን ያህል እንደተረዱት ለመለካት የሚያገለግል ነው፡፡ ከፍ ሲል ለማየት እንደተሞከረው የትምህርቱ አላማ መለካት የሚችል አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ የምዘና ስልቶቹ በግልጽ ካለመቀመጣቸው ጋር ተዳምሮ በትምህርቱ ሂደት የሚቀርበው ትምህርታዊ መረጃ የአወካከልና የአቀራብ ችግር ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ተማሪዎቹ ይረዱት አይረዱት ወይም ይገንዘቡት አይገንዘቡት የመታወቁ ሁኔታም አጠራጣሪ መሆኑንም ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ በተከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ምን ያህል የእውቀት ግንባታ አካሂደዋል የሚለው ጥያቄ ምላሽ እንዳያገኝ ያደርጋል፡፡ አጠቃላይ የትምህርት ስርአቱን ለተግባቦት ሂደት እንቅፋት ያጋልጠዋል፡፡ የተማሪዎቹ ግንዛቤ ምን ያህል እንደሆነ ለክቶ ተገቢውን ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎቹ በተገነዘቡትና እንዲገነዘቡት በሚጠበቀው ትምህርታዊ መረጃ መካከል ያለውን ክፍተት የመሙላት ተግባር እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡ ጽብረቃ በአንድ ትምህርታዊ ክንውን ላይ ያለን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ በማውጣት ጠንካራ ጎኑ የበለጠ የሚጠናከርበትን፣ ደካማ ጎኑ ደግሞ የሚሻሻልበት መንገድ የሚታቀድበት ሂደት ነው፡፡ በእለታዊ የትምህርት እቅዱ ላይ የጽብረቃ ተግባር አለመቀመጡ መምህራኑ በትምህርቱ ሂደት የነበረውን ጠንካራና ደካማ ጎን ፈትሸው ቀጣዩን የመማር ማስተማር ሂደት ለማሻሻል የሚያስችሉ ተግባራትን አለማከናወናቸውን ያሳያል፡፡ ጽብረቃ የእድሜ ልክ ትምህርት የሚቀሰምበት ከመሆኑ አንጻር በክንውኑ ሂደት ከነበረው ስህተት በመማር በቀጣዩ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ የማይከናወንና መምህራኑ ከሚሰሩት ስራ የእድሜ ልክ ትምህርት የሚያገኙበት ሁኔታ የደከመ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ተመሳሳይ የአተገባበር ችግሮች እንዳይታረሙና በዘላቂነት እየተከሰቱ የትምህርቱን ሂደት የሚያሰናክሉ እንቅፋቶች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

4.1.2. የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር

4.1.2.1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ

ፅ. የተማሪዎች በይነሰባዊ ፍላጎት

በይነሰባዊ ፍላጎት በማህበራዊ መስተጋብር ሂደት በሰዎች መካከል ለሚኖረው የእርስ በእርስ ግንኙነት መሟላት የሚገባው መሰረታዊ ፍላጎት ሲሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊዎች መካከል የሚኖር ውጤታማ የሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር መገለጫ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው (Wrench et al., 2009)፡፡ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ይቻል ዘንድ በተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ተግባራት መከናወናቸውን የተመለከቱ ሶስት ተግባራት ተካትተዋል (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ የነዚህን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 15 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 15፡ የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝሙት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
cri1 1	36	3	2.8144	1.00337	-.121	-.119	2.3300	3.0000	3.3300
cri1 6	36	3	1.9717	.44608	-.069	-.230	1.6700	2.0000	2.3300
cri1 14	36	3	2.1758	.40966	.035	1.933	2.0000	2.0000	2.3300
Total	36	9	6.9619	1.55267	-.246	-.352	5.9925	7.3300	7.9175

በበይነሰባዊ ፍላጎት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን ትኩረት የማግኘት ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን የተመለከተ (Cri1 1) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ትኩረት ማግኘት ከተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከል አንዱ ሲሆን መሟላቱ ተማሪዎቹ እርስ በእርስም ሆነ ከመምህራን ጋር የሚኖራቸው ማህበራዊ ግንኙነት ጥሩ እንዲሆንና በነጻነት ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በሰንጠረዥ 15 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.8144 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=1.200337 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.121 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው ባላይ በሚገኙት ምድቦች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ማእከል አድርጎ ለወስከምባይነት የተጠጋ መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.119 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ለወስከምባይነት የቀረበ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.33፣ 3.00ና 3.33 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ የመጀመሪያውና ሁለተኛው የመቁረጫ ነጥቦች አተገባበሩ ለሚጠበቀው የቀረበ መሆኑን ቢያሳይም ሶስተኛው የመቁረጫ ነጥብ በምልከታ በተገኘው አሰረጫጨት ላይ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። ስለዚህም በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹ ትኩረት የማግኘት ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት ክንውን ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህም ከተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከል አንዱ እንዳይሟላ ያደርጋል። አለመሟላቱ ተማሪዎቹ ለሌሎች ያላቸውን የጓደኝነት ስሜት መግለጽ፤ ለሌሎች እንደሚጨነቁ ማሳየት እንዲሁም ከሌሎች ትኩረትንና እንክብካቤን ማግኘት እንዳይችሉ ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂደት የእርስ በእርስ ግንኙነት የመመስረት ልምድን እንዳያዳብሩ ስለሚያደርጋቸው በክፍል ውስጥ በሚከናወነው መስተጋብር ላይ በነጻነት ለመሳተፍ ይቸገራሉ።

በበይነሰባዊ ፍላጎት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የአካቶ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን የተመለከተ (Cri1 6) ነው (አባሪ 3ና 4ንን ይመልከቱ)። የአካቶ ፍላጎት በአንድ በተወሰነ ቡድን የመካተት፣ በዚያ ቡድን ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ የመገኘትና የዚያ ቡድን አባልነትን የማረጋገጥ ፍላጎት ነው። መሟላቱ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚከናወን መስተጋብር ንቁ ተሳታፊ በመሆን ትምህርታዊ መረጃን እንዲጋሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በሰንጠረዥ 15 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.9717 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.44608 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። አብዛኞቹ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ -0.069 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ በምልከታ የተገኘውን መረጃ አማካይ ማእከል አድርጎ ለወሰከምባይነት በመጠኑ የተጠጋ መሆኑን ያሳያል። ማለትም ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ አለው። ዝብጠቱ -0.230 ሲሆን በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 1.67፣ 2.00ና 2.33 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታ የመቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይበት

መሆኑን መረዳት ይቻላል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ሁኔታው በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የአካቶ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት ክንውን ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል። አለመሟላቱ የተማሪዎቹ የአካቶ ፍላጎት እንዳይሟላ የሚያደርግ ሲሆን ተማሪዎቹ የአንድ ቡድን አባል በመሆን ለሌሎች ድጋፍ ማድረግና በአንድ ቡድን ውስጥ በመካተት ከቡድኑ አባላት እውቅናን፣ ፍቅርን፣ ማህበራዊ ግንኙነትንና ድጋፍን ማግኘት እንዳይችሉ ያደርጋል። ይህም በተማሪዎቹ መካከል በሚኖረው እርስ በእርስ የመደጋገፍና እውቀትን በጋራ የመገንባት ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

በበይነሰባዊ ፍላጎት ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጨረሻው የተማሪዎቹን የቁጥጥር ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት ክንውንን የተመለከተ (Cri1 14) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ተማሪዎች የቁጥጥር ፍላጎት ስላላቸው በአካባቢያቸው የሚከናወነውን ሁኔታ መቆጣጠርና ተጽእኖ ማሳደር እንዲሁም ተገቢ የሆነ አቅጣጫ የሚያሲዝ ቁጥጥር እንደረግባቸው ይፈልጋሉ። በሰንጠረዥ 15 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.1758 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.40966 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም በርከት ያሉ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ 0.035 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ማእከል አድርጎ አሰረጫጨቱ ለወስከምባይነት የቀረበ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ በተለያየ መጠን ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ አለው። ዝብጠቱ 1.933 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ለአማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 2.00ና 3.33 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ የመቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩንም ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ

የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የቁጥጥር ፍላጎት የሚያሟሉ ተግባራት ክንውን ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህ ሁኔታ የቁጥጥር ፍላጎታቸው እንዳይሟላ የሚያደርግ ሲሆን ተማሪዎች ለስነምግባር ችግር እንዲጋለጡ፣ የውሳኔ ሰጭነት ሚናን እንዳይጫወቱ፣ ህግን በራሳቸው የማክበር ሀላፊነትን እንዳይወስዱና በአካባቢያቸው ላይ ተጽእኖ ማሳደር እንዳይችሉ ያደርጋል።

በጥቅሉ የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራትን የክንውን ሁኔታ ለማወቅ አተገባበራቸውን የሚያሳዩትን መረጃዎች በድምር ማስላት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 15 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የበይነ ሰባዊ ፍላጎት ዘርፍን የክንውን ሁኔታ በድምር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 6.9619 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 9.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሬ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=1.55267 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ዝመቱ -0.246 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ማእከል አድርጎ አሰረጫጨቱ ለወስከምባይነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.352 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 5.9925፣ 7.3300ና 7.9175 ናቸው። መደበኛ አሰረጫጨት 6፣ 9ና 12 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ሰንጠረዥ 16፡ የተማሪዎቹን በይነ ሰባዊ ፍላጎት መሟላት የሚያስችሉ ተግባራትን የክንውን ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 9						Cohen's d effect size
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence Interval		
					Lower	Upper	
observed interpersonal needs of students	-7.876	35	.000	-2.03806	-2.5634	-1.5127	-2.6259

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም በበይነሰባዊ ፍላጎት ዘርፍ የተዳሰሱ ተግባራትን የክንውን ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 16ን ይመልከቱ)። በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-7.876, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -7.876 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-2.03806 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-2.6259 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል።

ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹ በይነሰባዊ ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት ክንውን ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህም የመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት የሚያሟላ እንዳይሆን ያደርጋል። የሚያሟላ አለመሆኑ ተማሪዎች የትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑ፣ በነጻነት ከሌሎች ጋር መረጃን መጋራት እንዳይችሉ፣ ለስነምግባር ችግር እንዲጋለጡ፣ የውሳኔ ሰጭነት ሚናን እንዳይጫወቱ፣ ህግን በራሳቸው የማክበር ሀላፊነትን እንዳይወስዱና በአካባቢያቸው ላይ ተጽእኖ ማሳደር እንዳይችሉ ያደርጋል።

፪. የክፍል አያያዝ

የክፍል አያያዝ በመማር ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ ያለውን አደረጃጀት ደርዝ የሚያሲይዙበት መንገድ ነው። ይህንን ዘርፍ የተመለከቱ ሶስት ተግባራት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የምልከታ ቅጽ ተካትተዋል። የአተገባበራቸውን ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 17 ቀርቧል።

በክፍል አያያዝ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው የተማሪዎቹ አቀማመጥ በክፍል ውስጥ ለሚከናወን ትምህርታዊ መስተጋብር ምቹ መሆኑን የተመለከተ (Cri1 3) ነው (አባሪ 3ና 4ን

ይመልከቱ)፡፡ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት በተሳታፊዎች መካከል የሚኖረውን የተግባቦት ሁኔታ ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ የተማሪዎች አቀማመጥ ሲሆን የሚደራጀው በመምህራን አማካኝነት ነው፡፡ በሰንጠረዥ 17 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የተማሪዎቹ አቀማመጥ በክፍል ውስጥ ለሚከናወን ትምህርታዊ መስተጋብር ምቹ መሆኑን የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.7958 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ ያነሰ ነው፡፡ ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች መጎዳኘታቸውን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=0.86991 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል፡፡ ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 17፡ የክፍል አደያዘን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
cri1 3	36	3	2.7958	.86991	.200	.082	2.3300	2.6700	3.3300
cri1 5	36	3	2.0744	.60187	-.045	-.389	1.6700	2.0000	2.5850
cri1 7	36	3	1.5097	.53232	1.870	6.443	1.0000	1.5000	1.6700
Total	36	9	6.3800	1.68886	.401	.372	5.3325	6.3300	7.2475

ዝመቱ 0.200 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጥቂቱ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ማእከል አድርጎ ለወስከምባይነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል፡፡ ማለትም ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ባልተመጣጠነ ሁኔታ የመረጃዎቹ ጉድኝት እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን ደካማ አተገባበር በሚያሳየውና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተቀኝ ያለው የመረጃ ጉድኝት አመዝኖ ይታያል ያሳያል፡፡ ዝብጠቱ 0.082 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ለአማካያቸው የቀረበ ጉድኝት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.33፣ 2.67ና 3.33 ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ የመጀመሪያው መቁረጫ ላይ በምልከታ የተገኘው ቢበልጥም ሁለተኛውና ሶስተኛው መቁረጫ ነጥቦች ግን ከሚጠበቀው ያነሱ ናቸው፡፡ ማነሳቸው በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይበት መሆኑን ለማወቅ ያስችላል፡፡ ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት አለ፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት

ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ይህ ደግሞ የተማሪዎቹ አቀማመጥ በክፍል ውስጥ ለሚከናወን የመማር ማስተማር ሂደት ምቹ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ይህም የተማሪዎቹ አቀማመጥ ትምህርታዊ መስተጋብሩ ለመምህር ተማሪና ለተማሪ ተማሪ መስተጋብር ምቹ በመሆኑ ረገድ ውስንነት ያለበት እንዲሆን ያደርገዋል።

በክፍል አያያዝ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ምቹ የሆነ የክፍል አያያዝ ዘይቤን የሚጠቀሙ መሆኑን የተመለከተ (Cri1 5) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ጥሩ የትምህርት ድባብ እንዲኖር በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች ዘንድ ውጤታማ የሆነ ግንኙነት መመስረት የሚያስችል የክፍል አያያዝ ዘይቤ በጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል። በሰንጠረዥ 17 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 2.0744 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.60187 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየደረጃዊ ልኬቶቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.045 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጥቂቱ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ማእከል አድርጎ በስተግራና በስተቀኝ ባልተመጣጠነ ሁኔታ እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ 2.00 ነው (አባሪ 10ን ይመልከቱ)። ዝብጠቱ -0.389 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በመጠኑ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የመቁረጫ ነጥቦች 1.67፣ 2.00ና 2.585 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። በምልከታ የተገኘውና የሚጠበቀው የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች በቀረበው ትንታኔ ላይ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ ምቹ የሆነ የክፍል አያያዝ ዘይቤን መጠቀማቸው ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ደካማ መሆኑ መምህራኑ ዲሞክራሲያዊ የክፍል

አያያዝ ዘይቤን የማይጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩን ያመላክታል፡፡ ይህ ደግሞ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል ነጻ ሆነ የሀሳብ ልውውጥ እንዳይኖር ለሚያደርግ ችግር ይዳርጋል፡፡ ተማሪዎች የጋራ ስራን እንዳይቀበሉ፣ ሀላፊነትን እንዳይወስዱ፣ ከፍተኛ የሆነ እርስ በእርስ መማር ማስተማርን እንዳያከናውኑና ውጤት ላይ ለመድረስ የሚያስችል ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

በክፍል አያያዝ ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጨረሻው በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የስነምግባር ችግር ሲያሳዩ አወንታዊ የሆነ የማስተካከያ ርምጃ የሚወሰድ መሆኑን የመለከተ (Cri1 7) ነው (አባሪ 2ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ የስነምግባር ችግር በተማሪዎች ላይ የሚታይ የመማር ማስተማሩ ሂደትን የሚያውክ ባህሪ ሲሆን በተማሪዎች ላይ ሲታይ አወንታዊ የሆነ የማስተካከያ ርምጃ በጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ በሰንጠረዥ 17 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 1.5097 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል፡፡ ማነሱ መደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=0.53232 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል፡፡ መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ችምችም ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)፡፡

ዝመቱ 1.870 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ (1.00) በስተግራ ጠንካራ ወደሚያሳዩት ምድቦች በተለያየ መጠን ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዝብጠቱ 6.443 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ለአማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውን ያሳያል፡፡ ይህም ደካማ አተገባበርን በሚያሳዩት ምድቦች ላይ ንብርብር ያለ የመረጃ ጉድኝት እንዲኖር አድርጓል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)፡፡ የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 1.00፣ 1.50ና 1.60 ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ሁለቱ የመቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ያስገነዝባል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ የስነምግባር ችግር ሲያሳዩ አወንታዊ የማስተካከያ ርምጃ መወሰዱ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በተማሪዎች፣ በመምህራንና በትምህርት ድባቡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር የደህንነት ችግር እንዲከሰት ያደርጋል፡፡

አጠቃላይ የክፍል አያያዙን እንዴትነት ለማወቅ በስሩ የተዳሰሱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎችን በድምር ማስላት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 17 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የክፍል አያያዙን እንዴትነት በድምር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 6.38 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 9.00 ያንሳል። ማነሱ መደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=1.68886 ነው። ይህም የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል። ዝመቱ 0.401 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ 6.00 ማእከል አድርጎ አሰረጫጨቱ ለወስከምባይነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል። ማለትም ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ጠንካራና ደካማ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች በተለያየ መጠን ከፍታው እየቀነሰ የሜሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ዝብጠቱ 0.372 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ለአማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 5.3325፣ 6.33ና 7.2475 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 6፣ 9ና 12 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ለመረዳት ያስችላል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የክፍል አያያዙን እንዴትነት የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 18ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 18፡ የክፍል አያያዙን የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 9						Cohen's d effect size
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence Interval		
					Lower	Upper	
observed classroom management	-9.308	35	.000	-2.62000	-3.1914	-2.0486	-3.1027

በሰንጠረዥ 18 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-9.308, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -9.308 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-2.6200 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-3.1027 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚተገበረው የክፍል አያያዝ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ደካማ መሆኑ በክፍል አያያዝ ረገድ ምቹ የመማር ማስተማር ሂደት እንዳይኖር የሚያደርግ ችግር መኖሩን ያመለክታል።

፫. ትምህርታዊ መስተጋብር

ትምህርታዊ መስተጋብር የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች የፍቺ ምስረታን የሚያከናውኑበት የእርስ በእርስ መስተጋብር ሂደት ነው። በምልከታ ቅጹ ላይ ትምህርታዊ መስተጋብርን የተመለከቱ ሰባት ተግባራት ተካትተዋል። የአተገባበራቸውን ሁኔታ የሚያሳዩት መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 19 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 19፡ የመማር ማስተማር መስተጋብርን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
cri1 2	36	3	2.8986	.92209	-.940	-.187	2.3300	3.0000	3.6700
cri1 4	36	3	2.3519	.68134	-.421	-.603	2.0000	2.5000	3.0000
cri1 8	36	3	1.5092	.38662	.330	-.613	1.3300	1.5000	1.6700
cri1 10	36	3	1.0925	.20524	2.129	3.387	1.0000	1.0000	1.0000
cri1 13	36	3	2.3700	.72086	-.474	.010	2.0825	2.3300	3.0000
cri1 19	36	3	1.8331	.48825	-.145	-.792	1.3300	2.0000	2.2475
cri1 20	36	3	1.0464	.16294	3.528	11.598	1.0000	1.0000	1.0000
Total	36	21	13.1017	2.64828	-1.062	.078	12.0825	13.8300	15.0000

በትምህርታዊ መስተጋብር ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ስለሚደርሱበት ውጤት አወንታዊ ግምት እንዲኖራቸው የሚደረግ መሆኑን የተመለከተ (Cri1 2) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ይህ ተግባር በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑና በፍላጎት የሚማሩበት ጥሩ የትምህርት ድባብ እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 2.8986 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎላ ብሎ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.92209 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየደረጃዊ ልኬቶቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.940 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። ዝብጠቱ -0.187 በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው የተጎዳኙ መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የመቁረጫ ነጥቦች 2.33፣ 3.00ና 3.67 ናቸው። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ የመጀመሪያውና ሁለተኛው የመቁረጫ ነጥቦች ተቀራራቢ ቢሆኑም ሶስተኛው ላይ ልዩነት አለ። ማለትም ሶስተኛው የመቁረጫ ነጥብ ላይ በምልከታ የተገኘው ከሚጠበቀው አንሶ ይታያል። ማነሱ የአይነተኛ ውጤትና ሌሎች የልይይት መጠን ልኬታዎች ከሚያሳዩት ውጤት ጋር ተዳምሮ በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤት፣ በልይይት መጠን ልኬታዎችና በመረጃ ሰንጠረዥ እንደታየው በርከት ያሉ መረጃዎች ደካማ በሚያሳዩት ምድቦች ላይ በርከት ብለው በመጎዳኘታቸው ነው (አባሪ 10ን ይመልከቱ)። ስለዚህም ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት በስተመጨረሻ ስስሚደርሱበት ግብ አወንታዊ ግምት እንዲኖራቸው መደረጉ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህም ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ጠንካራ ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ስለሚያደርግ በአእምሯቸው ውስጥ በሚኖረው የማወቅ ፍላጎት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

በትምህርታዊ መስተጋብር ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሁለተኛው መምህራኑ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ከሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን የተመለከተ (Cri1 4) ነው (አባሪ 2ን ይመልከቱ)። ይህ ተግባር በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ የሚያከናውኑትን ተግባር በቅርበት በመከታተል መማር ማስተማር ሂደቱን የሚያደናቀፉ ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 2.3519 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው።

ማነሱ መደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.68134 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየደረጃዊ ልኬቶቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.421 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.603 ሲሆን በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ ርቀው መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 2.50ና 3.00 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ያስገነዝባል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም መምህራኑ በክፍል ውስጥ ተማሪዎቹ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህም ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በሚያከናውኗቸው ተግባራት አማካኝነት ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት መከናወኑንና የክፍል ውስጥ ስነምግባር መጠበቁን ለችግር የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል።

በትምህርታዊ መስተጋብር ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል ሶስተኛው የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ መራሽ መሆኑን የተመለከተ (Cri1 8) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ተማሪ መራሽ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ምንን እንዴትና ለምን እንደሚማሩ እንዲያውቁና ኃላፊነትን እንዲጋሩ ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ መራሽ መሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 1.5092 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አንጻር የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.38662 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይ አሰረጫጨት በተለየ መጠን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 11ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ 0.330 ሲሆን በርከት ያሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ (በምልከታ የተገኘውን አማካይ) ማእከል አድርጎ

ወደ ወስከምባይነት የተጠጋ መሆኑን ያሳያል። ማለትም ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ጠንካራና ደካማ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ያልተመጣጠነው ከአማካዩ በታች ያለው የመረጃ ጉድኝት በዛ ብሎ የሚታይ በመሆኑ ነው። ዝብጠቱ -0.613 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ እያሻቀበ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ የመቁረጫ ነጥቦች 1.33፣ 1.50ና 1.67 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00. 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ መራሽ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ይህም ተማሪዎቹ ሀላፊነትን የሚጋሩበት፣ የሚሳተፉበትና በራሳቸው ችግር ፈቺ የሆኑ ተግባራትን የሚያከናውኑበት የመማር ማስተማር ሂደት የመከናወኑ ሁኔታ የደከመ እንዲሆን ያደርጋል። የክፍል ውስጥ መስተጋብሩንም ተማሪዎች ፍዝ ተቀባይ የሆኑበትና መምህራን ፈጣሪ ያልሆኑበት እንዲሆን ያደርገዋል።

አራተኛው ተግባር የመማር ማስተማሩ ሂደት ምልልሳዊ መስተጋብር የሚከናወንበት መሆኑን የተመለከተ (Cri1 10) ነው (አባሪ 3ና4ን ይመልከቱ)። ምልልሳዊ መስተጋብር በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል ጥሩ የሆነ የሀሳብ ልውውጥና የመረጃ ግብይት እንዲኖር ስለሚያደርግ ውጤታማ መማር ማስተማር ለማከናወን ያስችላል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 1.0925 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.20524 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። ማለትም በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ችምችም ብለው ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 2.129 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ (1.00) በስተግራ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች በጣም ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ

3.387 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ለአማካያቸው በጣም ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች ሙሉ በሙሉ 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው። ይ ነጥብ በጣም ደካማ አተገባበርን የሚያሳይ ምድብ ሲሆን በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን መረዳት ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ ለማየት እንደተሞከረው በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በመጎዳኘታቸው ነው። ስለዚህም የመማር ማስተማሩ ሂደት ምልልሳዊ መስተጋብር የሚከናወንበት መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይበት ነው። ይህም የመማር ማስተማሩ ሂደት ተራ መስተጋብር ጎልቶ የሚታይበት መሆኑን ያሳያል። ክስተቱ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ መረጃ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሳይሆን በአንድ አቅጣጫ የሚፈስበት፣ በክፍል ውስጥ የተጋጋለ የሀሳብ ልውውጥ የማይከናወንበት፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በሀሳብ ልውውጥ የጋራ የሆነ የሀሳብ ተረዳድቶ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ ተግባራትን የማያከናውኑበት ሁኔታ የሚታይበት መሆኑን ያስገነዝባል።

አምስተኛው ተግባር በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎቹ መካከል ላለ ልዩነት ምላሽ መስጠት የሚያስችል ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን የተመለከተ (Cri1 13) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ይህ ተግባር ሁሉም ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 2.37 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.72086 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየደረጃዊ ልኬቶቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ -0.474 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ 0.010 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ወደ አማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.08፣ 2.33ና 3.00 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ

ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች በቀረበው ትንታኔ ላይ ለማየት እንደተሞከረው ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በተማሪዎቹ መካከል ላለ ልዩነት ምላሽ መስጠት የሚያስችል ድጋፍ መደረጉ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ደካማ መሆኑ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በሚደረግ ድጋፍ የትምህርት ፍትሀዊነትን የማረጋገጡ ሁኔታ አደጋ የተጋረጠበት መሆኑን ያሳያል።

ስድስተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹ ትኩረትና ትጋት ሙሉ በሙሉ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ላይ መሆኑን የተመለከተ (Cri1 19) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ይህ ተግባር ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርታዊ ተግባር በጥሩ ተነሳሽነት እንዲያከናውኑ ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.8331 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.48825 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ -0.145 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ የተገኘውን አማካይ ማእከል አድርጎ ለወስከምባይነት የቀረበ መሆኑን ያመለክታል። ማለትም ከተገኘው አማካይ በስተግራና በስተቀኝ ጠንካራና ደካማ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ከፍታው ደረጃ በደረጃ እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.792 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 1.33፣ 2.00ና 2.2475 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩንም ያስገነዝባል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት

ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹ ትኩረትና ትጋት ሙሉ በሙሉ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ላይ መሆኑ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል። ይህም ተማሪዎቹ በሚከናወነው የክፍል ወስጥ መስተጋብር አእምሯቸውን ሙሉ በሙሉ አሰባስበው ንቁ ተሳታፊ በመሆን እውቀት የሚገነቡበት መንገድ መሰናክል ያለበት መሆኑን ያሳያል።

የመጨረሻው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት ተገቢ የሆኑ የማበረታቻ ስልቶች በጥቅም ላይ መዋላቸውን የተመለከተ (Cri1 20) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ማበረታታት ተማሪዎች ከአካባቢያቸው የሚያገኙትን አንድ ተግባር በተደጋጋሚ እንዲተገብሩት ወይም እንዳይተገብሩት የሚያርግ መቀስቀስ ሲሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ለትምህርቱ የሚኖራቸውን ተነሳሽነት ለመጨመር ያስችላል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.0464 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱንና የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሬ መሆኑን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ 0.16294 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። በርካታ መረጃዎች በጣም ደካማ በሚያሳየው ምድብ ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ 3.528 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ከፍታው በጣም እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 11.598 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ወደ አማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስኪደርስ ከፍታው በጥቂቱ እየጨመረ የሚሄድ የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የመቁረጫ ነጥቦች ሙሉ በሙሉ በጣም 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00፣ 3.00ና 4.00 ላይ እንዲያርፉ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ተገቢ የሆኑ የማበረታቻ ስልቶች በጥቅም ላይ መዋላቸው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ደካማ መሆኑ በተማሪዎቹ ዘንድ የተፎካካሪነትና የተነሳሽነት ስሜት እንዲፈጠር ስለማያደርግ በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ የስኬት መሰረት የሆነው ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዳይዳብር ምክንያት

ይሆናል። የሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ራሱ ለተግባራዊ ርምጃ እንዳይቀሰቅሳቸው እንዲሁም ከውስጥ የመነጨ የስኬታማነትና የብቁነት ፍላጎትም እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ይህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

የትምህርታዊ መስተጋብሩ ጥቅል አተገባበር ምን እንደሚመስል ለማወቅ በስሩ የተካተቱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች በድምር መታየት ይኖርባቸዋል። በሰንጠረዥ 19 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የትምህርታዊ መስተጋብሩን እንደኅትነት በድምር የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 13.1017 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 21.00 ያነሰ ነው። በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱንና የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሬ መሆኑን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ 2.64828 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው በተለየ መጠን በተለያዩ ምድቦች ተጎዳኝተዋል። ዝመቱ -1.062 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል። ዝብጠቱ 0.078 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ወደ አማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 12.0825፣ 13.83ና 15.00 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 14፣ 21ና 28 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። ስለዚህም በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የትምህርታዊ መስተጋብሩን እንደኅትነት የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 20ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 20፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለውን ትምህርታዊ መስተጋብር የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቴስት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 21						Cohen's d effect size
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence Interval		
					Lower	Upper	
observed teaching learning interaction	-17.895	35	.000	-7.8983	-8.7944	-7.0023	-5.9649

በሰንጠረዥ 20 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-17.895, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -17.895 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-7.8983 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-5.9649 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ይህም ትምህርታዊ መስተጋብሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ደካማ መሆኑ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን በጥሩ ሁኔታ እንዳያከናውኑ ያደርጋል። አለማከናወናቸው ደግሞ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቀውን ውጤት እንዳያስመዘግብ እንቅፋት ይሆናል።

፬. የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር

የመማር ማስተማር ስልት የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች የሚለወጡበት፣ እውቀትን የሚገነቡበት፤ የባህሪ ለውጥ የሚያመጡበት፣ መረጃን የሚገበያዩበትና አዲስ ክህሎትን የሚያዳብሩበት ብልሀት ነው። ይህ ብልሀት የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን እንዴትነት ለማወቅ ከተዳሰሱት ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን በስሩ ሰባት ተግባራትን ይዟል። የነዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 21 ቀርቧል።

በመማር ማስተማር ዘዴዎች አተገባበር ዘርፍ ከተዳሰሱት ተግባራት መካከል የመጀመሪያው በመማር ማስተማሩ ሂደት የንቁ መማር ማስተማር ዘዴዎች በጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑን የተመለከተ (Cri1 9) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ንቁ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ተማሪዎች የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑና ስለሚያከናውኑት ተግባር እንዲያስቡ የሚያደርጉ የትምህርት አቀራብ ዘዴዎች ናቸው። በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.6294 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱንና የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን ያሳያል። መደበኛ

ልይይቱ s=0.45653 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን ከሚጠበቀው አማካይ በታች ባሉት ምድቦች ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 21፡ የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበርን የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ሰሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
cri1 9	36	3	1.6294	.45653	.209	-.755	1.3300	1.6700	2.0000
cri1 11	36	3	1.2214	.23932	.629	-.739	1.0000	1.3300	1.3300
cri1 12	36	3	1.8986	.29564	.135	.446	1.6700	2.0000	2.0000
cri1 15	36	3	1.0183	.07666	4.051	15.260	1.0000	1.0000	1.0000
cri1 16	36	3	1.0458	.11574	2.180	2.913	1.0000	1.0000	1.0000
cri1 17	36	3	1.8706	.55878	.158	-.624	1.6700	1.6700	2.3300
cri1 18	36	3	1.8981	.72562	.772	.171	1.3300	1.6700	2.3300
Total	36	21	10.5822	1.37465	.359	.548	9.6700	10.3350	11.5800

ዝመቱ 0.209 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኝታቸውንና አሰረጫጨቱ በምልከታ የተገኘውን አማካይ ማእከል አድርጎ ወደ ወስከምባይነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት በስተግራና በስተቀኝ ጠንካራና ደካማ አተገባርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ ያለው ሲሆን የመረጃ ጉድኝቱ ደካማ አተገባበር በሚታይባቸው በስተቀኝ ባሉት ምድቦች አመዝኖ ይታያል። ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ደግሞ ከፍታው በጣም እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ አለው። ዝብጠቱ -0.755 ሲሆን በርከት ያሉ መረጃዎቹ ከአማካዩ ርቀው መጎዳኝታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 1.33፣ 1.67ና 2.00 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው ከፍ ሲል በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት የንቁ መማር ማስተማር ዘዴዎች በጥቅም ላይ

መዋላቸው ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያመለክታል። ደካማነቱ ዘዴዎቹን በጥቅም ላይ ቢውሉ ተማሪዎቹ ሊያዳብሩ የሚችሉት አሰራር፣ እውቀትና ክህሎት እንዳይዳብር ያደርጋል።

ሁለተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባር ተኮር የትምህርት አቀራረብ መከናወኑን የተመለከተ ነው (cri1 11)። ተግባር ተኮር ትምህርት ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርታዊ ተግባር እያከናወኑ እንዲማሩ ለማድረግ የሚያስችል የትምህርት አቀራብ ነው። አቀራረቡ ትምህርቱ እንዲገባቸው፣ እንዲጠቀሙበት፣ ሀሳብ እንዲያፈልቁና እንዲግባቡበት ለማድረግ ያስችላል። በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባር ተኮር የትምህርት አቀራረብ መከናወናወኑን የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.2214 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱንና የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን ያሳያል። መደበኛ ልይይቱ s=0.23932 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወሰከምባይነት በተለየ መጠን ከሚጠበቀው አማካይ በታች ባሉትና ደካማ አተገባርን በሚያሳዩት ምድቦች ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል። በርካታ የመረጃ ጉድኝት ያለው በጣም ደካማ አተገባርን በሚያሳየው ምድብ ላይ ነው (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ 0.629 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ከፍታው እየቀነሰና እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ -0.739 ሲሆን በርካታ መረጃዎች ከአማካዩ ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ አስከሚደርስ ድረስ ከግራ ወደ ቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 1.00፣ 1.33ና 1.33 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። ስለዚህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት አለ። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባር ተኮር የትምህርት አቀራረብ የመተግበሩ ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ይህም የትምህርት አቀራረቡ የተማሩትን ትምህርት በነባራዊው አለም እንዲተገብሩ በር የሚከፍት በመሆኑ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

ሶስተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት ልይይታዊ መማር ማስተማር በጥቅም ላይ መዋሉን የተመለከተ (Cri1 12) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ባህላዊ ዳራዎችን፣ የመማር ስልቶችን፣ ፍላቶጎችን፣ ችሎታዎችንና የትምህርት አቀባበል ችሎታዎችን ይዘው ወደ መማሪያ ክፍል ይመጣሉ፡፡ የሚሰጠው ትምህርት የእነዚህን ተማሪዎች ፍላጎት እንዲያሟላ ልይይታዊ መማር ማስተማር በጥቅም ላይ ሊውል ይገባል፡፡ በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 1.8986 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 የሚያንስ ሲሆን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱንና የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን ያሳያል፡ ፡ መደበኛ ልይይቱ s=0.29564 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች ባሉት ምድቦች ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)፡፡

ዝመቱ 0.135 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ማእከል አድርጎ አሰረጫጨቱ ወደ ወስከምባይነት የተጠጋ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለው 2.00 ነው (አባሪ 10ን ይመልከቱ)፡፡ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ከዚህ ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ጠንካራና ደካማ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ አለው፡፡ ያልተመጣጠነ ያሰኘው ደካማ አተገባበርን በሚያሳዩት ምድቦች ያለው የመረጃ ጉድኝት ብዙ መሆኑ ነው፡፡ ዝብጠቱ 0.446 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች ወደ አማካዩ ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 1.67፣ 2.00ና 2.00 ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ልይይታዊ መማር ማስተማር በጥቅም ላይ የመዋሉ ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸውና እንደየችሎታቸው ትምህርት እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

አራተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት ባለብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራት (Multi-level activities) በጥቅም ላይ መዋላቸውን የተመለከተ (Cri1 15) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)፡፡

የመማሪያ ክፍል የተለያየ ፍላጎትና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ያሉበት ነው። የነዚህን ተማሪዎች ፍላጎት መዳሰስ ይቻል ዘንድ ባለ ብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራት በጥቅም ላይ እንዲውሉ ይጠበቃል። በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት ባለብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራት በጥቅም ላይ መዋላቸውን የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.0183 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ሲሆን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሬ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ s=0.07666 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያሳያል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በጣም ደካማ አተገባርን በሚያሳየው ምድብ ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ 4.051 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት በስተቀኝ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ከፍታው በጣም እየመነመነ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ዝብጠቱ 15.260 ሲሆን በምልከታ የተገኙት መረጃዎች በከፍተኛ ሁኔታ ወደ አይነተኛ ውጤት ልኬታቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ከግራ ወደ ቀኝ ከፍታው በጥቂቱ እየጨመረ የሚሄድ በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በጣም በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ባለ ብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራት በጥቅም ላይ የመዋላቸው ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ ነው። ይህም በተማሪዎች መካከል ያለ ልዩነትን ለመዳሰስ የሚያስችል የትምህርት አሰጣጥ የማይከናወን መሆኑን ያሳያል።

አምስተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት ባለብዙ ደረጃ የመማር ማስተማር ማእከላት (Multi-level Learning Centers) በጥቅም ላይ መዋላቸውን የተመለከተ (Cri1 16) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። ባለብዙ ደረጃ የትምህርት ተግባራት ተማሪዎችን በመካከላቸው ባለው ልዩነት፣ ዳራዊ እውቀት፣ ፍላጎትና የትምህርት ግለ ታሪክ ላይ ተመስርቶ በማደራጀት ትምህርታዊ ተግባራትን በጋራ እንዲያከናውኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ቡድኖች ናቸው። በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.04558 ነው። ይህ ነጥብ

በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያነሰ ነው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=0.11574 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን ከአማካዩ በታች ባለውና በጣም ደካማ አተገባበርን በሚያሳየው ምድብ ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል (አባሪ 10ን ይመልከቱ)፡፡

ዝመቱ 2.180 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኝታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ምድብ በስተግራ ጠንካራ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ዝብጠቱ 2.913 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በጣም በርካታ መረጃዎች ወደ አማካያቸው በጣም ቀርበው መጎዳኝታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራ ጠንካራ አተገባርን በሚያሳዩት ምድቦች በጣም የመነመነ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታ መቁረጫ ነጥቦች ሙሉ በሙሉ 1.00 ላይ ያረፉ ናቸው፡፡ ይህ ነጥብ በጣም ደካማ አተገባበርን የሚያሳይ ምድብ ነው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ሁለቱ የመቁረጫ ነጥቦች በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ያስገነዝባል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በጣም በርካታ መረጃዎች በመጎዳኝታቸው ነው፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ባለብዙ የመማር ማስተማር ማእከላት በጥቅም ላይ የመዋላቸው ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው፡፡ ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት በተማሪዎቹ መካከል ያለውን ልዩነት ለመዳሰስ የሚያስችል የትምህርት አሰጣጥ በጥቅም ላይ የመዋሉ ሁኔታ የደከመ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስድስተኛው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ችግር ፈቺ ተግባራትን ማከናወናቸውን የተመለከተ (Cri1 17) ነው፡፡ ችግር ፈቺ መማር ማስተማር ተማሪዎች ውስብስብ የሆኑ የነባራዊው አለም ችግሮችን እየፈቱ አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦችን የሚገነዘቡበትና የትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የሚደረግበት የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.8706 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 የሚያንስ ሲሆን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ መደበኛ ልይይቱ 0.55878 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ ሰባዛ መሆኑን

ያሳያል። ማለትም መረጃዎቹ ተቀራራቢ በሆኑ ምድቦች ላይ ስብስብ ብለው ተጎዳኝተዋል። የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ አብዛኞቹ መረጃዎች ከሚጠበቀው አማካይ በታች የተጎዳኙ ናቸው (አባሪ 10ን ይመልከቱ)።

ዝመቱ 0.158 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ማእከል አድርጎ የመረጃዎቹ አሰረጫጨት ወደ ወስከምባይነት የተጠጋ መሆኑን ያሳያል። አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ጠንካራና ደካማ አተገባበርን ወደሚያሳዩት ምድቦች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ አለው። ዝብጠቱ -0.624 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው ርቀው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ደረጃ በደረጃ እያሻቀበ የሚሄድ ደላዳላ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያመለክታል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች በ1.67፣ 1.67ና 2.33 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00፣ 3.00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለመገንዛብ ያስችላል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። መረጃው በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ችግር ፈቺ ተግባራትን እንዲያከናውኑ መደረጉ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ይህም ተማሪዎቹ ችግር የመፍታት ችሎታን እንዳያዳብሩ ያደርጋል።

የመጨረሻው ተግባር በመማር ማስተማሩ ሂደት ልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ የሚከናወን መሆኑን የተመለከተ (Cri1 18) ነው (አባሪ 3ና 4ን ይመልከቱ)። የመማር ማስተማሩ ሂደት በመሰረተ ማህራዊ ግንባታውያን ዝንቅ የትምህርት ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን ልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ የሚከናወንበት እንዲሆን ይጠበቃል። በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የዚህን ተግባር አተገባበር የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 1.8981 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 3.00 ያንሳል። ማነሱ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ 0.72562 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል። ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል።

ዝመቱ 0.772 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያመለክታል። ዝብጠቱ 0.171 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ወደ አማካያቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡ ፡ ያልተመጣጠነ የተባለበት ምክንያት ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስቀተኝ ደካማ አተገባርን በሚያሳዩት ምድቦች ያለው የመረጃ ጉድኝት ብዙ በመሆኑ ነው። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 1.33፣ 1.67ና 2.33 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 2.00፣ 3፣00ና 4.00 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩንም ያሳውቃል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ መረጃዎች በመጎዳኘታቸው ነው። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ በጥቅም ላይ የመዋሉ ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑንና ተማሪዎቹ ከልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ ሊያገኙ የሚችሉትን ክህሎት የሚያዳብሩበት ሁኔታ የደከመ መሆኑን ያመለክታል።

የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበርን ጥቅል እንዴትነት ለማወቅ በስሩ የተካተቱትን ተግባራት አተገባበር የሚያሳዩ መረጃዎችን በድምር ማየት ያስፈልጋል። በሰንጠረዥ 21 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የመማር ማስተማር ዘዴዎች አተገባበር እንዴትነትን የሚያሳዩ መረጃዎች አማካይ 10.5822 ነው። ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 21.00 የሚያንስ ሲሆን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑንና ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። መደበኛ ልይይቱ 1.337465 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል ማለት ነው።

ዝመቱ 0.359 በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ከአማካያቸው በታች መጎዳኘታቸውንና አሰረጫጨቱ ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበትን ነጥብ ወይም አማካዩን ማእከል አድርጎ ለወስከምባይነት የቀረበ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ካለበት ነጥብ በስተግራና በስተቀኝ ደረጃ በደረጃ ከፍታው እየቀነሰ የሚሄድ ዝቅታ አለው። ዝብጠቱ 0.548 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርካታ መረጃዎች ወደ አይነተኛ ውጤታቸው ቀርበው መጎዳኘታቸውንና ከፍተኛ የመረጃ ጉድኝት ያለበት ነጥብ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በስተግራና በስተቀኝ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ዝቅታ ያለው መሆኑን ያሳያል። በምልከታ የተገኙት መረጃዎች

የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች የመቁረጫ ነጥቦች 9.67፣ 10.335ና 11.58 ናቸው። በመደበኛ አሰረጫጨት 14፣ 21ና 28 እንዲሆኑ ይጠበቃል። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል። በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ያስገነዝባል።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የመማር ማስተማር ዘዴዎች አተገባበር እንዴትነትን የሚያሳዩ መረጃዎች የስታቲስቲካዊ ተዛምዶ ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 22ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 22፡ የመማር ማስተማር ስልቶችን የአተገባበር ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 21						Cohen's d effect size
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence Interval		
					Lower	Upper	
observed implementation of teaching teachniques	-45.471	35	.000	-10.41778	-10.8829	-9.9527	-15.1570

በሰንጠረዥ 22 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-45.471, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -45.471 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-10.41778 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-15.1570 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የመማር ማስተማር ዘዴዎች አተገባበር ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ደካማ መሆኑ ተማሪዎቹ የተለያዩ

የመማር ማስተማር ስልቶች በጥቅም ላይ ሲውሉ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ሊያዳብሩ የሚችሉትን ክህሎት እንዳያዳብሩና ሊገነቡ የሚችሉትን እውቀት እንዳይገነቡ ያደርጋል፡፡

፮. የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ማጠቃለያ

የክፍል ውስጥ መስተጋብር መምህራንና ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተግባራትን በማከናወን እውቀትን የሚገነቡበት ማህበራዊ ተራክቦ ነው፡፡ ይህ ተራክቦ በማህበራዊ ግንባታውን የትምህርት ፍልስፍና እሳቤ የመማር መሰረት ሲሆን በሰዎች መካከል ቋንቋን ለመልመድ የሚያስችል የእርስ በእርስ ግንኙነት ይከናወንበታል፡፡ በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት በአራት ዘርፎች የተካተቱ ሀያ ተግባራት ያሉት የምልከታ ቅጽ ተዘጋጅቶ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የእነዚህ መረጃዎች ድምር ውጤት በገላጭ ስታቲስቲክስ ተሰልቶ በሰንጠረዥ 23 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 23፡ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን በጥቅል የሚያሳዩ መረጃዎች የገላጭ ስታቲስቲክስ ስሌት ውጤት

	ብዛት (N)	የሚጠበቅ አማካይ (expected mean)	የተገኘ አማካይ (observed Mean)	መደበኛ ልይይት (Std. Deviation)	ዝመት (Skewness)	ዝብጠት (Kurtosis)	ማእከላይ የሩብ ለኬታ (inter quartile range)		
							25	50	75
cri total	36	60	37.0258	6.55387	-.580	-.001	34.3325	37.6550	41.2400

በሰንጠረዥ 23 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን በጥቅል የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ 37.0258 ነው፡፡ ይህ ነጥብ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው 60.00 የሚያንስ ሲሆን በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱንና የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን ያሳያል፡፡ መደበኛ ልይይቱ s=6.55387 ሲሆን የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ማለትም መረጃዎቹ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው ወስከምባይነት በተለየ መጠን በየምድቦቹ ተጎዳኝተዋል፡፡ ዝመቱ -0.580 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአማካያቸው በላይ መጎዳኘታቸውን ያሳያል፡፡ ዝብጠቱ -0.001 ሲሆን በምልከታ የተገኙ በርከት ያሉ መረጃዎች ከአይነተኛ ውጤት ልኬታቸው ርቀው መጎዳኘታቸውን ያመለክታል፡፡ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የማእከላይ ሩብ ልኬታዎች መቁረጫ ነጥቦች 34.3325፣ 37.6550ና 41.2400 ናቸው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት 40፣ 60ና 80 እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች አሰረጫጨት ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታል፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከልም ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ያስችላል፡፡

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል። ውጤቱም የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን በጥቅል የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት በቀረበበት ሰንጠረዥ ቀርቧል (ሰንጠረዥ 24ን ይመልከቱ)።

ሰንጠረዥ 24፡ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን በጥቅል የሚያሳዩ መረጃዎች የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ውጤት

One-Sample Test

	Test Value = 60						Cohen's d effect size
	t	df	Sig. (2-tailed)	Mean Difference	95% Confidence Interval		
					Lower	Upper	
observed classroom interaction	-21.033	35	.000	-22.97417	-25.1917	-20.7567	-6.3160

በሰንጠረዥ 24 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት አለ (t=-21.033, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -21.033 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-22.97417 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-6.3160 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። መረጃው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል። በትምህርቱ ሂደት በተሳታፊዎቹ መካከል የሚደረገው የእርስ በእርስ መስተጋብር የደከመ መሆኑንም ያሳያል። መድከሙ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊዎች ጥሩ የፍቺ ምስረታና የእውቀት ግንባታ እንዳያከናውኑ እንቅፋት ይሆናል።

4.1.2.2. ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኘ መረጃ

የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች በአራት ዘርፎች ላይ ያጠነጠኑ ሲሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

፩. የተማሪዎች በይነሰባዊ ፍላጎት

ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑበትም የማይከናወኑበትም ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ አስችለዋል (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። ለተማሪዎች የሚሰጠው ትኩረት በአብዛኛው ለጥቂት ተማሪዎች ብቻ በሚሰጥ ትኩረት የተዋጠ ነው። በቡድን ስራ ሂደት ተማሪዎች በቡድን ውስጥ የመካተት እድል ቢገጥማቸውም የተካቶነትንም ሆነ የአካቶነትን ፍላጎት የሚያሟሉ ተግባራት ሲከናወኑ አልታዩም። በአብዛኛው ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉት፣ ተጽእኖ የሚያሳድሩትም ሆኑ በራሳቸው ተንቀሳቅሰው የተለያዩ ተግባራትን የማከናወን ሀላፊነትን የሚወጡት እውቅናን ያገኙ ጥቂት ተማሪዎች ናቸው። ይህ ደግሞ አብዛኞቹ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት በሚደራጁ በድኖች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የመሆን እድላቸው የጠበበ እንዲሆን፤ በዙሪያቸው ያለውን ነገር እንዳይቆጣጠሩ፤ ተገቢውን አቅጣጫ የሚያሲይዝ ቁጥጥር እንዳያገኙ እንዲሁም በአንድ በተወሰነ ቡድን በመካተት ለሌሎች ድጋፍ የማድረግና ተገቢውን ድጋፍ የማግኘት እድል እንዳያገኙ ያደርጋል። በክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ሂደት የተወሰኑ መምህራን ምንም አይነት አመራር የማይሰጡበት፣ ተማሪዎቹ ያለምንም መመሪያ በራሳቸው ትምህርታዊ ተግባራትን የሚያከናውኑበትና ሲቧደኑ በራሳቸው ፍላጎት የፈለጉትን ያህል ቁጥር ሆነው ቡድን የሚሰርቱበት ሁኔታ ይታያል።

በነዚህ የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎቹ እንደፈለጉ በክፍል ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፣ ያወራሉ፣ ከተሰጣቸው ትምህርታዊ ተግባር ውጪ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ፣ ይደባደባሉ፣ ወደ ውጪ ያያሉ፣ ረብሻው ሲያይል ከክፍል እንዲወጡ ይደረጋል። ከዚህ በተቀራኒ አንዳንድ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ ተማሪዎች ቋሚ ቡድን አላቸው። ወደ ቡድናችሁ ሲባሉ ከ4-7 ሆነው አንድ ቡድን ይመሰርታሉ። ተገቢ የሆነ አመራርም ይሰጣል። ይህ ሁኔታ የተማሪዎቹ የቁጥጥር ፍላጎት የሚሟላበትም የማይሟላበትም ሁኔታ መኖሩን ያሳያል። መሟላቱ በክፍል ውስጥ ጥሩ በይነሰባዊ ግንኙነት እንዲኖር ስለሚያደርግ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ አወንታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። አለሟሟላቱ ደግሞ በክፍል ውስጥ የሚኖረው በይነሰባዊ ግንኙነት ችግር እንዲገጥመው፣ በክፍል ውስጥ የሚኖረው የተማሪዎች ስነምግባር ብልሹ እንዲሆንና ክፍሉ ለስነስርአት ችግር የተጋለጠ እንዲሆን ያደርጋል።

፪. የክፍል አያያዝ

የክፍል አያያዙን አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች ጠንካራም ደካማም ሊባሉ የሚችሉ አተገባበሮች መኖራቸውን ያሳያሉ (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። ምልከታው በተካሄደባቸው ክፍሎች ታጋሽ፣ ፈላጭ ቆራጭና ዲሞክራሲያዊ የክፍል አያያዝ ዘይቤዎች አመዝነው የታዩበት ሁኔታ አለ። ታጋሽ የክፍል አያያዝ ዘይቤ በሚያመዝንባቸው የመማሪያ ክፍሎች በመማር ማስተማሩ ሂደት

ተማሪዎች ስነስርአት አያከብሩም። መደባደብ፣ መንጫጨትና ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር በክፍል ውስጥ ትርምስ እንዲፈጠር ስለሚያደርጉ የተማሪዎቹ ትኩረት ትምህርቱ ላይ የማይሆንበት ሁኔታ ጥቂት አይደለም። እንዲህ አይነቱ የክፍል አያያዝ ለተማሪዎቹ ውሳኔ ሰጭነት ቅድሚያ ይሰጣል። መምህራኑ ለተማሪዎች ውሳኔ ሰጭነት ቅድሚያ የሚሰጥበትን መንገድ በአግባቡ ባለመተግበራቸው ክፍሉ ለስነስርአት ችግር የተጋለጠና ስርአተ አልበኝነት የነገሰበት ሆኖ ታይቷል። ተማሪዎች ሲረብሹ ከክፍል እንዲወጡ ወይም ኩርኩም እንዲቀምሱ የሚደረግበት ሁኔታም አለ። ፈላጭ ቆራጭ የክፍል አያያዝ ዘይቤ በገነነባቸው የመማሪያ ክፍሎች የመምህሩ የበላይነት ሰፍኖ ታይቷል። ይህ ደግሞ የመማሪያ ክፍሉን ፍርሀት የነገሰበት ስላደረገው ተማሪዎቹን በነጻነት የሚጠበቅባቸውን ተግባር የሚያከናውኑ የተግባቡቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ ሳይሆን ከመምህሩ የሚተላለፈውን መረጃ የሚቀበሉ ፍዝ ተመልካች አድርጓቸዋል። ዲሞክራሲያዊ የክፍል አያያዝ በሚንጸባረቅባቸው ክፍሎች ደግሞ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ሀላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡበት ሁኔታ ታይቷል። እነዚህ የመማሪያ ክፍሎች ጥሩ የክፍል ውስጥ ዲሲፕሊን የሰፈነባቸውና ጥሩ አመራር የሚሰጥባቸው ሆነው ተገኝተዋል።

በምልከታው ሂደት ግጥምጥምና ተለምዷዊ የተማሪዎች አቀማመጥ በጥቅም ላይ ሲውሉ የታዩ ሲሆን የፈረስ ኩቴ አቀማመጥ በጥቅም ላይ የዋለበት አጋጣሚ የለም። ይህም የተማሪዎቹ አቀማመጥ በክፍል ውስጥ ለሚከናወን መስተጋብር ምቹነት የጎደለው መሆኑን ያሳያል። በክፍል ውስጥ ተለምዷዊ፣ ግጥምጥምና የፈረስ ኩቴ አቀማመጦች በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ከሶስቱ የአቀማመጥ አይነቶች ለተማሪ-ተማሪና ለተማሪ-መምህር መስተጋብር ምቹ የሆነው የፈረስ ኩቴ አቀማመጥ ነው። ተለምዷዊው አቀማመጥ ለመምህር ተማሪ መስተጋብር ምቹ ቢሆንም ለተማሪ ተማሪ መስተጋብር ምቹ ባለመሆኑ ተመራጭነቱ እምብዛም ነው። በተመሳሳይ ግጥምጥም አቀማመጥ ለተማሪ ተማሪ መስተጋብር ምቹ ቢሆንም መምህሩን ከተማሪዎች እይታ ስለሚያስወጣ ተመራጭነት የለውም። ምልከታው በተካሄደባቸው ክፍሎች የታዩት አቀማመጦች ግጥምጥምና ተለምዷዊ መሆናቸው የተማሪዎቹ አቀማመጥ ጥሩ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንዲኖር የሚያስችል በመሆኑ ረገድ ውስንነት የሚታይበት መሆኑን ያመለክታል።

፫. ትምህርታዊ መስተጋብር

ትምህርታዊ መስተጋብሩን አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች በሰባት ተግባራት ዙሪያ ያጠነጠኑ ናቸው (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። ከነዚህ መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለት ተግባራት ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ስለሚደርሱበት ውጤት አወንታዊ ግምት እንዲኖራቸው መደረጉንና መምህራኑ ተማሪዎቹ ከሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን የተመለከቱ ናቸው። በአባሪ 6 ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው

ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ስለሚደርሱበት ውጤት አወንታዊ ግምት እንዲኖራቸው የመደረጉ ሁኔታ የደከመ ነው። መድከሙ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚያከናውኑት እያንዳንዱ ተግባር ስኬት ላይ ለመድረስ የሚያስችል መሆኑን እንዳይገነዘቡ ስለሚያደርግ ለመማር በሚኖራቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ውስጣዊ ተነሳሽነት አንድን ተግባር ለማከናወን የሚቀሰቅስ ጠንካራው የተነሳሽነት አይነት እንደመሆኑ መጠን በአሉታዊ ተጽእኖ ስር የወደቀ መሆኑ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን ከውስጥ በመነጨ ፍላጎት እንዳያከናውኑ ያደርጋል። ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን ሲያከናውኑም እንደዚሁ መምህራኑ ከተማሪዎቹ ጎላ ሄደው ቁጭ የሚሉበት ሁኔታ ይታያል። አብዛኛውን ጊዜ በተማሪዎቹ መካከል እየተዘዋወሩ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን የሚያከናውኑበትን ሁኔታ ሲቆጣጠሩ አይታዩም። ይህ ሁኔታ መምህራኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎቹ ከሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ጋር ያላቸው ቁርኝት የላላ መሆኑን ያሳያል። መላላቱ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባሩን ትኩረት ሰጥተው እንዳያከናውኑ ያደርጋል።

ሶስተኛውና አራተኛው ተግባራት የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ መራሽና ምልልሳዊ መስተጋብር የሚከናወንበት መሆኑን የተመለከቱ ናቸው። በአባሪ 6 ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የመማር ማስተማሩ በአመዛኙ መምህሩና ጥቂት እውቅና ያላቸው ተማሪዎች በሚያከናውኑት ተግባር ስለሚከናወን በርካታ ተማሪዎች ፍዝ ተቀባይ የሚሆኑበት አካሄድ ጎልቶ ይታያል። በተመሳሳይ የክፍል ውስጥ ያለው መስተጋብር በአብዛኛው ጥቂቶች የሚናገሩበትና ብዙዎች ተቀባይ የሚሆኑበት ነው። ይህ ሁኔታ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ከምልልሳዊነቱ ይልቅ ተራነቱ እንዲያመዝን ያደርጋል። ተራ መስተጋብር የሚባለው መረጃ በአንድ አቅጣጭ ብቻ የሚፈስበት ነው። በመስተጋብሩ ሂደት ተማሪ መራሽነትም ሆነ ምልልሳዊነት ደክሞ መታየቱ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚፈለገውን ውጤት እንዳያስመዘግብ፣ ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑ እንቅፋት የሚፈጥር አተገባበር መኖሩን ያመለክታል።

ለተማሪዎች የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ የተገኙት መረጃዎችም እንደዚሁ ትምህርታዊ ተግባራት ሲከናወኑ መምህራን ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የተለየ ድጋፍ ሲያደርጉ ያማይታይ መሆኑን ያስገነዝባሉ። ከፍ ሲል ለማየት እንደተሞከረውም ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን ሲያከናውኑ መምህራን የተወሰነ ቦታ ላይ ቁጭ ብለው እስከሚጨርሱ የሚጠብቁበት ሁኔታ ይታያል። ተማሪዎቹ እንዲያከናውኑ የተሰጣቸውን ትምህርታዊ ተግባር ለማከናወን ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መሆን አለመሆኑን በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ሲቆጣጠሩ አይታይም። ተማሪዎችም የክፍል ውስጥ ተግባራት ሲሰጣቸው በራሳቸው ይሰራሉ፣ ከጓደኞቻቸው ላይ ያያሉ ወይም ዝም ብለው ይቀመጣሉ እንጂ ከመምህራኑ ድጋፍ ለመጠየቅ አይደፍሩም (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚደረገው ድጋፍ

የደከመ መሆኑን ያሳያል። መድከሙ መጠነኛ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደሚፈለገው ደረጃ መምጣት የሚችሉ ተማሪዎች ወደ ኋላ እንዲቀሩ፣ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አካል ጉዳተኞች ተገቢውን ድጋፍ እንዳያገኙና የክፍል ውስጥ መስተጋብር ሂደቱ ተሳታፊ እንዳይሆኑ ያደርጋል። የትምህርት ፍትሀዊነትን የሚያረጋግጡ ተግባራት እንዳይከናወኑ የሚያደርግ ችግር መኖሩንም ያመለክታል።

ስድስተኛውና ሰባተኛው ተግባራትም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ላይ ስለመሆኑና ተገቢ የሆኑ የማበረታቻ ስልቶች በጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የሚገልጹ ናቸው። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹ ትኩረት ከትምህርቱ ውጪ የሚሆንበት ሁኔታ ጥቂት አይደለም። ትምህርታዊ ተግባራት በቡድን ሲከናወኑ የተወሰኑ ተማሪዎቹ ፍዝ ሆነው ይቀመጣሉ፤ በትምህርት ሰአት ከትምህርቱ ውጪ የሆኑ ተግባራትንም ያከናውናሉ። በተለይ ግዴለሽ የክፍል አያያዝ ዘይቤ በሚንጸባረቅባቸው ክፍሎች በክፍል ውስጥ የሚከሰት ስርአተ አልበኝነት የተማሪዎቹ ትኩረት እንዲበታተን ያደርጋል። ይህ ሁኔታ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ክንውን ላይ እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ሲሆን ትምህርታዊ መረጃውን በሚገነዘቡበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በተመሳሳይ መምህራኑ ሆነ ብለው የማበረታቻ ስልቶችን ሲጠቀሙ አይታዩም። የማይፈለግን ባህሪ ለማዳበር የሚያስችሉ አወንታዊ ማበረታቻዎችን ይጠቀማሉ። ለምሳሌ ያህል ረባሽ ተማሪዎችን ደጋግመው ጥያቄ የሚጠይቁበትና በጣም ጥቂት ለሆኑ ንቁ ተማሪዎች ማህበራዊ ማበረታቻ የሚሰጡበት ሁኔታ አለ። ይህም በመምህራኑ የማበረታቻዎች አጠቃቀም ላይ ችግር መኖሩን ያሳያል። ችግሩ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ውስጣዊ ተነሳሽነትን እንዳያዳብሩ ያደርጋል። የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ወጣ ያለ ባህሪ የሚያሳዩ ተማሪዎችን ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች ትኩረት ለማግኘት ሲሉ የማይፈለጉ ባህርያትን እንዲያሳዩ ይጋብዛል። ማህበራዊ ማበረታቻ መጠቀማቸው ጥሩ ቢሆንም ዘላቂነት ያለው አይደለም። ከዚህም በላይ ለጥቂት ተማሪዎች ብቻ የሚሰጥ መሆኑ ሌሎች ተማሪዎች ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከትን እንዲያዳብሩና የበታችነት እንዲሰማቸው ያደርጋል።

፬. የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር

የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበርን አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የንቁ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ ተግባር ተኮርና ልይይታዊ የመማር ማስተማር ስልቶች፤ ባለብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራትና የመማር ማስተማር ማእከላት እንዲሁም ችግር ፈቺ ተግባራትና ልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ የሚተገበሩበት ሁኔታ ደካማ መሆኑን አመልክቷል (አባሪ 6ን ይመልከቱ)። የንቁ የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር በጥቅም ላይ

የሚውሉበት ሁኔታ በጣም አነስተኛ ነው። ይህም የመማር ማስተማሩ ሂደት ተለምዷዊነት ጎልቶ እንዲታይበት አድርጓል። በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ተግባራቱን የማከናወን ኃላፊነት በአብዛኛው ጥቂት ተማሪዎችና በመምህራኑ ላይ የወደቀ ሲሆን የመማር ማስተማሩ ሂደትን አሳታፊ እንዳይሆን አድርጎታል። መምህራን የቡድን ተግባራትን የሚያጧጡፉበት ሁኔታም የደከመ ነው። ተግባር ተኮርና ልይይታዊ መማር ማስተማር፤ ባለብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራትና የመማር ማስተማር ማእከላት፤ ችግር ፈቺ ተግባራት እንዲሁም ልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ አይከናወኑም። አለመከናወናቸው የተማሪዎቹን የብስለት ደረጃ፣ የትምህርት አቀባበልና የመማር ስልት ያገናዘበ ትምህርት የሚያገኙበት አሰራር በጥቅም ላይ እንዳይውል አድርጓል። ሻል ባሉ አካላት ድጋፍ እየተደረገላቸው በልቀታዊ የእውቀት ግንባታ ክልል ትምህርታዊ ተግባራትን እያከናወኑ በሂደት ራሳቸውን እንዲችሉ የሚደረግበትንና ችግር ፈቺ የሆኑ የአሰራር ክህሎትን የሚያዳብሩበትን ሁኔታም አጥብቦታል። ይህም የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በማህበራዊ ግንባታውያን የትምህርት ፍልስፍና ንድፈ ሀሳብ የሚመሩ አካሄዶች እንዳይኖሩት አድርጓል።

4.1.2.3. ከሰነድ ምርመራ የተገኘ መረጃ

የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን አስመልክቶ ከሰነድ ምርመራ የተገኘው መረጃ የትምህርት እቅዶቹ በጥቅም ላይ የሚውሉት የመማር ማስተማር ዘዴዎች በግልጽ የተቀመጡባቸው አለመሆናቸውን የተመለከተ ነው። የትምህርት እቅድ ትግበራ ባይሆንም የትግበራ መሰረት ነው። በመርህ ደረጃ መምህራኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ገብተው የሚተገብሩት በእለታዊ የትምህርት እቅዳቸው ላይ ያቀዱትን መሆኑ እሙን ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በእለታዊ የትምህርት እቅድ ላይ በግልጽ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ይህም መከናወን ያለበት ተግባር በአግባቡ መከናወኑን ለማረጋገጥ ያስችላል። የመማር ማስተማር ዘዴዎች በትምህርት እቅዱ ላይ አለመቀመጣቸው የቀረበውን ትምህርታዊ መረጃ ወደ ተማሪዎቹ ለማድረስ የሚያገለግለው የማስተማሪያ ዘዴ በግልጽ እንዳይታወቅ ያደርጋል። አለመታወቁ የትምህርቱ ሂደት ከትምህርታዊ መረጃውና ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚራመድ የማስተማሪያ ዘዴን በጥቅም ላይ የማዋል ችግር እንዲገጥመው ያደርጋል። ይህ ሁኔታ የመማር ማስተማር ዘዴዎች የመልእክት መተላለፊያ ከመሆናቸው አንጻር የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ የመልእክት መተላለፊያ ችግር እንዲገጥመውና የተግባቦት እንቅፋት እንዲፈጠር የሚያደርግ መሰናክል የገጠመው እንዲሆን ያደርጋል። ሁኔታው ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ ትምህርታዊ መረጃውን በሚቀስሙበት፣ የእውቀት ግንባታን በሚያካሂዱበትና ጽብረቃ በሚያከናውኑበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

4.2. የውጤት ማብራሪያ

4.2.1. የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም

የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወነውን የመረጃ ልውውጥ እንዲሳለጥ ለማድረግ የሚያስችል የመምህራን ችሎታ በጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድ መሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውጤታማ የሆነ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ትምህርታዊ መረጃን ተስተዋይ በሆኑ ምልክቶች ለመወከል ስለሚያስችል የመረጃ ፍሰትን ያሳልጣል። መምህራን የመረጃ የተግባቦት ክህሎታቸውን በአግባቡ መጠቀም ባልቻሉበት ሁኔታ በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ መረጃ በጥሩ ሁኔታ እንዲንሸራሸር ማድረግ፣ ከተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች ጋር የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፣ የእውቀት ግንባታ እንዲከናወን ለማድረግ ያሚያስችሉ ተግባራትን አስመልክቶ አመራር መስጠት፣ ከተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት መመስረትና ጥሩ የክፍል ውስጥ በይነሰባዊ መስተጋብር ማከናወን ይቸገራሉ። ይህ ሁኔታ ጥሩ የሆነ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም መምህራን በማስተማር ስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ያስገነዝባል። በዚህ መሰረት ይህ ጥናት ካነሳቸው አምስት ዝርዝር ጥያቄዎች መካከል የመጀመሪያው "የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴት ያለ ነው?" የሚል ሲሆን ምላሹ "ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው።" ይሆናል። እዚህ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስቻለው የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች በጥቅል ሲመረመሩ የተደረሰበት ውጤት ነው።

አጠቃላይ የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም አስመልክቶ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በአምስቱም ዘርፎች የተካተቱ ተግባራት አተገባበርን የሚያሳዩ መረጃዎች በጥቅል ታይተዋል። የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን፤ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን እንዲሁም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ያሳያሉ። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል (t=-4.342, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -4.342 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-13.55667 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ

ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-1.4475 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው (4.1.1ን ይመልከቱ)። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎችም ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ የመምህራኑ ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀሞች ጥሩ ሲሆኑ በሌሎቹ ላይ ድክመት የሚታይ መሆኑን አሳይተዋል (4.1.1.2ና 4.1.1.3ን ይመልከቱ)። ስለዚህም በጥቅሉ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። ደካማ መሆኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት ችግር ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ጥናቱ ላነሳው የመጀመሪያ ዝርዝር ጥያቄ መልስ ሰጥቷል።

በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ስር የተካተቱት ዘርፎች የክስተት ሁኔታ በንጽጽር ሲታይ ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ዘርፎች ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ፣ የጥያቄ አጠያየቅና የመረጃ ግብይት ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይባቸዋል (4.1.1ና 4.2.1ን ይመልከቱ)። በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በትምህርት የሚዳብር ጉዳይ ነው። ይህ ከሆነ በአጠቃቀም ረገድ ሌሎቹ ዘርፎች ደካማ ሲሆኑ የቃላዊ እና ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘት "እንዴት ሊከሰት ቻለ?" የሚል ጥያቄ ያስነሳል። Hargie & Dickson, (2005) እንደገለጹት ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎች በጣም የተሳሰሩ ሲሆኑ ማህበረሰቡ በየእለቱ በሚያከናውነው ማህበራዊ መስተጋብር ስለሚጠበቀምባቸው ከባህል ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። ልዩነቱ የመጣው ምናልባትም ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎች ከባህል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው በመሆኑ መምህራኑ ከስልጠና ሂደት ብቻ ሳይሆን ካደጉበትና ከሚኖሩበት ማህበረሰብም ጭምር ስለሚያዳብሩት ሊሆን ይችላል።

የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ጥሩ መሆኑ በትምህርታዊ የተግባቦት ስርአቱ ውስጥ ያለውን የመረጃ ፍሰት እንደሚያሳልጥ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። ይህ ማለት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ድክመት ያለበት መሆኑ በተግባቦት ስርአት ውስጥ ባለው የመረጃ ፍሰት መሳለጥ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። የተግባቦት ስርአት ግብይታዊ እንደመሆኑ መጠን መረጃ ግብይታዊ በሆነ መንገድ በተሳታፊዎቹ መካከል ይፈስበታል። በተግባቦት ሂደት ግንዛቤ የመፍጠር ሂደት የሚከናወነውም በአምስቱም የስሜት ህዋሳት አማካኝነት ከውጪው አለም በሚወሰድ ግብኣት አማካኝነት መረጃን በመቀበል ነው። ከፍ ሲል በቀረበው የመረጃ ትንተና እንደታየው ግን ጥናቱ በተካሄደባቸው የመማሪያ

ክፍሎች ያለው የመማር ማስተማር ሂደት የተወሰኑ ሰዎች መረጃ የሚያስተላልፉበትና አብዛኞቹ የሚቀበሉበት ነው (4.2.1ን ይመልከቱ)። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት በአብዛኞቹ ተማሪዎች ዘንድ ግንዛቤ የሚፈጠረው በአምስቱም የስሜት ህዋሳት መረጃን በግብኣትነት በመውሰድና እውቀትን በሚያከናውኑት መስተጋብር አማካኝነት በመገንባት አለመሆኑን ያሳያል። ይልቁንም አብዛኞቹ ተማሪዎች በመስማት ላይ ለተመሰረተ ግብኣት የተጋለጡ መሆናቸውን ያመለክታል። የመማር ማስተማር ሂደቱ የተወሰኑ ሰዎች መረጃን የሚያስተላልፉበትና አብዛኞቹ የሚቀበሉበት መሆኑ በክፍል ውስጥ ያለው የተግባቦት ስርአት ከግብይታዊነቱ ይልቅ መስመራዊነቱ እንደሚያመዝን ያሳያል። መስመራዊነቱ ማመዘኑ የትምህርት ስርአቱን እውቀት በማህበር የሚገነባበትና ማህበራዊ የሆነ የጋራ ግንዛቤ የሚጨበጥት እንዳይሆን ያደርገዋል። እውቀት በማህበር ካልተገነባበትና ማህበራዊ የጋራ ግንዛቤ ካልተጨበጠበት ደግሞ ከተመሰረተበት መሰረተ ግንባታውያን የትምህርት የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ሀሳብ ጋር አይራመድም ማለት ነው።

በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው በመማሪያ ክፍል ውስጥ እውቀት የሚገነባው በግብይታዊ መማር ማስተማር ነው። መምህራንና ተማሪዎች ለመማር ማስተማር ሂደቱ ግብኣት የሚሆኑ ጉዳዮችን ይዘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገናኛሉ። ከዚያም በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ተግባራትን እየተገበሩ በሚያከናውኑት የመረጃ ልውውጥ ግብኣቶቹ ተብላልተው አዲስ ውጤት ወይም ውጽኣትን ያስገኛሉ። ይህ ውጽኣት በትምህርቱ ሂደት የሚፈጠረው የጋራ ግንዛቤ ወይም የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። ይሁን እንጂ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ይህ ሁኔታ በክፍል ውስጥ እንዲኖር የሚጠበቀውን የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት ያዳክመዋል። የመረጃ ፍሰቱ ከተዳከመ ትምህርታዊ መረጃ በጥሩ ሁኔታ ተወክሎ አይቀርብም። ጥሩ የትምህርት አመራርም አይሰጥም ማለት ነው። በዚህ የተነሳ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራቱን የሚያከናውኑበትን ሁኔታ አስመልክቶ የሚያገኙት መረጃ ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ ይሆናል።

በመረጃ ትንተናው እንደታየው የትምህርቱ አላማ የአነዳፍ ችግር አለበት። ስለዚህም የትምህርቱ አላማ ከግብ መድረሱን በትክክል መለካት አይቻልም። ጽብረቃ ስማይከናወንም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው ችግር ተፈትሾ በቀጣይ የሚወሰደው የማሻሻያ ርምጃ አይቀየስም ማለት ነው። ባጭሩ ጎልቶ የሚታየው ጥቂቶች ተናጋሪ ወይም ሰሪ፣ ፤ ብዙዎች ደግሞ አድማጭ ወይም ተመልካች የሆኑበት የመማር ማስተማር ሂደት ነው። ይህ ደግሞ በግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ውስጥ ከሚከሰተው የተግባቦት ሂደት አንጻር ሲታይ ተማሪዎቹ በሚጠበቀው ሁኔታ ከሚያከናውኑት ተግባር አዳዲስ መረጃዎችን እየቀሰሙ እውቀትን እንዲገነቡ አያደርጋቸውም። ስለዚህም በክፍል ውስጥ የሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት የሚጠበቀውን ውጽኣት ማስገኘት የተሳነው ይሆናል። ምክንያቱም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የቋንቋ አጠቃቀም በብቃት ማበልጸግ የሚያስችል

ማህበራዊ መስተጋብር አይከናወንም፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚጠበቀውን ያህል በክፍል ውስጥ የትምህርታዊ መረጃዎች በጥሩ ሁኔታ መንሸራሸር፣ በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መካከል በማህበር የጋራ ግንዛቤን ጨብጦ የጋራ መግባባት ላይ መድረስና እውቀትን መገንባት እንዲኖር አይጠበቅም፡፡ በጥቅሉ የመማር ማስተማሩ ሂደት በተሟላ ሁኔታ መምህራንና ተማሪዎች በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር አዳዲስ ግንዛቤዎችን የሚጨብጡበት፣ የአሰራር ክሂሎችን የሚያዳብሩበት፣ አዳዲስ መልእክቶችን የሚገነዘቡበት፣ ሀሳብ የሚጋሩበት፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት፣ እውቀታቸውን የሚገነቡበት፣ ግንዛቤያቸውን አስመልክቶ ግብረ መልስ የሚሰጣጡበትና ስብእናቸው የሚቀረጽበት የመማር ማስተማር ሂደት ነው ማለት ያዳግታል፡፡

ይህ ጥናት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ይህም በትምህርት ስርአቱ ላይ ችግር የሚፈጥር የተግባቦት እንቅፋት መኖሩን ያስገነዝባል፡፡ የትምህርታዊ ተግባቦት ስርአቱ በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ግብይታዊ ከመሆን ይልቅ መስመራዊ ወደ መሆን እንደሚያዘነብል ለማወቅም ያስችላል፡፡ ስለዚህም በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ በስራ ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሰራር እንዴት በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አሰራር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል? በቀጣይ የሚሰለጥኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአሰለጣጠን ሁኔታስ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ምን መምሰል አለበት? ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትስ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ መምህራንን የሚያሰለጥኑበት ሁኔታ ምን ይመስላል? በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች አሰራርስ ምን ያህል በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አሰራር የተቃኘ ነው? ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማህበራዊ ግንባታውን የትምህርት ፍልስፍና አሰራር መሰረት ሰልጥነው የሚወጡ መምህራን በስራ አለም ሲሰማሩ የሚሰማሩበት የስራ አውድ የሚያሳድርባቸውን ተጽእኖ እንዴት መቋቋም ይቻላል? የሚሉ በቀጣይ መጠናት ያለባቸው ጥያቄዎች እንዲነሱ ያደርጋል፡፡

መምህርነት ሙያ እንደመሆኑ መጠን ሰልጣኞቹ በንድፈ ሀሳብ በሚያገኙት ብቻ ሳይሆን በአተገባበር ከአሰልጣኞቻቸው በሚያገኙት ልምድም ሙያዊ ማንነታቸው ይገነባል፡፡ በመሆኑም የአሰልጣኝ መምህራን ማንነት ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ መምህራኑ በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አሰራር መሰረት ቢሰለጥኑም እንኳ ወደ ማስተማር ስራ ሲገቡ የአሰራር ዘይቤውን ተለምዷዊ ባደረገው የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስለሚዋጡ የሰለጠኑበትን ሁኔታ ትተው በተግባር እየተተገበረ ባለው አሰራር ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የጥናቱ ሞዴል የሆነው ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ እንደሚያመለክተው

አውድ ወይም አካባቢ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ስለዚህም ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የመምህራኑ ስልጠና ሂደት ብቻ ሳይሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች በአጠቃላይ እንዴት መለወጥ አለባቸው የሚለው ጉዳይ ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል።

በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን አስመልክቶ የተዳሰሱት ተግባራት በአምስት ዘርፍ ሊፈረጁ ይችላሉ። የየዘርፎቹን ተናጠላዊ አተገባበር የሚያሳዩ ከምልከታ፣ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች ቀደም ሲል የተተረጎሙ ሲሆን እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

4.2.1.1. *የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም*

ቃላዊ መግባቢያዎች የሚባሉት የተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች ቃላትን በመጠቀም መረጃ የሚወክሉባቸው መንገዶች ናቸው። ሰዎች ጥሩ የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ችሎታ አላቸው የሚባለው ተገቢ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀምን በጥቅም ላይ ማዋል ሲችሉ ነው። በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት የሚፈለገውን ግብ ማግኘት እንዲቻል ቀላል፤ የተግባቦቱ ተሳታፊዎች በቀላሉ የሚረዱትና አግባቢ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም በጥቅም ላይ መዋል እንደሚኖርበት በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ ተሞክሯል። የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምን እንዴትነት የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛና የልይይት መጠን ልኬታዎች የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን፣ በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት መኖሩንና ጠንካራ አተገባበር የጎላ መሆኑን ያሳያሉ። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን አመላክተዋል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል (t=2.527, df=35, p<0.05)። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ1195 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በላይ ሲሆን በምልከታ የተገኘው ውጤት ከሚጠበቀው የበለጠ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ ይታያል። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው 2.527 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። የጉልህት ደረጃው sig.=0.016 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=0.842 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት መካከለኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል።

ልዩነቱ የመጣው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው፡፡ ይህም የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስችሏል (4.1.1.1ን ይመልከቱ)፡፡ በተመሳሳይ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን አመልክቷል (4.1.1.2 ይመልከቱ)፡፡ ይህ መረጃ በምልከታ በተገኙ መረጃዎች ትንተና የተደረሰበትን ውጤት የሚያጠናክር ነው፡፡ የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በክፍል ውስጥ ጥሩ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረግም ያስችላል፡፡

በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው የመማር ማስተማር ሂደት ግብይታዊ በሆነ መንገድ መረጃ የሚሰራጭበት የተግባቦት ስርአት ነው፡፡ ሁለቱም መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ በማያቋርጥ ሂደት አዳዲስ መረጃዎችን ይገበያዩበታል፤ የጋራ ግንዛቤንም ይጨብጡበታል፡፡ የተግባቦት ስርአት እውን የሚሆነውም መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ የሚተላለፈውን መረጃ በተመሳሳይ ሁኔታ ሲረዱትና በተረዱት መረጃ ላይ ተመስርተው አዳዲስ ሀሳችቦን እያፈለቁ በግብአትነት ማስተላለፍ ሲችሉ ነው፡፡ መምህራን በትምህርታዊ ተግባቦት ስርአት ውስጥ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊ ከመሆን ባለፈ የተግባቦት ስርአቱ በጥሩ ሁኔታ መካሄድ እንዲችል ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ፣ የሀሳብ ልውውጡ የሚካሄድበትን መንገድ ፈር የሚያሲይዙና አመራር የሚሰጡ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ የተግባቦቱ ሂደት በጥሩ ሁኔታ መካሄድ እንዲችል፣ ለተግባቦት እንቅፋት እንዲከሰት ለሚያደርግ መሰናክል የተጋለጠ እንዳይሆን፣ የጋራ ግንዛቤ የሚጨበጥበትና የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ የሚችል እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረት መማር የአዳዲስ ፍቺዎች ግንባታ የሚካሄድበት ነው፡፡ የፍቺ ግንባታው የሚከናወነው የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች በማህበር ሆነው ትምህርታዊ ተግባራትን ሲያከናውኑ ነው፡፡ ትምህርታዊ ተግባራቱ በአግባቡ መከናወን እንዲችሉ የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ምቹ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም ተማሪዎች የትምህርታዊ ተግባራቱን አተገባበር፣ የሚተላለፈውን ትምህርታዊ መረጃም ሆነ የሚሰጠውን ግብረ መልስ ያለ ችግር እንዲቀበሉት ለማድረግ ያስችላል፡፡ በጥሩ ስሜት ትምህርታዊ ተግባራቱን እንዲያከናውኑም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ ደግሞ ትምህርታዊ ተግባቦቱ ስርአተ ሂደቱን ጠብቆ ያለእንቅፋት እንዲከናወን ለማደረግ ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በምእራፍ ሁለት የጥናቱ ሞዴል በሆነው ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ለማየት እንደተሞከረው መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የየራሳቸውን ዳራዊ እውቀትና ክህሎት ይዘው አዲስ በሚቀርበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ

የተለያዩ ተግባራትን ሊያከናውኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገናኙና አዲስ በሚቀርበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ ሀሳብ ሲለዋወጡ ግብይታዊ የተግባቦት ሂደትን ያከናውናሉ፡፡ የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚያከናውኑት ተግባቦት መረጃ ሲተላለፍ የጋራ መግባባት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የጋራ መግባባት መኖሩ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑት ተግባራት በአግባቡ እንዲከናወኑና የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ግብኣት ሆነው የመጡት ጉዳዮች ተብላልተው የሚጠበቀውን ውጤት በውጽኣትነት ማስገኘት እንዲችሉ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ስለዚህም የመምህራኑ ቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ የመማር ማስተማሩ ሂደት የታሰበለትን አላማ ከግብ ማድረስ እንዲችል አወንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

4.2.1.2. *የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም*

ኢቃላዊ መግባቢያዎች ሰዎች በቃላት አማካኝነት የሚያስተላልፏቸውን መረጃዎች የተሟሉ የሚያደርጉ አካላዊ ቋንቋና ልዕለ ልሳናዊ ባህርያት ናቸው፡፡ አካላዊ ቋንቋ ሰዎች የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም ማለትም በእቋቋም፤ በገጽ ግላጼዎች፤ በአይን ግጥምጥሞሽ እንዲሁም ጭንቅላትን በማወዛወዝና በማነቃነቅ መልእክትን የሚወክሉበት መንገድ ነው፡፡ ልዕለ ልሳናዊ ባህርያት የሚባሉትም እንደዚሁ በንግግር ሂደት በሚደመጡ ድምጸ ቅላጼዎች፣ የንግግር ፍጥነት፣ በንግግር ቆምታ፣ በድምጽ መጠን አማካኝነት መልእክት የሚወከልባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምን የሚያሳዩ በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች መደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱንና የመረጃ አሰረጫጨቱ የተለያየ መሆኑን አሳይተዋል፡፡ ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለመረዳት አስችሏል፡፡ ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል (t=3.883, df=35, p<0.05)፡፡ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው 3.883 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው፡፡ በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ4.51085 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል፡፡ ርቀቱ ከዜሮ በላይ መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው በላይ መሆኑንና ጠንካራ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያል፡፡ የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል፡፡ ይህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡

የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=1.294478 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በላይ በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ይህም የመምህራኑ ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስችሏል (4.1.1.1.ን ይመልከቱ)። የመምህራኑን ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም አስመልክቶ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው (4.1.1.2ን ይመልከቱ)። ሁኔታው በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል አወንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ተግባቦት በመልእክት አስተላላፊና በመልእክት ተቀባይ መካከል የመልእክት ግብይት የሚከናወንበት ነው። ኢቃላዊ መግባቢያዎች በክንውኑ ሂደት በቃላዊ መግባቢያዎች አማካኝነት የሚተላለፈውን መልእክት ይደግፋሉ ወይም ያጠናክራሉ። ስለዚህም የመምህራኑ ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ በተግባቦቱ ሂደት ጥሩ የሆነ የመረጃ ዝውውር እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል፡ ፡ መረጃ በምልክት ተወክሎ የሚተላለፍበት ሁኔታ የተግባቦቱን ሂደት ለሚያሰናክል የተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ እንዳይሆንም ያደርጋል። ለተግባቦት እንቅፋት አለመጋለጡ ተግባቦቱ ስርአተ ሂደቱን ጠብቆ በማያቋርጥ ሁኔታ እንዲከናወንና የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ስለዚህም የተግባቦቱ ሂደት የታለመለትን አላማ ከግብ ማድረስ ያስችላል።

በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ዝንቅ መሰረት መማር በክፍል ውስጥ በሚከናወን ማህበራዊ መስተጋብር አማካኝነት የአዳዲስ ፍቺ ምስረታ የሚከናወንበት መሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። የመምህራኑ ኢቃላዊ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ የተግባቦቱ ተሳታፊዎች በትምህርቱ ሂደት በሚተላለፈው መረጃ ረገድ በማህበር ትምህርታዊ ተግባራትን ሲያከናውኑ የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ አዳዲስ ፍቺዎችን መመስረት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። መምህራን የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት አመራር ሰጪዎች እንደመሆናቸው መጠን ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚያደርጉት መስተጋብር ውጤታማ መሆን የሚችለው የሚያስተላልፉት መልእክት መተርጎም ሲችል ነው። እንዲተረጎም በኢቃላዊ ምልክቶች ወክለው የሚያስተላልፉት መልእክት በቃላዊ ምልክቶች ከተላለፈው መልእክት ጋር የሚጣጣም መሆን ይኖርበታል። ኢቃላዊ ምልከቶቹ መልእክቱንም ለተግባቦቱ አውድ በሚመች ሁኔታ ወክለው በትክክል ማስተላለፍ የሚችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ይህም ተማሪዎቹ በሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ረገድ እርስ በእርስ እንዲረዳዱ ለማድረግ ያስችላል። ስለዚህም የመምህራኑ ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም በጥሩ ሁኔታ ላይ መገኘቱ

በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አካሄድ መሰረት ተማሪዎቹ በማህበር በሚከናወን መማር ማስተማር እውቀትን እንዲገነቡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በምእራፍ ሁለት በቀረበው ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ እንደታየው መምህራንና ተማሪዎች የየራሳቸውን ዳራዊ እውቀትና የመማር ማስተማር ስልት ይዘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገናኛሉ። ከተገናኙ በኋላ በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ረገድ የተላያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን አከናውነው የጋራ ግብ ላይ መድረስ የሚያስችል ግንዛቤን መጨበጥ የሚችሉት መምህራን በኢቃላዊ መግባቢያዎች ወክለው በሚያስተላልፉት መረጃ ረገድ መናበብ ሲችሉ ነው። መናበብ ሲኖር በጋራ ለአንድ አላማ ትምህርታዊ ተግባራትን ማከናወን፣ መረጃን መተንተን፣ ማብራራት፣ መገምገም፣ ማዋሀድና የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ ይከናወናል። የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያስመዘግብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተከናወኑት ተግባራት ተብላልተው የሚፈለገውን ውጤት አስገኙ ማለት ተግባ-ግብይታዊ የሆነው የመማር ማስተማር ማሕቀፍ የሚፈለገውን ውጽኣት ማስመዝገብ ችሏል ማለት ነው።

4.2.1.3. *የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ*

በመማር ማስተማሩ ሂደት የመረጃ ፍሰቱ የሚሳለጠውና የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት የሆነው የትምህርቱ አላማ በተማሪዎች ዘንድ ተተርጉሞ በአእምሯቸው የሚሰርጸው የትምህርቱን አላማ ወክለው የሚቀርቡት ትምህርታዊ መረጃዎች በስርአት ተደራጅተው ሲቀርቡ ነው። ትምህርታዊ መረጃዎች የሚባሉት በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ከምንጮቻቸው ወደ ተቀባዮቻቸው የሚፈሱ መልእክቶች ናቸው። እነዚህ መልእክቶች በትምህርት ይዘትነት ተወክለው የቀረቡ የትምህርቱ ዓላማዎች ናቸው። በተሳታፊዎቹ ዘንድ የነጋሪትና የአግባቢነት ዋጋ አላቸው። በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወኑ ተግባራት አማካኝነት በመምህራንና በተማሪዎች ዘንድ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያደርጉ በመሆናቸው እንደሚያግባቡ በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ ተሞክሯል።

የመምህራኑን የትምህርታዊ መረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ እንዴትነት የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና ሰባዛ መሆኑን እንዲሁም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታሉ። በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን አመላክተዋል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል ($t=-19.335$, $df=35$, $p<0.05$)።

የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -19.335 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው፡፡ በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-9.22444 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል፡፡ ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰና ደካማ አተገባበር የሚታይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል፡፡ ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ፡፡ የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-6.44516 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል (4.1.1.1ን ይመልከቱ)፡፡ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ውጤትም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክር ነው (4.1.1.2ና 4.1.1.3ን ይመልከቱ)፡፡ ይህ ሁኔታ የመማር ማስተማሩ ሂደት መረጃ የሆነው የትምህርቱ አላማ በምልክት ተወክሎ ወደ ተማሪዎቹ በሚደርስበት ሁኔታ ላይ የተግባቦት እንቅፋት ሊፈጥር የሚችል ችግር መኖሩን ያሳያል፡፡ ችግር መኖሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹና መምህራኑ መረጃን በሚገበያዩበት ሁኔታና በሚያከናውኑት የእውቀት ግንባታ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

በምእራፍ ሁለት ከተዳሰሱት ሀሳቦች አንጻር ሲታይ አሉታዊ ተጽእኖው በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ በግብረመልስ አሰጣጥ ሂደት ከተቀመጠው አላማ አንጻር ራሳቸውን እንዳይገመግሙና ምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው አስበው እንዳይንቀሳቀሱ ምክንያት ይሆናል፡፡ የመማር ማስተማሩ ሂደት ግብ ተኮር እንዳይሆንና ምዘናና ጽብረቃ በተገቢው መንገድ እንዳይከናወኑ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎቹ ከውስጥ በመነጨ ተነሳሽነት ትምህርቱን እንዳይከታተሉ፣ የሚፈለገው ውጤት ላይ እንዳይደርሱ፣ ከሚያከናውኑት ተግባር ያልተጠቃለለ ወይም የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡ መረጃዎችን ጥልቅ በሆነ ስርአታዊ አካሄድ ፈትሸው የራሳቸውን ግንዛቤ በሚገነቡበትን ሁኔታ ያዳክማል፡፡ ስለዚህም የተግባቦት ስርአቱ ተሳታፊዎች መረጃን የሚለዋወጡበት፣ የጋራ ግንዛቤንም በመጨበጥ እውቀታቸውን የሚገነቡበትና ነጻ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ የሚያካሂዱበት እንዳይሆን ምክንያት ይሆናል፡፡ የተግባቦት ስርአቱን መረጃ ግብይታዊ በሆነ መንገድ የሚፈስበት ግብይታዊ ሳይሆን በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚሰራጭበት መስመራዊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ ሳይሆን ፍዝ ተመልካች ለሚያደርጉ ችግሮች ይዳርጋቸዋል፡፡ ፍዝ ተመልካች መሆናቸው በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረት በማህበር አዳዲስ የፍቺ ምስረታ እንዳያካሂዱ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሁኔታም የደከመ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

በመረጃ አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ ያለው ድክመት በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውስጥ የተለያዩ ልምዶች፣ ዳራዊ እውቀት፣ ችሎታና የመማር ስልት ይዘው ወደ መማሪያ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ረገድ እርስ በእርስና ከመምህራን ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር የጋራ ግንዛቤን በሚጨብጡበት ሁኔታ ላይ መሰናክል ይሆናል። ምክንያቱም ከፍ ሲል የታየው አሉታዊ ተጽእኖ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በክፍል ውስጥ በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር አማካኝነት የቀደመ ልምዳቸውንና አዲስ የሚያገኙትን መረጃ አስተሳስረው አዳዲስ ግንዛቤዎችን እንዳይጨብጡ ያደርጋል። በሌላ አገላለጽ ግብኣቶቹ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተዋህደው አዲስ ውጽኣትን እንዳይፈጥሩ እንቅፋት ይሆናል። አዲስ ውጽኣት አለመፈጠሩ የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤት አልባ መሆኑን ያሳያል። ውጤት አልባነቱ ትምህርታዊ የተግባቦት ስርአቱ የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ የተሳነው እንዲሆን ያደርገዋል።

4.2.1.4. *የጥያቄ አጠያየቅ*

የጥያቄ አጠያየቅ ትምህርታዊ መረጃን በምልክት ወክሎ ወደ ተማሪዎች ለማድረስ የሚያስችል መንገድ ነው። ውጤታማ የጥያቄ አጠያየቅ የመማር ማስተማር ሂደት የመሰረት ድንጋይ ሲሆን መምህራንና ተማሪዎች ምልልስ እንዲጀምሩና በቀጣይም ምሁራዊ ትንታኔ መስጠት እንዲችሉ በር እንደሚከፍት በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ ተሞክሯል። ጥሩ የጥያቄ አጠያየቅ ችሎታ መምህራንን በማስተማር ስራቸው የተዋጣላቸው ያደርጋቸዋል። ተማሪዎቻቸው የቀረበላቸውን ትምህርታዊ መረጃ በጥልቀት እንዲፈትሹ፣ በትምህርታዊ መረጃዎች ላይ ትንታኔ እንዲሰጡ፣ ከሌሎቹ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች ጋር እንዲናበቡና በትምህርቱ ሂደት ስለሚያነሷቸው ጽሁፎች ማሰብ እንዲችሉ ለማድረግ ያስችላል። በመካከላቸው የሚታዩ ልዩነቶችን ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ ተማሪዎች ችግርን በጋራ የመፍታት ችሎታን፣ ተጠየቃዊ አስተሳሰብንና ሂሳዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

የመምህራኑን የጥያቄ አጠያየቅ እንዴትነት የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፣ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን እንዲሁም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን አመልክተዋል። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ አስችሏል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል ($t=-10.265$, $df=35$, $p<0.05$)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -19.335 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-4.64889 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው

ያነሰና ደካማ አተገባበር የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-3.42157 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም የመምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ተችሏል (4.1.1.1ን ይመልከቱ)። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት ያጠናክራሉ (4.1.1.2ንና 4.1.1.3ን ይመልከቱ)።

የመምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ መረጃን በሚገነዘቡበት ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። አሉታዊ ተጽእኖው በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል። ቁልፍ የሆነውን ትምህርታዊ መረጃ በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በሚከናወኑ ተግባራት አማካኝነት ፈልገው ማግኘትና ግንዛቤ መጨበጥ እንዳይችሉ ምክንያት ይሆናል። የአመክንዮ ተግባራትን ማለትም መገምገምን፣ መተንተንን፣ ማነጻጸርና ማወዳደርን በመጠቀም መረጃን ፈልፍሎ የማውጣትና የመገንዘብ ችሎታን በሚያዳብሩበት ሁኔታ የደከመ እንዲሆን ያደርጋል። ገጠመኞችን፣ ክስተቶችን፣ ሂደቶችን፣ ድምዳሜዎችን፣ እውነታዎችን፣ የግል አስተያየቶችንና በመካከላቸው ያለውን ትስስር አውጥቶ የማሳየት ችሎታን እንዳያዳብሩም እንቅፋት ይሆናል። ተማሪዎቹ በአመክንዮ በነገሮች መካከል ያለን የመንስኤና የውጤት ትስስር ፈትሾ ድምዳሜ ላይ የመድረስ ተግባራትን እንዳያከናውኑ መሰናክል ይሆናል። ሽቅብ አመክንዮን፣ ምንጨታዊ አመክንዮንና ንጽጽርን በመጠቀም ቁሳቁሶችን፣ ገጠመኞችን፣ ክስተቶችን፣ ሂደቶችን፣ ድምዳሜዎችን፣ እውነታዎችን፣ የግል አስተያየቶችንና በመካከላቸው ያለውን ትስስር አውጥቶ የማሳየት ችሎታንም እንዳያዳብሩ ያደርጋል።

በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረት የመማር ማስተማር ሂደት የመረጃ ልውውጥ የሚካሄድበት የተግባቦት ስርአት ተደርጎ እንደሚታይ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። በዚህ የተግባቦት ስርአት ውስጥ ተማሪዎች አዲስ በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ረገድ ከመምህራን ጋር የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ ይችሉ ዘንድ የሀሳብ ልውውጥ የሚያደርጉት በሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት አማካኝነት መረጃዎችን ፈልፍለው ማውጣት እንዲያስችሉ ተደርገው በተቀረጹ ጥያቄዎች አማካኝነት ነው። ጥያቄዎችን የመማር ማስተማር ሂደት የመሰረት ድንጋይ ያሰኛቸውም ይኸው ነው። ከዚህ አንጻር የመምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ድክመት ያለበት መሆኑ ተማሪዎች በትምህርታዊ ተግባቦት

ስርአት ውስጥ ጥያቄዎቹን ተንተርሰው በሚፈለገው ደረጃ የሀሳብ ልውውጦችን እንዳያደርጉ እንቅፋት ይሆናል። መረጃ በተግባቦት አላባውያን የሚያልፍበት ሂደት ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ እንዲሆንም ያደርጋል ማለት ነው። ይህ ደግሞ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በቀረበላቸው ትምህርታዊ መረጃ ላይ የጋራ ግንዛቤን በሚጨብጡበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

የመምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ድክመት ያለበት መሆኑ በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውጤታማት ላይም ተመሳሳይ ችግር እንዲከሰት ያደርጋል። ጥያቄዎች አዲስ በሚቀርበው ትምህርታዊ መረጃ ረገድ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የትምህርት ግብኣት ሆነው ከሚገኙ ጉዳዮች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። ትምህርታዊ መረጃውን በትምህርታዊ ክንውን መልክ ወደ ተማሪዎቹ ለማድረስ ያስችላሉ። በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያየ ዳራዊ እውቀት፣ ልምድ፤ የመማር ማስተማር ስልትና ችሎታ ያላቸው መምህራንና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መስተጋብርን የሚያከናውኑትና ሀሳብ የሚለዋወጡት መምህራን ቀርጸው ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሲሰሩ ነው። መምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ድክመት አለበት ማለት ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ እንደሚፈለገው ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ፤ ሀሳብ እንዲለዋወጡ፤ በሀሳብ አመክንዮ ጽንሰ ሀሳቦችን ፈልፍለው እንዲያወጡ፤ በግል፣ በጥንድና በቡድን ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ፤ ሀሳቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር ተመልክተው እንዲተነትኑ እንዲሁም እንዲገመግሙ የማድረግ አቅም ያንሳቸዋል ማለት ነው። ይህ ደግሞ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በግብኣትነት የተገኙት ጉዳዮች ተብላልተው የሚያስገኙት ውጽአት ወይም ውጤት አመርቂ እንዳይሆን ያደርጋል። ስለዚህም የመምህራኑ የጥያቄ አጠያየቅ ድክመት ያለበት መሆኑ ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ የተሳነው እንዲሆን ያደርገዋል። በሌላ አገላለጽ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ የተሳነው እንዲሆን ምክንያት ይሆናል።

4.2.1.5. *የመረጃ ግብይት*

የመረጃ ግብይት የሚባለው የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ ሀሳብ የሚለዋወጡበት፣ በራሳቸው መርሆዎችን ፈልገው የሚያገኙበትና የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሂደት መሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት የሆነው የትምህርቱ አላማ በተማሪዎች ዘንድ ተተርጉሞ በአእምሯቸው እንዲሰርጽ፣ የመረጃ ፍሰቱ እንዲሳለጥና መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡ ለማድረግ ስለሚያስችል ትምህርታዊ መረጃ ይቀሰምበታል። ስለዚህም ወላንሳ የሆነ የመረጃ ፍሰት ያለበት፤ በአንድምታ መሰላል የመረጃ ግብይት የሚካሄድበት፤ ጽብረቃዊ ማዳመጥ የሚከናወንበት፤ ሂደታዊ የምዘና ስልቶች በጥቅም ላይ የሚውሉበት፤ በምዘናው ውጤት ላይ ተመስርቶ ግብረ መልስ የሚሰጥበት፤ በተማሪዎቹ ዳራዊ

እውቀት፣ በአዲሱ ትምህርታዊ መረጃና ተማሪዎቹ አዲስ የሚቀሰሙት እውቀት በነባራዊው አለም በጥቅም ላይ በሚውልበት ሁኔታ መካከል ትስስር የሚፈጠርበት፤ ጽብረቃ የሚከናወንበት እንዲሁም የትምህርታዊ መረጃው ጭምቃሳብ የሚከለስበት መሆን ይኖርበታል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለውን የመረጃ ግብይት እንዴትነት የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን እንዲሁም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያመለክታሉ። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ አስችሏል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል (t=-6.069, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -6069 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-5.38917 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰና ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-2.0229 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም የመረጃ ግብይቱ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል (4.1.1.1ን ይመልከቱ)። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው (4.1.1.2ና 4.1.1.3ን ይመልከቱ)።

በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ ያለው የመረጃ ግብይት ደካማ መሆኑ በምእራፍ ሁለት ከቀረበው ሀሳብ አንጻር ሲመረመር በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ረገድ የጋራ ግንዛቤ በሚጨበጥበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። አሉታዊ ተጽእኖው በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል። ተማሪዎቹ የሌሎችን ሀሳብ የመግለጽ ነጻነት ሳይጥሱ እምነታቸውን፣ አስተሳሰባቸውን፣ ግንዛቤያቸውን፣ ድጋፋቸውንና ተቃውሟቸውን በማስረጃ አስደግፈው በግልጽ ከማቅረብ ይልቅ ከመምህራኑ ወይም ሻል ካሉ ተማሪዎች የሚተላለፈውን ሀሳብ አሜን ብለው የሚቀበሉ አሜነኛ እንዲሆኑ ያደርጋል። የትምህርት አሰጣጡን በትክክለኛ ማስረጃ ላይ በተመሰረተ አመክንዮ ድምዳሜ ላይ ከማድረስ ይልቅ ግልብ ድምዳሜ ላይ

የሚያደርስና የማመዛዘን ችሎታ እንዳይዳብር ለሚያደርግ ችግር የሚያጋልጥ እንዲሆን ያደርገዋል። በትምህርቱ ሂደት የተሰነዘሩ ሀሳቦችን መገምገም፣ በራስ አባባል መግለጽ፣ ጨምቆ የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረስ፣ በተገለጹ ሀሳቦች ላይ ተንተርሶ ማብራሪያ የሚሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዳይከናወኑ ምክንያት ይሆናል። ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራቱን በብቃት ማከናወናቸውን አስመልክቶ በቂ መረጃ እንዳይገኝ የሚያርግ ሲሆን አለመገኘቱ በግብረመልስ አሰጣጡ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ተማሪዎቹ ተረጋግተው በግንዛቤያቸውና እንዲገነዘቡት በሚጠበቀው መረጃ መካከል ያለውን ክፍተት እንዳያገናዝቡና በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበውን መረጃ ጭምቃሳብ እንዳይጨብጡ ያደርጋል።

ቀደም ሲል በ4.2.1.1 ላይ ለማየት እንደተሞከረው የትምህርቱ አላማ መለካት የሚችል አይደለም። ይህ ሁኔታ የምዘና ስልቶቹ በግልጽ ካለመቀመጣቸው ጋር ተዳምሮ በትምህርቱ ሂደት የሚቀርበው ትምህርታዊ መረጃ አወካከልና አቀራብ ችግር ያለበት መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም የቀረበውን ትምህርታዊ መረጃ ተማሪዎቹ ይረዱት አይረዱት ወይም ይገንዘቡት አይገንዘቡት የመታወቁ ሁኔታም አጠራጣሪ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ በተከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ምን ያህል የእውቀት ግንባታ አካሂደዋል የሚለው ጥያቄ ምላሽ እንዳይገኝ ያደርጋል። የተማሪዎቹ ግንዛቤ ምን ያህል እንደሆነ ለክቶ ተገቢውን ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎቹ በተገነዘቡትና እንዲገነዘቡት በሚጠበቀው ትምህርታዊ መረጃ መካከል ያለውን ክፍተት የመሙላት ተግባር እንዳይከናወን ያደርጋል። ጽብረቃ በአንድ ትምህርታዊ ክንውን ላይ ያለን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ በማውጣት ጠንካራ ጎኑ የበለጠ የሚጠናከርበት፣ ደካማ ጎኑ ደግሞ የሚሻሻልበት መንገድ የሚታቀድበት ሂደት መሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። በመማር ማስተማሩ ሂደት ጽብረቃ አለመከናወኑ መምህራኑ በትምህርቱ ሂደት የነበረውን ጠንካራና ደካማ ጎን ፈትሸው ቀጣዩን የመማር ማስተማር ሂደት ለማሻሻል የሚያስችሉ ተግባራትን አለመቀየሳቸውን ያሳያል። ጽብረቃ የእድሜ ልክ ትምህርት የሚቀሰምበት ከመሆኑ አንጻር በክንውኑ ሂደት ከነበረው ስህተት በመማር በቀጣዩ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለመከናወኑንም ያስገነዝባል። ይህም ተመሳሳይ የአተገባበር ስህተቶች እንዳይታረሙና በዘላቂነት እየተከሰቱ የትምህርቱን ሂደት የሚያደናቅፉ እንቅፋቶች እንዲሆኑ ያደርጋል። ክስተቱ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ እንዲገበዩ የሚፈለገውን እውቀት በበቂ ሁኔታ እንዳይገበዩ የሚያደርግ መሰናክል መኖሩንና አጠቃላይ የትምህርታዊ ተግባቦት ስርአቱ ለተግባቦት ሂደት እንቅፋት የተጋለጠ መሆኑን ያሳያል ።

ትምህርታዊ የተግባቦት ስርአት በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች ዘንድ መረጃ ግብይታዊ በሆነ መንገድ የሚሰራጭበት መሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። መረጃ ያለእንቅፋት መሰራጨት የሚችለው በመረጃ ግብይት ሂደት አማካኝት በተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል የመረጃ ልውውጥ ሲከናወን ነው። የመረጃ ግብይቱ ደካማ መሆኑ መረጃ በሚወከልበት፣ በሚተረጎምበት፣ በሚንሸራሸርበት፣ በሚብላላበትና ግብረ መልስ በሚሰጥበት ሂደት ላይ ችግር መኖሩን ያመለክታል። ድክመት መኖሩ የተግባቦት ሂደቱ

ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል። መጋለጡ ደግሞ ተሳታፊዎቹ ጽንሰ ሀሳቦችን፣ አመለካከቶችን፣ ነባራዊ እውነታዎችንና የግል አስተያቶችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መጋራት እንዳይችሉና በተግባቡቱ ሂደት በተላለፈው መረጃ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደርሱ የሚያደርግ የተግባቦት ሂደት እንቅፋት የተጋረጠባቸው መሆኑን ያስገነዝባል። ሁኔታው የተግባቡቱን ሂደት ያውከዋል። ስለዚህም መምህራን በትምህርቱ ሂደት ማስተላለፍ በተፈለገው መረጃ ረገድ ከተማሪዎቻቸው ጋር በጥሩ ሁኔታ ለመግባባት ይቸገራሉ። በዚህም የተነሳ የትምህርቱ ሂደት የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ የተሳነው ይሆናል።

የመረጃ ግብይቱ ደካማ መሆኑ ከትምህርታዊ የተግባቦት ስርአት አንጻር ሲመረመር በክፍል ውስጥ ግብአት ሆነው የተገኙት ጉዳዮች ተብላልተው ውጽኣት እንዲሆኑ በሚከናወነው የመረጃ ልውውጥ ረገድ ችግር መኖሩን ያሳያል። ከፍ ሲል ለማየት እንደተሞከረው የመረጃ ግብይቱ ደካማ መሆኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ነጻ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ እንዳይኖር ያደርጋል። ስለዚህም የሀሳብ ልውውጥ ሂደቱ ወላንሳ ከመሆን ይልቅ አሜነኛ፣ ሞገደኛ ወይም አሜነኛ-ሞገደኛ የመሆን ሁኔታ ያመዘነበት ይሆናል። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹን የሌሎችን ስሜት የሚጎዱ፣ መብት የሚጋፉና ጫና የሚያደርጉ ሰዎችን ቁጡና አሜነኛ ሳይሆኑ በአሳማኝ ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ በራስ መተማመን በተሞላበት ሁኔታ እንዳይጋፈጡ ያደርጋቸዋል። በቀደመ እውቀት ላይ ተመስርቶ መረጃን መምረጥ፣ ማመዛዘን፣ መተንተንና በተከናወነው ትንታኔ ላይ ተመስርቶ ድምዳሜ ላይ መድረስን እንዳያከናውኑ እንቅፋት ይሆናል። መረጃ የሚለዋወጡበትን የተግባቦት ስርአትም ግብይታዊ ሳይሆን በአንድ አቅጣጫ መረጃ የሚፈስበት መስመራዊ እንዲሆን ያደርገዋል።

በተመሳሳይ በመረጃ ግብይቱ ላይ ያለው ድክመት ከተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ አንጻር ሲመረመር ማሕቀፉ እንዲያስመዘግብ በሚጠበቀው ውጽኣት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። መልእክት ተቀባዮች መልእክት አስተላላፊዎች የሚያስተላልፉትን መልእክት በትኩረት በሚከታተሉበት፣ ጥያቄ በሚጠይቁበት፣ የተላለፉትን መልእክቶች በራሳቸው አባባል በሚገልጹበትና በሚገመግሙበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በተከናወነው ተግባር ውጤታማነት ላይ እንዲጸበርቁና ተገቢውን የማሻሻያ ርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደርጋል። አንድን ተግባር ሲያከናውኑ ከንውኑ በሚፈልገው አተገባበርና በክንውኑ መካከል የነበረውን ክፍተት ፈትሸው ክፍተቱን ለመሙላት የሚያስችሉ አካሄዶችን እንዳይቀይሱ መሰናክል ይሆናል። መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት የነበራቸውን አተገባበር መለስ ብለው ሙያው በተመሰረተበት ንድፈ ሀሳብ መጠገጊያነት በመፈተሽ በአተገባበር ሂደት የነበራቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተው ድምዳሜ ላይ እንዳይደርሱና ድምዳሜውን በቀጣይ ለሚያከናውኑት የማስተማር ስራ ውጤታማነት በጥቅም ላይ እንዳያውሉ ያደርጋል። በመማር

ማስተማሩ ሂደት በትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት የተሰራጨ መረጃዎች ጭብጥ ተጨምቆ እንዳይቀርብ፣ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በተግባቦቱ ሂደት ባከናወኑት ተግባርና በተሰራጨው መረጃ ረገድ የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውን ማረጋገጥ እንዳይቻል፣ በተሰራጨው ትምህርታዊ መረጃ ላይ መጸብረቅ እንዳይቻልና የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደረስ እንቅፋት ይሆናል። በጥቅሉ የመረጃ ግብይት ሂደቱ መምህራንና ተማሪዎች በተላለፈው መረጃ ረገድ የጋራ ግንዛቤን እንዳይጨብጡ ለሚያደርግ ችግር እንዲጋለጡ ያደርጋል። ይህ ደግሞ በግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውስጥ በሚከናወነው ትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ግብኣት ሆነው የተገኙት ጉዳዮች ተብላልተው ውጽኣቱን በሚያስገኙበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ስለዚህም የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ የሚችል ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አዳጋች ነው።

4.2.2. በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ በትምህርት ደረጃ የታየ ልዩነት

የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በትምህርትና በስልጠና የሚዳብር ነው (Hargie, 2006)። በዚህ መሰረት የጥናቱን ዋና አላማ መሰረት አድርጎ ይህ ጥናት ካነሳቸው ዝርዝር ጥያቄዎች መካከል አንዱ "የትምህርት ደረጃ ልዩነት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት እንዲኖር አድርጓል?" የሚል ነበር። ክህሎቱ በትምህርትና በስልጠና የሚዳብር እንደመሆኑ መጠን የትምህርት ደረጃ ልዩነት የአጠቃቀም ልዩነት እንዲያመጣ ይጠበቃል። በዚህ ጥናት የታዩት ተጠኚዎች የትምህርት ደረጃ ዲግሪና ዲፕሎማ ነው (ሰንጠረዥ 2ን ይመልከቱ)። በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ በሰለጠኑ መምህራን መካከል ያለው የትምህርት ደረጃ ልዩነት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት እንዲኖር ማድረጉን የሚያሳይ የስታቲስቲካዊ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 9 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 25፡ የትምህርት ደረጃ ልዩነት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ያመጣውን ልዩነት የሚያሳዩ መረጃዎች

Report

observed comminicative skills

educn	Mean	N	Std. Deviation
Diploma	70.7763	24	20.72361
Degree	87.7775	12	2.86752
Total	76.4433	36	18.73160

በሰንጠረዥ 25 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራንን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳየው አማካይ 87.7775 ነው። በመደበኛ

አሰረጫጨት 90 እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን የሚያሳየው አማካይ ደግሞ 70.7763 ነው፡፡ በመደበኛ አሰረጫጨት 90 እንዲሆን ይጠበቃል፡፡በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ላይ ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው ያነሰ ነው፡፡ ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከዲፕሎማዎቹ በአማካይ በ17.0012 ይበልጣል፡፡ 20.72361 የሆነው መደበኛ ልይይት የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ በሆነ መምህራን መካከል ያለው የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ልዩነት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ ከሆነው (2.86752) እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ በሆነ መምህራን መካከል ያለው ልዩነት ከዲፕሎማዎቹ ያነሰ ነው፡፡ በጥቅሉ ምንም እንኳ በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው ያነሰ ቢሆንም በንጽጽር ሲታይ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከዲፕሎማዎቹ የተሻለ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል፡፡

በሁለቱም ደረጃዎች ያሉት መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የክፍል ከሚጠበቀው አንጻር በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሁለቱም አጠቃቀም ከሚጠበቀው ያነሰ ነው፡፡ ማነሱ ደግሞ በሁለቱም የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቀውን ያህል የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዳይኖርና የመረጃ ፍሰቱ ለተግባቦት እንቅፋት እንዲጋለጥ የሚያደርግ ችግር ያለበት ነው፡፡ ሁኔታው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ሲሆን የመምህራኑ የስልጠና ሁኔታ ምን ይመስላል?፡፡ ለተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ተገቢውን ትኩረት የሰጠ ነው ወይ? ይህ ሁኔታስ በሁሉም መምህራን ላይ ይታያል ወይ? የሚሉት ጉዳዮች በቀጣይ መጠናት ያለባቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከፍ ሲል ለማየት እንደተሞከረው ይህ ጥናት ያነሳው ሁለተኛ ዝርዝር ጥያቄ በመምህራኑ መካከል ያለው የትምህርት ደረጃ ልዩነት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት ማምጣቱን የተመለከተ ነበር፡፡ መልሱ አዎ በጣም ጥቂት ልዩነት አምጥቷል የሚል ነው፡፡ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪና ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው ያነሰ ሲሆን የዲግሪዎቹ ከዲፕሎማዎቹ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

4.2.3. የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር

የመማሪያ ክፍል ሰዎች የመምህርነትንና የተማሪነትን ሚና ወስደው እርስ በእርስ ለማማር የሚሰባሰቡበት ስፍራ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ለመማማር በሚካሄደው ተግባቦት ማህበራዊ ግንኙነቱ ደርዝ

የሚይዝበት መንገድ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ተብሎ እንደሚጠራ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። የክፍል ውስጥ መስተጋብር የትምህርታዊ ተግባቦት ተሳታፊዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚቀርቡ ትምህርታዊ መረጃዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የንቁ መማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም የሚያከናውኑት ተራክቦ ነው። ይህ ተራክቦ መረጃን መረዳት፣ መገንዘብ፣ ማብላላት፣ ማዋሀድና እውቀትን መገንባት እንዲኖር በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ ተግባራት በመሳተፍ ትምህርታዊ መረጃዎችን የመለዋወጥ ተግባር ይከናወንበታል። ልውውጡ ተማሪዎቹ የሚቀርቡላቸውን ትምህርታዊ መረጃዎች አስመልክቶ የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጡና የቋንቋ ችሎታቸው እንዲዳብር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህ ሀሳብ የክፍል ውስጥ መስተጋብር የእውቀት ግንባታ ሂደት መሰረት የሚጣልበት መሆኑን ያስገነዝባል።

ይህ ጥናት ካነሳቸው መሰረታዊ ዝርዝር ጥያቄዎች መካከል ሁለተኛው "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ያለው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር እንዴት ያለ ነው?" የሚል ሲሆን ምላሹ "ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው።" ይሆናል። እዚህ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስቻለው የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች በጥቅሉ ሲመረመሩ የተደረሰበት ውጤት ነው። የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን አስመልክቶ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን እንዲሁም የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊ መሆኑን ያሳያሉ። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን አመልክቷል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል (t=-21.033, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -21.033 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-22.97417 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-6.3160 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው (4.1.2.1ን ይመልከቱ)። መረጃው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያመለክታል።

ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው (4.1.2.2ና 4.1.2.3ን ይመልከቱ)።

የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ደካማ መሆኑ በትምህርቱ ሂደት በተሳታፊዎች መካከል የሚደረገው የእርስ በእርስ መስተጋብር የደከመ መሆኑንና የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊዎች ጥሩ የፍቺ ምስረታና የእውቀት ግንባታ እንዳያከናውኑ ለሚያደርግ እንቅፋት የተጋለጠ መሆኑን ያሳያል። በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረት የመማር ማስተማር ሂደት የተግባቦት ስርአት ነው። የተግባቦት ስርአት ሰባት አላባውያን ያሉት ሲሆን ከመካከላቸው አንዱ የመልእክት መተላለፊያ (channel) ነው። የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት መተላለፊያ ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ የተገነባበት የትምህርት አቀራረብ ስልት ነው። የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆኑ ከትምህርታዊ ተግባቦት አላባውያን መካከል አንዱ የሆነው የመልእክት መተላለፊያው ድክመት ወይም ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ችግሩ መልእክት ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ የሚተላለፍበት ሁኔታ ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ መሆኑን ያሳያል። በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውስጥ የመልእክት አስተላላፊነትንና የመልእክት ተቀባይነትን ሚና የሚወስዱት መምህራንና ተማሪዎች ናቸው። የመልእክት መተላለፊያው ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ ነው ማለት መረጃ የሚፈለገውን ያህል ከአንዱ የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ወደ ሌላው አይተላለፍም። ስለዚህም መልእክት አስተላላፊነትን የወሰዱት ተሳታፊዎች መረጃን በትክክል ወክለው ቢያስተላልፉም እንኳ መልእክት ማስተላለፊያው ላይ ችግር ስላለ መልእክት ተቀባይ የሆኑት ተሳታፊዎች የተሟላ መረጃ አይደርሳቸውም። ስለዚህም ተቀብለው በትክክል አይተረጉሙትም። ተርጉመው ካልተረዱት ደግሞ ትክክለኛ ግብረ መልስ መስጠት አይችሉም። ስለዚህም መልእክት አስተላላፊ የነበረው የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ትክክለኛ ግብረ መልስ አያገኝም። ይህ ደግሞ በቀጣይ የሚካሄደውን የተግባቦት ሂደት ያውከዋል። የተግባቦት ሂደቱ መታወኩ የተግባቦት ሂደቱ ተሳታፊዎች በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደርሱና ጥሩ የሆነ የጋራ ግንዛቤ እንዳይጨብጡ ያደርጋል።

የጥናቱ ሞዴል በሆነው ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ውስጥ ተማሪዎችና መምህራን ግብኣት የሆኑትን አዲስ የትምህርት ይዘት፣ ዳራዊ እውቀትና ግላዊ ባህሪ ይዘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገናኛሉ። በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከናወነው ማህበራዊ መስተጋብር አማካኝነት እነዚህን ጉዳዮች አብላልተውና መረጃ ተለዋውጠው አዲስ ግንዛቤን ይጨብጣሉ። ይህ ግንዛቤ በቀደመ እውቀታቸው ላይ አዲስ ግንዛቤን የሚያክል የእውቀት ግንባታ እንዲካሄድ ያደርጋል። የእውቀት ግንባታው ሲካሄድ የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤት አስገኘ፤ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊዎች አዲስ የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥን አመጡ ማለት ነው። ይህ ለውጥ የተግባ-ግብይታዊ የመማር

ማስተማር ማሕቀፉ ውጽኣት ነው። በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ ድክመት አለ ማለት የሚፈለገውን ያህል ማህበራዊ መስተጋብር አይከናወንም። ካልተከናወነ በክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ተሳታፊዎች መካከል ነጻ የሆነ የሀሳብና የአሰራር ልውውጥ አይካሄድም። ልውውጡ ባልተካሄደበት ሁኔታ ቀደም ሲል በነበራቸው እውቀት ላይ አዲስ እውቀትን ለማከል የሚያስችላቸውን ግንዛቤ አይጨብጡም። ምክንያቱም መስተጋብሩ ደካማ ስለሆነ የቀረበውን ትምህርታዊ መረጃ መረዳት፣ መተርጎም፣ ማብላላት፣ ማዋሀድና ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ማስተሳሰርን አያከናውኑም። ስለዚህም ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚፈለገውን ውጤት ወይም ውጽኣት ማስገኘት ይሳነዋል።

በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው ቋንቋ በማህበራዊ መስተጋብር ይለመዳል። በትምህርታዊ ተግባቦት መሰረተ ሀሳብና በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ማብራሪያ ላይ እንደተገለጸው ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብር መረጃን ከአንዱ ወደ ሌላው የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ የሚተላለፍበት መንገድ ነው። የጥናቱ ውጤት የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆኑን አሳይቷል። ይህ ማለት ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘት የሚገነዘቡበት፣ የቀደመ እውቀታቸው አካል የሚያደርጉበትና በጥቅም ላይ ማዋልን የሚለማመዱበት ማህራዊ መስተጋብር ደካማ ነው። ይህም የቋንቋውን አጠቃቀም የሚለምዱበት ሁኔታ የደከመ መሆኑን ያሳያል። በጥቅሉ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆኑ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱን፣ የግብይታዊ መማር ማስተማር ማሕቀፉንም ሆነ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የቋንቋውን አጠቃቀም የሚለምዱበትን መንገድ ያውከዋል። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚፈለገውን ያህል ውጤት ማግኘት ያዳግታል።

በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር መምህራን በስልጠና ሂደት የሚያዳብሩት ጉዳይ ነው። በምእራፍ ሶስት እንደተገለጸው ደግሞ በጥናቱ የተወሰዱት ሁሉም መምህራን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር ሙያ ሰልጥነው የወጡ ናቸው። ይህም መምህራንን በሚያሰለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የሚሰጠው ቦታ ምን ይመስላል? በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ሲሰለጥኑ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበርን በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ከመማር ባለፈ በተግባር የሚተረጉሙበትን መንገድ ምን ያህል ይለማመዳሉ? መምህራኑ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ላይ ምን ያህል ግንዛቤ አላቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል። ከዚህ በተጨማሪ በምእራፍ ሁለት በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ለማየት እንደተሞከረው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች አንዱ የትምህርት ቤት አውድ ነው። ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመምህርነት ሰልጥነው የሚወጡ መምህራን በማስተማር ስራ ሲሰማሩ የሚገቡበት የትምህርት ቤት አውድ በስልጠና ሂደት በገበዩት እውቀት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድረው በምን መልኩ ነው? ምናልባት በከፍተኛ ትምህርት ሰልጥነው ቢውጡም እንኳ በስራ አለም ያለው አካባቢያዊ ተጽእኖ በትምህርት አለም ላይ የቀሰሙትን እውቀትና

ልምድ ወደ ጎን ትተው በትምህርት ቤት አውድ ውስጥ በስፋት የሚተገበረውን አሰራር እንዲከተሉ ያደርጋቸው ይሆን ወይ? የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት፡፡ ይህ መልስ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ርምጃ መወሰድ ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡

በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አራት ዋና ዋና ዘርፎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ የነዚህን ዘርፎች ተናጠላዊ የአተገባበር ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.2.3.1. *የተማሪዎች በይነሰባዊ ፍላጎት መሟላት*

በይነሰባዊ ፍላጎቶች በአንድ የተግባቦት ሂደት ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያከናውኑ ተሳታፊዎች ለሚኖራቸው የእርስ በእርስ ግንኙነት መሟላት ያለባቸው ሰብኣዊ ፍላጎቶች ሲሆኑ የቁጥጥር፣ የአካቶና ትኩረት የማግኘት ፍላጎቶች ናቸው፡፡ በአንድ የመማሪያ ክፍል ጥላ ስር ተሰባስበው የሚገኙ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን በጥሩ ሁኔታ ማከናወን እንዲችሉ እነዚህ ሰብኣዊ ፍላጎቶች መሟላት እንደሚኖርባቸው በምእራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡ የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራትን የክንውን ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣራና የተለያየ መሆኑን እንዲሁም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታዩን ያሳያሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል (t=-7.876, df=35, p<0.05)፡፡ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -7.876 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው፡፡ በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-2.03806 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል፡፡ ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል፡፡ ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል፡፡ Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ፡፡

የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-2.6259 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የተማሪዎቹ በይነሰባዊ ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ

የሚያስችሉ ተግባራት ክንውን ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ይታይበታል (4.1.2.1ን ይመልከቱ)። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው (4.1.2.2ን ይመልከቱ)። በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎቶች ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት ክንውን ከሚጠበቀው አንጻር ድክመት ያለበት መሆኑ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በጥሩ ሁኔታ እንዳይከናወን የሚያደርግ እንቅፋት ይፈጥራል።

የተማሪዎቹን በይነሰባዊ ፍላጎት ማሟላት በሚያስችሉ ተግባራት አተገባበር ደካማ መሆኑ በክፍል ውስጥ በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በውጤት ማብራሪያው ለማየት እንደተሞከረው በመማር ማስተማሩ ሂደት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመምህራንን ትኩረት የሚያገኙት፣ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉት፣ ተጽእኖ የሚያሳድሩትም ሆኑ በራሳቸው ተንቀሳቅሰው የተለያዩ ተግባራትን የማከናወን ሀላፊነትን የሚወጡት በአብዛኛው ጥቂት ተማሪዎች ናቸው (4.1.2.ን ይመልከቱ)። ተማሪዎች በቡድን ውስጥ የመካተት እድል ቢገጥማቸውም የተካቶነትም ሆነ የአካቶነት ፍላጎታቸውን የሚያሟሉ ተግባራት ሲከናወኑ አይታዩም። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ ተገቢውን አቅጣጫ እንዲይዙ ለማድረግ የሚያስችል ቁጥጥር የመደረጉ ሁኔታ የደከመ ነው። ይህ ሁኔታ በክፍል ውስጥ የሚኖረው በይነሰባዊ ግንኙነት ለአደጋ የተጋለጠ እንዲሆን ያደርጋል። ለአደጋ መጋለጡ በክፍል ውስጥ የሚኖረው የተማሪዎች ስነምግባር እንዲበላሽና ክፍሉ ለስነስርአት ችግር እንዲጋለጥ በር የሚከፍት ጉዳይ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ በአንድ በተወሰነ ቡድን በመካተት ለሌሎች ድጋፍ የማድረግ፣ በዚያ ቡድን ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ የመገኘት፣ የዚያ ቡድን አባልነትን የማረጋገጥና ተገቢውን ድጋፍ የማግኘት እድል እንዳያገኙ ያደርጋል። ለሌሎች ያላቸውን የጓደኝነት ስሜት የመግለጽ፣ ለሌሎች እንደሚጨነቁ የማሳየት፣ ከሌሎች ትኩረትንና እንክብካቤን የማግኘት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት የእርስ በእርስ ግንኙነት የመመስረት ልምድን እንዳያዳብሩ ስለሚያደርጋቸው በክፍል ውስጥ በሚከናወነው መስተጋብር ላይ በነጻነት ለመሳተፍ ይቸገራሉ። ስለዚህም የአንድ ቡድን አባል በመሆን ለሌሎች ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም ከቡድኑ አባላት እውቅናን፣ ፍቅርን፣ ማህበራዊ ግንኙነትንና ድጋፍን ማግኘት ይሳናቸዋል። ይህም በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት በተማሪዎቹ መካከል የሚኖረውን እርስ በእርስ የመደጋገፍ፣ ግንዛቤን የመጨበጥና በጋራ እውቀትን የመገንባት ሂደት ያዳክመዋል። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ የውሳኔ ሰጭነት ሚናን እንዳይጫወቱ፣ ህግን በራሳቸው የማክበር ሀላፊነት እንዳይወስዱና በአካባቢያቸው ላይ ተጽእኖ ማሳደር እንዳይችሉ ያደርጋል። በግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ከተማሪዎች እንዲሁም ተማሪዎች ከመምህራን የሚያደርጉትን መስተጋብር ስለሚቀንሰው የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚፈለገውን የትምህርት ውጤት ወይም ውጽኣት ማስገኘት የተሳነው እንዲሆን ያደርጋል። በክፍል ውስጥ የሚከናወነው ማህበራዊ መስተጋብር እንዲቀንስ

ስለሚያደርግ የተማሪዎቹ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ በሚዳብርበት ሁኔታ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

4.2.3.2. *የክፍል አያያዝ*

የክፍል አያያዝ የመማሪያ ክፍሉ ማህበራዊ አደረጃትና ውጫዊ ገጽታ ደርዝ የሚይዝበት መንገድ መሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። ማህበራዊ አደረጃጀት ተማሪዎቹ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑበት ሁኔታ የሚደራጅበትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ ነው። ውጫዊ ገጽታ ደግሞ በክፍል ውስጥ ጥሩ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይከናወን ዘንድ የተማሪዎቹ አቀማመጥ ፈር የሚይዝበት አሰራር ነው። የክፍል አያያዙን አስመልክቶ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን እንዲሁም የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን ያሳያሉ። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለመረዳት አስችሏል።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል (t=-9.308, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -9.308 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-2.6200 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-3.1027 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚተገበረው የክፍል አያያዝ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው።

ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የክፍል አያያዙ ድክመት ያለበት መሆኑን ያሳያሉ። ይሁን እንጂ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙ መረጃዎች ጥናቱ በተካሄደባቸው ክፍሎች በክፍል አያያዝ ረገድ ድክመት ቢታይም በጠንካራነት የሚነሱ አተገባበሮች መታየታቸውን ያመለክታሉ። በጥንካሬ የሚነሱት

አተገባበሮች ዴሞክራሲያዊ የክፍል አያያዝ ገኖ በሚታይባቸው የመማሪያ ክፍሎች ያሉ ጥሩ አመራርና ጥሩ የክፍል ውስጥ ዲሲፕሊን ናቸው። በደካማነታቸው የሚነሱት ደግሞ በክፍል አያያዝ፣ በተማሪዎች አቀማመጥና የስነስርአት ግድፈት ሲከሰት በሚወሰዱ ርምጃዎች ረገድ የታዩ ክስተቶች ናቸው። ግዴለሽነት ጎልቶ የሚታይባቸው የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎች ለስነስርአት ችግር የተጋለጡ በመሆናቸው ትኩረታቸውን አሰባስበው በትምህርቱ ላይ የማያደርጉበት ሁኔታ በስፋት ይታያል። የመምህራን የበላይነት ገኖ የሚታይባቸው ክፍሎችም አሉ። እነዚህ የመማሪያ ክፍሎች ፍርሀት የነገሰባቸው በመሆናቸው ተማሪዎች በነጻነት የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊዎች የማይሆኑበት ጥቂት አይደለም። ይህ መረጃ ዲሞክራሲያዊ የክፍል አያያዝ ባለባቸው ክፍሎች ጠንካራ አተገባበር የሚታይ ቢሆንም ታጋሽና ፈላጭ ቆራጭ የክፍል አያያዝ ዘይቤዎች በሚታዩባቸው የመማሪያ ክፍሎች የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን የሚያውኩ ጉዳዮች መኖራቸውን ያመለክታል። በጥቅም ላይ ሲውሉ የታዩት የተማሪዎች አቀማመጦች ተለምዷዊና ግጥምጥም ሲሆኑ የፈረስ ኩቴ አቀማመጥ ሲተገበር አልታየም። ይህም መምህሩን ወይም ተማሪዎቹን ከእይታ የሚያስወጣ በመሆኑ በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪ-ተማሪና የተማሪ-መምህር መስተጋብር ለችግር የተጋለጠ መሆኑን ያስገነዝባል።

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች የስነስርአት ግድፈት ሲያሳዩ የማስተካከያ ርምጃው አካላዊ ቅጣት የሚሆንበት ሁኔታ አለ (4.1.2ን ይመልከቱ)። አካላዊ ቅጣት የባህሪ ለውጥ ማምጣት ይቻል ዘንድ በአካል ላይ የህመም ስሜት እንዲሰማ የሚያደርግ የሀይል እርምጃ የመውሰድ ተግባር ሲሆን ከዘመናዊው ተማሪ መራሽ አሰራር ጋር የሚራመድ አይደለም (UNESCO, 2006)። ይህ ተግባር መምታትን፣ መግረፍን፣ ተንኳሽ የሆኑ ኢቃላዊ ምልክቶችን መጠቀምን፣ ማግለልን፣ የተለየ ትኩረት በተማሪዎች ላይ ማድረግንና ማንበርከክን ያካትታል። ምንም እንኳ የአካላዊ ቅጣት ሀሳብ አራማጆች ትክክለኛ የባህሪ ማረሚያ መንገድ ነው ብለው የሚያምኑ ቢሆንም ሳይንሳዊ የሆኑ ጥናቶች በስነምግባር ማረሚያነቱ ውጤት አልባ ከመሆኑም ባሻገር በተማሪዎች አካልና አእምሮ ላይ የጤና ችግር የሚያስከትል ተግባር መሆኑን አረጋግጠዋል። በመሆኑም አካላዊ ቅጣት ተማሪዎችን የሚያሸቆጠቁጥ መስሎ ቢታይም ከዘመናዊው ተማሪ መራሽ አሰራር አንጻር የሚደገፍ አይደለም። ዘመናዊው ተማሪ መራሽ አሰራር ተማሪዎች እንዲመረምሩ፣ እንዲያስቡ፣ ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ ሂሳዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩና ለጥያቄዎች መልስ መፈለግን እንዲወዱ የሚያደርግ ነው። ከዚህ አንጻር አካላዊ ቅጣት ተማሪዎችን ከማሰብ፣ ከመጠየቅ፣ ለጥያቄዎች መልስ ከመፈለግ፣ ነገሮችን በሂስ አይን ከማየትና ግላዊ አላማን ከግብ ከማድረስ ይገድባል (Naz, Khan & Daraz, 2011)። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን ውጤታማነት ከማደናቀፍ አልፎ ማህበረሰብን ተወዳዳሪ፣ ፈጣሪና ለዋጭ ሀይል እንዳያፈራ ያደርጋል።

ከዚህ በተጨማሪ አካላዊ ቅጣት ከህግ ጋር የሚጣረስ አሰራርን ያሰፍናል። ምክንያቱም እንደ Negarit Gazeta (1960) ድንጋጌ እያንዳንዱ ሰው የማሰብና የሰውን ስሜት በማይጎዳና ህግ ባልጣሰ ሁኔታ

ሀሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፡፡ በሚያከናውናቸው ተግባራትም የሌሎችን መብትና ስሜት ማክበር ይጠበቅበታል፡፡ በኢፌድሪ ህገ መንግስት እያንዳንዱ ሰው ደህንነቱ ተጠብቆ በነጻነት የመኖር መብት አለው (Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, 1994)፡፡ ከዚህ አንጻር ተማሪዎች አካላዊ ቅጣት እንዲቀጡ ማድረግ ሀገሪቷ የምትተዳደርበትን ህገ መንግስትም ሆነ የፍትሐ ብሔር ህግ የጣሰ አሰራር ነው፡፡ የሰዎችን ደህንነት ይጎዳል፤ ሀሳብን በነጻነት ከመግለጽም ይገድባል፡፡ መምህራን የተማሪዎቻቸውን አካላዊና አእምሯዊ እድገት የመቅረጽ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ መምህራኑ ከሚያከናውኑት ተግባር ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ በሀይል እየገሩ የሚቀርጹት ተማሪ በማህረሰቡ ውስጥ ኃላፊነትን በሚረከብበት ጊዜ ሁሉን ነገር በሀይል የሚያስፈጽም እንጂ አዳዲስ ሀሳቦችን የሚያፈልቅና ራሱን ለህግ የሚያስገዛ እንዲሆን አይጠበቅም፡፡ ስለዚህም በተማሪዎች ላይ የሚወሰድ አካላዊ ቅጣት ሊታረም ይገባዋል፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደት የስነምግባር ችግርን ለመቆጣጠር አወንታዊ የሆነ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ አወንታዊ የባህሪ ማስተካከያዎች የሚባሉት ሁሉም ተማሪዎች በትምህርታዊ ተግባራት መሳተፋቸውን ማረጋገጥ፣ ለልዩነቶች ቦታ መስጠት፣ ትምህርታዊ ተግባራት የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችን ያማከሉ መሆናቸውን ማረጋገጥና ሁሉም ተማሪዎች ከተንኳሽ ንግግር ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ናቸው፡፡ የተማሪዎችን ስም ጠርቶ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ ተማሪዎቹን በሙሉ በአይን መቆጣጠር፣ የረብሻ ባህርያትን ሲያሳዩ ወዲያውኑ ርምጃ መውሰድ፣ ተገቢ የሆነ ግብረመልስ መስጠት፣ ጥሩ ባህሪ በአርኣያነት ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግና ተማሪዎች ለሚያበረክቱት አስተወጽኦ አወንታዊ ማበረታቻዎችን መጠቀም ረብሻን አወንታዊ በሆነ መንገድ ለመቆጣጠር ያስችላሉ፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ተገቢ የሆነ ባህሪ በጥሩ ሁኔታ ሊበረታታ የሚችለው እያንዳንዱ የተግባቡቱ ሂደት ተሳታፊ መብትና ግዴታውን እንዲያውቅ በማድረግ መሆኑን Porter (2000)፣ Ciaccio (2004)ና Mackay (2006) ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የስነምግባር ችግር ሲያሳዩ አወንታዊ የሆነ የማስተካከያ ርምጃ በጥቅም ላይ መዋሉ ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ መሆኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ተማሪዎቹን በነጻነት የሚጠበቅባቸውን ተግባር የሚያከናውኑ የተግባቡቱ ሂደት ንቁ ተሳታፊ ሳይሆን ከመምህሩ የሚተላለፈውን መረጃ የሚቀበሉ ፍጡ ተመልካች ያደርጋቸዋል፡፡ በጥቅሉ ሲታይ በክፍል አያያዙ ላይ የታየው ድክመት በትምህርታዊ ተግባቡት ሂደቱ ያለው መስተጋብር ጥሩ የሆነ የመረጃ ግብይት የሚካሄድበት እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ ጥሩ የመረጃ ግብይት ካልተካሄደበት ደግሞ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚፈለገውን ውጽኣት ማስገኘት ይሳነዋል፡፡

4.2.3.3. *ትምህርታዊ መስተጋብር*

ትምህርታዊ መስተጋብር የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች የፍቺ ምስረታን የሚያከናውኑበት የእርስ በእርስ መስተጋብር ሂደት መሆኑ በምእራፍ ሁለት ተገልጿል። የፍቺ ምስረታ በትምህርትነት በቀረበው መረጃ ረገድ የሚፈጠር የጋራ ግንዛቤ ነው። የፍቺ ምስረታ የሚከናወንበት የክፍል ውስጥ መስተጋብር ትምህርታዊ ተግባራት የሚከናወኑበትን፣ ተማሪዎች የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑበትን፣ ከመምህራን ወይም የተሻለ ችሎታ ካላቸው ብጤዎች ድጋፍ የሚያኙበትን፣ ሀሳብ የሚለዋወጡበትን፣ የሚተላፍላቸውን የመረጃ ግብኣት የሚቀበሉበትንና እነሱም መረጃን በግብኣትነት የሚያስተላልፉበትን ክንውን ይመለከታል። የትምህርታዊ መስተጋብሩን የአተገባበር ሁኔታ በጥቅል የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ በጣም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን እንዲሁም የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን አሳይተዋል። ይህም በምልከታ በተገኘውና በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን አመልክቷል።

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል (t=-17.895, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -17.895 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-7.8983 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-5.9649 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው (4.1.1.1ን ይመልከቱ)፡ ይህም ትምህርታዊ መስተጋብሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን ያሳያል። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው (4.1.1.2ን ይመልከቱ)።

ከምልከታም ሆነ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ትምህርታዊ መስተጋብሩ ድክመት ይታይበታል። ድክመቱ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን በጥሩ ሁኔታ

እንዳያከናውኑና ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት የሚያከናውኑት እያንዳንዱ ተግባር ስኬት ላይ ለመድረስ የሚያስችል መሆኑን እንዳይገነዘቡ ያደርጋል፡፡ አለመገንዘባቸው ደግሞ ትምህርቱን ለመማር በሚኖራቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው ውስጣዊ ተነሳሽነት አንድን ተግባር ለማከናወን የሚቀሰቅስ ጠንካራው የተነሳሽነት አይነት እንደመሆኑ መጠን በአሉታዊ ተጽእኖ ስር የወደቀ መሆኑ ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራትን ከውስጥ በመነጨ ፍላጎት እንዳያከናውኑና የቀረበላቸውን ትምህርታዊ መረጃ የማወቅ ፍላጎት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለዚህም በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት መስተጋብር የደከመ ይሆናል፡፡ መምህራኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎቹ ከሚያከናውኗቸው ትምህርታዊ ተግባራት ጋር ያላቸው ቁርኝት መላላቱ ተማሪዎቹን ትምህርታዊ ተግባራትን ትኩረት ሰጥተው እንዳያከናውኑ ለሚያደርግና ለስነምግባር ችግር ይዳርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ መራሽ አለመሆኑ ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ አለመሆኑ ተማሪዎቹ ሀላፊነትን የሚጋሩበት፣ የሚሳተፉበትና በራሳቸው ችግር ፈቺ የሆኑ ተግባራትን የሚያከናውኑበትን የመማር ማስተማር ሂደት ያዳክመዋል፡፡ ይህ ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን ተማሪዎች ፍጥ ተቀባይ የሆኑበትና የመምህራን የበላይነት የሚንጸባረቅበት እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ መረጃው ተማሪዎቹ የሚማሩት ከሚያከናውኑት ተግባር ሳይሆን ከሚነገራቸው ወይም ሌሎች ከሚያከናውኑት ተግባር መሆኑን ያመለክታል፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደት ምልልሳዊ መስተጋብር የሚከናወንበት ሁኔታ ባይታጣም በአብዛኛው ግን ተራ መስተጋብር የሚከናወንበት መሆኑ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን መረጃ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሳይሆን በአንድ አቅጣጫ የሚፈስበት፣ በክፍል ውስጥ የተጋጋለ የሀሳብ ልውውጥ የማይከናወንበት፣ ተማሪዎች በሚያከናውኑት የሀሳብ ልውውጥ አማካኝነት የጋራ ግንዛቤን ለመጨበጥ የሚችገሩበት እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚፈለገውን ውጤት እንዳያስመዘግብና ተማሪዎቹ ሙሉ በሙሉ በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው የክፍል ውስጥ መስተጋብር ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በክፍል ውስጥ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚደረገው ድጋፍ ዝቅተኛ መሆኑ መጠነኛ ድጋፍ ተደርጎላቸው ወደሚፈለገው ደረጃ መምጣት የሚችሉ ተማሪዎች ወደ ኋላ እንዲቀሩና የክፍል ውስጥ መስተጋብር ሂደቱ ተሳታፊ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ ክስተቱ የትምህርት ፍትሀዊነትን የሚያረጋግጥ አሰራር የተዘረጋ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ የተማሪዎቹ ሙሉ ትኩረት በትምህርቱ ላይ አለመሆኑ የክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ክንውን ላይ እንዳይሳተፉ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ የተለያዩ የማበረታቻ አይነቶችን አለመጠቀማቸው ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ለሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ውስጣዊ ተነሳሽነትን እንዳያዳብሩ ምክንያት ይሆናል፡፡ እንዲሁም የማይፈለግን ባህሪ የሚያዳብሩ አወንታዊ ማበረታቻዎችን መጠቀማቸው

ተማሪዎች ያልተፈለገ ባህሪን እንዲያዳብሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ወጣ ያለ ባህሪ የሚያሳዩ ተማሪዎችን ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች ትኩረት ለማግኘት ሲሉ የማይፈለጉ ባህርያትን እንዲያሳዩ ይቀሰቅሳል። መምህራኑ ማህበራዊ ማበረታቻን መጠቀማቸው ጥሩ ቢሆንም ዘላቂነት ያለው ካለመሆኑም በላይ ለጥቂት ተማሪዎች ብቻ የሚሰጥ መሆኑ ሌሎቹ ተማሪዎች ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከትን እንዲያዳብሩና የበታችነት እንዲሰማቸው ያደርጋል። በጥቅሉ መምህራኑ ማበረታቻዎችን የሚጠቀሙበት ሁኔታ ደካማ መሆኑ በተማሪዎቹ ዘንድ የተፎካካሪነትና የተነሳሽነት ስሜት ስለማይፈጥር በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ የስኬት መሰረት የሆነው ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዳይዳብር ምክንያት ይሆናል። የሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር ራሱ ለተግባራዊ ርምጃ አይቀሰቅሳቸውም፤ ከውስጥ የመነጨ የስኬታማነትና የብቁነት ፍላጎትም አይኖራቸውም። ይህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

በአጠቃላይ በትምህርታዊ መስተጋብሩ ላይ የታየው ድክመት በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውስጥ ግብይታዊ የሆነ የመረጃ ፍሰትና ውጤታማነት እንዳይኖር ያደርጋል። የተግባቦት ሂደቱን መረጃ ከሁሉም ተሳታፊዎች ወደ ሁሉም ተሳታፊዎች የሚፈስበት ግብይታዊ ከመሆን ይልቅ በመደበኛነት ከተወሰኑ ተሳታፊዎች ወደ ተወሰኑ ተሳታፊዎች የሚፈስበት መስመራዊ ሞዴልን የተከተለ እንዲሆን ያደርገዋል። የተግባቦት ሂደቱን ተሳታፊዎችም በአንድ ጊዜ መረጃ የሚቀበሉና መረጃ የሚያስተላልፉ ከመሆን ይልቅ መረጃ የመቀበል ተግባርን ብቻ የሚያከናውኑ ያደርጋቸዋል። ይህ ደግሞ የትምህርት አሰጣጡን ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ሆነው አብሮ በመስራት በማህበር እውቀትን የሚገነቡበትና የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት ሂደት እንዳይሆን ያደርገዋል። ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉንም ግብኣት ሆነው የተገኙት ጉዳዮች በትምህርታዊ መስተጋብር አማካኝነት ተብላልተው የሚፈለገውን ውጽኣት የሚያስገኙበት እንዳይሆን ለሚያርጉ መሰናክሎች ያጋልጠዋል። የትምህርቱ ሂደት ተሳታፊ የሆኑት ጥቂት ተማሪዎች ብቻ መሆናቸው ከሚያከናውኑት ተግባር የሚማሩትና የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ የሚያመጡት እነዚያ ጥቂት ተማሪዎች እንዲሆኑ ያደርጋል። ቋንቋ በማህራዊ መስተጋብር የሚዳብር ከመሆኑ አንጻር ሲታይም የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸውን የሚያዳብሩት የመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ የሆኑት ጥቂት ተማሪዎች ብቻ መሆናቸውን ያመለክታል።

4.2.3.4. *የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር*

የመማር ማስተማር ስልቶች የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች በሚያከናውኑት ተግባር አማካኝነት መረጃ የሚለወጡባቸው፤ እውቀትን የሚገነቡባቸው፤ የአሰራር፣ የአስተሳሰብና የባህሪ ለውጥ የሚያመጡባቸው፤ አዳዲስ ግንዛቤዎችን የሚጨብጡባቸው እንዲሁም በተግባራዊ ልምምድና

በክፍል ውስጥ በሚከናወን የመማር ማስተማር ሂደት አዳዲስ ክህሎትን የሚያዳብሩባቸው በመርህ የተደገፉ አሰራሮች ናቸው፡፡ እነዚህ አሰራሮች የንቁ መማር ማስተማር ስልቶች ትግበራ፤ ተግባር ተኮር የትምህርት አቀራረብን፤ ልይይታዊ መማር ማስተማርን፤ ባለብዙ ደረጃ የመማር ማስተማር ተግባራት በጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ፤ ባለብዙ ደረጃ የመማር ማስተማር ማእከላት አደረጃጀትን፤ የችግር ፈቺ ተግባራት ክንውንን እንዲሁም ልቀታዊ የትምህርት አቀራረብን ይመለከታሉ፡፡ በዚህ ዘርፍ የተዳሰሱ ተግባራትን የአተገባበር ሁኔታ የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን እንዲሁም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን ያሳያሉ፡፡ ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን አመልክቷል፡፡

ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል (t=-45.471, df=35, p<0.05)፡፡ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -45.471 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው፡፡ በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-10.41778 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል፡፡ ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል፡፡ ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል፡ ፡ ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ፡፡ የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-15.1570 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው (4.1.2.1ን ይመልከቱ)፡፡ ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው፡፡ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው (4.1.2.2ና 4.1.2.3ን ይመልከቱ)፡፡

የንቁ መማር ማስተማር ስልቶች በጥቅም ላይ አለመዋላቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ዘመናዊ የሆኑ የመማር ማስተማር ዘዴዎች በጥቅም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ የደከመ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ መስተጋብር ከሚያከናውኗው ተግባራት የሚማሩበት ሁኔታ እንዲደክም ያደርገዋል፡፡ በማህበር በሚያከናውኑት ተግባር እውቀትን በሚገነቡበት ሁኔታ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ

ያሳድራል፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት በእለታዊ የትምህርት እቅድ ላይ በግልጽ አለመቀመጣቸው መከናወን ያለበት ተግባር በአግባቡ መከናወን አለመከናወኑን ማረጋገጥ እንዳይቻል ለሚያደርግ ችግር ያጋልጣል፡፡ በትምህርቱ ሂደት የቀረበውን ትምህርታዊ መረጃ ወደ ተማሪዎቹ ለማድረስ የሚያገለግለው የማስተማሪያ ዘዴ በግልጽ እንዳይታወቅም ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመማር ማስተማሩ ሂደት ከትምህርታዊ መረጃውና ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚራመድ የማስተማሪያ ዘዴን በጥቅም ላይ የማዋል ችግር እንዲገጥመው ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ የመማር ማስተማር ዘዴዎች የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት የመልእክት መተላለፊያ መንገዶች ከመሆናቸው አንጻር ሲታይ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ የመልእክት መተላለፊያ ችግር እንዲገጥመውና የተግባቦት እንቅፋት እንዲፈጠርበት የሚያደርግ መሰናክል መኖሩን ያስገነዝባል፡፡ ሁኔታው ተማሪዎቹ ትምህርታዊ መረጃውን በሚቀስሙበትና የእውቀት ግንባታን በሚያካሂዱበት መንገድ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

በመረጃዎቹ ላይ የቀረበው ትንታኔ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባር ተኮር የትምህርት አቀራረብ፣ ልይይታዊ መማር ማስተማር፣ ባለብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ማእከላት፣ ባለ ብዙ ደረጃ ትምህርታዊ ተግባራት፣ የችግር ፈቺ ተግባራት ክንውንና ልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ የመተግበሩ ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር በጣም ደካማ ነው፡፡ ደካማ መሆኑ የትምህርት አቀራረቡ ፍቺ ላይ የሚያጠነጥን፣ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን ለማዳበር የሚያስችልና የተማሩትን ትምህርት በነባራዊው አለም በጥቅም ላይ እንዲያውሉ በር የሚከፍት በመሆኑ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ተማሪዎች እንደየ ፍላጎታቸውና እንደየ ችሎታቸው ትምህርት እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡ በተማሪዎች መካከል ያለ ልዩነትን ለመዳሰስ የሚያስችል የትምህርት አሰጣጥ የማይከናወን መሆኑንም ያሳያል፡፡ ተማሪዎቹ ችግር የመፍታት ችሎታንም ሆነ ከፍተኛ የአስተሳብ ችሎታዎችን እንዳያዳብሩ፤ ከልቀታዊ የትምህርት አቀራረብ ሊያገኙ የሚችሉትን ክህሎትም እንዳያጎለብቱ ምክንያት ይሆናል፡፡ በጥቅሉ ተማሪዎቹ በማህበራዊ ግንባታውያን የትምህርት ፍልስፍና መሰረት የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች በጥቅም ላይ ሲውሉ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ሊያዳብሩ የሚችሉትን ክህሎት እንዳያዳብሩና እንዲገነቡ የሚጠበቀውን እውቀት እንዳይገነቡ እንቅፋት ይሆናል፡፡

በትምህርታዊ የተግባቦት ስርአት ውስጥ የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር ድክመት መኖሩ የመማር ማስተማሩ ሂደት ለተግባቦት እንቅፋት እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡ በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው የመማር ማስተማር ስልቶች የመልእክት መተላለፊዎች ናቸው፡፡ የተግባቦት ሂደቱ በመረጃ መተላለፊያዎች ረገድ ለተግባቦት እንቅፋት ተጋለጠ ማለት ከተግባቦት ሂደት አላባውያን መካከል አንዱ በሆነው በመልእክት መተላለፊያው ላይ የተግባቦት ሂደቱን የሚያውክ ችግር አለ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም መረጃ የሚጠበቀውን ያህል ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ መድረስ

አይችልም። ይህ ደግሞ በተግባቦት ሂደቱ ውስጥ በመልእክት አስተላላፊዎችና በመልእክት ተቀባዮች መካከል የጋራ ግንዛቤ እንዳይፈጠር ያደርጋል። ምክንያቱም መልእክት ከመልእክት አስተላላፊ መንጭቶ መልእክት ተቀባይ ዘንድ እንዲደርስ፣ እንዲተረጎም፣ በመልእክት ተቀባይ ግብረ መልስ እንዲሰጥበትና የተሰጠው ግብረ መልስ ወደ መልእክት አስተላላፊ እንዲደርስ በመልእክት መተላለፊያው ማለፍ ይኖርበታል። የመልእክት መተላለፊያዎቹ ላይ ድክመት አለ ማለት መረጃ እንደ ልብ ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ አይደርስም፣ ቢደርስም እንኳ በተሳሳተ መንገድ ሊተረጎምና ግብረ መልስ ሊሰጥበት ይችላል። ስለዚህም የተግባቦት ሂደቱ ይደናቀፋል። መደናቀፉ ደግሞ የጋራ ግንዛቤ እንዳይጨበጥ ያደርጋል።

በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መማር አለምን የመረዳት፣ የመገንዘብና ፍቺ የመመስረት ሂደት ነው። ይህ ሂደት ረቂቅ ጽንሰ ሀሳቦችንና ማስረጃዎችን የመረዳት፤ ነባራዊ እውነታዎችን የማወቅና የማስታወስ፤ በአተገባበር ብልሀቶች የመጠበብ፤ በበነባራዊ እውነታዎች፣ በግላዊ አመለካከቶችና በሀሳብ አመክንዮዎች መካከል ያለውን ልዩነት አብጠርጥሮ የመለየት፣ ክስተቶችን እደየአውዱ የመረዳት፤ ለተወሰኑ አውዶች ምቹ የሆኑ ባህርያትን የማዳበር እንዲሁም የመለወጥ ሂደት ነው። የተግባቦቱ ሂደት የመልእክት መተላለፊያ ድክመት ካለበት ይህ በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አተያይ መማር የሚባል ተግባር የክንውን ሁኔታ መሰናክል ይገጥመዋል። ስለዚህም የጋራ ግንዛቤ የመፈጠሩ ሁኔታ ይደናቀፋል። በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውስጥም ቢሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ግብኣት ሆነው የተገኙት ነገሮች ውጽኣት ማስገኘት ይችሉ ዘንድ የሚብላሉት በመማር ማስተማር ስልቶች አማካኝነት በሚከናወነው የመረጃ ልውውጥና የትምህርታዊ ተግባራት ትግበራ ነው። የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር ድክመት አለበት ማለት ግብኣት ሆነው የተገኙት ነገሮች ውጽኣቱን ያስገኙ ዘንድ በሚብላሉበት መንገድ ላይ ችግር አለ ማለት ነው። ስለዚህም ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚፈገለውን ውጤት ወይም ውጽኣት ማስገኘት የተሳነው ይሆናል።

4.2.4. በትምህርት ደረጃ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ የታየ ልዩነት

የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ልክ እንደ ተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሁሉ መምህራን በስልጠና ሂደት የሚያዳብሩት ሲሆን በመምህርነታቸው ከሚጠበቅባቸው የማስተማር ስነዘዴ እውቀት የሚመደብ ነው። በትምህርት የሚዳብር እንደመሆኑ መጠን በአተገባበር ረገድ በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ በሰለጠኑ መምህራን መካከል ልዩነት እንዲኖር ይጠበቃል። በዚህ መሰረት ይህ ጥናት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪና ዲፕሎማ በሆነ መምህራን መካከል የአተገባበር ልዩነት አለ ወይ የሚል ጥያቄ

አንስቷል። በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ በሰለጠኑ መምህራን መካከል ያለው የትምህርት ደረጃ ልዩነት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት እንዲኖር ማድረጉን የሚያሳይ የአማካይ ንድጽር ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 26 ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 26፡ የትምህርት ደረጃ ልዩነት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ያመጣውን ልዩነት የሚያሳዩ መረጃዎች

Report

observed classroom interaction

educn	Mean	N	Std. Deviation
Diploma	35.6925	24	6.52164
Degree	39.6925	12	6.00858
Total	37.0258	36	6.55387

በሰንጠረዥ 25 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራንን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የሚያሳየው አማካይ 39.6925 ነው። በመደበኛ አሰረጫጨት 60 እንዲሆን ይጠበቃል። የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን የሚያሳየው አማካይ ደግሞ 35.6925 ነው። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት 60 እንዲሆን ይጠበቃል። በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ላይ ያሉ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው ያነሰ ነው። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከዲፕሎማዎቹ በአማካይ በ4.00 ይበልጣል። 6.52164 የሆነው መደበኛ ልይይት የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ በሆነ መምህራን መካከል ያለው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ልዩነት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ ከሆነው (6.00858) በጥቂቱ እንደሚበልጥ ያሳያል። በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ በሆነ መምህራን መካከል ያለው ልዩነት ከዲፕሎማዎቹ በጥቂቱ ያነሰ ነው። በጥቅሉ ምንም እንኳ በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው ያነሰ ቢሆንም በንጽጽር ሲታይ በመካከላቸው የሰፋ ልዩነት ባይኖርም የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከዲፕሎማዎቹ በጥቂቱ የተሻለ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል።

በሁለቱም ደረጃዎች ያለው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው አንጻር በቂ አይደለም። ምክንያቱም የሁለቱም አተገባበር ከሚጠበቀው ያነሰ ነው። ማነሱ ደግሞ በሁለቱም የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቀውን

ያህል የመማር ማስተማር ሂደት እንዳይከናወንና በትምህርቱም የሚፈለገው ውጤት እንዲገኝ ለማድረግ የማያስችል ነው። ሁኔታው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ሲሆን የመምህራኑ የስልጠና ሁኔታ ምን ይመስላል?። ለክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ተገቢውን ትኩረት የሰጠ ነው ወይ? ይህ ሁኔታስ በሁሉም መምህራን ላይ ይታያል ወይ? የሚሉት ጉዳዮች በቀጣይ መጠናት ያለባቸው መሆኑን ያመለክታል።

ከፍ ሲል ለማየት እንደተሞከረው ይህ ጥናት ያነሳው አራተኛ መሰረታዊ ጥያቄ "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የትምህርት ደረጃ ልዩነት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት አምጥቷል ወይ?" የሚል ነበር። መልሱ አዎ በጣም ጥቂት ልዩነት አምጥቷል የሚል ነው። የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪና ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው ያነሰ ሲሆን የዲግሪዎቹ ከዲፕሎማዎቹ በጥቂቱ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

4.2.5. የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ተዛምዶ

ይህ ጥናት ካነሳቸው ዝርዝር ጥያቄዎች መካከል አንዱ "በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ አለ?" የሚል ነው (1.4ን ይመልከቱ)። እንደ Antonius (2003)ና Muijs (2004) አገላለጽ ለዚህ ጥያቄ መልስ ማግኘት ይቻል ዘንድ የመረጃ ትንተናው በሁለት ደረጃዎች ማለፍ ይኖርበታል። የመጀመሪያው የሁለቱን ተላውጦዎች እንዴትነት መመርመር ሲሆን ሁለተኛው በመካከላቸው ተዛምዶ መኖሩ ማረጋገጥ ነው። የተላውጦዎቹን እንዴትነት መመርመር በ4.1. ስር በተከናወነው የመረጃ ትንተና ታይቷል። ቀጥሎ ደግሞ በተላውጦዎቹ መካከል ያለው ተዛምዶ ተተንትኖ ቀርቧል። በሁለቱ መካከል ያለውን ለመመርመር ያገለገለው የፒርሰን የተዛምዶ ስሌት (Pearson Correlation) ነው። ይህ ቀመር በእኩሌታ ልኬት የተገለጹ መረጃዎች ባሏቸው ሁለት ተላውጦዎች መካከል ያለን ንጥላዊ ተዛምዶ (linear association) ለመለካት ያስችላል። የሁለቱን ተላውጦዎች የክስተት ሁኔታ የሚያሳዩ መረጃዎች የፒርሰን የተዛምዶ ስሌት ውጤት በሰንጠረዥ 27 ቀርቧል።

በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያሳየው የፒርሰን የስታቲስቲካዊ ተዛምዶ ስሌት ውጤት በ0.01 የነጻነት ደረጃ rs=0.885 ነው። በMuijs (2004) እንደተገለጸው በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር እንዴትነት መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ በጣም ጠንካራ ተዛምዶ አለ። የተዛምዶ ውጤቱ ከዜሮ በላይ መሆኑ

ተዛምዶው አወንታዊ መሆኑን ያሳያል። ይህ ማለት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ጠንካራ የሆኑ መምህራኑ በሚያስተምሩበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ጥሩ የሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይከናወናል። በሌላ አገላለጽ የተጠኝዎቹ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲቀንስ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩም አብሮ ይቀንሳል። ሲጨምርም እንደዚያው አብሮ ይጨምራል።

ሰንጠረዥ 27፡ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያሳዩ መረጃዎች

Correlations

		observed communicatve skills	observed classroom interaction
observed communicatve skills	Pearson Correlation	1	.885**
	Sig. (2-tailed)		.000
	N	36	36
observed classroom interaction	Pearson Correlation	.885**	1
	Sig. (2-tailed)	.000	
	N	36	36

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መካከል የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል። ስለዚህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ትምህርታዊ መረጃም ሆነ ተማሪዎች ስለሚያከናውኑት ተግባር የሚሰጥ መመሪያ ወደ ተማሪዎች የማድረስ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። መምህራኑ ትምህርታዊ መረጃንና የአተገባበር መመሪያን በጥሩ ሁኔታ ወደ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ወክለው ማስተላለፍ ባልቻሉበት ሁኔታ የመማር ማስተማሩ ሂደት በጥሩ ሁኔታ ሊካሄድ አይችልም። በትምህርትነት የሚቀርቡ መረጃዎችም ግልጽና ተስተዋይ (understandable) ሊሆኑ አይችሉም። ትምህርታዊ መረጃዎቹም ሆኑ የሚተላፉት የአተገባበር መመሪያዎች ግልጽና ተስተዋይ ካልሆኑ በተማሪዎች መካከል የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት አይኖርም። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ምንን እንዴት እንደሚያከናውኑት ለማወቅ ይቸገራሉ። ይህ ሁኔታ ጥሩ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲኖር ጥሩ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንደሚኖር ያሳያል። የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲዳከምም እንደዚሁ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ይዳከማል።

ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባር በጠቅላላ መምህሩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚተገብሩት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ የተመሰረተ ነው። ጥሩ የሆነ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በክፍል ውስጥ ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖርና ተማሪዎች የሚያከናውኑትን የክፍል ውስጥ መስተጋብር በጥሩ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህም የተግባቦት

ክህሎት አጠቃቀም ለማስተማር ሙያ ጠንካራ የሆነ መሳሪያ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህም የጥናቱ ውጤት እንዳሳየው መምህራን በክፍል ውስጥ የተግባቦት ክህሎታቸውን የሚጠቀሙበት ሁኔታ በክፍል ውስጥ ከሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ጋር አወንታዊ የሆነ ተዛምዶ አለው። የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ጥሩ ሲሆን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጥሩ ይሆናል። በአንጻሩ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲደክም የክፍል ውስጥ መስተጋብሩም ይደክማል።

ይህ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለ ተዛምዶ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ ላይም ሆነ በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው የተግባቦት ክህሎት የተግባቦት ሂደቱ መልእክት የሆነው ትምህርታዊ መረጃ ሲተላለፍ በምልክት የሚወከልበትና የመረጃ ፍሰቱ የሚሳለጥበት መንገድ ነው። በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ ድክመት መኖሩ የመረጃ ፍሰቱ እንዳይሳለጥ ያደርጋል። አለመሳለጡ ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በአግባቡ እንዳይከናወን ምክንያት ይሆናል። የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ የተገነባው በተግባቦት ስርአቱ ውስጥ መልእክት መተላለፊያ በሆኑት የትምህርት አቀራረብ ስልቶች ነው። ስለዚህም የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆን የመረጃ መተላለፊያው ድክመት እንዲኖርበት ያደርጋል። ይህ ማለት መልእክት ከአስተላላፊው ፈልቆ ተቀባዩ ዘንድ በሚደርስበት መንገድ ላይ የተግባቦት እንቅፋት ሊፈጥር የሚችል ችግር አለ። ስለዚህም መልእክቱ በሚፈለገው ሁኔታ ለመልእክት ተቀባይ አይደርስም። በሚፈለገው ሁኔታ ካልደረሰ እንደሚፈለገው ሊተረጎምና ግንዛቤ ሊሆን አይችልም። አለመቻሉ በግብረ መልስ አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ስለሚያሳድር ቀጣዩ የተግባቦት ሂደት በሚፈለገው መንገድ እንዳይከናወን እንቅፋት ይሆናል። እንቅፋቱ መልእክት ተቀባይና መልእክት አስተላላፊ ሀሳብ ለሀሳብ እንዳይረዳዱና የጋራ ግንዛቤ እንዳይጨብጡ ያደርጋል።

በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው ተግባቦት በሂደት የሚከናወን ሲሆን ቀደም ሲል የተከናወነባቸው እያንዳንዱ የተግባቦት ሂደት ውጤታማነት በቀጣይ በሚከናወነው የተግባቦት ሂደት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ስለዚህም ቀደም ሲል የተከናወነው ተግባቦት ስኬታማ አለመሆኑ በቀጣይ በሚከናወነው የተግባቦት ሂደት ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በመሆኑም በተግባቦቱ ሂደት መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ የሆኑት አካላት የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ይቸገራሉ። የጋራ ግንዛቤንም አይጨብጡም። ይህ ደግሞ በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውስጥ ግብኣት ሆነው የተገኙት ጉዳዮች ተብላልውና ተዋህደው የሚያስገኙት ውጽኣት የሚጠበቀውን ያህል እንዳይሆን ያደርጋል። በሌላ አገላለጽ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቀውን ያህል የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት የሚችል እንዳይሆን የሚያደርግ እንቅፋት ይገጥመዋል ማለት ነው። የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲደክም በክፍል ውስጥ የሚከናወነው ማህበራዊ መስተጋብር ደካማ

ይሆናል። ደካማ መሆኑ የመማር ማስተማር ሂደቱ ተሳታፊዎች የቋንቋ አጠቃቀም የሚጠበቀውን ያህል እንዳይጸብር ለሚያደርግ ችግር የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ መረጃው ይህ ጥናት ያነሳው አምስተኛ ዝርዝር ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ ለማድረግ አስችሏል። ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ጥያቄው በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ መኖሩን የተመለከተ ሲሆን መልሱ በጣም ጠንካራ የሆነ አወንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ያመለከተ ነው።

4.3. የጥናቱ ግኝትና ድምዳሜ

ይህ ጥናት "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ተዛምዶ" በሚል ርእስ ተከናውኗል። መሰረታዊ ጥያቄው "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ አለ ወይ?" የሚል ሲሆን በስሩ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች አንስቶ መልስ ሰጥቷል።

1ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴት ያለ ነው?

2ኛ. የተለያየ የትምህርት ደረጃ ባላቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት ይታይባቸዋል?

3ኛ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴት ያለ ነው?

4ኛ. የተለያየ የትምህርት ደረጃ ባላቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት ይታይባቸዋል?

5ኛ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር የመንስኤና ውጤት ትስስር አለው?

አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ጋር ተዛምዶ ያለው መሆኑን ለሚጠይቀው መሰረታዊ ጥያቄ መልሱ "አዎ! በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል በጣም ጠንካራ አወንታዊ ተዛምዶ አለ።" የሚል ነው። እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቻለው እያንዳንዱን ዝርዝር ጥያቄ ለመመለስ በተከናወነው የመረጃ ትንተና የተደረሰበት ውጤት ነው።

ጥናቱ ያነሳው አንደኛ ዝርዝር ጥያቄ "የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴት ያለ ነው?" የሚል ሲሆን መልሱ "በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው።" የሚል ነው። እዚህ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስቻለው ከምልከታ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ በተገኙ

መረጃዎች ላይ በቀረበው ትንታኔ የተደረሰበት ድምዳሜ ነው (4.1.1ና 4.2.1ን ይመልከቱ)። በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ስር የተዳሰሱ ተግባራት አተገባበርን የሚያሳዩ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን እንዲሁም የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን አመልክተዋል። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ አስችሏል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመልክቷል (t=-4.342, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -4.342 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-13.55667 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-1.4475 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው። ስለዚህም የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል። ደካማ መሆኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታል።

በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ስር አምስት ዘርፎች ተዳስሰዋል። እነዚህ ዘርፎች የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም፤ የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም፤ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራብ፤ የጥያቄ አጠያየቅ፤ እንዲሁም የመረጃ ግብይት ናቸው። የነዚህን ዘርፎች ተናጠላዊ አተገባበር ማወቅ ይቻል ዘንድ የተሰሉት የአይነተኛ ውጤት ልኬታዎች፣ የልይይት መጠን ልኬታዎችና የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት እንዳመለከቱት የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀምና ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ሲገኙ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራብ፤ የጥያቄ አጠያየቅ እንዲሁም የመረጃ ግብይት ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ናቸው። የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በትምህርት የሚዳብር ከመሆኑ አንጻር የሌሎቹ ዘርፎች የአተገባበር ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ሲሆን የቃላዊ እና የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም እንዴት ከሚጠበቀው አንጻር ጥሩ ሊሆን ቻለ የሚል

ጥያቄ ያስነሳል፡፡ Hargie & Dickson, (2005) እንደገለጹት ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎችን ሰዎች ከህጻንነታቸው ጀምሮ በሚያድጉበት ማህረሰብ ስለሚጠቀሙባቸው ከባህል ጋር ጥብቅ ትስስር አላቸው፡፡ ምናልባትም ይህ ሁኔታ በክፍል ውስጥ በሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት ያለው የቃላዊ እና የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም የተሻለ እንዲሆን አድርጎ ሊሆን ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

ሁለተኛው ዝርዝር ጥያቄ የተለያየ የትምህርት ደረጃ ባላቸው መምህራን መካከል በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት መኖሩን የተመለከተ ነው፡፡ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በትምህርትና በስልጠና የሚዳብር ነው (Hargie, 2006)፡፡ ስለዚህም የትምህርት ደረጃ ልዩነት የአጠቃቀም ልዩነት እንዲያመጣ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ጥናት የታዩት ተጠኚዎች የትምህርት ደረጃ ዲግሪና ዲፕሎማ ነው፡፡ በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ በሰለጠኑ መምህራን መካከል ያለው የትምህርት ደረጃ ልዩነት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የአጠቃቀማቸውን ሁኔታ የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ ንጽጽር ተከናውኗል፡፡ በዚህ መሰረት በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራንን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳየው አማካይ 87.7775 ነው፡፡ የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን የሚያሳየው አማካይ ደግሞ 70.7763 ነው፡፡ የሁለቱም በመደበኛ አሰረጫጨት 90 እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ላይ ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው ያነሰ ነው፡፡ ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከዲፕሎማዎቹ በአማካይ በ17.0012 ይበልጣል፡፡ የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም መደበኛ ልይይት 20.72361 ሲሆን የዲግሪዎቹ 2.86752 ነው፡፡ ይህም በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ በሆነ መምህራን መካከል ያለው ልዩነት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ ከሆነው እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡ በሌላ አገላለጽ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ በሆነ መምህራን መካከል ያለው ልዩነት ከዲፕሎማዎቹ ያነሰ ነው፡፡ በጥቅሉ ምንም እንኳ በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው ያነሰ ቢሆንም በንጽጽር ሲታይ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከዲፕሎማዎቹ የተሻለ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስችሏል፡፡

ሶስተኛው ዝርዝር ጥያቄ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ እንዴት ያለ እንደሆነ የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት በምልከታ፣ በተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና በሰነድ ምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑ ሲሆን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን አሳይተዋል፡፡ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን

አስመልክቶ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣሬና የተለያየ መሆኑን እንዲሁም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን አመልክተዋል። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ አስችሏል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል (t=-21.033, df=35, p<0.05)። የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ዋጋው -21.033 ሲሆን ልዩነቱ df=35 ነው። በተከናወነው 36 ምልከታ የተገኘው አማካይ በ-22.97417 ከሚጠበቀው አማካይ ይርቃል። ርቀቱ ከዜሮ በታች መሆኑ በምልከታ የተገኘው አማካይ ከሚጠበቀው ያነሰ መሆኑን ለማወቅ ያስችላል። ይህም ደካማ አተገባበር ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ያመለክታል። የጉልህት ደረጃው sig.=0.000 ሲሆን ከ0.05 ያንሳል። ስለዚህም Antonius (2003) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ። የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማወቅ የCohen's d የጥንካሬ መለኪያ የተሰላ ሲሆን ውጤቱ Cohen's d=-6.3160 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ በተገኘውና በሚጠበቀው አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ያመለክታል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርከት ያለ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ስለዚህም የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው (4.1.2ና 4.2.2ን ይመልከቱ)።

አራተኛው ዝርዝር ጥያቄ የተለያየ የትምህርት ደረጃ ባላቸው መምህራን መካከል በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት መኖሩን የተመለከተ ነው። የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር በትምህርትና በስልጠና የሚዳብር ነው (Hargie, 2006)። ስለዚህም የትምህርት ደረጃ ልዩነት የአተገባበር ልዩነት እንዲያመጣ ይጠበቃል። ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ ጥናት የታዩት ተጠኚዎች የትምህርት ደረጃ ዲግሪና ዲፕሎማ ነው። በዲግሪና በዲፕሎማ ደረጃ በሰለጠኑ መምህራን መካከል ያለው የትምህርት ደረጃ ልዩነት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የአተገባበሩን ሁኔታ የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች አማካይ ንጽጽር ተከናውኗል። በዚህ መሰረት በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራንን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የሚያሳየው አማካይ 39.6925 ነው። የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምን የሚያሳየው አማካይ ደግሞ 35.6925 ነው። የሁለቱም በመደበኛ አሰረጫጨት 60 እንዲሆን ይጠበቃል። በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ላይ ያሉ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው ያነሰ

ነው። ሁለቱ በንጽጽር ሲታዩ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከዲፕሎማዎቹ በአማካይ በ4.00 ይበልጣል። የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ የሆነ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር መደበኛ ልይይት 6.52164 ሲሆን የዲግሪዎቹ 6.00858 ነው። ይህም የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ በሆነ መምህራን መካከል ያለው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ልዩነት የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ ከሆነው በጥቂቱ እንደሚበልጥ ያሳያል። በሌላ አገላለጽ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ በሆነ መምህራን መካከል ያለው ልዩነት ከዲፕሎማዎቹ በጥቂቱ ያነሰ ነው። በጥቅሉ ምንም እንኳ በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው ያነሰ ቢሆንም በንጽጽር ሲታይ በመካከላቸው የሰፋ ልዩነት ባይኖርም የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከዲፕሎማዎቹ በጥቂቱ የተሻለ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስችላል።

አምስተኛው መሰረታዊ ጥያቄ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ የሚጠይቅ ሲሆን መልሱም "አዎ! በመካከላቸው ጠንካራ የሆነ አወንታዊ ተዛምዶ አለ።" የሚል ነው። በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ለመመርመር ያገለገለው የፒርሰን የተዛምዶ ስሌት (Pearson Correlation) ነው። በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያሳየው የፒርሰን የስታቲስቲካዊ ተዛምዶ ስሌት ውጤት በ0.01 የነጻነት ደረጃ rs=0.885 ነው። በMuijs (2004) እንደተገለጸው በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር እንዴትነት መካከል በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ በጣም ጠንካራ ተዛምዶ አለ። የተዛምዶ ውጤቱ ከዜሮ በላይ መሆኑ ተዛምዶው አወንታዊ መሆኑን ያሳያል። ይህ ማለት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ጠንካራ የሆኑ መምህራን በሚያስተምሩበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ጥሩ የሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይከናወናል። የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ደካማ የሆነ መምህራን በሚያስተማሩበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለው የክፍል ውስጥ መስተጋብር የደከመ ነው ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ የተጠኝዎቹ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲቀንስ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩም አብሮ ይቀንሳል። ሲጨምርም እንደዚያው አብሮ ይጨምራል።

በዚህ ምእራፍ እስካሁን ድረስ የቀረበው የመረጃ ትርጎማና ማብራሪያ ጥናቱ ላነሳው መሰረታዊ ጥያቄ መልስ ማግኘት አስችሏል። ጥያቄው "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ አለ ወይ?" የሚል ሲሆን መልሱም "አዎ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል በጣም ጠንካራ አወንታዊ ተዛምዶ አለ።" ነው። ምክንያቱም ቀደም ሲል

ለማየት እንደተሞከረው የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩ መረጃዎች ትንተና የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን የሚያሳዩ መረጃዎች ላይ የተከናወነው ትንተናም የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን አመልክቷል፡፡ የፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ስሌት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ጉልህ የሆነ በጣም ጠንካራ አወንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ለማወቅ አስችሏል፡፡ ስለዚህም የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲደክም የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ይደክማል፤ ሲጠነክርም እንደዚያው አብሮ ይጠነክራል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት እንዳሳየው የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ደካማ ነው፡፡ ይህም በትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ያለው የመረጃ ፍሰት እንዳይሳለጥ ለሚያደርግ የተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተግባቦት ስርአት ግብይታዊ እንደመሆኑ መጠን መረጃ በተለያዩ አቅጣጫዎች በተሳታፊዎቹ መካከል ይፈስበታል፡፡ በዚህ ምእራፍ በቀረበው የመረጃ ትንተና እንደታየው ግን ጥናቱ በተካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች ያለው የመማር ማስተማር ሂደት የተወሰኑ ሰዎች መረጃ የሚያስተላልፉበትና አብዛኞቹ ተቀባይ የሆኑበት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ በአብዛኛው በመስማት ላይ ለተመሰረተ ግንዛቤ እንዲጋለጡና በአምስቱም የስሜት ህዋሳት መረጃን በግብአትነት የሚወስዱበት ሁኔታ ውሱን እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚከናወነው የተግባቦት ስርአትም መረጃ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚፈስበት ግብይታዊ ከመሆን ይልቅ በአንድ አቅጣጫ የሚፈስበት መስመራዊ እንዲሆን ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የትምህርት ስርአቱ እውቀት በማህበር የሚገነባበት፣ ማህበራዊ የሆነ የጋራ ግንዛቤ የሚጨበጥበትና ከመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ጋር የሚራመድ አሰራር የሰፈነበት እንዳይሆን የሚያርግ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑ በክፍል ውስጥ የሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት የሚጠበቀውን ውጽኣት ማስገኘት የተሳነው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ እውቀት የሚገነባው በግብይታዊ መማር ማስተማር ነው፡፡ መምህራንና ተማሪዎች ለመማር ማስተማር ሂደቱ ግብኣት የሚሆኑ ጉዳዮችን ይዘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገናኛሉ፡፡ ከዚያም በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ተግባራትን እየተገበሩ በሚያከናውኑት የመረጃ ልውውጥ ግብኣቶቹ ተብላልተው ውጽኣትን ያስገኛሉ፡፡ ይህ ውጽኣት በትምህርቱ ሂደት የሚፈጠር የጋራ ግንዛቤ ወይም የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑ በክፍል ውስጥ እንዲኖር የሚጠበቀውን የተሳለጠ የመረጃ

ፍሰት ያዳክመዋል። የመረጃ ፍሰቱ ከተዳከመ ጥሩ የትምህርት አመራር አይሰጥም ማለት ነው። ይህም ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራቱን የሚያከናውኑበትን ሁኔታ አስመልክቶ የሚያገኙት መረጃ ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ እንዲሆን ያደርጋል። ይህ ደግሞ ከተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ አንጻር ሲታይ ተማሪዎቹ በሚጠበቀው ሁኔታ ከሚያከናውኑት ተግባር አዳዲስ መረጃዎችን እየቀሰሙ እውቀትን እንዲገነቡ አያደርጋቸውም።

በዚህ ምእራፍ በቀረበው የመረጃ ትንተና ለማየት እንደተሞከረው በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር የሚሳተፉት ጥቂቶች ሲሆኑ አብዛኞቹ ፍዝ ተመልካች ናቸው። ይህ ማለት በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የቋንቋ አጠቃቀም በብቃት ማበልጸግ የሚያስችል ማህበራዊ መስተጋብር አይከናወንም። ይህ ደግሞ በተግባቦት ሂደቱ በተሳታፊዎች መካከል የሚኖረውን የትምህርታዊ መረጃዎች መንሸራሸር የሚጠበቀውን ያህል እንዳይሆን ያደርገዋል። የሚጠበቀውን ያህል አለመሆኑ በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መካከል በማህበር የጋራ ግንዛቤን ጨብጦ የጋራ መግባባት ላይ መድረስና እውቀትን መገንባት እንዳይጠበቅ ያደርጋል። በጥቅሉ የመማር ማስተማሩ ሂደት በተሟላ ሁኔታ መምህራንና ተማሪዎች በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር አዳዲስ ግንዛቤዎችን የሚጨብጡበት፣ የአሰራር ክሂሎችን የሚያዳብሩበት፣ አዳዲስ መልእክቶችን የሚገነዘቡበት፣ ሀሳብ የሚጋሩበት፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤን የሚጨብጡበት፣ እውቀታቸውን የሚገነቡበት፣ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸውን በሚገባ የሚያዳብሩበት ግንዛቤያቸውን አስመልክቶ ግብረ መልስ የሚሰጣጡበትና ስብእናቸው በተሟላ ሁኔታ የሚቀረጽበት ነው ማለት ያዳግታል።

ስለዚህም በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ የታየው ድክመት በቀጣይ መጠናት ያለባቸው ጥያቄዎችን አስነስቷል። እነዚህ ጥያቄዎች በስራ ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን አሰራር እንዴት በማህበራዊ ግንባታውያን አሰራር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል? በቀጣይ የሚሰለጥኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአሰለጣጠን ሁኔታስ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ ምን መምሰል አለበት? ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትስ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ መምህራንን የሚያሰለጥኑበት ሁኔታ ምን ይመስላል? በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች አሰራርስ ምን ያህል በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረተ ሀሳብ የተቃኘ ነው? በዘመናዊ የማስተማር ዘዴ ሰልጥነው የሚወጡት መምህራን በስራ አለም ሲሰማሩ የሚሰማሩበት የስራ አውድ የሚያሳድርባቸውን ተጽእኖ እንዴት መቋቋም ይቻላል? የሚሉ ናቸው።

በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረት የመማር ማስተማር ሂደት የተግባቦት ስርአት ነው። የተግባቦት ስርአት ሰባት አላባውያን ያሉት ሲሆን ከመካከላቸው አንዱ የመልእክት መተላለፊያ (channel) ነው። የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት መተላለፊያ ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ የተገነባበት የትምህርት አቀራረብ ስልት መሆኑን Wrench et al. (2009) አስገንዝበዋል። ከዚህ አንጻር የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆኑ ከትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት አላባውያን መካከል አንዱ የሆነው የመልእክት መተላለፊያው ድክመት ወይም ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ይህ ደግሞ መልእክት ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ በሚተላለፍበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውስጥ የመልእክት አስተላላፊነትንና የመልእክት ተቀባይነትን ሚና የሚወስዱት መምህራንና ተማሪዎች ናቸው። ስለዚህም መረጃ ከመምህራን ወደ ተማሪዎች፤ ከተማሪዎች ወደ መምህራን እንዲሁም ከተማሪዎች ወደ ተማሪዎች የሚተላለፍበት መንገድ የተግባቦት እንቅፋት አለበት። እንቅፋቱ መረጃ የሚፈለገውን ያህል ከአንዱ የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ወደ ሌላው እንዳይተላለፍ መሰናክል ይሆናል። የመልእክት አስተላላፊነትን ተግባር የሚያከናውኑት ተሳታፊዎች መረጃን ወክለው ቢያስተላልፉም እንኳ መልእክት መተላለፊያው ላይ ችግር ስላለ መልእክት ተቀባይ የሆኑ ተሳታፊዎች ዘንድ የተሟላ መረጃ አይደርስም። የተሟላ መረጃ ባልደረሰበት ሁኔታ መረጃውን በትክክል እንዲተረጉሙት አይጠበቅም። ተርጉመው ካልተረዱት ደግሞ ትክክለኛ ግብረ መልስ መስጠት አይችሉም። ስለዚህም መልእክት አስተላላፊ የነበረው የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ትክክለኛ ግብረ መልስ አያገኝም። ይህ ደግሞ በግብረ መልሱ ላይ ተመስርቶ በቀጣይ ግብይታዊ በሆነ መንገድ የሚካሄደውን የተግባቦት ሂደት ያውከዋል። የተግባቦት ሂደቱ መታወኩ የተግባቦት ሂደቱ ተሳታፊዎች በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደርሱና ጥሩ የሆነ የጋራ ግንዛቤ እንዳይጨበጡ ያደርጋል።

የጥናቱ ሞዴል በሆነው ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍ ውስጥ ተማሪዎችና መምህራን ግብኣት የሆኑትን አዲስ የትምህርት ይዘት፣ ዳራዊ እውቀትና ግላዊ ባህሪ ይዘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገናኛሉ። በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከናወነው ማህበራዊ መስተጋብር አማካኝነት እነዚህን ጉዳዮች አብላልተውና መረጃ ተለዋውጠው አዲስ ግንዛቤን ይጨብጣሉ። ይህ ግንዛቤ በቀደመ እውቀታቸው ላይ አዲስ ግንዛቤን የሚያክል የእውቀት ግንባታ እንዲካሄድ ያደርጋል። የእውቀት ግንባታው ሲካሄድ የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤት አስገኘ፤ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊዎች አዲስ የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥን አመጡ ማለት ነው። ይህ ለውጥ የተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውጽኣት ነው። ይሁን እንጂ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ ድክመት ካለ የሚፈለገውን ያህል ማህበራዊ መስተጋብር አይከናወንም ማለት ነው። አለመከናወኑ ደግሞ በክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ተሳታፊዎች መካከል ነጻ የሆነ የሀሳብና የአሰራር ልውውጥ አይካሄድም።

ልውውጡ ባልተካሄደበት ሁኔታ ቀደም ሲል በነበራቸው እውቀት ላይ አዲስ እውቀትን ለማከል የሚያስችላቸው የጋራ ግንዛቤን አይጨብጡም፡፡ ምክንያቱም መስተጋብሩ ደካማ ስለሆነ የቀረበውን ትምህርታዊ መረጃ መረዳት፣ መተርጎም፣ ማብላላት፣ ማዋሀድና ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ማስተሳሰርን አያከናውኑም፡፡ ስለዚህም ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚፈለገውን ውጤት ወይም ውጽኣት ማስገኘት ይሳነዋል፡፡

በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው የቋንቋ አጠቃቀም በማህበራዊ መስተጋብር ይዳብራል፡፡ በትምህርታዊ ተግባቦት መሰረተ ሀሳብና በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ማብራሪያ ላይ እንደተገለጸው ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብር በተግባቦት ሂደት ተሳታፊዎች መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረስ ያስችላል፡፡ የጥናቱ ውጤት የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆኑን አሳይቷል፡፡ ይህ ማለት አዲስ በቀረበው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ ተማሪዎቹ ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያከናውኑበት መንገድ የደከመ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የቋንቋ ትምህርት ይዘቱን የሚገነዘቡበት፣ የቀደመ እውቀታቸው አካል የሚያደርጉበትና በጥቅም ላይ ማዋልን የሚለማመዱበት ማህራዊ መስተጋብር ደካማ ነው፡፡ ስለዚህም የቋንቋውን አጠቃቀም የሚለምዱበት ሁኔታ የደከመ ነው፡፡ በጥቅሉ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆኑ የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱን፣ የተግባ-ግብይታዊ መማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚያስገኘውን ውጤትም ሆነ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎቹ የቋንቋ አጠቃቀሙን የሚያጎለብቱበትን መንገድ ያውከዋል፡፡ ስለዚህም የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚፈለገውን ያህል ውጤት ያስገኛል ማለት ያዳግታል፡፡

የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር መምህራን በስልጠና ሂደት የሚያዳብሩት ጉዳይ ነው፡፡ ሁሉም ተጠኝ መምህራን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማስተማር ሙያ ሰልጥነው የወጡ መሆናቸው በምእራፍ ሶስት ተገልጿል፡፡ ምንም እንኳ የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚከናወነው የክፍል ውስጥ መስተጋብር ጥቂት ልዩነት የሚታይበት ቢሆንም የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ደካማ የሆነው መምህራኑ ስልጠና ያልወሰዱ በመሆናቸው ነው የሚል ሀሳብ ማንሳት አይቻልም፡፡ ይልቁንም መምህራንን በሚያሰለጥኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የሚሰጠው ቦታ ምን ይመስላል? በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ሲሰለጥኑ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበርን በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ከመማር ባለፈ በተግባር የሚተረጉሙበትን መንገድ ምን ያህል ይለማመዳሉ? ሰልጣኝ መምህራኑ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ላይስ ምን ያህል ግንዛቤ አላቸው? የሚል ጥያቄ እንዲነሳ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በምእራፍ ሁለት በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ላይ በቀረበው ማብራሪያ እንደተገለጸው የትምህርት ቤት አውድ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተጽእኖ

ከሚያሳድሩ ጉዳዮች አንዱ ነው። ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመምህርነት ሰልጥነው የሚወጡ አዳዲስ መምህራን በማስተማር ስራ ሲሰማሩ የሚገቡበት የትምህርት ቤት አውድ በስልጠና ሂደት የገበዩትን እውቀትና ክህሎት በሚተገብሩበት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድረው በምን መልኩ ነው? ምናልባት በከፍተኛ ትምህርት ሰልጥነው ቢውጡም እንኳ በስራ አለም ያለው አካባቢያዊ ተጽእኖ በትምህርት አለም ላይ የቀሰሙትን እውቀትና ልምድ ወደ ጎን ትተው በትምህርት ቤት አውድ ውስጥ በስፋት የሚተገበረውን አሰራር እንዲከተሉ ያደርጋቸው ይሆን ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት አለባቸው።

በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ያለው ተዛምዶ በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደቱ ላይም ሆነ በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በምእራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው የተግባቦት ክህሎት የተግባቦት ሂደቱ መልእክት የሆነው ትምህርታዊ መረጃ ሲተላለፍ የመረጃ ፍሰቱ የሚሳለጥበት መንገድ ነው። በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ላይ ድክመት መኖሩ የመረጃ ፍሰቱ እንዳይሳለጥ ያደርጋል። አለመሳለጡ ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በአግባቡ እንዳይከናወን ምክንያት ይሆናል። የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ የተገነባው በተግባቦት ስርአቱ ውስጥ መልእክት መተላለፊያ በሆኑት የትምህርት አቀራረብ ስልቶች ነው። ስለዚህም የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ ሲሆን የመረጃ መተላለፊያው ድክመት ይኖርበታል። ይህ ማለት መልእክት ከአስተላላፊው መንጭቶ ተቀባዮች ዘንድ በሚደርስበት መንገድ ላይ የተግባቦት እንቅፋት ሊፈጥር የሚችል መሰናክል አለ። ስለዚህም መልእክቱ በሚፈለገው ሁኔታ ለመልእክት ተቀባዮች አይደርስም። በሚፈለገው ሁኔታ ካልደረሰ እንደሚፈለገው ሊተረጉመምና ግንዛቤ ሊሆን አይችልም። አለመቻሉ በግብረ መልስ አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ስለሚያሳድር የተግባቦት እንቅፋት ይፈጥራል። ይህ የተግባቦት እንቅፋት መልእክት ተቀባይና መልእክት አስተላላፊ ሀሳብ ለሀሳብ እንዳይረዳዱና የጋራ ግንዛቤ እንዳይጨብጡ ያደርጋል። አለመፈጠሩ ደግሞ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚጠበቀውን ውጽኣት ማስገኘት እንዳይችል ምክንያት ይሆናል።

በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው ተግባቦት በሂደት የሚከናወን ሲሆን ቀደም ሲል የተከናወነው እያንዳንዱ የተግባቦት ሂደት ውጤታማነት በቀጣይ በሚከናወነው የተግባቦት ሂደት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። እስካሁን ድረስ በቀረበው ትንታኔ ለማየት እንደተሞከረው የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የማስተማር ስልቱ ከተገነባበት የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ጋር ጠንካራ የሆነ አወንታዊ ተዛምዶ አለው። ይህ ማለት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ጠንካራ ሲሆን የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ በጥሩ ሁኔታ ይተገበራል፤ ደካማ ሲሆንም እንደዚሁ በደከመ ሁኔታ ይተገበራል። የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀሙም ሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መድከማቸው መረጃ በትክክል ወደ ተግባቦት ሂደት ተሳፊዎች እንዳይደርስና የደረሰውንም የተግባቦቱ ሂደት

ተሳታፊዎች በትክክል ተቀብለው እንዳይተረጉሙት ያደርጋል። ተርጉመው ካልተረዱት ደግሞ ትክክለኛ ግብረመልስ መስጠት አይችሉም። ስለዚህ መልእክት አስተላላፊው ትክክለኛ ምላሽ አያገኝም። ይህም የተከናወነው የተግባቦት ሂደት ስኬታማነት አደጋ ላይ እንዲወድቅ ያደርጋል። ቀደም ሲል የተከናወነው ተግባቦት ስኬታማ አለመሆኑ በቀጣይ በሚከናወነው የተግባቦት ሂደት ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በመሆኑም በተግባቦቱ ሂደት መልእክት አስተላላፊና መልእክት ተቀባይ የሆኑት አካላት የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ይቸገራሉ። የጋራ ግንዛቤንም አይጨብጡም። ይህ ደግሞ በተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውስጥ ግብኣት ሆነው የተገኙት ጉዳዮች ተብላልውና ተዋህደው የሚያስገኙት ውጽኣት የሚጠበቀውን ያህል እንዳይሆን ያደርጋል። በሌላ አገላለጽ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጠበቀውን ያህል የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት የሚችል እንዳይሆን የሚያደርግ እንቅፋት ይገጥመዋል ማለት ነው።

ምእራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

5.1. ማጠቃለያ

የመማር ማስተማር ሂደት መምህራንና ተማሪዎች ተግባቦትን የሚያከናውኑበት የተግባቦት ሂደት ሲሆን ውጤታማነቱ የተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር አማካኝነት የጋራ ግንዛቤን መጨበጥ በመቻላቸው ይገለጣል (Hamm, 2006; Wrench et al., 2009; Berko et al., 2010)። በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አተያይ መማር ተማሪዎች የተሻለ ችሎታ ባላቸው አካላት ድጋፍ እየተደረገላቸው በላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል በሚያከናውኑት ትምህርታዊ ተግባር እውቀታቸውን የሚገነቡበት ሂደት ነው። የላቀ የእውቀት ግንባታ ክልል ተማሪዎች ቀደም ሲል የማያውቁትን ጉዳይ ለማወቅ የሚያስችል የአእምሮ ክልል ነው። ተማሪዎች በዚህ የእውቀት ግንባታ ክልል ውስጥ እውቀታቸውን እንዲገነቡ በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር ተሳታፊ መሆን አለባቸው። ለዚህም መምህራን መስተጋብሩን ማደራጀትና ክንውኑን በአመራር ሰጪነት መምራት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ደግሞ የዳበረ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ችሎታን ይጠይቃል። መምህራን የዳበረ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ችሎታ ባለቤት መሆናቸው በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው የመማር ማስተማር ሂደት በራሱ ተግባቦት ስርዓት መሆኑና ይህንን የተግባቦት ስርአት ውጤታማ ለማድረግ ደግሞ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ በWrench et al. (2009) መገለጹ ነው። እንደ Hargie (2006) አባባል የትኛውንም የትምህርት አይነት የሚያስተምሩ መምህራን የተግባቦት ክህሎት መሻሻል የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችል ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይህንን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በአማርኛ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ሲመረመሩ የማስተማር ዘይ ችግር መኖሩን ያመለከቱ ቢኖሩም ትኩረታቸውን የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ የተመለከቱ ሆነው አልተገኙም። በመሆኑም ይህ ጥናት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ መርምሮ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚያስችል የመፍትሄ ሀሳብ ሰንዝሯል።

የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ አለ ወይ?" የሚል ነው። በዚህ መሰረት የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች አንስቶ መልስ ሰጥቷል።

1ኛ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም እንዴት ያለ ነው?

2ኛ. በመምህራኑ መካከል ያለ የትምህርት ደረጃ ልዩነት በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ላይ ልዩነት እንዲኖር አድርጓል ወይ?

3ኛ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚከናወነው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር እንዴት ያለ ነው?

4ኛ. በመምህራኑ መካከል ያለ የትምህርት ደረጃ ልዩነት በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበራቸው ረገድ ልዩነት እንዲኖር አድርጓል?

5ኛ. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ አለ?

ለነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርሳናት ተነበዋል፤ በተለያዩ ምሁራን የተሰነዘሩ ንድፈ ሀሳቦች ተከልሰው ቀርበዋል፤ እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ትስስር ያላቸው ጥናቶች ተፈትሸዋል።

ጥናቱ ሲከናወን የተመረኮዘባቸው ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች አሉ። የምርምር ቀመረ እሳቤው የድኅረ አወንታውያን ቀመረ አሳቤ ነው ማሕቀፉ መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ነው። ምክንያቱም እንደ Ethiopian National Agency for UNESCO (2001)ና Ministry of Education (2008) በስራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የትምህርት ስርአት የመሰረተ ግንባታውንን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ ጥናቱ ያነሳው ርእሰ ጉዳይ ይህንን ንድፈ ሀሳብን መከተልን ይጠይቃል። መሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ ዝንቅ ከሁሉም የመማር ንድፈ ሀሳቦች ጠንካራ ጎን በመውሰድ የተቀናበረ ሲሆን የሀሳቡ አስኳል እውቀት የሚያስተላልፉት ወይም የሚቀበሉት ጉዳይ ሳይሆን የሚገበየው አካል በሚያደርገው መስተጋብር የሚፈጥረውና የሚገነባው ጉዳይ እንደሆነ ይገልጻል (Jarvis et al., 2004; Brown, 2007; Light, 2008; Panasuk & Lewis, 2012)። በዚህ መሰረት ይህ ጥናት መሰረቱን በሁሉም ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አተያይ ላይ አድርጓል።ስለዚህም በቋንቋ ትምህርት ሂደት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረግ መስተጋብር ተማሪዎችን በትምህርታቸው ውጤታማ ለማድረግ ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪም ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፍን ለዚህ ጥናት በሚመች መልኩ በማቀናበር የጥናቱ ሞዴል አድርጓል።

ይህ ጥናት እነዚህን ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች ተመርኩዞ ሲከናወን አላማውን ከግብ ለማድረስ የተጠቀመባቸው የአጠናን ዘዴዎችም አሉ። በተግባቦት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ምርምሮችን የሚያደርጉ ተመራማሪዎች ተግባቦታዊ ባህሪው በሚከሰትበት ተፈጥሯዊ መቼት ተገኝተው ክስተቱን የሚመለከቱ፣ የሚያዳምጡና የሚመዘግቡ መሆን ይኖርባቸዋል (Lorio, 2009)። በዚህ መሰረት ይህ ጥናት አይነታዊ ምርምርን መከተል ያለበት ቢሆንም Tavakoli (2010) በገለጹት መሰረት የጥናቱ ርእስ የሚጋብዘውን አይነታዊና መጠናዊ ምርምርን ያሚያቀናጀውን ጥምር የምርምር ንድፍ ተጠቅሟል። የተለያዩ ጥምር የምርምር ንድፎች ያሉ ቢሆንም ለዚህ ጥናት ያገለገለው Ary et al. (2010) በገለጹት መሰረት ቅደም ተከተላዊ ጥምር የምርምር ንድፍ ነው። ቅደም ተከተላዊ ጥምር አይነታዊና መጠናዊ መረጃዎችን በቅደም ተከተል የመተንተን ተግባር የሚከናወንበት ነው።

Dawson (2007) በገለጹት መሰረት ጥናቱ ያነሳቸውን የምርምር ጥቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ማግኘት ይቻል ዘንድ ይሆንታዊና ኢይሆንታዊ ንሞናዎች በጥቅም ላይ ውለዋል። ለጥናቱ አቅራቢ ካላቸው ምቹነት አኳያ በምቾት ንሞና በአዲስ አበባ መስተዳድር የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10፣ 11ና 12 የሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በተጠኝነት ተወስደዋል። በነዚህ ወረዳዎች ውስጥ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን የመንግስት ትምህርት ቤቶች በእጣ ናሙና ተመርጠዋል። 8ኛና 10ኛ ክፍሎች ተማሪዎች ለብሔራዊ ፈተና የሚዘጋጁባቸው በመሆናቸው እንዲሁም 11ኛና 12ኛ ክፍሎች ትምህርቱ በብሄራዊ ፈተናነት የማይሰጥ መሆኑ ተጽእኖ እንዳያሳድር በመፍራት ከጥናቱ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጓል። በአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ላይ ያሉት ተማሪዎች ህጻናት በመሆናቸው መምህራኑ ከተማሪዎቹ ጋር የሚግባቡበት መንገድ በጥናቱ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽእኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከጥናቱ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጓል። በሶስቱ ወረዳዎች ባሉ የመንግስት ትምህርት ቤቶች 5ኛ፣ 6ኛ፣ 7ኛና 9ኛ ክፍሎች አማርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ 12 መምህራን መካከል በመማር ማስተማሩ ሂደት በቪዲዮ ካሜራ ለመቀረጽ ፈቃደኛ የሆኑ ስድስት ተጠኚዎች ማለትም አራት የመጀመሪያ ደረጃና ሁለት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጠቅላይ ንሞና በተጠኝነት ተወስደዋል።

ከነዚህ ተጠኝዎች መረጃ የተሰበሰበው በአጭር ጊዜ ምልከታ፣ በተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና በሰነድ ምርመራ ነው። የአጭር ጊዜ ምልከታ Hargie & Dickson (2005)ና Ary et al. (2010) የገለጹትን መነሻ በማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራኑን ትምህርታዊ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሏል። ምልከታው የተካሄደው በተጠኝነት የተመረጡት መምህራን በሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ተገኝቶ የመማር ማስተማሩ ሂደትን በመመልከትና በቪዲዮ ካሜራ በመቅረጽ ነው። Camic et al. (2003)ና Muijs (2004) በገለጹት መሰረት በምልከታ የተገኘው መረጃ በጽሁፍ ሳይተረጎም የምልከታ

ቅጾችን በመጠቀም ለሶስት ቀናት ስልጠና የተሰጣቸው ተመልካቾች በደረጃዊ ልኬት እንዲገልጹት ተደርጓል። የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ እንዲያስችል ያገለገለው የምልከታ ቅጽ በይነሰባዊ የተግባቦት ችሎታ አጣርቶ መሰነጃ (Interpersonal Communication Competence Inventory /ICCI) ሞዴልን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። እንደዚሁም የክፍል ውስጥ መስተጋብሩን እንዴትነት አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገለው የምልከታ ቅጽ የተዘጋጀው የግንባታውያንን የመማር ማስተማር ሞዴል (constructivist teaching Learning model) መሰረት አድርጎ ነው። ደረጃዊ ልኬትን በመጠቀም ወደ መጠን የተለወጡ መረጃዎች ትክክለኛነታቸውና አስተማማኝነታቸው ተረጋግጦ፤ ከቃለ መጠይቅና ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻ ከተገኙ አይነታዊ መረጃዎች ጋር እየተመሳከሩ ተተንትነዋል።

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የመረጃዎችን ትክክለኛነትና አስተማማኝነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል። የምልከታ ቅጾቹን፣ የእለታዊ ማስታወሻ ቅጹንና የተመልካቾች የስልጠና መምሪያውን ትክክለኛነት ለመጠበቅ በባለሙያዎች እንዲገመገሙና በተሰጠው አስተያየት መሰረት እንዲስተካከሉ ተደርጓል። የምልከታ ቅጾቹን የበይነ ገምጋሚና የመረጃዎቹን የበይነ ተመልካች አስተማማኝነት ለማስላት ያገለገለው ስታቲስቲካዊ ስሌት ክሮንባኽ አልፋ ነው። የምልከታ ቅጾቹ አስተማማኝ መረጃ ማስገኘት የሚችሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የበይነ ገምጋሚ አስተማማኝነት ውጤት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የምልከታ ቅጽ α=0.921 ሲሆን የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ α=0.919 ነው። እንደ Ary et al. (2010) አገላለጽ የሁለቱም የምልከታ ቅጾች የበይነ ተመልካች አስተማማኝነት በጣም ከፍተኛ ነው። እንዲሁም ምልከታው ከተካሄደ በኋላ ተመልካቾቹ በሰጧቸው ነጥቦች መካከል የእርማት አስተማማኝነት መኖሩን ለማረጋገጥ የተሰላው የበይነ ተመልካች አስተማማኝነት ውጤት ሲታይ የመምህራኑን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም የሚያሳዩት መረጃዎች α=0.924፤ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩን የሚገልጹት መረጃዎች ደግሞ α=0.877 ነው። እነዚህ ውጤቶች ተመልካቾቹ በሰጧቸው ነጥቦች መካከል ያለው ግጥምጥሞሽ እንደየ ቅደም ተከተላቸው በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ መሆኑን በማመልከታቸው መረጃዎቹ ለትንተና ተወስደዋል።

የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎቹ የይዘት ትንተናና የሰነድ ትንተና ናቸው። Ayeni et al. (2019) እንደገለጹት እነዚህ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በድኅረ አወንታውያን የምርምር ቀመረ እሳቤ ማሕቀፍነት በሚከናወኑ ምርምሮች በጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። የይዘት ትንተና በንግግር ወይም በጽሁፍ የቀረበን መረጃ ወደ መጠናዊ መረጃነት ለመለወጥ የሚያገለግል አካሄድ ነው (Tavakoli, 2012; Ary, et al., 2010)። በመሆኑም በምልከታ የተሰበሰበን መረጃ በቁጥር ለመግለጽ አገልግሏል። Jupp (2006) የገለጹትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በቁልቁል አካሄድ ለተዘጋጁ የተለያዩ ተግባራት ወካዮችን በመስጠት የእያንዳንዱ ወካይ የክንውን ሁኔታ በቁጥር ተገልጸው በመጠናዊ የመረጃ

መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል። በዚህ አካሄድ ገላጭ ስታቲስቲክስ፣ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት፣ የኮሄንስ ዲ የልዩነት ጥንካሬ መለኪያ ስሌት፣ የአማካይ ንጽጽርና የፒርሰን የተዛምዶ ስሌት በጥቅም ላይ ውለዋል። Jupp (2006)፣ Ary, et al. (2010)ና Tavakoli (2012) በገለጹት መሰረት የሰነድ ትንታኔ ተጠኝ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱ በአግባቡ መከናወን ይችሉ ዘንድ ለትግበራ ያዘጋጇው እለታዊ የትምህርት እቅዶችና ተመራማሪዋ በምልከታው ሂደት በእለታዊ ማስታወሻዎቿ የመዘገበቻቸውን መረጃዎች ለመተንተን አገልግሏል።

"በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ መካከል ተዛምዶ አለ ወይ?" ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ መልሱ "አዎ! በመካከላቸው ጠንካራ አወንታዊ ተዛምዶ አለ።" የሚል ነው። እዚህ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያስቻለው እያንዳንዱን ዝርዝር ጥያቄ ለመመለስ በተከናወነው የመረጃ ትንተና የተደረሰበት ውጤት ነው። ከምልከታ፣ ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ውጤት እንዳሳየው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ያለው የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምም ሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ናቸው። የተጠኝ መምህራን የትምህርት ደረጃ ዲግሪና ዲፕሎማ ሲሆን በሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ያለው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ይሁን እንጂ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምም ሆነ በሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች በሚከናወነው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የትምህርት ደረጃቸው ዲግሪ የሆነ መምህራን ተሸለው ተገኝተዋል። ይህም በመካከላቸው ያለው የትምህርት ደረጃ ልዩነት የአተገባበር ልዩነት እንዲኖር ያደረገ መሆኑን ለማወቅ አስችሏል። በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር መካከል ተዛምዶ መኖሩን ለማወቅ የተሰላው የፒርሰን የተዛምዶ ስሌት ውጤት በ0.01 የነጻነት ደረጃ rs=0.885 ነው። በMuijs (2004) እንደተገለጸው በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር እንዴትነት መካከል በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ የሆነ በጣም ጠንካራ ተዛምዶ አለ። የተዛምዶ ውጤቱ ከዜሮ በላይ መሆኑ ተዛምዶው አወንታዊ መሆኑን ያሳያል። ይህ ማለት የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ጠንካራ የሆኑ መምህራን በሚያስተምሩበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ጥሩ የሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይከናወናል። የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀማቸው ደካማ የሆነ መምህራን በሚያስተማሩበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለው የክፍል ውስጥ መስተጋብር የደከመ ነው ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ የተጠኝዎቹ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ሲቀንስ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩም አብሮ ይቀንሳል። ሲጨምርም እንደዚያው አብሮ ይጨምራል።

የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በአምስት ዘርፎች ተከፍሎ ታይቷል። እነዚህም የቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም፤ የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም፤ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራብ፤ የጥያቄ አጠያየቅ እንዲሁም የመረጃ ግብይት ናቸው። የነዚህን ዘርፎች ተናጠላዊ አተገባበር የሚያሳዩ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤት ልኬት፣ የልይይት መጠን ልኬትና የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤቶች የቃላዊ እና የኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀሞች ከሚጠበቀው አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ሲገኙ የመረጃ አደረጃጀትና አቀራብ፤ የጥያቄ አጠያየቅ እንዲሁም የመረጃ ግብይት ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆናቸውን አመልክተዋል። የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በትምህርት የሚዳብር ከመሆኑ አንጻር የሌሎቹ ዘርፎች የአተገባበር ሁኔታ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ሲሆን የቃላዊ እና ኢቃላዊ መግባቢያዎች አጠቃቀም እንዴት ከሚጠበቀው አንጻር ጥሩ ሊሆን ቻለ የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። Hargie & Dickson (2005) እንደገለጹት ቃላዊና ኢቃላዊ መግባቢያዎችን ሰዎች ከህጻንነታቸው ጀምሮ በሚያድጉበት ማህረሰብ ይጠቀሙባቸዋል። ስለዚህም ከባህል ጋር ጥብቅ ትስስር አላቸው። ምናልባትም ይህ ሁኔታ መምህራኑ የተሻለ አጠቃቀም እንዲኖራቸው አድርጎ ሊሆን የሚል ምላሽ ተሰጥቶታል። ይህ እንዳለ ሆኖ ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም በጥቅሉ ሲታይ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙት መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው። የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታል።

ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ጥናቱ በተካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የተከናወነው የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበርም እንደዚሁ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ነው። የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ አራት ዘርፎችን የያዘ ነው። እነዚህም የተማሪዎቹን በይነ ሰባዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችሉ ተግባራት ክንውን፣ የክፍል አያያዝ፣ ትምህርታዊ መስተጋብርና የመማር ማስተማር ስልቶች አተገባበር ሲሆኑ ሲሆን ሁሉም ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ ናቸው። የነዚህን ዘርፎች የአተገባበር ሁኔታ የሚያሳዩ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች የአይነተኛ ውጤትና የልይይት መጠን ልኬታዎች በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች በርካታ የመረጃ ጉድኝት መኖሩን፤ የመረጃ አሰረጫጨቱ ኢታጣፊና የተለያየ መሆኑን እንዲሁም ደካማ አተገባበር ጎልቶ መታየቱን አመልክተዋል። ይህም በመደበኛ አሰረጫጨት በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው መረጃ አሰረጫጨት መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ አስችሏል። ልዩነቱ በስታስቲካዊ ስሌት ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የተሰላው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ያመለከተ ሲሆን የCohen's d የልዩነት ጥንካሬ መለኪያ ስሌት ውጤት ደግሞ በሚጠበቀውና በምልከታ በተገኘው የመረጃ አሰረጫጨት መካከል ያለው ልዩነት ጠንካራ መሆኑን አሳይቷል። ልዩነቱ የመጣው በአይነተኛ ውጤትና በልይይት መጠን ልኬታዎች እንደታየው በመደበኛ አሰረጫጨት ከሚጠበቀው አማካይ በታች

በርካታ የመረጃ ጉድኝት በመኖሩ ነው። ከተመራማሪ እለታዊ ማስታወሻና ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ ግኝት የሚያጠናክሩ ናቸው።

የዚህ ጥናት ውጤት እንዳሳየው የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ደካማ ነው። ይህም በትምህርታዊ የተግባቦት ሂደት ያለው የመረጃ ፍሰት እንዳይሳለጥ ለሚያደርግ የተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ መሆኑን ያመለክታል። የተግባቦት ስርአት ግብይታዊ እንደመሆኑ መጠን መረጃ በተለያዩ አቅጣጫዎች በተሳታፊዎቹ መካከል ይፈስበታል። በዚህ ምእራፍ በቀረበው የመረጃ ትንተና እንደታየው ግን ጥናቱ በተካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች ያለው የመማር ማስተማር ሂደት የተወሰኑ ሰዎች መረጃ የሚያስተላልፉበትና አብዛኞቹ ተቀባይ የሆኑበት ነው። ይህ ሁኔታ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ በአብዛኛው በመስማት ላይ ለተመሰረተ ግንዛቤ እንዲጋለጡና በአምስቱም የስሜት ህዋሳት መረጃን በግብአትነት የሚወስዱበት ሁኔታ ውሱን እንዲሆን ያደርጋል። በክፍል ውስጥ የሚከናወነው የተግባቦት ስርአትም መረጃ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚፈስበት ግብይታዊ ከመሆን ይልቅ በአንድ አቅጣጫ የሚፈስበት መስመራዊ እንዲሆን ምክንያት ይሆናል። ይህ ደግሞ የትምህርት ስርአቱ እውቀት በማህበር የሚገነባበት፣ ማህበራዊ የሆነ የጋራ ግንዛቤ የሚጨበጥበትና ከመሰረተ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ጋር የሚራመድ አሰራር የሰፈነበት እንዳይሆን የሚያርግ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምም ሆነ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆናቸው ተግባ-ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚጠበቀውን ውጽኣት ማስገኘት የተሳነው እንዲሆን ያደርጋል። በመማሪያ ክፍል ውስጥ እውቀት የሚገነባው በግብይታዊ የመማር ማስተማር ሂደት በሚከናወን የክፍል ውስጥ መስተጋብር ነው። መምህራንና ተማሪዎች ለመማር ማስተማር ሂደቱ ግብኣት የሚሆኑ ጉዳዮችን ይዘው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ይገናኛሉ። ከዚያም በክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ተግባራትን እየተገበሩ በሚያከናውኑት የመረጃ ልውውጥ ግብኣቶቹ ተብላልተው ውጽኣትን ያስገኛሉ። ይህ ውጽኣት በትምህርቱ ሂደት የሚፈጠር የጋራ ግንዛቤ ወይም የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። ግንዛቤው በቀደመ እውቀታቸው ላይ አዲስ ግንዛቤን የሚያክል የእውቀት ግንባታ እንዲካሄድ ያደርጋል። የእውቀት ግንባታው ሲካሄድ የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤት አስገኘ፤ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊዎች አዲስ የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥን አመጡ ማለት ነው። ይህ ለውጥ የግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ ውጽኣት ነው። ይሁን እንጂ በመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምም ሆነ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ላይ ድክመት ካለ በክፍል ውስጥ እንዲኖር የሚጠበቀውን የተሳለጠ የመረጃ ፍሰት ያዳክመዋል። ይህም ተማሪዎቹ ትምህርታዊ ተግባራቱን የሚያከናውኑበትን ሁኔታ አስመልክቶ የሚያገኙት መረጃ ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ እንዲሆን ያደርጋል። መጋለጡ ተማሪዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚያከናውኑት ተግባር በሚጠበቀው ሁኔታ አዳዲስ መረጃዎችን እየቀሰሙ እውቀትን እንዲገነቡ አያደርጋቸውም። እንዲሁም

የሚፈለገውን ያህል ማህበራዊ መስተጋብር አይከናወንም ማለት ነው። አለመከናወኑ ደግሞ በክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ተሳታፊዎች መካከል ነጻ የሆነ የሀሳብና የአሰራር ልውውጥ እንዳይካሄድ ያደርጋል፡ ፡ ልውውጡ ባልተካሄደበት ሁኔታ ቀደም ሲል በነበራቸው እውቀት ላይ አዲስ እውቀትን ለማከል የሚያስችላቸው የጋራ ግንዛቤን አይጨብጡም። ምክንያቱም መስተጋብሩ ደካማ ስለሆነ የቀረበውን ትምህርታዊ መረጃ መረዳት፣ መተርጎም፣ ማብላላት፣ ማዋሀድና ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ማስተሳሰርን አያከናውኑም። ስለዚህም ግብይታዊ የመማር ማስተማር ማሕቀፉ የሚፈለገውን ውጤት ወይም ውጽኣት ማስገኘት ይሳነዋል።

የቋንቋ አጠቃቀም በማህራዊ መስተጋብር ይዳብራል። በዚህ ምእራፍ በቀረበው የመረጃ ትንተና ለማየት እንደተሞከረው በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወነው ትምህርታዊ መስተጋብር የሚሳተፉት ጥቂቶች ሲሆኑ አብዛኞቹ ፍዝ ተመልካች ናቸው። ይህ ማለት በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የቋንቋ አጠቃቀም በብቃት ማበልጸግ የሚያስችል ማህበራዊ መስተጋብር አይከናወንም። ስለዚህም በተግባቦት ሂደቱ ተሳታፊዎች መካከል የሚኖረው የትምህርታዊ መረጃዎች መንሸራሸር የሚጠበቀውን ያህል አይሆንም። አለመሆኑ በተግባቦቱ ሂደት ተሳታፊዎች መካከል በሚከናወን መስተጋብር የጋራ ግንዛቤን ጨብጦ የጋራ መግባባት ላይ መድረስና እውቀትን መገንባት እንዳይጠበቅ ያደርጋል። በጥቅሉ የመማር ማስተማሩ ሂደት በተሟላ ሁኔታ መምህራንና ተማሪዎች በሚያከናውኑት ትምህርታዊ መስተጋብር አዳዲስ ግንዛቤዎችን የሚጨብጡበት፣ የአሰራር ክሂሎችን የሚያዳብሩበት፣ አዳዲስ መረጃዎችን የሚገነዘቡበት፣ ሀሳብ የሚጋሩበት፣ ፍቺን የሚመሰርቱበት፣ እውቀታቸውን የሚገነቡበት፣ ባገኙት ግብኣት ላይ የተመሰረተ ሀሳብ የሚያፈልቁበት፣ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታቸውን በሚገባ የሚያዳብሩበት ግንዛቤያቸውን አስመልክቶ ግብረ መልስ የሚሰጣጡበትና ስብእናቸው በተሟላ ሁኔታ የሚቀረጽበት ነው ማለት ያዳግታል።

በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸው በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳብ መሰረት የመማር ማስተማር ሂደት የተግባቦት ስርአት ነው። የተግባቦት ስርአት ሰባት አላባውያን ያሉት ሲሆን ከመካከላቸው አንዱ የመልእክት መተላለፊያ (channel) ነው። የትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት መልእክት መተላለፊያ ደግሞ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ የተገነባበት የትምህርት አቀራረብ ስልት መሆኑን (Wrench et al., 2009) አስገንዝበዋል። ከዚህ አንጻር የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ደካማ መሆኑ ከትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት አላባውያን መካከል አንዱ የሆነው የመልእክት ማስተላለፊያው ድክመት ወይም ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ይህ ደግሞ መልእክት ከመልእክት አስተላላፊ ወደ መልእክት ተቀባይ በሚተላለፍበት ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። በትምህርታዊ ተግባቦት ሂደት ውስጥ የመልእክት አስተላላፊነትንና የመልእክት ተቀባይነትን ሚና የሚወስዱት መምህራንና ተማሪዎች ናቸው። ስለዚህም መረጃ ከመምህራን ወደ ተማሪዎች፤ ከተማሪዎች ወደ መምህራን

እንዲሁም ከተማሪዎች ወደ ተማሪዎች የሚተላለፍበት መንገድ ለተግባቦት እንቅፋት የተጋለጠ ነው። እንቅፋቱ መረጃ የሚፈለገውን ያህል ከአንዱ የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ወደ ሌላው እንዳይተላለፍ መሰናክል ይሆናል። የመልእክት አስተላላፊነትን ተግባር የሚያከናውኑት ተሳታፊዎች መረጃን ወክለው ቢያስተላልፉም እንኳ በመልእክት መተላለፊያው ላይ ችግር ስላለ መልእክት ተቀባይ የሆኑ ተሳታፊዎች ዘንድ የተሟላ መረጃ አይደርስም። የተሟላ መረጃ ባልደረሰበት ሁኔታ መረጃውን በትክክል እንዲተረጉሙት አይጠበቅም። ተርጉመው ካልተረዱት ደግሞ ትክክለኛ ግብረ መልስ መስጠት አይችሉም። ስለዚህም መልእክት አስተላላፊ የነበረው የተግባቦት ሂደት ተሳታፊ ትክክለኛ ግብረ መልስ አያገኝም። ይህ ደግሞ በግብረ መልሱ ላይ ተመስርቶ በቀጣይ ግብይታዊ በሆነ መንገድ የሚካሄደውን የተግባቦት ሂደት ያውከዋል። የተግባቦት ሂደቱ መታወኩ የተግባቦት ሂደቱ ተሳታፊዎች በቀረበው ትምህርታዊ መረጃ ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደርሱና ጥሩ የሆነ የጋራ ግንዛቤ እንዳይጨበጡ ያደርጋል።

በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምም ሆነ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ የታየው ድክመት በቀጣይ መጠናት ያለባቸው ጥያቄዎችን አስነስቷል። እነዚህ ጥያቄዎች በስራ ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን አሰራር እንዴት በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አሰራር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል? በቀጣይ የሚሰለጥኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአሰለጣጠን ሁኔታስ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ ምን መምሰል አለበት? ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትስ በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ረገድ መምህራንን የሚያሰለጥኑበት ሁኔታ ምን ይመስላል? በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ሲሰለጥኑ የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበርን በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ከመማር ባለፈ በተግባር የሚተረጉሙበትን መንገድ ምን ያህል ይለማመዳሉ? ሰልጣኝ መምህራኑ በክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ላይስ ምን ያህል ግንዛቤ አላቸው? በተግባቦት ክህሎት አጠቃቀም ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች አሰራርስ ምን ያህል በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው? በዘመናዊ የማስተማር ዘዴ ሰልጥነው የሚወጡት መምህራን በስራ አለም ሲሰማሩ የሚሰማሩበት የስራ አውድ የሚያሳድርባቸውን ተጽእኖ እንዴት መቋቋም ይቻላል? የሚሉ ናቸው።

5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

- ይህ ጥናት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበሩ ደካማ መሆናቸውን አሳይቷል። ጥናቱ በጥቂት ተጠኝዎች ላይ የተከናወነ እንደመሆኑ መጠን

አጠቃላይ በትምህርት ስርአት ውስጥ ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል አውቆ ወደ ቀጣይ ርምጃ ለመሄድ ሰፊ ናሙና ወስዶ የክስተቱ ሁኔታ የሚጠናበትና መፍትሄ የሚፈለግበት ሁኔታ ቢመቻች የበለጠ ውጤት ማግኘት ይቻላል፡፡

- ይህ ጥናት የመምህራኑ የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ከሚጠበቀው አንጻር ደካማ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ይህ ማለት በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የተግባቦት ክህሎትን በአግባቡ እየተጠቀሙ አይደለም፤ በሚያስተማሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥም ያለው መስተጋብር ደካማ ነው፡፡ ስለዚህም መምህራንን የሚያሰለጥኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን አዘጋጅተው በስራ ላሉ መምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና የሚሰጡበትን ሁኔታ ቢቀይሱና በስራ ላይ ቢያውሉት የመማር ማስተማሩን ሂደት ማሻሻል የሚያስችል ተግባር ማከናወን ይቻላል፡፡

- በዚህ ጥናት በተጠኝነት የተወሰዱት መምህራን በከፍተኛ ትምህርት ሰልጥነው የወጡ ናቸው፡፡ የስልጠናው ሂደት በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ ላይ ወደ ተመሰረተ አሰራር የማያመጣቸው ከሆነ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ ያለው አሰራር "ችግር ይኖርበት ይሆን?" የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በመሆኑም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው የመምህራን ስልጠና ሂደት በትክክልም በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ አተያይ ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚመረምር ጥናት ቢጠናና አሰራሩ የሚስተካከልበት ሁኔታ ቢመቻች በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚታየውን ችግር መቅረፍ ይቻላል፡፡

- ጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው በስራ ላይ ያሉ መምህራን የተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና የክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር የመሰረተ ግንባታውያንን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ የመከተል ችግር ይታይበታል፡፡ በመሆኑም በስራ ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የትምህርት አቀራብ እንዴት በማህበራዊ ግንባታውያን መርህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል? መምህራንን የሚያሰለጥኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለተግባቦት ክህሎት አጠቃቀምና ለክፍል ውስጥ መስተጋብር አተገባበር ምን ያህል ትኩረት ሰጥተዋል? በቀጣይ የሚሰለጥኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአሰለጣጠን ሁኔታስ ምን መምሰል አለበት? ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትስ መምህራንን የሚያሰለጥኑበት ሁኔታ ምን ይመስላል? የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች አሰራርስ ምን ያህል በመሰረተ ግንባታውያን የመማር ንድፈ ሀሳቦች ዝንቅ መሰረተ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው? የሚሉ

ጥያቄዎችን የዳሰሱ ጥናቶች ቢጠኑ የመማር ማስተማሩ ሂደትን የበለጠ ውጤታማ ማድረግ ይቻላል።

የማጣቀሻ ጽሁፎች

ሂሩት ካሳው (1997)፡፡ በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር የሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሴትና የወንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ ለአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

መሰለ መኩሪያ (1990)፡፡ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም የአማርኛ መርሀ-ትምህርት ትግበራ ሂደትን ከስነዘዴ አኳያ መገምገም፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ ለአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

ሰይድ ይመር (1993)፡፡ በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ (የመማር ማስተማር ሂደት ግምገማ) በሰባት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ናሙናነት፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ ለአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

ኤልያስ አድማሱ (1997)፡፡ በኦሮሚያ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ መሠረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ ለአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/፡፡

የኢፌድሪ ህገ መንግስት (1987)፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የኢፌድሪ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር ፪ (1987):: አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ኢ.ፌ.ድ.ሪ. የትምህርት ፖሊሲ (1987)፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ያለው እንዳወቀ (1998)፡፡ ***የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር***፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

Adamson, H.D. (2005). *Language Minority Students in American Schools: an Education in English*. London: Lawrence Erlbaum Associates Publishers.

Akpınar, K. D. (2009). Developing Communication Skills of EFL Teacher Trainees. *Journal of Language & Linguistic Studies*, 5, 110-126.

Anderson, N.J. (2005). L2 Learning Strategies. In E. Hinkel (Ed.) *Handbook of Research in Second Language Teaching & Learning* (PP. 757-771). New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates.

Arends, R. I. & Kilcher, A. (2010). *Teaching for Student Learning: Becoming an Accomplished Teacher.* New York: Routledge.

Ary, D., Jacobs, L. C., & Sorensen, C. (2010). *Introduction to Research in Education* (10th Ed.). Australia: Cengage Learning.

Assanova, G. S., & Kim, C. H. (2014). Formation of Students' Intercultural Communicative Competence in Business Communication. *Middle-East Journal of Scientific Research*, 19, 642-646.

Attard, A., Iorio, E, & D., Geven, k., (2010). *Student-Centered Learning: Toolkit for Students, Staff and Higher Education Institutions*. Berlin: Laserline.

Ayeni, E. O., Saman, U. P. & Kasimu, S. (2019). Facts & Fiction in Positivism & Neo Positivism. *Research on Humanities & Social Sciences*, 9, 21-33.

Babonea, A., & Munteanu, A. (2012). Towards Positive Interpersonal Relationships in the Classroom. *International Conference of Scientific Paper* (PP: 1-4). Brasov: 'Spiru Haret' University.

Bada, S. O. (2015). Constructivism Learning Theory: a Paradigm for Teaching & Learning" in *Journal of Research & Method in Education*, 2015, 66-70.

Balli, S. J. (2009). *Making a Difference in the Classroom: Strategies that Connect with Students*. USA: Rowman & Littlefield Education.

Bambaeeroo, F., & Shokrpour, N. (2017). The Impact of the Teachers' Non-verbal Communication on Success in Teaching. *Journal of Advances in Medical Education & Professionalism*, 5, 51-59.

Barkai, J. (1990). Nonverbal Communication from Other Side: Speaking Body Language. *San Diago Law Review*, 27, 101-125.

Barker, A. (2011). *Improve Your Communication Skills* (Rev. Ed.). London: Kogan Page Ltd.

Barroso, K. & Pon, S. (2004). *CALPRO Professional Development Module, Effective Lesson Planning*. AIR: Sacramento.

Barry, B E. (2011). *Student Nonverbal Communication in the Classroom*. New York: United States Military Academy.

Beatty, L. 2004. Transforming Student Learning with in Student Communication Systems. *Educause Center for Applied Research Bulletine*, Issue 3, 2-13.

Beglar, D., & Hurt, A. (2002). Implementing Task Based Learning" in Richards, J. C., & Renandya, W. A. (Eds.), (2002). *Methodology in Language Teaching: an Anthology of Current Practice*. Cambridge: Cambridge University Press.

Berhanu B. (2009). Language Determination in Ethiopia: What Medium of Instruction?. Ege, S., Aspen, H., Teferra, B., & Bekele, S. (Eds). (2009). *Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies*, 1089-1101

Berko, R., Aithken J. E., & Wolvin, A. (2010). *ICOMM: Interpersonal Concepts and Competencies - Foundations of Interpersonal Communication*. USA: Rowman & Littlefield Publishers, Inc.

Beyhan, Ö., & Köksal, O. (2013). Learner Perceptions of Building Constructivist Learning Environments in Secondary Schools. *Journal of Educational & Instructional Studies in the World*, 3, 171-180.

Bhargava, A. (2011). Perception of Student Teachers about Teaching Competencies. *American International Journal of Contemporary Research*, 1, 77-81.

Bhattacharjee, J. (2015). Constructivist Approach to Learning– an Effective Approach of Teaching Learning. *International Research Journal of Interdisciplinary & Multidisciplinary Studies (IRJIMS)*, *I, 65-74* .

Brok, P., Brekelmans', M., & Wubbels, T. (2004). Interpersonal Teacher Behaviour and Student Outcomes. *School Effectiveness & School Improvement*, 15, 407-442.

Brown, H. D. (2000). *Teaching by Principle: an Interactive Approach* to Language Pedagogy. USA: Pearson Education Inc.

Brown, H. D. (2002). English Language Teaching in the 'post-Method' Era: toward Better Diagnosis, Treatment, & Assessment. n Richards, J. C., & Renandya, W. A. (Eds.), (2002). *Methodology in Language Teaching*: *an Anthology of Current Practice*. Cambridge: Cambridge University Press.

Brown, H. D. (2007). *Principles of Language Learning & Teaching* (5th Ed.). USA: Pearson Education Inc.

Brown, G. & Atkins, M. (2002). *Effective Teaching in Higher Education*. London: Methuen & Co. Ltd.

Brown, K. (2009). *Concise Encyclopedia of Languages of the World*. Amsterdam: Elsevier Ltd.

Browne, D. L. (2002). Ethiopia in Marlow-Ferguson, R. (Ed.), (2002). *World Education Encyclopedia: a Survey of Educational Systems Worldwide* (2nd Ed.), (pp. 425-434). Detroit: Gale Group.

Brumfit, C. & Mitchell, R. (1990). The Language Classroom as a Focus of Research. In Brumfit, C. & Mitchell, R. (Eds.), (1990). *Research in Language Classroom: ELT Documents 133* (PP 3-16). Hong Kong: Modern English Publications & the British Council.

Byrd, J. (2008). *Guide Book for Student-Centered Classroom Discussions* (1st Ed.). USA: Interactivity Foundation.

Camic, P. M., Rhodes, J. E., & Yardley, L. (2003). *Qualitative Research in Psychology: Expanding Perspectives in Methodology & Design*. Washington: American Psychological Association.

Ciaccio, J. (2004). *Totally Positive Teaching: a Five-Stage approach to Energizing Students and Teachers***.** Alexandria: Association for Supervision and Curriculum Development.

City Government of Addis Ababa Education Bureau (2014/2015). Education Statistics Annual Abstract. Education Management Information System: Addis Ababa Education Bureau. (Unpublished)

Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (1994). Addis Ababa: Berhanenna Selam Printing Press.

Cook, V. (2008). *Second Language Learning & Language Teaching* (4th Ed.). London: Hodder Education.

Corbeta, P. (2003). *Social Research: Theory, Methods & Techniques*. London: SEAGE Publications Ltd.

Cornu, R. (2005). Towards Constructivist Classrooms: the Role of the Reflective Teacher. *Journal of Educational Enquiry*, 6, 50-64.

Creese, A. (2005). *Teacher Collaboration and Talk in Multilingual Classrooms* (2nd Ed.). Clevedon: Multilingual Matters Ltd.

Cross, K., Patricia, A., & Thomas, A. (1988). *Classroom Assessment Techniques: a Handbook for Faculty*. Michigan: the Board of Regents of the University of Michigan.

Crystal, D. (2000). *The Cambridge Encyclopedia of Language* (2nd Ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Dawson, C. (2007). *A Practical Guide to Research Methods: a Use- Friendly Manual for Mastering Research Techniques & Projects* (3rd Ed.). Oxford: How to Books Ltd.

Dewey, J. (1938). *Experience & Education*. New York: Collier Books.

Dixon, T. & Hara, M. (2006). *Communication Skills: Making Practice-Based Learning Work***.** A Resource Commissioned by the Marketing Practice Based learning Work Project, an Educational Development Project funded through FDTL Phase 4 Project Number 174/02 & Produced by Staff from University of Ulster.

